ኢነዴክስ (Simpson Dominance Index (D)) ((0.10)፣ የማርጋሌፍ ኢንዴክስ (ኤም)(Margalef's index (M') richness index) (5.32) እና ኢቭነስስ ጠቋሚ (Evenness Index (E)) (0.77) ዝቅተኛ በዓይን የሚታዩ በውሃ ውስጥ የሚገኙ ተክሎች (Macrophytes) ተመዝግቧል፤ በእነዚህ የብዝሃ ህይዎት መለኪያዎችም መሰረት የጣና ሐይቅ ዉሃ መረጃዉ ሲተነተን መካከለኛ የጥራት ደረጃ ላይ መሆኑን ያሳያል። ይሁን እንጂ የኢሆርኒያ (Eichhornia)፣ ፖታሞጌተን (Potamogeton) እና ሳይፔረስ (Cyperus) ያሉ በዓይን የሚታዩ በውሃ ውስጥ የሚገኙ ተክሎች (Macrophytes) መገኘት በተወሰኑት የናሙና መሰብሰቢያ ስፍራዎች ከፍኛ የዉሃ ብክለት እንዳለ ያሳያል። ስለሆነም የሰዉ ልጅ በሚያደርገዉ የቀን ተቀን መስተጋብር በጣና ሐይቅ ብዝሃ ህይዎት፣ የዉሃ ጥራትና የአካባቢዉ ማህበረሰብ መተዳደሪያ እሴት ላይ ያስከተለዉ ተፅእኖ ከፍተኛ መሆኑን ያመላክታል።የሰው ልጅ እንቅስቃሴ በውሃ ጥራት እና ብዝሃ ህይወት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ በተዘዋዋሪ የአካባቢዉን ማህበረሰብ አኗኗር ይጎዳል። በመሆኑም በአካባቢዉ ማህበረሰብ አኗኗር ላይ ባለዉ ተፅዕኖ ምክረ-ሃሳብ ለመስጠት እንዲያስችል ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ያሳተፈ ተጨማሪ የምርምር መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም ማለትም ቁልፍ መረጃ ሰጪ አካላትን ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ የትኩረት ቡድን ውይይት በማካሄድ፣ ምልከታዎችን በማከናዎን፣ የታተሙ እና ያልታተሙ የመረጃ ምንጮችን በመገምገም፣ እንዲሁም ፎቶግራፎችን በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል። ጣና ሐይቅ የተለያዩ ዕፅዋትና እንስሳት መገኛ ሲሆን በተጨማሪም በዚሁ የጥናት ቦታ ብቻ የሚገኙ ልዩ የእንስሳት እና የእፅዋት ዝርያዎችም ማዕከል ነዉ። በጣና ሐይቅ በዓይን የሚታዩ በውሃ ውስጥ የሚገኙ ተክሎች (Macrophytes) እና የደን ሃብት ምንጭ ሲሆን በዋነኛነት ለባህላዊ ህክምና፣ ለማገዶ እንጨት፣ ለገመድ፣ ለአእዋፋት መኖሪያነት፣ ለእንስሳት መኖ ወዘተ. የሚያገለግሉሃብቶች ምንጭ ነዉ።ከእንስሳት መካከል አሳ፣ ጉማሬ፣ አዞ፣ አከርካሪ የሌላቸው ወዘተ. የመሳሰሉት በዚሁ ሀይቅ ይገኛሉ። የጣና ሐይቅ አካባቢ በኢትዮጵያ ብቻ ለሚገኙ የከብት ዝርያዎች (የፎገራ ዝርያ) እና ለመስክ ሰብሎች ጥሩ የምርምር ማዕከል

ነው። በጣና ሀይቅ ዙሪያ ካሉት ዋና ዋና ሃብቶች መካከል መሬት ዋነኛዉ ሃብት ነዉ፣ ከእፅዋት ሃብቶች መካከልም (የውሃ ተክሎች እና የደን ሃብቶች) የሚገኙ ሲሆን፣ የዱር እንስሳት ሃብቶች (ዓሳና መሰሎች የሰዉልጅ መተዳደሪያ ምንጭ ናቸዉ)፤የጣና ሐይቅ የባህል፣ መልክዓ ምድር (አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት) መስህብ ማዕከል ነዉ። የጣና ሐይቅ በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ምክንያት በተፈጠሩ አካባቢያዊ ችግሮች ተጋልጧል። ለምሳሌ፡- የአፈር መሸርሸር፣ በደለል መሞላት፣ የደን መጨፍጨፍ፣ የውሃ መጠን መቀነስ፣ ወጥ ያልሆነ ዝናብና ጎርፍ መከሰት፣ በመጤ የአረም ዝርያ መወረር፣ ብክለት ተጠቃሽ ችግሮች ናቸው። የእነዚህ ችግሮች መንስኤዎችም ልቅ ግጦሽ፣ የእርሻ መሬት መስፋፋት፣ የዉሃ ዳርቻ መሬቶችን ማልማት (ባህር ሸሽ)፣ የወል መሬት ወረራ፣ እፅዋትን ማጥፋት እና የምግብ እና የማገዶ እንጨት ፍላጎትን ለማሟላት የብዝሃ ህይዎት መመናመንመገለጫዎች ናቸው። የጣና ሐይቅና ዳርቻ ረግረጋማ መሬቶች መጥፋት የሐይቁን ስነ-ምህዳር እና የአካባቢው ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ ተመልክቷል። የስነ-ምህዳር ምሰሶዎችም እርስ በርስ የማይነጣጠሉና ተያያዥ በመሆናቸዉ በአንዱ ላይ የሚከሰተዉ ተፅዕኖ በሌላኛዉ ላይ በጉልህ ይታያል:: ስለሆነም የተዛምዶ ትንተና በጣና ሀይቅ ፊዚዮኬሚካል ባህርያት እና ማክሮ ኢንቨርተብሬትስ መካከል ተካሂዷል። ይህም ከብዙዎቹ የፊዚዮኬሚካላዊ ባህርያት እና ማክሮ ኢንቨርተብሬትስ ቤተሰቦች መካከል ያለው ትስስር በጉልህ ተስተውሏል:: አንዳንድ ተዛምዶዎችን ለመጥቀስ ያህል፣ በሀይቁ አካላዊ፣ ኬሚካላዊ እና ስነ-ህይዎታዊ ባህሪያት መካከል የታዩት ለውጦች፣ በውሃ ውስጥ ያሉ ነፍሳት ላይ ጉልህ ተጽእኖ አሳድረዋል፡ ፡ ይህም በተራው ሀይቁ በሚኖረዉ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። መሠረታዊ የመረጃ ትንተና (RDA(Canonical redundency analysis)) እና የዝርያ-አካባቢያዊ ባህርያት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ፒ ኤች (pH), ካንዴም(Cd)፣ ብር፣ ሊድ (Pb) እና ሳልፌት ($SO^{2-}_4$) እና ቬሊዴ ( Velidae)፣ ክሪኖሚዴ (Chironomidae)፣ ፊሲዴ (Physidae)፣ ጄሪዴ (Gerridae) ኮሪክሲዴ (Corixida)፣ ዲቲኬዲ (Dytiscidae)፣ ካኒዴ (Caenidae)፣ ኮኖግሪኖዴ (Coenogrionidae)፣ ሲሙሊዴ (Simuliidae) እና ስፔንዴ (Psephenidae) የአሉናዊ ተፅዕኖ

ተዛምዶዎችን ሲያመላክቱ ፣ ሙሲዴ (Mus-sidae) ግን የአካባቢዉን ባህርያት መለወጥ አዎንታዊ ተፅዕኖ ተዛምዶ ያመላክታል። ይህ ጥናት በጣና ሐይቅ ውስጥ ለስነ-ምህዳሩ መዛበት ዋነኛ ምክንያት ተብለዉ ከሚጠቀሱት ዉስጥ የግብርና ስራዎች፣ የከተሞች ስፋፋት እና ከኢንዱስትሪ መስፋፋት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ተፅዕኖዎች የውሃ ጥራትን በመቀነስና እና ብዝሃ ህይወትን በማዳከም ብሎም በማጥፋት ግምባር ቀደም ምክንያቶች ናቸው ሲል ይደመድማል። በመሆኑም የጣና ሐይቅንና በዉስጡ ያሉ ሃብቶችን በዘላቂነት ለመጠቀም የዘላቂ ልማት ፅንሰ-ሃሳብ መርህን በመተግበር የጣና ሐይቅን ከብክለት ለመከላከል፣ የሐይቁን ብዝሃ ህይዎት ለመጠበቅ የጣና ሐይቅን በአግባቡ ለመያዝና ለመቆጣጠር የሚያስችል ስራ መተግበር እንደሚገባ የመፍትሄ ሀሳብ ቀርቧል።

**ቁልፍ** ቃላት: የውሃ ጥራት፤ ስነ-ሕይወታዊ ግምገማ; የውሃ ብክለት; የጣና ሀይቅ።

Year of Graduation 2021

## An investigation of the nature, causes and effects of long-term environmental degradation on watershed natural resources: a case of Belbela-Wadecha watershed ecosystem, Central Ethiopia

Adugna Jabessa Shuba

### ABSTRACT

Land degradation is a process in which the value of the biophysical environment is affected by a combination of nature and human-induced processes acting upon the land. It is viewed as any change or disturbance to the land perceived to be undesirable. Soil degradation is one aspect of land degradation and others are vegetation or water resource degradation. The Belbela-Wadecha water-shed eco-system in its current state is practically

## የረዥም ጊዜ የአካባቢ መራቆት በተፋሰስ የተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚያስከትለው ጉዳት መንስኤ፣ ባህርይና ተጽእኖ፡ በማእከላዊ ኢትዮጵያ፣ በልበላ-ዋዴቻ ተፋሰስ ስነ-ምህዳር ላይ የተደረገ ጥናት፤

በአዱኛ ጃቤሳ ሹባ

### አጠቃሎ

የመሬት መራቆት በተፈጥሮ እና በሰውሰራሽ ምክንያቶች የተነሳ

በመሬት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚፈጥር ሂደት ነው። ይህ ተጽእኖም መሬቱ ተፈላጊ እንዳይሆን የሚያደርግ ነዉ። የአፈር መራቆት አንዱ የመሬት መራቆት ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ የእፅዋት ወይም የውሃ ሀብት መበላሸት ናቸው። የበልበላ-ዋዴቻ የተፋሰስ ስነ-ምህዳር አሁን ባለበት ሁኔታ ለመሬት መራቆት የተጋለጠ ነው። በመሆኑም የሚሰጠው ጥቅም ተሟጧል። በአካባቢው እፅዋት ጠፍተዋል፤ አፈር ተሸርሽሮ ጉድጓዶች

a degraded phenomenon, and thus the previous benefits it could provide would have been affected, as a result. As can be perceived from physical observation, vegetation has vanished, soils are eroded, gullies have formed, reservoirs are filled up with sediments, canals are blocked/ clogged, dam water storages have declined, and flooding has caused major damages. Reportedly, malarial incidents have become high because of a formation of damp soils due to the stagnation of water. As a result, existing economic, social, and environmental benefits have been affected in a way imposing a hard and unusual way of experiencing patterns of life. Since 1985, different LandSat satellites have been used to observe the Earth from space and provide data that helps the public and scientific community to understand the state and condition of the Earth's surface through time. In order to assess the land change, remote sensing (RS) imageries from the LandSat satellites have been used. Satellite remote sensing can help to enhance largely the capabilities of monitoring the actual state of land uses in a comprehensive and timely manner. It fulfils the requirements for monitoring and mapping the status of agricultural land use and land change, because satellites deliver objective and timely (every 5-6 days) information regularly. The high spatial detail of satellite images (10-meter pixels) enhances tracing these activities at different scales: from the single field level (study area) and even up to country level. In this study, the methodologies that were deployed to assess land degradation (land cover changes) of the study area relied on the processes of remotely sensed imageries using different satellites of LandSats 4-5 Thematic Mapper (TM), and LandSats 7 and 8. The main dominant bands were bands 1, 2, 3, 4, 5, 6 and band 7 based on the types of LandSats.

ተፈጥረዋል፤ የውሃ ማጠራቀሚያዎች በደለል ተሞልተዋል፤ ቦዮች በቆሻሻ ተደፍነዋል፤ የውሃ ግድቦች ፈርሰዋል፤ የጎርፍ መጥለቅለቅ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። በውሃ ማቆር የተነሳ እርጥበት ያለው አፈር በመፈጠሩ፣ የወባ በሽታ ተከስቷል። በዚህም የተነሳ ነባር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ሀብቶች በመጎዳታቸው፣ በነዋሪዎች ላይ ከባድ እና ያልተለመደ አሉታዊ የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ አምጥቷል። ከ1985 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ የመሬት ምልከታ ሳተላይቶች ምድርን ለመልክዓምድራዊ ጥናት ጥቅም ላይ ውለዋል፡ ፡ እነዚህ ሳተላይቶች ምድርን ከህዋ በመመልከት ለሳይንሳዊው ማህበረሰቡ ጥናት መረጃዎችን ያቀርባሉ። የመሬት ለውጥን ለመገምገም ከላንድሳት ሳተላይቶች የርቀት ዳሳሽ (RS) ምስሎች ይልካሉ። የሳተላይት የርቀት ዳሰሳ የመሬት አጠቃቀምን ትክክለኛ ሁኔታ፣ ሁሉን አቀፍ እና ወቅታዊ የመከታተል አቅምን ለማሳደግ ይረዳል። የግብርና የመሬት አጠቃቀምን እና የመሬትን ለውጥ ሁኔታ ለመከታተል እና ካርታ ለማውጣት የሚያስፈልጉትን መረጃዎችን ያሟላል፤ ምክንያቱም ሳተላይቶች ተጨባጭ እና ወቅታዊ (በየ 5-6 ቀናት) መረጃዎችን በመደበኛነት ያቀርባሉ። የሳተላይት ምስሎች ከፍተኛ የቦታ ዝርዝር (10 ሜትር ፒክሰሎች) ያደርጋሉ፤ እነዚህን እንቅስቃሴዎች በተለያየ ሚዛን መከታተልን መረጃዎችን ያጎለብታል። ይህም ከአንድን የተለየ ውስን ቦታ ጀምሮ እስከ ሀገር አቀፍ መጠነ-ስፊ ጥናቶች ለማከናወን ጥቅም ላይ ይውላል። በዚህ ጥናት የጥናቱ አካባቢ የመሬት መራቆትን (የመሬት ሽፋን ለውጦችን) ለመገምገም የተዘረጉት ዘዴዎች ከርቀት በሚታዩ ምስሎች ሂደት ላይ የተመሰረቱት የተለያዩ ሳተላይቶች LandSats 4-5 Thematic Mapper (TM) እና LandSats 7 and 8 ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ባንዶች 1፣ 2፣ 3፣ 4፣ 5, 6 እና 7 በ LandSats አይነቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በአጠቃላይ የአረንጓዴ፣ ቀይ እና ሰማያዊ (አርጂቢ) ቀለሞች እና የእፅዋት ነጸብራቅ በኢንፍራሬድ (NIR) ባንዶች ውስጥ በትንተናው ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል። በተጨማሪም በመካከለኛው ኢትዮጵያ የበልበላ ዋዴቻ ተፋሰስ ስነ-ምህዳር የአካባቢ መራቆትን መንስኤና ተፅእኖን ለመዳሰስ በትኩረት ቡድን ውይይት፣ በመጠይቅና ከሰነዶች የተሰበሰቡ መረጃዎች ላይ ትንተና ተደርጓል። የአካባቢው ነዋሪዎች በሙከራ ፕሮጄክት ውስጥ

In general, Green, Red and Blue (RGB) colours and reflectance of vegetation in Near Infrared (NIR) bands were used in the analysis. In addition, qualitative primary data was sought through focus group discussions, questionnaire survey and secondary information from document analyses to explore the causes and effects of environmental degradation in Belbela-Wadecha watershed ecosystem in Central Ethiopia. The participating communities were also involved from the beginning through Participatory Action Research (PAR), in identifying causes of degradation in the watershed and responding to them through a pilot trial project. The combination of data collected from satellite remote sensing, the Participatory Action Research process, physical ground observation, questionnaire survey, focus groups discussions and the secondary data was analysed qualitatively and quantitatively and the results interpreted to help in designing future directions in watershed resource management. Furthermore, the integration of the results of both qualitative and quantitative research analyses helped in making conclusions and recommendations towards improving the natural setting of the ecosystem. The main findings and conclusions hinged on ensuring the parallel and harmonious operation of both environmental management and agricultural irrigation systems with a view to achieve sustainable environmental, social and economic well-being. Because of ecosystem restoration and sustainable downstream irrigation agriculture, it was hoped that this would lead to the improvement of livelihood sustenance through economic, social and environmental benefits.

**Keywords:** Watershed degradation; LULC, NDVI; natural resources, poverty; environment; ecosystem; RS; infrared; GIS; PAR; IWRM; enforcement of laws, development; sustainability.

ተሳትፈው ምላሽ ሲሰጡ፣ የተፋሰስ መበላሸት መንስኤዎችን በመለየት በአሳታፊ አክሽን ጥናት (PAR) በኩል ከመጀመሪያው ጀምሮ ተሳትፈዋል። ከሳተላይት የርቀት ዳሰሳ የተሰበሰቡ መረጃዎች ጥምር፣ አሳታፊ የድርጊት ጥናት ሂደት፣ የመልከአምድራዊ ምልከታ፣ የመጠይቅ ጥናት፣ የትኩረት ቡድኖች ውይይቶች እና የሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች በጥራት እና በመጠን የተተነተኑ ሲሆን፣ ውጤቱም በተፋሰስ ሀብት አስተዳደር ላይ የወደፊት አቅጣጫዎችን ለመንደፍ ይረዳል ተብሎ ተተርጉሟል። በተጨማሪም የጥራት እና የቁጥራዊ ምርምር ትንተና ውጤቶች የተፈጥሮን የስነ-ምህዳር አቀማመጥ ለማሻሻል የሚረዱ መደምደሚያዎች አስቀምጠዋል፤ መወሰድ ያለባቸውን የመፍትሄ ርምጃዎች አመላክተዋል። ዋናዎቹ ግኝቶች እና መደምደሚያዎች ዘላቂ የሆኑ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ለማምጣት፣ የአካባቢ አያያዝ እና የግብርና መስኖ ስርዓቶች በቅንጅታዊ አሰራር የሚከናወኑበትን መንገድ ማረጋገጥ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የስርዓተ-ምህዳር መልሶ ማቋቋምና ቀጣይነት ያለው የታች መስኖ ግብርና በኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ጥቅሞችን በመጠበቅ የማህበረሰቡን መተዳደሪያ ማሻሻል ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- የተፋሰስ መበላሸት፤ LULC፤ NDVI፤ የተፈጥሮ ሀብቶች ድህነት፤ አካባቢ፤ ስነ-ምህዳር፤ RS፤ ኢንፍራሬድ፤ ጂአይኤስ፤ PAR፤ IWRM፤ የህግ አፈፃፀም፤ ልማት፤ ዘላቂነት።

# Evaluation of phytoremediation potentials of Phytolacca Dodecandra, Adhatoda Sschimperiana and Solanum Incanum for selected heavy metals in field setting located in central Ethiopia

Alemu Shiferaw Debela

## ABSTRACT

Pollution of soil by trace metals has become one of the biggest global environmental challenges resulting from anthropogenic activities. Therefore, restoration of metal contaminated sites needs due attention. The use of phytoremediation technologies as a nature-based solution to pollution, could support successful implementation of green economic development strategies, with economically affordable and environmentally friendly benefits. The present investigation employed an exploratory study approach on the phytoremediation potentials of three selected native plants; Phytolacca dodecandra (L'Herit), Adhatoda schimperiana (Hochst) and Solanum incanum L, dominating areas close to heavy metal contamination sources in metropolitan centres of Addis Ababa. In this work, concentration of six heavy metals of interest chromium (Cr), lead (Pb), cadmium (Cd), nickel (Ni) copper (Cu) and zinc (Zn) were examined in soil and in different tissues (leaves, stems and roots) of selected plants (both seedlings and mature plants), in dry and rainy seasons using atomic absorption spectrophotometer. Efficiency of phytoremediation is discussed based on calculated values of Bio-concentration Factor (BCF), Translocation Factors (TF) and Bioaccumulation Coefficient (BAC). Phytolacca dodecandra showed BCF, TF

# በመካከለኛው ኢትዮጵያ በሚገኘው የመስክ አካባቢዎች፣ የእንዶድ፤ ሰንሰል እና እምቧይ የተመረጡ መርዛማ ከባድ ብረቶችን ከተበከለ አፈር ውስጥ ለማስወገድ (የፎቶሪሚዲየሽን) ያላቸው  አቅም ግምገማ

አለሙ ሽፈራው ደበላ

## አጠቃሎ

ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ ከሚደርሱ የአፈር ብክለቶች መካከል በከባድ ብረት አማካኝነት የሚደርሰው ብክለት ትልቁ አለም አቀፍ ተግዳሮት ነው:: በመሆኑም በመርዛማ ከባድ ብረት (Toxic heavy metals) የተበከሉ ቦታዎችን መልሶ ማከም ተገቢ ትኩረት ያስፈልገዋል። የፋይቶሬሜዴሽን (phytoremediation) ቴክኖሎጂዎችን እንደ ተፈጥሯዊ የብክለት መፍትሄ መጠቀም የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂዎችን በተሳካ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ይረዳል። በዚህ ጥናት ከተመረጡ ሦስት ሀገር-በቀል ተክሎች መካከል ፋይቶሬሜዴሽን አቅም ላይ የአሰሳ ጥናት ተከናውኗል። ጥናቱ የተከናወነው በ Phytolacca dodecandra (እንዶድ)፣ Adhatoda schimperiana (ሰንሰል) እና Solanum incanum (እምቧይ) ላይ ሲሆን እነዚህ እፅዋቶች በመሃከለኛ አደዲሰ አባባ በከባድ ብረቶች የተበከሉ ቦታዎች በብዛት ይገኛሉ። በዚህ ሥራ ውስጥ ስድስት የከባድ ብረቶች ማለትም፣ ክሮምሚየም (Cr)፣ ሊድ (Pb)፣ ካድሚየም (Cd)፣ ኒኬል (Ni) ኮፐር (Cu) እና ዚንክ (Zn) ብክለት ለማጥናት በአፈር ውስጥ እና በተለያዩ የእጽዋቶች አካላት  (ቅጠሎች፤ግንድ እና ስር) ላይ ምርመራ ተደርጓል። በተመረጡ እፅዋት (በችግኞች እና ያደጉ ተክሎች)፣ በደረቅ እና ዝናባማ ወቅቶች የአቶሚክ አብዞርቢሽን ስፔክትሮፎቶሜትር በመጠቀም ምርመራ ተደርጓል። በባዮ ኮንሰንትሬሽን ፋክተር (BCF)፣ ትራንስሎኬሽን ፋክተሮች (TF) እና ባዮአኩሙሌሽን ኮፊሸንት (BAC) እሴቶች ላይ በመመርኮዝ የፋይቶሬሜዲሽን ውጤታማነት ተብራርቷል። እንዶድ BCF, TF እና BAC> 1 ለ Zn, Pb, Ni, Cu እና Cd ሰንሰል ያሳየው BCF, TF እና BAC> 1 ለ Zn, Cu, Ni እና Cr; እንደዚሁም

and BAC > 1 for Zn, Pb, Ni, Cu and Cd Adhatoda schimperiana gave BCF, TF and BAC > 1 for Zn, Cu, Ni and Cr; likewise, BCF, BAC and TF values of > 1 were noted in Solanum incanum for Zn, Cu, Pb and Ni. Based on these scenarios, the three plants could be utilised for phytoextraction of contaminated soil. Conversely, BCF and BAC for Cr levels in tissues of Phytolacca dodecandra were all < 1, which indicates unsuitability for phytoremediation of Cr in contaminated soils. Besides, Adhatoda schimperiana retained Pb and Cd in their roots showing root BCF > 1, while BAC and TF < 1, which highlights its suitability for phytostabilization. Moreover, BCF, TF and BAC values of < 1 noted for Cr and Cd in Solanum incanum reveal that Solanum incanum may not be a good candidate for remediation of Cr and Cd contaminated environments. In conclusion, results from this study revealed that the selected plants can accumulate substantial amounts of the above trace metals in their tissues and can serve as prospective phytoremediators of most of these metals. Phytoextraction and phytostabilisation were the main mechanisms of remediation in this study.

**Keywords:** Contaminated soil; heavy metals; plant uptake; Translocation factor; Bioconcentration factor; Phytoremediation; Phytoextraction; Phytostabilization.

እምቧይ BCF፣ BAC እና TF > 1 ውጤት ለZn፣ Cu፣ Pb እና Ni ተመዝግቧል። በመቀጠልም፣ በነዚህ ሁኔታዎች ላይ በመመስረት፣ ሦስቱ እፅዋቶች የተበከለ አፈርን ለማፅዳት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ተረጋግጧል። በተቃራኒው፣ በእንዶድ ሁሉም ቲሹዎች ውስጥ የCr BCF እና BAC <1 ናቸው። ይህም የሚያሳየው በተበከለ አፈር ውስጥ ለ Cr ለፋይቶሬሜዲሽን እንዶድ ውጤታማ አለመሆኑን ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሰንሰል ለPb እና ለCd BCF > 1 ሲያሳይ BAC እና TF <1 ተመዝግቧል ይህም ለፋይቶስታቢላይዜሽን ተስማሚ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም፣ BCF፣ TF እና BAC< 1 ለ Cr እና Cd በ እምቧይ የተገለጹት እምቧይ በ Cr እና Cd የተበከሉ አካባቢዎችን ለማከም ውጤታማ ስለመሆኑ ጥናቱ አሳይቷል። በአጠቃላይ፣ ከዚህ ጥናት የተገኙ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የተመረጡት እፅዋት ከላይ የተጠቀሱትን መርዛማ ብረቶችን በከፍተኛ መጠን በአካላቸው ውስጥ ሊያከማቹ እንደሚችሉ እና ለአብዛኞቹ መርዛማ ብረቶች ፋይቶሬሚዲያተሮች ሊሆኑ ይችላሉ። በዚህ ጥናት ውስጥ Phytoextraction (ማከማቸት) እና phytostabilization (ማረጋጋት) ዋና የማከሚያ ዘዴዎች ሆነው አገልግለዋል።

**ቁልፍ ቃላት:**- የተበከለ አፈር፤ ከባድ ብረቶች፤ የእፅዋትን መቀበል፤ ትራንስሎኬሽን ፋክር፤ ባዮኮንሴንትሬሽን ፋክተር፤ ፋይቶሬሜድዲሽን፤ ፋይቶኤክስትራክሽን፤ ፋይቶስታቢላይዜሽን

# Native tree species-based afforestation/ reforestation for carbon sequestration: contributions to sustainable development through clean development mechanisms in Ethiopia

Assefa Tofu Chofore

## ABSTRACT

The daunting tasks of responding to climate change and ensuring sustainable development (SD) are high on the political agenda among world leaders. From the onset, the clean development mechanism (CDM) outlined in Article 12 of the Kyoto Protocol (KP), state that CDM activities should contribute to SD in the host country while reducing greenhouse gas (GHG) emissions. Nevertheless, many scholars have criticized CDM for failing to deliver on its twin objectives. In Ethiopia in particular, there was lack of afforestation/ reforestation (A/R) CDM research specific to the nation; specifically, research as to whether A/R-CDM met the stipulated twin objectives of SD and mitigation (reducing GHG). This study was conducted in the Humbo district of Wolyaita Zone, Southern Nations - Nationality and People Regional (SNNPR) state of Ethiopia, where A/R-CDM was implemented in pursuit of these twin objectives. Humbo is located between 6°46’48.47 and 6°41’04.28N; and between 37°48’35.44 and 37° 55’14.51E, between altitudinal gradients 1 200 and 1 900 m.a.s.l. The climate of the study area is characterised by annual temperatures between 25°C and 28°C, and by total annual rainfall between 800 to 1 000 mm. The objectives of the study were to quantify the change of above ground and below ground carbon pools of native tree species;

# ሀገር በቀል ዛፎችን መሰረት ያደረገ የደን ልማት ለካርቦን Aልቀት መቀነስ - በኢትዮጵያ ለዘላቂ እድገት ለማምጣት ከብክለት የጸዱ የልማት ዘዴዎች የመጠቀም አስተዋጽኦ፤

በአሰፋ ጦፉ ጬፎሬ

## አጠቃሎ

ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ የመስጠት እና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ለዓለማችን መሪዎች አስጨናቂ የፖለቲካ አጀንዳዎች ናቸው። በኪዮቶ ፕሮቶኮል (KP) አንቀጽ 12 ላይ የተገለጹት የንፁህ ልማት ዘዴዎች አንዱ ነጥብ፣ በአስተናጋጅ ሀገሮች የግሪንሀውስ ጋዝ (GHG) ልቀትን በመቀነስ ለዘላቂ አበርክቶ ልኖራቸዉ ይገባል ይላል። ቢሆንም፣ ብዙ ምሁራን እነዚህን አላማዎች ማሳካት አላሳኩም በማለት ተችተዋል። በተለይ በኢትዮጵያ የደን ልማት ጉዞ የሲዲኤም (CDM) ጥናት አልተደረገም። በተለይም A/R ንፁህ የልማት ዘዴ፣ (A/R CDM) የተደነገጉትን የኤስዲ (SD) መንትያ አላማዎችን ማሟላቱን እና GHG መቀነስን ላይ ያተኮረ ምርምር አልነበረም። ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ በወላይታ ዞን ሁምቦ ወረዳ ነው፡፡ ሁምቦ በ6°46’48.47 እና 6°41’04.28N መካከል የሚገን ሲሆን፤ በ 37 ° 48’35.44 እና 37 ° 55’14.51E ከፍታ መካከል፣ 1200 እና 1900 m.a.s.l. ይገኛል። የጥናቱ አካባቢ የአየር ንብረት አመታዊ የሙቀት መጠን ከ25°ሴ እስከ 28°ሴ ሲሆን፣ በአጠቃላይ አመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ800 እስከ 1000 ሚ.ሜ. ነው። የጥናቱ ዓላማ የሀገር በቀል ዛፎችን ከመሬት በላይ እና ከመሬት በታች ያለ የካርቦን ጠመዳ መጠንን ለመለካት፤ የ FMNR የደን ልማት ስራዎችን ሳቢነትና ውጤታማነት ለመገምገም፤ የA/R-CDM ለማህበረሰቡ የሚያበረክተውን ዘላቂ ልማተ አስተዋጽኦ ለመተንተንና በአገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች ላይ የተመሰረተ A/R-CDM የአየር ንብረት ፖሊሲ ውጤታማነትን ለመገምገም ነው፡፡ ከመሬት በላይ ባዮማስ (AGB) እና ከመሬት በታች ባዮማስ (BGB) የካርበን ጠማጆችን (pools) አስመልክቶ ከአገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች

to assess the attractiveness of FMNR forestry practices; to examine A/R-CDM contributions to community level SD; and to assess the effectiveness of the climate change mitigation policy founded on native tree species-based A/R-CDM. Data regarding above ground biomass (AGB) and below ground biomass (BGB) carbon pools of native tree species was collected through non-destructive techniques to quantify the change in carbon sequestration and associated carbon trading. A multi-stage random cluster household (HH) sampling approach was used to assess the attractiveness of farmer managed natural regeneration (FMNR) forestry practice. To examine the contribution of A/R-CDM to community level SD, three dimensions of SD were evaluated, namely (local) environmental, social, and economic. Two indicators were considered per each dimension. With regard to local environmental SD, community access to natural resources, as well as changes to the local climate were considered. With regard to the social dimension, job creation and changes to social support structures were considered. With regard to the economic dimension, economic activities of the area and local skill development were considered. Focus group discussions and key informant interviews were used to triangulate the survey as well as to assess policy perspectives. Results revealed that the Humbo native tree species-based A/R-CDM, which employed FMNR forestry practices, sequestered a net total of 73,138; 84,848; 103,769 and 111,657 $tCO_2e$ along 2011, 2014, 2015 and 2016 years, respectively, across 2,728 ha. In terms of carbon leakage due to fuel wood collection activity displacement, a net zero was found since the average volume of fuelwood collected from the project area, after the area was closed off, was found to be 5.1 - 6.1 $M^3$, while before the area was closed

ላይ ያለውን ለውጥ ለማጥናት መረጃዎች ተሰብስበዋል። በዚህ ጥናት ባለ ብዙ ደረጃ የዘፈቀደ ክላስተር ቤተሰብ የናሙና አወሳሰድ፣ በገበሬ የሚተዳደር የተፈጥሮ እድሳት (FMNR) የደን ልማትን ማራኪነት ለመገምገም ጥቅም ላይ ውሏል። የA/R-CDM በማህበረሰብ ደረጃ ዘላቂ ልማት ያበረከተውን አስተዋፅኦ ለማጥናት ሶስት የዘላቂ ልማት መለኪያዎች ተገምግመዋል፤ እነሱም፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ናቸው። በእያንዳንዱ መለኪያዎች ሁለት ሁለት አመልካቾች ተወስደዋል። ከአካባቢያዊ መለኪያዎች ጋር በተያያዘ፣ የህብረተሰቡ የተፈጥሮ ሀብት ተደራሽነት፣ እንዲሁም በአካባቢው የአየር ንብረት ላይ የሚታዩ ለውጦች ግምት ውስጥ ገብተዋል። ከማህበራዊ ገጽታ ጋር በተያያዘ፤ የስራ እድል ፈጠራና የማህበራዊ ድጋፍ መዋቅራዊ ለውጦች የተወሰዱ ሲሆን፣ ከኢኮኖሚው ልኬት አንፃር የአከባቢው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እና የአካባቢ ክህሎት ልማት ታሳቢ ተወስደዋል። የዳሰሳ ጥናቱን በሶስት ክፍል ለማስቀመጥና የፖሊሲ አመለካከቶችን ለመገምገም የሚያግዙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ የትኩረት ቡድን ውይይቶችና ቃለ-መጠይቆች ጥቅም ላይ ውለዋል። የጥናቱ ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት፣ የFMNR የደን ልማት በA/R-CDM ላይ የተመሰረተው የሁምቦ ሀገር በቀል የዛፍ ዝርያ፣ በድምሩ 73,138፣ 84,848፣ 103,769 እና 111,657 $tCO_2e$ እንደቅደም ተከተሉ በ2011፣ 2014፣ 2015 እና 2016 በአ.አ በ2,728 ሄክታር ላይ ተጠምድዷል። በማገዶ እንጨት መሰብሰብ እንቅስቃሴ ምክንያት የባከነ የተጠወደ ካርበን (Leakage) በተመለከተ ከፕሮጀክቱ አካባቢ የሚሰበሰበው አማካይ የየማገዶ አንጨት መጠን ከ 5.1 - 6.1 $M^3$, ከ 5.1 - 6.1 $M^3$ የባከነ የተጠወደ ካርበን መጠን ዜሮ ሆኖ ተገኝቷል። ይህ ቁጥር ከፕሮጀክቱ በፊት 4.3 $M^3$ ነበር። ይህ የሆነበት ምክንያት ፕሮጀክቱ FMNR የደን ልማቶችን በመጠቀሙ ነው። በተመሳሳይ በእንስሳት ግጦሽ ምክንያት የተከሰተው የባከነ የተጠወደ ካርበን ዜሮ ሆኖ ተገኝቷል፤ ምክንያቱም ከፕሮጀክቱ አካባቢ ከአራት ዓመታት በኋላ በአካባቢው ተዘግቶ በነበረው መሬት ላይ የሚግጡ እንስሳት ቁጥር 11,383 ከብቶች, 429 አህዮች እና 4,108 ፍየሎች ከፕሮጀክቱ በፊት ከ8,684 ከብቶች እና 2,288 ፍየሎች ከፍ በማለቱ ነው። በሌላ አነጋገር ከፕሮጀክቱ ቦታ አጠገብ ባለው መሬት ላይ

off, that number was 4.3 $M^3$. This was due to the project employing FMNR forestry practices. Similarly, the leakage due to livestock grazing activity displacement also was found to be a net zero, since the number of animals grazing on land adjacent to the project area after four years of the area's being closed off reached 11,383 cattle, 429 donkeys and 4,108 goats, unlike 8,684 cattle and 2,288 goats before the project. In other words, the number of livestock owned by farmers on the land adjacent to the project site was not adversely affected by the closing off of the site, which prevented grazing on the area allocated to A/R-CDM. The livestock management training provided by the project developer improved the farmers' rearing efficiency. Another expected leakage due to soil pitting for A/R was also found to be nil since soil disturbance did not take place because of FMNR practices. These results indicated that systematic regeneration of native tree species through FMNR forestry practices is an effective method to develop carbon sinks. From the point of view of FMNR attractiveness, the results revealed that the practice improved land cover change. The use of FMNR avoided the projected eight years reforestation investment cost of US$ 2,751,312.00 which could have been used if plantation forestry was undertaken. This showed that Humbo A/R-CDM might not have happened if FMNR is had not been introduced, as CDM has no pre-finance mechanism. With regard to community level SD contributions, the establishment of forest protection and development farmers' cooperatives, as well as the granting of communal land-user rights certification, resulted in legal ownership of the land to the community, whereas before, the land was considered "no man's land," and subject to open access. The land-user rights and carbon ownership in turn

በአርሶ አደሮች ለተያዙ የቤት እንስሳት የቦታው መዘጋት አሉታዊ ተጽእኖ ባለመፍጠሩ፣ ለA/R CDM በተከለለዉ ቦታ ላይ ግጦሽ እንዳይደረግ አድርጓል። ይህን ያስቻለዉ በፕሮጀክት አልሚዎች የተሰጠው የእንስሳት እርባታ አስተዳደር ስልጠናም የአርሶ አደሩን የግጦሽ አስተዳደር ብቃት አሻሽሏል። በFMNR መሰረት መጠቀም ምክንያት በአፈር መረባበሽ አልተከሰተም የባከነ የተጠወደ ካርበንም አልተመዘገበም። እነዚህ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በFMNR መሰረት ሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን የካርቦን ጠመዳ ልማት ውጤታማ ዘዴ ነው። FMNRን መጠቀሙ የደን ሽፋን አሻሽሏል። FMNR ን መጠቀም ሊወጣ የሚገባዉን 2,751,312.00 የአሜሪካ ዶላር የደን መልሶ ማልማት ወጪንም አስቀርቷል። ይህ የሚያሳየው FMNRን ባንጠቀም ሁምቦ A/R-CDM ላይኖር እንደሚችል ነው ፡ ፡ በማህበረሰብ አቀፍ ደረጃ የኤስዲ አስተዋፅዖን በተመለከተ የደን ጥበቃና ልማት፣ የገበሬዎች ህብረት ስራ ማህበራት መመስረት፣ የጋራ የመሬት ተጠቃሚነት መብት መረጋገጥ፣ ለህብረተሰቡ ህጋዊ የመሬት ባለቤትነት አስገኝቷል። የመሬት ተጠቃሚ መብቶች እና የካርቦን ባለቤትነት ህብረተሰቡ ከአለም አቀፍ የካርበን ብድር ገዥ ጋር ውል እንዲፈራረም አስችሎታል። ከአካባቢው የአየር ሁኔታ አንጻር የአገር በቀል ዛፍ ዝርያዎችን በ FMNR አሰራር መተግበሩ በሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴ፣ መስከረም (JJAS) እና መጋቢት፣ ሚያዝያ እና ግንቦት (MAM) በአከባቢዉ ዝናብ መጨመርንም አሳአቷል። ይህም የአገር በቀል ዛፍ ዝርያዎችን መሰረት ያደረገ A/R CDM ፕሮጀክት፣ የአካባቢውን ማይክሮ አየር ሁኔታ በማሻሻል ረገድ ሚና እንዳለው አሳይቷል። ከስራ እድል አንፃርም እንደ ዛፍ ምልመላ፣ ደን መሳሳት፣ ደን ጥበቃ፣ የህብረተሰቡ የጋራ መጋዘን እና የዱቄት ወፍጮ ጥበቃ ያሉ የስራ እድሎች ተፈጥረዋል። በሁምቦ A/R-CDM ውስጥ ከተሳተፉት ጋር ሲነጻጸር የስራ እድሎች መገኘት በጣም ከፍ ያለ ነው። በማህበራዊ ድጋፍ አወቃቀሮች ረገድ፣ አሥር ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የፕሮጀክቱ ባለቤት ሆነው የተቋቋሙት የሁምቦ A/R CDM ሰባት የህብረት ስራ ማህበራት ወደ አንድ የደን ጥበቃና ልማት ዩኒየን አድገዋል። ከኢኮኖሚያዊ ልኬት አንፃር፣ ፕሮጀክቱ በአጠቃላይ US$ 3,873,298.00 ዋጋ ያለው የካርቦን ክሬዲት ኮንትራት ከUS$ 4.4 ለ1 $tCO_2e$ ዋጋ ተፈራርሟል። ይህም

empowered the community to sign a contract with an international carbon credit buyer. In terms of the local microclimate, the regeneration of native tree species was correlated with increased rainfall in the area in June, July, August and September (JJAS) and March, April and May (MAM). This suggested that the native tree species-based A/R-CDM project played a role in improving the local micro-climate. In terms of sociological SD, the study showed that new employment opportunities were created including tree pruning, thinning, forest guarding, and jobs at the community warehouse and community flourmill. The availability of employment opportunities was significantly higher for those who participated in the Humbo A/R-CDM, when compared to those who didn't. In terms of social support structures, in less than ten years, seven Humbo A/R-CDM project owner farmers' cooperatives, initially established as owners of the project, evolved into one forest protection and development union. This enabled the institutionalisation of grassroots organisations towards a common communal and international agenda of care for the environment. In terms of economic effects, the project enabled a carbon credit contract worth a total of US$ 3,873,298.00, signed at the sell rate of US$ 4.4 per tCO2e, for a total of 880,295 tCO2e across a 30-year crediting period. This is a new business model for the community, the country, and global businesses, all doing their part in climate change mitigation - CDM. As of the first A/R-CDM verification, the community received a total of US$ 321,807.2 in 2011. Consequently, the community received 373,331.2 in 2014, 456,583.6 in 2015 and 491,290.8 in 2016. In terms of revenue from logging, selective harvesting is planned to take place in years 12, 24 and 36. The community is projected to earn at least US$ 15,150.00 per ha[1] (a

በ30 ዓመታት የብድር ጊዜ ውስጥ በድምሩ 880,295 $tCO_2e$ ለማስገኘት ያስችላል። ይህ ለማህበረሰቡ፣ ለአገሪቱ እና ለአለም አቀፍ ንግዶች አዲስ የንግድ ሞዴል መሆኑንማ ለኢትዮጵያ አመልክቷል። ከመጀመሪያው A/R ንፁህ የልማት ዘዴ ማረጋገጫ ጀምሮ በ2011 ህብረተሰቡ በድምሩ 321,807.2 ዶላር አግኝቷል። ቀጥሎም ማህበረሰቡ በ2014 373,331.2፣ በ2015 456,583.6 እና በ2016 እ አ አ 491,290.8 ገቢ አግኝቷል። በተጨማሪም፣ በየ12፣ 24 እና 36 አመት ለማካሄድ ታቅዶ በነበረዉ በ12ኛው አመት ብቻ የደን ምርት ቢያንስ 15,150.00 ዶላር በሄ/ር አና አጠቃላይ 3.9 ሚሊዮን ዶላር ገቢ ልያስገኝ እንደሚል ተተንብዮአል። እነዚህ የልቀት ቅነሳ A/R CDM ጥቅማጥቅሞች፣ ኢትዮጵያ 36,434,400 ሄ/ር መሬት ለA/R ንፁህ የልማት ዘዴ ተገቢ ቢኖራትም፣ ሀገሪቱ A/R ንፁህ የልማት ዘዴን ለመተግበር ባለመቻሏ መጠነ ሰፊ ጥቅማጥቅሞች ቀርተውባታል። በኢትዮጵያ በዓይነቱ ብቸኛው የሆነው የሁምቦ A/R CDM ፕሮጀክት ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዙ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌዎችን፣ በተለይም ከመሬት ተጠቃሚ መብቶችና ህልውና ጋር በተያያዙ የፖሊሲ ምቹነት ዙሪያ የተገኙ የምርምር ውጤቶች አመልክተዋል። ከአለም አቀፍ ጉዞ ጋር የሚስማማ ደረጃውን የጠበቀ የደን ልማት ማዳሄድ፣ በተጨማሪም የኪዮቶ ፕሮቶኮል (KP) በወቅቱ ማፅደቁ፣ የተሰየመ ብሄራዊ ባለስልጣን (ዲ ኤን ኤ) ማቋቋም እና በዲኤንኤ ለፕሮጀክት የፀደቀ መመሪያ መኖሩ ምቹ ሁነታዎች መኖሩ ተረጋግጧል። ነገር ግን የካርቦን ባለቤትነት መብትን ግልጽ ማድረግ እና ለደን ካርበን ጥቅማ ጥቅም መጋራት ዘዴን መዘርጋት አንደሚያስፈልግ ግኝቶቹ አሳይተዋል። በተጨማሪም ሁምቦ A/R-ንፁህ የልማት ዘዴ በአየር ንብረት ማህበረሰብ ብዝሃ ህይወት (CCB ) ሰርተፍኬት መልክ ተጨማሪ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የበጎ ፈቃድ ግምገማዎችን አድርጓል። ነገር ግን፣ ለማህበረሰቡ እና ለፕሮጀክት ገንቢ ከCCB የወርቅ ደረጃ ማረጋገጫ ቢሰጠውም፣ ያስገኛቸው ምንም አይነት ጥቅማጥቅሞች አልነበሩም፤ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ አሻሚነት ከመጀመሪያው ሊጸዳ ይገባል። ይህ የሚያመለክተው በገበያ ወይም በውጤት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ አምጪ ጋሶች ለመቀነስ በሚሰራበት ጊዜ ሁሉ ድንጋጌዎቹን መረዳት እንደሚያስፈልግ ነው።

total of US$ 3.9 million) from the first forest harvest in year 12 alone. These benefits in emission reduction (ER) and SD suggest that massive cross-dimensional benefits were foregone due to the country's refusal to welcome A/R-CDM in its first commitment period, despite having 36,434,400 ha of land eligible for A/R. This research results in the area of policy perspectives indicated that the Humbo A/R-CDM project, the only one of its kind in Ethiopia, was made possible by environment related constitutional provisions, especially those pertaining to land-user rights, and the existence of a nationally standardized definition of a forest that complies with the international range. Additionally, the timely ratification of the Kyoto Protocol (KP), the establishment of a designated national authority (DNA) and a letter of approval by the DNA to the project developer were found to be enablers. Yet, defining land use, clarifying carbon ownership rights and bringing an inclusive benefit sharing mechanism for forest carbon are among the key instruments the country has yet to put in place to prove local readiness for such development opportunities. The Humbo A/R-CDM also undertook voluntary assessments to obtain additional certification in the form of the Climate Community Biodiversity (CCB) certification, and was certified to be of gold standard for its premium. However, there were no benefits to the host community and the project developer from the CCB gold standard certification. Such ambiguity could have been cleared from the onset. This implied whenever going for market and/or result-based climate change mitigation, it is necessary to understand the provisions. This study revealed that the Humbo native tree species-based A/R-CDM via FMNR forestry practices met the CDM twin objectives as specified in Article 12 of the KP in 1997, namely the double

ይህ ጥናት እንደሚያሳየው በFMNR የደን ልማት በኩል በሁምቦ ሀገር በቀል ዘፎች ላይ የተመሰረተዉ A/R CDM በ1997 በኪዮቶ ፕሮቶኮል አንቀጽ 12 ላይ በተገለፀው መሰረት የ ንፁህ የልማት ዘዴ መንትያ አላማዎችን ያሟላ ሲሆን፣ እነዚህም የ GHG ልቀትን መቀነስ እና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን የዘላቂ ልማት ግቦችን ማሳደግ መቻሉ ናቸው። በዚህ ጥናት የተገኙች ውቴቶች ከላይ የተገለጹት ቢሆኑም፣ በሁምቦ A/R-ንፁህ የልማት ዘዴ፣ ቦታ ሁሉንም የካርቦን ጠመዳ ቻይ አካላትን ዉጠቶችን ለመረዳት ተጨማሪ ጥናት ያስፈልጋል።

**ቁልፍ ቃላቶች፡-** የደን ልማት/ደን መልሶ ማልማት፣ ንፁህ የልማት ዘዴ፣ የካርቦን ዝርጋታ፣ የገበሬው የተፈጥሮ እድሳት፤፣ ዘላቂ ልማት እና የአየር ንብረት ለውጥ፤

aims of achieving mitigations of GHG emissions and assisting developing countries in SD. Yet, more research is needed to understand all eligible A/R carbon pools sequestered at Humbo A/R-CDM site.

**Keywords:** Afforestation/reforestation; clean development mechanism; carbon sequestration; farmer managed natural regeneration; sustainable development and climate change.

## Policy responses to urban environmental problems: the case of solid and liquid waste management in the major urban centres of Tigray National Regional State

Gebretsadkan Gebremichael Berhe

### ABSTRACT

The highly accelerated rates of growth that the cities and towns of the Tigray National Regional State witnessed in the recent past has been followed by a growing problem of urban and peri-urban environmental degradation in the region. Environmental deterioration owing to poor waste management does not only adversely affect human health and well-being but also tends to hold back the rates of growth of the urban and regional economy. The main purpose of this research has, therefore, been to examine the extent to which urban environmental problems in general and shortcomings in waste management issues in particular have achieved commensurate policy responses from regional and local authorities as the threats they posed to good

## ለከተሞች የአካባቢ ችግሮች የፖሊሲ ምላሾች፡ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዋና ዋና ከተሞች የደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አስተዳደር/አያያዝ ላይ የተደረገ ጥናት፤

በገብረጻድቃን ገብረሚካኤል በርሀ

### አጠቃሎ

በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ከተሞች ያሳዩትን የተፋጠነ የዕድገት መጠን ተከትሎ፣ የከተማና የከተማ ዙርያ አካባቢያዊ መራቆት እየጨመረ ነው። በደካማ የቆሻሻ አያያዝ ምክንያት አካባቢ መበላሸቱ በሰው ጤና እና ደህንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ፣ የከተማ እና የክልል ኢኮኖሚ እድገትን ወደ ኋላ የመመለስ አዝማሚያ አለው። የዚህ ጥናት ዋና አላማ የከተማ አካባቢያዊ ችግሮች፣ በተለይም ደግሞ፣ የቆሻሻ ኣስተዳደር ድክመቶች በባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ እየጠነከሩ መጥተው በማህበረሰቡ አኗኗርና እና ስራ ላይ ያደረሱትን አደጋዎች፣ ከክልል እና ከአከባቢው ባለስልጣናት የተመጣጠነ የፖሊሲ ምላሾች ማግኘታቸውን ለመፈተሽ ነው። በአጭሩ በዚህ ጥናት የአካባቢ ችግር በፖሊሲ ደረጃ ያገኘውን ትኩረት፣ የተከተለውን የአተገባበር ስልት እና የተግባራዊ አፈጻጸሙ ደረጃ በጥልቀት ተዳሷል። ለዚህም ተመራማሪው የምርምር ፍልስፍናውን እና አቀራረቡን እንደ ቅደም ተከተላቸው

living and working conditions intensified over the decades. In short, the status of environmental considerations at policy level and their implementation strategies and degree of execution at the grassroots level has been thoroughly assessed in this study. To this end, the researcher has primarily defined his research philosophy and approach as pragmatism and mixed methods, respectively. The convergence model of a mixed methods triangulation design has been used. He employed a semi-structured questionnaire, in-depth interviews and observation as instruments of primary data collection. Household heads, personnel and decision-makers were basic sources of data. Multi-stage sampling techniques were used to select sample units that involve both probability and non-probability sampling techniques. The researcher used descriptive statistical techniques and thematic content analysis techniques supported by SPSS and Atlas ti programs to analyse the primary data. The main findings of the study revealed in many ways that urban liquid waste and solid waste management practices in the Tigray National Regional State is woefully far from adequate. The main indicators of the markedly low level of development of the region's municipal waste management services include lack of appropriate liquid waste collection and treatment systems; limited access to and substandard private and public toilet services; lack of and poor management of liquid waste dumping sites; poor solid waste collection service delivery; very low collection coverage, and poorly managed landfills. The study has also shown that the responses of the region's policy-makers to such unquestionably severe problems are not worth mentioning. Nothing shows this better than the fact that the region has no municipal waste management policy. The other major weakness of the policy-makers

ፕራግማቲዝም እና ድብልቅ ዘዴዎች በማለት ገልጿል። የድብልቅ ዘዴዎች የሶስት ማዕዘን ንድፍ የመገጣጠም ሞዴልን (beem) ጥቅም ላይ አውለዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ በከፊል የተዋቀረ መጠይቅ፣ ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ እና መስክ ምልከታን የመጀመሪያ_ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አድርጎ ተጠቅሟል። በዚህም የቤተሰብ መሪዎች፣ የቆሻሻ አስተዳደር ሰራተኞች እና ውሳኔ ሰጪዎች መሰረታዊ የመረጃ ምንጮች ነበሩ። ሁለቱንም የይሆናል እና_የማይሆን የናሙና አመራረጥ ቴክኒኮችን የሚያካትቱ የባለብዙ ደረጃ ናሙና አመራረጥ ቴክኒኮች  የናሙና ኣባላትን ለመምረጥ ጥቅም ላይ ውለዋል። ተመራማሪው ዋናውን መረጃ ለመተንተን በSPSS እና Atlas ti Programs የተደገፉ ገላጭ ስታቲስቲካዊ ቴክኒኮችን እና ጭብጥ ይዘት ትንተና ቴክኒኮችን ተጠቅመዋል። የጥናቱ ዋና ግኝቶች በትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የከተሞች የፈሳሽ ቆሻሻ እና የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር አሰራር እጅግ ደካማና የወረደ መሆኑን በብዙ መልኩ አሳይቷል። በክልሉ የማዘጋጃ ቤት የቆሻሻ ኣስተዳደር አገልግሎቶች ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ዋና ዋና አመልካቾች ከሆኑት መካከል፣ ተገቢ የፈሳሽ ቆሻሻ አሰባሰብ እና የማከም ስርዓት አለመኖር፣ የግል እና የህዝብ መጸዳጃ ቤት አገልግሎቶች ውስን እና ከደረጃ በታች መሆን፣ የፈሳሽ ቆሻሻ መጣያ ቦታዎች እጥረት እና ደካማ አያያዝ፣ ደካማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ አገልግሎት አሰጣጥ፣ በጣም ዝቅተኛ የመሰብሰብ አገልግሎት ሽፋን እና በአግባቡ የማይተዳደሩ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ሆነው ተገኝተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ እንደሚያሳየው የክልሉ ፖሊሲ አውጪዎች ለእንደዚህ አይነት ከባድ ችግሮች የሰጡት ምላሽ ከግምት የሚገባ አይደለም። ይህን ደግሞ በክልሉ የማዘጋጃ ቤት የቆሻሻ አወጋገድ ፖሊሲ ኣለመኖሩ በራሱ ከማንም በላይ በተሻለ ሃቁን የሚያሳይ ነው። ሌላው በዚህ ረገድ የፖሊሲ አውጪዎች ዋነኛ ድክመት በሴክተሩ ለሚታየው አጠቃላይ ተቋማዊ የአቅም ድክመት ምላሽ አለመስጠት ነው። ምንም እንኳን ስልታዊ ጠቀሜታ ቢኖረውም፣ የ4Rs መርህ፣ እንደ ቆሻሻ አስተዳደር ዘዴ፣ በአካባቢ እና በክልል አስተዳደር ችላ ተብሏል። በዚህም መሰረት መንግስት የ4Rs ዘዴዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እና የሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት እና በቆሻሻ አወጋገድ ስራ ላይ የተሰማሩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት፤ የተቋማዊ የፋይናንሺያል እና

in this regard is their irresponsiveness to the deficient institutional capacities of the sector as a whole. What is more, despite its strategic importance, the 4Rs principle, as a waste management approach, has also been overlooked by the local and regional administration. Accordingly, the researcher recommends that the government should work aggressively on implementing the 4Rs approach and strengthen the institutional and financial and material capacity of the relevant public institutions and MSEs involved in waste management activities.

**Keywords:** Waste; waste characteristics; waste collection service; spatial disparities; on-site waste handling; waste management approach; policy responses.

ቁሳዊ (የማቴሪያል) አቅማቸውን ለማጠናከር መስራት እንዳለበት ተመራማሪው አሳስበዋል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- ቆሻሻ፣ የቆሻሻ ባህሪያት፣ የቆሻሻ አሰባሰብ አገልግሎት፣ የከቦታ ቦታ ልዩነቶች፣ የቦታው ላይ(on-site) የቆሻሻ አያያዝ፣ የቆሻሻ ኣስተዳደር ዘዴዎች፣ የፖሊሲ ምላሾች፤

## Assessment of industrial waste load of River Borkena and its effect on Kombolcha town and the surrounding communities

Kebebew Kassaye Beyene

### ABSTRACT

Water pollution is a major threat to the human population and dumping of pollutants into the water body results in rapid deterioration of water quality and affects the ecological balance in the long run. The present study was undertaken to assess pollution load from river Borkena. In urban and suburban parts of Kombolcha, the use of industrial wastewater for irrigation purposes is a common practice. Local farmers in Borkena watershed use the wastewater to irrigate their agricultural fields for cultivation of vegetables. But they suffered from loss of productivity of leafy vegetables and skin injury because of their exposure to the wastewater during irrigation practices. That is why this

## የቦርከና ወንዝ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ በኮምቦልቻ ከተማ እና አካባቢው ማህበረሰቦች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ፤

ክበበው ካሳዬ በየነ

### አጠቃሎ

የውሃ ብክለት በሰው ልጆች ላይ ትልቅ ስጋት ከሆነ ውሎ አድሯል። የውሀ ብክለት የውሃ ጥራት በፍጥነት እንዲያሽቆለቁል ከማድረጉም በላይ ሥነ-ምህዳራዊ ሚዛን ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። የዚህ ጥናት ዋና አላማ ከቦርከና ወንዝ የሚደርሰውን የብክለት ጫና ለመገምገም ነው። በኮምቦልቻ ከተማ እና የከተማ ዳርቻዎች በኢንዱስትሪ ተረፈ-ምርት የቆሸሸ ውሃን ለመስኖ አገልግሎት መጠቀም የተለመደ ተግባር ነው። በቦርከና ተፋሰስ የሚገኙ የአካባቢው አርሶ አደሮች ቆሻሻ ውሃን ለእርሻ ማሳቸውና ለአትክልት ልማት ይጠቀማሉ። በመሆኑም፣ በመስኖ ተግባር ወቅት ለቆሻሻ ውሃ በመጋለጣቸው በቆዳቸው ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዚህም የተነሳ፣ በቦርከና ወንዝ ላይ ያለውን የኢንዱስትሪ ቆሻሻ መጠን እና በተፋሰስ ውስጥ ባሉ ማህበረሰቦች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ላይ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። ይህ

study focused on assessing the amount of industrial waste load on river Borkena and its effects on communities in the watershed. The main aim of this study was to assess the physico-chemical characteristics of the River Borkena before and after industrial waste was discharged into it by the waste carrier small streams; and its environmental impact on the surrounding communities and vegetable farms. The methodology consisted of a basic survey to assess the physical and chemical characteristics of the river water, and a case study performed through focus group discussions with the community authorities and farmers in the study area who used the river water mainly for irrigation purposes. Sampling was conducted at six sites in the study area during low and high flow periods with an interval of three months for a period of one year in order to account for the seasonal hydrological cycle of the river water. Laboratory measurements of river water and leafy vegetables for metal concentration were determined to investigate the effect of the use of the river water for growing vegetables and other personal cases. The findings of this study showed that metal concentrations in leafy vegetables and irrigation water are within the permissible limits of FAO/WHO standards and not significant for the time being but will become a challenge in the near future if not well addressed. The concentrations of metals in leafy vegetables provide baseline data and it shows that, in the current situation, consumption of leafy vegetables grown in the study area may not have health risks in the context of metal concentrations. To avoid the entrance of metals into the food chain, municipal or industrial wastes should not be drained into the river and farmlands without prior treatment. The continuous monitoring of the soil, vegetable plant and irrigation water quality are prerequisites for the

ጥናት የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ወደ ወንዙ ከመፍሰሱ በፊት እና በኋላ ያለውን ልዩነት፣ ቆሻሻው የቦርከና ወንዝ የፊዚዮ-ኬሚካላዊ ባህሪያትን ላይ የሚያስከትለውን ለውጥና ለውጡ በአካባቢው ማህበረሰቦች እና የአትክልት እርሻዎች ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ መመርመር ነው። ጥናቱ የተከተለው ዘዴ፣ 1) የወንዙን ውሃ አካላዊ እና ኬሚካላዊ ባህሪያት ለመገምገም መሰረታዊ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤ 2) የወንዙን ውሃ በዋናነት ከሚጠቀሙ የማህበረሰብ አካላትና አርሶ አደሮች ጋር በትኩረት ቡድን ውይይት ማድረግ ናቸው። ለዚህም፣ የወንዙን ውሃ ወቅታዊ የሀይድሮሎጂ ዑደት ለመገመት በዝቅተኛ እና ከፍተኛ የውሃ ፍሰት ጊዜ ውስጥ በ 6 ቦታዎች ናሙናዎች ተወስደዋል። የወንዝ ውሃ እና ቅጠላማ አትክልቶች ለብረታ ብረት ክምችት የላብራቶሪ መለኪያዎች፣ የወንዙን ውሃ ለአትክልትና ለሌሎች ጉዳዮች ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስከትለውን ውጤት ለመመርመርም ተግባራዊ ተደርገዋል። የጥናቱ ግኝቶች በቅጠላማ አትክልቶች እና በመስኖ ውሃ ውስጥ ያለው የብረታ ብረት ክምችት በFAO/WHO መስፈርቶች በሚፈቀደው ገደብ ውስጥ የሚገኙ እንደሆኑ አሳይቷል። ነገር ግን በትኩረት ካልተሰራ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሁኔታው ፈታኝ እንደሚሆን ይጠበቃል። በቅጠላማ አትክልቶች ውስጥ ያለው የብረታ ብረት ክምችት መነሻ መረጃን ይሰጣል፤ እናም አሁን ባለው ሁኔታ በጥናቱ አካባቢ የሚበቅሉ ቅጠላማ አትክልቶችን መመገብ ከብረት ክምችት አንፃር የጤና አደጋ ላይኖረው እንደሚችል ጥናቱ ያሳያል። ብረታ ብረት ወደ ምግብ ሰንሰለት እንዳይገቡ ለመከላከል የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች ያለ ቅድመ ህክምና ወደ ወንዙ እና የእርሻ መሬቶች መፍሰስ የለባቸውም፡፡ የአፈር፣ የአትክልትና የመስኖ ውሃ ጥራት ላይ የሚደረግ ቀጣይነት ያለው ክትትል በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ የጤና አደጋዎችን ለመከላከል ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው። በመጨረሻም፣ ይህ ጥናት ለሚመለከታቸው የክልል እና የፌደራል የመንግስት መስሪያ ቤቶች የመረጃ ክፍተቶችን በመሙላት በተፋሰሱ ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦችን የሚጠቅሙ ደንቦችና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ እንደ ግብአት ሊጠቀሙበት ይችላል።

**ቁልፍ ቃላት:**- የውሃ ጥራት፣ ቅጠላማ አትክልቶች፣ የኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች፣ የመከታተያ ንጥረ ነገሮች፤

prevention of potential health hazards to human beings. Finally, this study fills the gaps in information for concerned regional and federal governmental offices and may use it as an input to design regulations and policies which benefits the communities in the watershed area.

**Keywords:** Water quality; leafy vegetables; industrial waste; trace elements.

## Assessing Farmers' Adaptation to Climate Change through Agroforestry Practices in Hadiya Zone, Ethiopia

Yohannes Horamo More

### ABSTRACT

Climate change negatively affects agricultural production, the natural resources base, and the livelihoods of communities. As such, adapting to climate change through agroforestry practices is important for sustainable agriculture. This study aimed to assess farmers' adaptation to climate change through agroforestry practices in the Hadiya zone, in Ethiopia. Stratified random sampling techniques were employed. Data were collected through structured and semi-structured questionnaires and from Landsat images. Data were analysed using SPSS version 23, ArcGIS10.3 and Participatory Learning Action tools. In this study, three major agroforestry systems, five common agroforestry practices, six major and seven minor associated food and cash crops, more than 14 common multipurpose tree species, four common tree propagation or seedling sources, nine common tree niches versus population and five common tree management practices were identified, analysed and recorded in the order of

## በኢትዮጵያ ውስጥ በሀድያ ዞን አርሶአደሮች የአየር ንብረት ለውጥ እንዲስማማ ለማድረግ በጥምር እርሻ ደን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ምዘና

በዮሐንስ ሆራሞ ሞሬ

### አጠቃሎ

የአየር ንብረት ለውጥ በግብርና ምርታማነት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝ፣ በማህበረሰብ የኑሮ መተዳደሪያ ሁኔታና ደረጃ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረ ይገኛል። የጥምር እርሻ ደን በራሱ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲስማማ ለማድረግ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች ውስጥ ሲሆን ለዘላቂ ግብርና ልማት በጣም ጠቃሚ ነው። ይህ ጥናትም የተመሠረተው በኢትዮጵያ ውስጥ በሀድያ ዞን አርሶአደሮች የአየር ንብረት ለውጥ እንዲስማማ ለማድረግ በጥምር እርሻ ደን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን ለመመዘን ነበር። ጥናቱ የተካሄደውም በደረጃ የተከፈለና እንዳመጣለት/እንዳገኘ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ በመጠቀም የተሠራ ነበር፡ ፡ የጭብጥ አሰባሰብም በከፊልና በሙሉ በታቀደ ቃለ መጠይቅ እና በሳተላይት ከመሬት በተወሰዱ ምስሎች ናሙና የተመሰረተ ነው። የተሰበሰበው ጭብጥ የተተነተነው በማህበራዊ ሳይንስ እስታትስቲክስ ፓኬጅ ዓይነት 23፣ አርክ.ጂ.አይ.ኤስ 10.3 እና ተሳትፎኣዊ ትምህርትና ጭብጥ ትመና መሣሪዎችን በመጠቀም ነበር። በዚህ ጥናት መሠረት 3 ዋና ዋና የጥምር እርሻ ደን መዋቅር፣ አምስት የጥምር እርሻ ደን አተገባበሮች፣ ተያያዥነት ያላቸው ስድስት ዋና ዋና እና ሰባት አነስተኛ የምግብና የገቢ ማመንጫ ሰብሎች፣

priority in adapting to climate change. The major finding from the focus groups or key informant interviews is that income generation is of primary importance in deciding whether to plant trees. Farmers preferred *Grevillea robusta* as the best agroforestry or multi-purpose tree species compared to other existing indigenous or introduced multi-purpose tree species. *Mellia azedarach* and *Cupressus lusitanica* were the least preferred tree species. The hierarchical multiple regression analysis revealed that climate change alone explained 27 percent of the variance in livestock production, $F (1, 290) = 104.84$, $P < .001$, $R = .52$, $R^2 = .27$; and that the climate changes alone explained 42 percent of the variance in crop production, $F (1, 290) = 213.62$, $P < .05$, $R = .65$, $R^2 = .42$. The land cover analysis indicated that over four decades, land under agricultural use increased throughout the period while land under shrubs decreased throughout the years from 1991–2017. Agroforestry systems and practices should be encouraged in the study area to enhance adaptation to climate change by addressing food, wood, and income needs. Consequently, this helps farmers to develop their livelihood assets.

**Keywords:** Climate change; adaptation; agroforestry adoption; smallholder farmers; land cover change; Ethiopia.

ከአሥራ አራት በላይ የሆኑ ዘርፈ ብዙ ጠቃሜታ ያላቸው የዛፍ ዓይነቶች፣ አራት የተለመዱ የችግኝ ማባዣ ምንጮች፣ ዘጠኝ የተለመዱ የዛፍ መትከያ ቦታዎች እና አምስት የጥምር እርሻ ደን ዛፎች አያያዝ ወይም እንክብካቤ ዘዴዎችን መለየት መተንተንና የአየር ንብረት ለውጥ እንዲስማማ ከማድረግ አንፃር በጠቀሜታ ደረጃቸው በተብራራ ሁኔታ መመዝገብ ተችሏል። ሌሎች የጥናቱን ግኝቶችበተመለከተ በናሙና ከተወሰዱ የጩብጥ ሰጪ ቡድኖች የተገኘ ትንተና መሠረት ምግብና ገቢ ማመንጨት የጥምር እርሻ ደን ተከላ ቀዳሚና ጠቃሚ ምክንያት እንደሆነ ታውቋል። ከዚህ ሌላ ዘርፈ ብዙ ጠቃሜታ ካላቸው ዛፎች ውስጥ የአርሶአደሮች ቀዳሚ ምርጫቸው ግራቪሊያ ሮቡስታ ሲሆን የመጨረሻ ምርጫቸውም ሜሊያ አዘደራች (ኒም) እና ኩፐርሰስ ሉስታኒካ (የፈረንጅ ጥድ) መሆናቸውንም ጥናቱ ያመለክታል፡፡ በማህበራዊ ሳይንስ እስታትስቲክስ ፓኬጅ ዓይነት 23 የሄራርኪያል ማልቲፕል ርግሬሽን የጩብጥ ትንተና ዘዴ እንዳመለከተው የአየር ንብረት ለውጥ ብቻውን 27 በመቶ ለውጥ በእንስሳት ሀብት ልማት ኤፍ(1፣290)=104. 84፣ ፒ<.001፣አር= 52፣አር$^{2,}$ = 27 እና የአየር ንብረት ለውጥ ብቻውን 42 በመቶ ለውጥ በሰብል ልማት ኤፍ(1፣290)=213. 62፣ ፒ<.05፣አር= .65፣አር$^{2,}$ = 42 ለማምጣት የሚያስችል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የመሬት አጠቃቀም ሽፋን ትንተናም ባለፉት አራት አሥርት ዓመታት (1991-2017) የእርሻ መሬት መጠን እየጨመረ እናየደን ሽፋን መጠን እየቀነስ መምጣቱን ጥናቱ በግልጽያሳያል፡፡ ስለሆነም ጥናቱ በተጠናበት አካባቢ የጥምር እርሻ ደን ምግብን፣ የእንጨት ውጤቶችንና የገቢ ፍላጎትን መሠረት በማድረግ ከተሠራ የአየር ንብረት ለውጥ እንዲስማማ ከማድረግ ባሻገር ለአርሶአደሮች የመተዳደሪያ ፀጋ በመጨመር አገልግሎት ይሰጣል።

**ቁልፍ ቃሎች**፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ እንዲስማማ ማድረግ፣ የጥምር እርሻ ደን ፣ በአነስተኛ ይዞታ አምራች አርሶአደሮች፣ የመሬት አጠቃቀም ሽፋን ለውጥ፣ኢትዮጵያ

Year of Graduation 2022

# Land use/cover changes, driving forces and influence on soil properties in Rib watershed, Ethiopia

Fentanesh Hail Buruso

## ABSTRACT

Land use/cover (LULC) change has resulted from complex interactions of natural phenomena and human activities. Population growth coupled with economic growth has increased the demand of land resources for centuries and is causing changes at various levels ranging from local to global scales. Land use practice affects the distribution and supply of soil nutrients to plants by altering soil properties. This study was aimed at understanding the magnitude of LULC changes and its drivers. It also attempts to examine the influence of LULC on soil properties in Rib watershed. Satellite imageries of 1986, 1996, 2006, and 2016, field observation and four key informant interviews were employed. In addition, soil samples were taken over natural forest, grazing and cultivated lands in the two agroecological zones (Dega and High Dega) with five replications. The samples were taken at two depths: 0-15cm (surface layer) and 15-30cm (subsurface layer) and mixed up to obtain composite and representative samples. A household survey was also employed to obtain data on farmers' perception of drivers of LULC changes. Image analysis was accomplished on ERDAS Imagine and Arc GIS software to detect land use/cover changes. Descriptive statistics, pair-wise ranking technique, Multivariate analysis of variance (MANOVA), and Spearman's rank correlation coefficient analyses in

# የመሬትአጠቃቀም/የሽፋንለውጦች፣ገፊ ምክንያቶች እና በአፈርባህርያት ላይ የሚያስከትለው ተጽእኖ፡ በርብ ተፋሰስ፤ ኢትዮጵያ

በፈንታነሽ ሃይሌ ቡሩሶ

## አጠቃሎ

የመሬት አጠቃቀም/የሽፋን ለውጥ የሚፈጠረው በተፈጥሮ ክስተቶች እና በሰዎች ተግባራት መስተጋብርነው።የህዝብ ቁጥር መጨመር ከኢኮኖሚ እድገትጋር ተዳምሮ የመሬትሃብት ፍላጎትን ለዘመናት በማሳደጉ ከሀገር እስከ አለም አቀፍ ደረጃ ያሉ የመሬት አጠቃቀም/የሽፋን ለውጦች እንዲመጡ አድርጓል።የመሬት አጠቃቀም የአፈርን ባህሪያት በመለወጥ የአፈርን ንጥረ ነገሮች ስርጭት እና ለተክሎች ያለውን ተደራሽነት ይወስናል፡፡ይህ ጥናት የመሬት አጠቃቀም/ ሽፋን ለውጦችን እና ገፊ ምክንያቶችን ለመረዳት ያለመ ነው።በተጨማሪም ጥናቱ በርብ ተፋሰስ ውስጥ ያለውን የመሬት አጠቃቀም/ሽፋን ለውጥ በአፈር ባህሪያት ላይ ያለዉን ተጽእኖ ለመመርመር ይሞክራል፡፡ በዚህ ጥናት በአዉሮፓዊያኑ ዘመን አቆጣጠ በ1986፣ 1996፣ 2006 እና 2016 የሳተላይት ምስሎች፤ የመስክ ምልከታዎች እና አራት ቁልፍ የመረጃ ሰጭ ቃለ-መጠይቆች ስራ ላይ ውለዋል።በተጨማሪም በሁለቱ የአግሮኢኮሎጂ ዞኖች (ደጋ እና ከፍተኛ ደጋ) የተፈጥሮ ደን፣የግጦሽ እና እርሻ መሬቶች(ማሳ) ላይ የአፈር ናሙናዎች ተወስደዋል።ናሙናዎቹ የተወሰዱት ከየመሬቱ ሁለት የተለያዩ የጥልቀት ደረጃዎች ሲሆን፣ እነሱም ከ0-15 ሴ.ሜ (የላይኛው ሽፋን) እና ከ15- 30 ሴ.ሜ (የከርሰምድር ንጣፍ) ናቸው፡፡ አርሶ አደሮች ስለ መሬት አጠቃቀም/ ሽፋን ለውጥ መንስኤዎች በሚኖራቸዉ ግንዛቤ መረጃ ለማግኘት ተሞክሯል።የመሬት አጠቃቀም/ሽፋን ለውጦችን ለመለየት በERDAS እና Arc GIS ሶፍትዌር ላይ የምስል ትንተና ተከናውኗል።ገላጭ ስታቲስቲክስ፣ጥንድ ጥበባዊ የደረጃ አሰጣጥ ቴክኒክ፣የልዩነት ልዩነት (MANOVA) እና

SPSS were employed. The findings of this study revealed an expansion of cropland and settlement, plantation, and bare land by 39.01, 24.88 and 5.62 ha/year, respectively between 1986 and 2016. On the contrary, natural forest, grassland, and grazing land have decreased by 30, 26.6 and 12.9 ha/year, respectively. Plantation shows increasing trends in Dega agroecological zone, whereas in the High Dega cultivated/farmlands and settlements, bare land has increased rapidly at the expense of other LULC. Significant differences ($p<0.05$) were also observed in OC, Ca2+, clay, and silt fractions between the soils of natural forest, grazing land, and cultivated in the two agro-ecologies. Soils of natural forest have higher OC, OC stock and TN. For instance, soils of natural forest have higher OC stock (188.32 Mg/ha) as compared to soils of cultivated lands (72.75 Mg/ha). The BD of cultivated land was significantly higher than natural forest and grazing lands. LULC changes were driven by increasing demands for new farmlands and increasing demand for eucalyptus wood in rural and urban centres. Moreover, weakness in law enforcement on natural resource conservation, low level of public participation in watershed management, and low level of livelihood diversification were among the drivers of change. Therefore, the study has suggested that the watershed ought to be enriched with watershed restoration and natural resource conservation activities.

**Keywords:** Driving forces; Ethiopia, land use/cover changes; Rib watershed; soil properties.

factors that affect the performance of a school. The main research question that guided this study was: How does the principals' leadership behaviour influence the performance of government secondary schools in the Southern region of Ethiopia? A qualitative method, using a case study design was employed through analysing documents, observation and interviews as a means of data collection. Through face-to-face and semi-structured, open-ended in-depth interviews with 30 participants, the researcher uncovered personal views of principals' leadership behaviour on school performance. Principals used the autocratic as well as the democratic and laissez-faire style. With increasing educational qualifications, the employees exhibit more of the democratic leadership tendencies and those who are educated less are inclined towards the autocratic leadership style. The lack of a compelling vision and mission for government schools continues to be a major obstacle in any effort to improve schools. It was developed as a strategy that the principals were well equipped with knowledge and skills in management and leadership to transform the Secondary Schools of the Southern Region of Ethiopia.

***Key words:*** *Principal; leadership behaviour; school performance; secondary schools; Southern Ethiopia*

ዘይቤ እና መገለጫቸው ምንድነው? የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከሁሉም በላይ የጥናት ዋና ጥያቄ፡ በደቡብ ክልል በሚገኙ የመንግስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አፈጻጸም ላይ የርዕሰ መምህራን የአመራር ባህሪ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል? የሚለው ነው። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች የተሰበሰቡት የጥራት ዘዴ፣ የጉዳይ ጥናት ዲዛይን በመጠቀም ሰነዶችን፣ ምልከታዎችን እና ቃለመጠይቆችን በመጠቀም ሲሆን፣ ፊት ለፊት እና በከፊል የተዋቀረ፣ ክፍት የሆነ ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች የተደረጉት ከ30 ተሳታፊዎች ጋር ነው፡ ፡ ተመራማሪው ስለ ርእሰ-መምህራኑ አመራር ባህሪና በትምህርት ቤት አፈጻጸም ላይ ያላቸውን ግላዊ አመለካከትም ዳስሷል። ርእሰ መምህራን አውቶክራቲክን እንዲሁም ዲሞክራሲያዊ እና ላይሴዝ-ፋይር ዘይቤን ተጠቅመዋል። የትምህርት መመዘኛዎች እየጨመረ በመምጣቱ የተነሳ ሰራተኞቹ ብዙ የዴሞክራሲያዊ አመራር ዝንባሌዎችን አሳይተዋል። በትምህርት ቤቶች አስገዳጅ ራዕይ እና ተልእኮ አለመኖሩ፣ ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል በሚደረገው ጥረት ሁሉ ትልቅ እንቅፋት ሆኖ ተገኝቷል። የደቡብ ክልል 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሸጋገር፣ ርዕሳነ-መምህራን በአስተዳደርና በአመራር ዕውቀትና ክህሎት የታጠቁ መሆናቸው እንደ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል።

**ቁልፍ ቃላት:**- ዋና የአመራር ባህሪ፣ የትምህርት ቤት አፈፃፀም፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፤

# Under-representation of women in senior leadership positions of public universities in south Ethiopia

Tafano Ouke Labiso


## ABSTRACT

The purpose of this study was to explore the causes of underrepresentation of women in senior leadership positions of public universities in south Ethiopia. To achieve this, the vice-presidents, deans and/or directors of public universities in south Ethiopia were involved as the target population. Four public universities: Wachamo, Wolaita Sodo, Dilla and Hawassa were involved as research sites. Four vice-presidents (one from each university), twelve deans and academic directors (three from each university) who constituted a focus group of four participants from each of the four universities, participated in the study. An exploratory case study design was used in this qualitative study.

The purposive sampling technique was used for the selection of the samples. Unstructured interviews were conducted with the vice-presidents of the selected universities and focus group discussions were held with college deans and directors. Participant observation was conducted on issues related to women empowerment at the universities under study. The findings showed that women were greatly underrepresented in senior academic leadership positions at all the selected public universities of south Ethiopia because of various institutional, women-related, economic, socio-cultural, political and legal factors.

The study identified some gaps in the government's oversight role of monitoring and evaluating the implementation


# በደቡብ ኢትዮጵያ የህዝብ ዩኒቨርስቲዎች በከፍተኛ የአመራር ቦታዎች ላይ ያሉ ሴቶችን ዝቅተኛ ውክልና ማሰስ

በታፋኖ ኡኬ ላቢሶ


## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ከፍተኛ አመራር ላይ ያሉ ሴቶች ውክልና ዝቅተኛ መሆን ያለባቸውን ምክንያቶች ለመዳሰስ ነው። ይህንንም ለማሳካት በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ምክትል ፕሬዝዳንቶች፣ ዲኖች እና/ወይም ዳይሬክተሮች የታለመው ህዝብ ሆነው ተሳትፈዋል። አራት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ዋቻሞ፣ ወላይታ ሶዶ፣ ዲላ እና ሀዋሳ የምርምር ሳይቶች ሆነው ተሳትፈዋል። ከአራቱ ዩኒቨርስቲዎች የተውጣጡ አራት ተሳታፊዎችን ያካተተ የትኩረት ቡድን ያቋቋሙት አራት ምክትል ፕሬዝዳንቶች (ከየዩኒቨርሲቲው አንድ)፣ 12 ዲኖች እና የአካዳሚክ ዳይሬክተሮች (ሶስት ከየዩኒቨርሲቲው) በጥናቱ ተሳትፈዋል። በዚህ የጥራት ጥናት ውስጥ የዳሰሳ ጥናት ንድፍ ጥቅም ላይ ውሏል።

ለናሙናዎቹ ምርጫ ዓላማ ያለው የናሙና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። ከተመረጡት ዩኒቨርሲቲዎች ምክትል ፕሬዝዳንቶች ጋር ያልተዋቀረ ቃለ ምልልስ የተደረገ ሲሆን ከኮሌጅ ዲኖች እና ዳይሬክተሮች ጋር የትኩረት ቡድን ውይይት ተካሂዷል። በጥናት ላይ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች የሴቶችን ተጠቃሚነት በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ የተሳታፊዎች ምልከታ ተካሂዷል። በደቡብ ኢትዮጵያ በተመረጡት የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሴቶች በከፍተኛ የአካዳሚክ አመራር ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ውክልና ያልነበራቸው በተለያዩ ተቋማዊ ፣ሴቶች ፣ኢኮኖሚያዊ ፣ማህበራዊ-ባህላዊ እና ፖለቲካዊ-ህጋዊ ጉዳዮች የተነሳ ሴቶች በከፍተኛ ደረጃ ውክልና እንዳልነበራቸው ግኝቶቹ ያሳያሉ።

ጥናቱ የከፍተኛ ትምህርት ህግን ጨምሮ በፌዴራል መንግስት በተደነገገው ዩኒቨርስቲዎች የሴቶችን ተጠቃሚነት ማጎልበት ፖሊሲዎች በመከታተል እና በመገምገም የመንግስት የክትትል ሚና ላይ አንዳንድ ክፍተቶችን ተመልክቷል። ከዚህም በላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

of women empowerment policies at universities prescribed by the Federal Government including the higher education legislation. Moreover, higher education institutions (HEIs) themselves have also failed to empower women through different mechanisms. Therefore, it could be concluded that HEIs pay little attention to the empowerment of women. Currently, there are some initiatives meant to empower women. However, these, seem to be a reaction to pressure by the higher political authorities. It could be concluded that women are still illiterate about their rights and are not keen to be empowered. Negative societal attitudes and lack of attractive incentives for the leadership positions contribute to the underrepresentation of women in senior positions. Furthermore, a shortage of teaching staff in academia plays a negative role in this underrepresentation.

Finally, it is recommended that the government, society, institutions, and women themselves should step up efforts to empower women, particularly their appointment to senior leadership positions. This is critical as they constitute half of the population of both the institutions and the country. Finally, the study proposes a model that could be adopted by the government, HEIs and different institutions to improve the empowerment of women, especially their appointment to senior leadership positions in HEIs.

**Keywords:** Women leadership; senior positions; higher education; women underrepresentation; leadership diversity.

ራሳቸው ሴቶችን በተለያዩ ዘዴዎች ማብቃት አልቻሉም። ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሴቶችን አቅም ለማጎልበት ብዙም ትኩረት አይሰጡም ብሎ መደምደም ይቻላል። በአሁኑ ጊዜ ሴቶችን ለማብቃት የታቀዱ አንዳንድ ውጥኖች አሉ። ይሁን እንጂ እነዚህ በከፍተኛ የፖለቲካ ባለስልጣናት ግፊት ምላሽ ይመስላል. ሴቶች አሁንም ስለመብታቸው ማንበብና መጻፍ የማይችሉ እና የስልጣን መጎልበት ፍላጎት የላቸውም ብሎ መደምደም ይቻላል። አሉታዊ ማህበረሰባዊ አመለካከቶች እና ለአመራር ቦታዎች የሚስቡ ማበረታቻዎች አለመኖር በከፍተኛ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉ ሴቶች ዝቅተኛ ውክልና እንዲኖራቸው አስተዋፅኦ ያደርጋሉ. በተጨማሪም በዚህ ዝቅተኛ ውክልና ውስጥ በአካዳሚ ውስጥ የማስተማር ባለሙያዎች እጥረት አሉታዊ ሚና ይጫወታል.

በመጨረሻም መንግስት፣ ህብረተሰብ፣ ተቋማት እና ሴቶች ራሳቸው ሴቶችን ለማብቃት በተለይም በከፍተኛ አመራርነት ሹመት ላይ ርብርብ እንዲያደርጉ ይመከራል። ከሁለቱም የተቋማትም ሆነ የሀገሪቱ የህዝብ ብዛት ግማሽ ያህሉ በመሆናቸው ይህ ወሳኝ ነው። በመጨረሻም ጥናቱ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሻሻል በመንግስት፣በከፍተኛ አመራርነት ቦታ ላይ የሚኖራቸውን ሹመት ለማሻሻል በመንግስት፣በመ/ቤቶች እና በተለያዩ ተቋማት ሊወሰዱ የሚችሉበትን ሞዴል ሀሳብ አቅርቧል።

**ቁልፍ ቃላት:** የሴቶች አመራር, ከፍተኛ የሥራ መደቦች, ከፍተኛ ትምህርት, የሴቶች ዝቅተኛ ውክልና, የአመራር ልዩነት

# An investigation of effective implementation of instructional supervision practice in secondary schools in Hawassa, Ethiopia

Tibebu Legesse Tezera


## ABSTRACT

The purpose of the study was to investigate the effective implementation of instructional supervision practices in secondary schools of Hawassa City Administration in Ethiopia. The study focuses particularly on the practices and roles of supervisors in the implementation of instructional supervision, and the factors affecting its implementation in secondary schools. Basic questions related to the availability of instructional supervision strategies and their implementation, the roles of instructional leaders, perceptions of instructional supervision, and challenges for proper implementation of instructional supervision were raised. In addition, strategies for strengthening the effective implementation of instructional supervision were also addressed. The study was framed within the Theory of Change in Teachers' viewpoints on instructional practices. In fact, there is a strong link with the instructional leadership strategies and the role of supervisors for the effective implementation of instructional supervision practices. The Instructional Supervision Model was used as it integrates the activities of instructional supervision in the schools. Moreover, this study reviewed global perspectives on educational supervision and provided an overview of the study context with an emphasis on improvement of instructional supervision. Philosophically, this study followed the pragmatist research paradigm,


# በሀዋሳ ከተማ በሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ሂደት የሱፐርቨዥን አፈጻጸምና ውጤታማነት ላይ የተደረገ ጥናት፤

በጥበቡ ለገሰ ተዘራ


## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓላማ በሀዋሳ ከተማ አስተዳደር፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማስተማር ሂደት የተደርጉ የድጋፍና ክትትል አፈጻጸምና ውጤታማነትን ለመመርመር ነው። ጥናቱ በተለይ በትምህርት ድጋፍና ክትትል ትግበራ ውስጥ የሱፐርቫይዘሮች ድጋፍ እና ሚናዎች በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አተገባበር ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ሁኔታዎች ላይ ያተኩራል። በዚህም የስራ መመሪያ አተገባበር ስልቶች መገኘት እና የአፈፃፀም መገምጊያ በተደራጀ መልኩ መኖር፣ የአመራሮች ሚናና ተግባር የሚገልጽ መመሪያ መኖር፣ የትምህርት ክትትልና ድጋፍ ግንዛቤ እና በእቅድ የተቀመጡ ስራዎች በደንብና በመመሪያ መሰርት በተቀመጠላቸው ስልቶች ድጋፍና ክትትል በአግባቡ እንዳይወጡ ተግባራዊነት ላይ ከተጋረጡ ተግዳሮቶች ጋር የተያያዙ መሰረታዊ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በተጨማሪም በማስተማር ሂደት የተደርጉ የድጋፍና ክትትል አሰራር ውጤታማ ትግበራ የማጠናከር ስልቶችም ትኩረት ተደርጎባቸዋል። ጥናቱ የተቀረፀው በመምህራን ሁለንተናዊ የለውጥ ፅንሰ-ሀሳብና በማስተማር ልምምዶች ላይ ነው። በመሰረቱ የትምህርት አመራር የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም እና የሱፐርቫይዘሮችን ሚና ውጤታማ በሆነ መልኩ በመማር ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ ለማድረግ ጠንካራ ግንኙነት ያስፈልጋል። በመማር ማስተማሩ ሂደት የድጋፍና ክትትል ሞዴል በትምህርት ቤቶች ውስጥ የማስተማር ክትትል ተግባራትን ለማዳበር ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚህም በላይ ጥናቱ በትምህርት ድጋፍና ክትትል ዙሪያ ላይ ያለውን ዓለምአቀፋዊ አመለካከቶች ገምግሟል። ስለዚህም የጥናቱ አውድ አጠቃላይ እይታ በመማር ማስተማር ድጋፍና መሻሻል ላይ አፅንዖት ሰጥቷል። ጥናቱ የተቀላቀሉ የምርምር አቀራረቦችን በመጠቀም የፕራግማቲስት ፍልስፍና ፓራዳይምን ተከትሏል።

employing mixed research approaches. It also employed an explanatory sequential design in which both quantitative and qualitative data were collected simultaneously, interpreted separately and combined at the time of discussion for better understanding of the problem. Data were gathered from 160 supervision teams (vice-principals, senior teachers, unit leaders and department heads), 185 teachers. In addition, 14 principals and supervisors took part in interviews. One focus group discussion was also conducted with the city educational experts. Data were gathered through survey questionnaires, semi-structured interviews, FGD question guides and document reviews. Quantitative data was analysed through the descriptive approaches such as percentage, mean, grand mean and inferential statistics, known as standard division and t-test. Qualitative data collected through interviews and FGDs was summarised through thematic and narrative techniques, and finally triangulated. The results indicated that the quantitative and qualitative data supported one another. It was found that school supervision in line with strategies was inadequate. In addition, school supervision corresponding to the expected standards was not effectively done. The extent to which instructional supervisors design various intervention strategies so as to assist teacher's professional improvement was insufficient. Evidence showed that instructional supervisors' role in building effective relationship in schools was weak. Supportive, directive, conflict management and monitoring and supervising roles in the implementation of instructional supervision were also found to be inadequate. The teachers did not have enough support from supervisors in order to improve their instructional skills, and there was a negative perception of teachers about the implementation

በተጨማሪም ለችግሩ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት በቁጥርም ሆነ በጥራት መረጃዎች በአንድ ጊዜ የሚሰበሰቡበት፣ በተናጥል የሚተረጎሙበት እና በቃለምልልስ ወቅት የተጣመሩበት የማብራሪያ ቅደም ተከተል ንድፍ ተሠርቷል። ለጥናቱ አስፈላጊው መረጃ የተሰበሰበው ከ160 የሱፐርቪዥን ቡድኖች (ምክትል ርዕሳነ መምህራን፣ ከፍተኛ መሪ መምህራን፣ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች እና የመፈረቃ አስተባባሪዎች)፣ 185 መምህራን፣ 14 ርእሰ መምህራን እና ሱፐርቫይዘሮች በቃለ መጠይቅ በማሳተፍ ነው። የትኩረት ቡድን ውይይትም ከከተማው ከፍተኛ የትምህርት ባለሙያዎች ጋር ተካሂዷል። የመረጃው መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም የዳሰሳ መጠይቆች፣ በከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆች፣ የትኩረት ቡድን የጥያቄ መመሪያዎች እና የሰነድ ግምገማዎች ናቸው። የቁጥር መረጃው የተተነተነው በመቶኛ፣ አማካኝ፣ ግራንድ አማካኝ እና ኢንፈርንሺያል ስታቲስቲክስ ባሉ ገላጭ አቀራረቦች ሲሆን፣ ይህም መደበኛ ክፍፍል እና t-test በመባል ይታወቃል። በቃለ መጠይቆች እና በትኩረት ቡድን የተሰበሰበው የጥራት መረጃ በቲማቲክ እና በትረካ ቴክኒኮች ተጠቃሎ እንዲመሳከር ተደርጉዋል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው አኃዛዊ እና ጥራት ያለው መረጃ እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው። የጥናቱ ውጤት የተቀመጡ የስራ ስልቶች ጋር በተያያዘ የተጣጣመ የትምህርት ቤት ክትትልና ትግበራ እንደሌለ አሳይቷል። በተጨማሪም፣ እንዲተገበር ከሚጠበቀው መመዘኛ ጋር የሚዛመድ የት/ቤት ክትትል በብቃት አልተሰራም። የመምህራንን ሙያዊ መሻሻል ለማገዝ የትምህርት ተቆጣጣሪዎች የተለያዩ የማብቂያ ስልቶችን የሚነድፉበት መጠን በቂ ሆኖ አልተገኘም። በሌላ በኩል በትምህርት ቤቶች ውስጥ ውጤታማ ግንኙነትን ለመፍጠር የሱፐርቫይዘሮች ሚና ደካማ ሆኖ ተገኝቷል። በተጨማሪም በሱፐርቫዥን ትግበራ ውስጥ የድጋፍና ክትትል መመሪያ፣ የግጭት አስተዳደር እና የክትትልና የመቆጣጠር ሚናዎችም በቂ እንዳልሆኑ በጥናቱ ተረጋግጧል። መምህራኑ የማስተማር ክህሎታቸውን ለማሻሻል ከሱፐርቫይዘሮች በቂ ድጋፍ አልነበራቸውም፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪ በመምህራኑ የማስተማር ድግፍና ክትትል ትግበራ ላይ አሉታዊ አመለካከት ነበር። በአንፃሩ የበቂ ሱፐርቫይዘሮች፣ የአመራር ክህሎት፣ የሙያ መተግበሪያ መመሪያዎች፣

of instructional supervision. On the other hand, effective implementation of instructional supervision was hampered by a lack of qualified instructional supervisors, management skills, professional manuals, cooperation, and motivation for work and a lack of training and funding. Inadequate facilities and assignment of a small number of supervisors hindered proper implementation of instructional supervision. Moreover, lack of commitment on the part of teachers and school leaders, lack of effective stakeholder support, lack of respect among stakeholders, lack of a participatory supervisory approach and lack of adequate guidance between instructional leaders hampered instructional supervision. Based on the findings, instructional leaders, teachers, supervisors, school instructional supervision teams and school communities need to be well equipped with basic knowledge and skills on the implementation of school instructional supervision, through pre-service and in-service training, experience-sharing programmes, seminars, workshops and discussion forums about the different approaches of supervision in order to enhance the professional growth of teachers and improve their instructional practices. This could help in fostering critical thinking and the problem-solving capacity of the supervisors. Moreover, the instructional leaders in schools need to plan for continuous training and orientation on the nature, practice and significance of instructional supervision. Suggestions were made to solve the factors that hinder proper implementation of instructional supervision.

**Keywords:** Curriculum development; effective implementation; instructional development; instructional supervision; leadership, monitoring; supervision practice; supervisory roles; supervisory skills; teacher development.

በትብብር እና በምክክር የመስራት የሥራ ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ጥናቱ አሳይቱዋል፤ እንዲሁም የሥልጠናና የገንዘብ ድጋፍ ባለመኖሩ የመማር ማስተማር ሂደትን እየደገፈና እያበቁ ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት ፈጥሯል። ለስራው የሚያስፈልጉ በቂ ግበአቶች አለመኖራቸው እና አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሱፐርቫይዘሮች በየትምህርት ቤቶቹ መመደብ የሚደረገውን ድጋፍና ክትትል በትክክል ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት ሆነዋል። ከዚህም በላይ የመምህራንና የት/ቤት አመራሮች ቁርጠኝነት ማነስ፣ የባለድርሻ አካላት ውጤታማና በቂ ድጋፍ አለመስጠት፣ በባለድርሻ አካላት መካከል መከባበር አለመኖር ፣ አሳታፊ የሱፐርቫዥን አሰራር አለመኖር እና በአመራሮች መካከል በቂ የስራ መመሪያ አለመስጠት፤ የሚደረገውን ድገፍና ክትትል ውጤታማ እንዳይሆን አድረገዋል ። በግኝቶቹ መሰረት የትምህርት አመራሮች፣ መምህራን፣ ሱፐርቫይዘሮች፣ የት/ቤቱ የሱፐርቫይዘሮች ቡድን እና የት/ቤት ማህበረሰቦች በትምህርት ቤት ትምህርታዊ ድጋፍና ክትትል አተገባበር ላይ መሰረታዊ ዕውቀትና ክህሎት በመታጠቅ በቅድመ አገልግሎት እና በስራ ላይ ስልጠና፣ የልምድ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው። የተለያዩ የክትትልና ድጋፍ ዘዴዎችን፣ ማለትም ፕሮግራሞች፣ ሴሚናሮች፣ አውደ ጥናቶች እና የውይይት መድረኮች በመዘርጋት የመምህራንን ሙያዊ እድገት ማጎልበት እና የማስተማር ተግባራቸውን ማሻሻል ይኖርባቸዋል። ይህ ሂሳዊ አስተሳሰብን እና የሱፐርቫይዘሮች በትምህርት ቤቶች የሚፈጠሩ ችግሮችን የመፍታት አቅም ለማዳበርም ያግዛል። በተጨማሪም፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የትምህርት አመራሮች፣ ስለ ትምህርታዊ ሱፐርቫዥን ምንነት፣ አሠራር እና ጠቀሜታ ቀጣይነት ያለው ሥልጠና እና አቅጣጫ እንዲኖራቸው ማቀድ አስፈላጊ መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። የሱፐርቨዥን ድጋፍና ክትትልን በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅፋት የሆኑትን ነገሮች ለመፍታትም ጥቆማዎች ተሰጥተዋል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- የስርዓተ ትምህርት ልማት፣ ውጤታማ ትግበራ፣ የትምህርት ልማት፣ የትምህርት ክትትል፣ አመራር፣ ክትትል፣ የሱፐርቫዥን ልምምድ፣ የሱፐርቪዥን ሚናዎች፣ የመምህራን እድገት፤

Year of Graduation 2022

# The state of leadership practices in a sample of polytechnic colleges of Addis Ababa, Ethiopia

Adane Abeje Yalew

## ABSTRACT

The inadequacy of research into leadership in polytechnic colleges prompted this research to explore the state of leadership practices in Technical and Vocational Education and Training (TVET) colleges of Addis Ababa, Ethiopia. This study was guided by the constructivist paradigm. It followed a qualitative approach and employed a grounded theory design. The study involved 26 participants who were selected through the purposive sampling technique from three polytechnic colleges in Addis Ababa. Data were collected using three instruments: the structured interview, the Focus Group Interview (FGI) and observation. The interviews were conducted face-to-face with Prime Deans (PDs) and officials. After that, the FGIs and observations were conducted to triangulate the data gathered through the structured interviews. Thematic analysis and constant comparative analysis methods were employed to analyse data. A zigzag method was used in moving back and forth during data analysis. The findings showed that there was inadequate policy support for effective TVET leadership practices in the sample colleges. The available TVET strategy was not changed into actionable directives and guidelines. Leadership practices were mostly guided by campaigns and ad-hoc letters. The position of the PD was not filled with a merit-based approach and lacked transparency. PDs were not

# የፖሊቴክኒክ ኮሌጆች የሚከተሉት የአመራር ልምድ በአዲስ አበባ

በአዳነ አበጀ ያለው

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በአዲስ አበባ በሚገኙ ሶስት ፖሊቴክኒክ ኮሌጆች ውስጥ ያለውን የአመራር አተገባበር ሁኔታ መቃኘት ነው። ይህ ጥናት የተመራው በኮንስትራክቲቪስት ኢንተርፕረቲብ ፓራዳይም እይታ ነው። ይህ ጥናት የንድፈ ሃሳብ ስልት አቀራረብን እና ግራዉንድድ ቲዎሪ ዲዛይንን ተጠቅሟል። ጥናቱ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ሶስት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ተመራማሪው በወሰነው አመቺ የንሞና ቴክኒክ የተመረጡ 26 ተሳታፊዎችን መሰረት ያደረገ ነው። ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በተዋቀረው ቃለ መጠይቅ፣ በትኩረት ቡድን ቃለመጠይቅ (FGI) እና በምልከታ የተሰበሰበ ሲሆን ቃለ መጠይቆቹ የተካሄዱት ከተመረጡ ዲኖች እና በየደረጃው በሚገኙ ውስን የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ዘርፉን ከሚመሩ ባለስልጣናት ጋር ነው። በቃለመጠየቅ የተገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በትኩረት ቡድን ቃለመጠይቅ እና ምልከታዎች ተካሂደዋል። መረጃን ለመተንተን የቴማቲክ ትንተና እና የማያቋርጥ የንጽጽር ትንተና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በመረጃ ትንተና ወቅት ወደኋላ እና ወደፊት በመመላለስ የዚግዛግ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በናሙና ኮሌጆች ውስጥ ውጤታማ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ተግባራት በቂ የፖሊሲ ድጋፍ እንዳልነበረው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። አሁን ያለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂ ወደ ተግባራዊ የዕለት ከዕለት መመሪያ ተለዉጦ ወደኮሌጆቹ አልወረደም። የአመራር ልምምዶች የሚከናወኑት በአብዛኛው በዘመቻዎች እና በአድሆክ ደብዳቤዎች ነበር። ዲኖች በመዋቅሩ ላይ በመሪነት ሲቀመጡ በብቃት ላይ ያልተመሰረተ እና ግልጽነት የጎደለው ሆኖ ተገኝቷል። ዲኖችም ለአሰልጣኞች አርአያ አልነበሩም። በከፍተኛ ባለስልጣናት ጣልቃገብነት የመወሰን ስልጣናቸው ስለተዳከመ ራሳቸውን

role-models for trainers. PDs were not autonomous as their decision-making power was crippled by the interventions of higher officials. Vision formulation was not participatory. Business-as-usual PDs did not have any place in the dynamic sample colleges. Effective leadership was deemed important to produce skilled graduates to fill the middle-level human power needs of industries, enterprises and labour markets but was not practised well. The need to practise effective leadership was found not debatable. Leadership in the sample colleges was predominantly different from other sectors' leadership due to the emphasis on technology creativity, invention, innovation and hard skills. PDs' confirmation that they used a democratic leadership style was not supported by the views of trainers. In principle, effective leadership practices have a positive impact on the colleges' outcomes. Nonetheless, this could not be ascertained practically. The leadership practices could not indicate the evidence about the contributions at impact level to the socio-economic growth and development of Addis Ababa. The achievements were at the immediate output level. Sustainable change and transformation were not depicted as there were a high number of unemployed graduates, which was confirmed by the tracer study of the sample colleges. Idle blue collar workers were produced due to the absence of relevant skills that equipped graduates. The procedure to reward and motivate the winners of innovation was bureaucratic, unsustainable and unrealistic. The situation led to repercussions in the colleges, which demotivated the trainers. The additive effects of transformational and transactional leadership styles were substantial to creativity, invention and innovation; reward and motivation packages; team building; individual efforts and wise use of scarce resources.

ችለው አይሰሩም ነበር። ራዕይም ሲዘጋጅ አሳታፊ አልነበረም። በኢንዱስትሪዎች፣ በኢንተርፕራይዞች እና በሰራተኛ ገበያው በመካከለኛ ደረጃ የሰው ሃይል ፍላጎትን ለማሟላት በሰለጠነ ምሩቃን ለማፍራት ውጤታማ አመራር አስፈላጊ ነው ተብሎ ቢታሰብም በጥሩ ሁኔታ አልተሰራም። ውጤታማ አመራር የመለማመድ አስፈላጊነት አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም። ዲኖች ዲሞክራሲያዊ የአመራር ዘይቤ መጠቀማቸውን ማረጋገጡ በአሰልጣኞች አስተያየት አልተደገፈም። በመርህ ደረጃ ውጤታማ የአመራር ልምዶች በኮሌጆች ውጤቶች ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ያላቸው ቢሆንም ይህ በተግባር ሊረጋገጥ አልቻለም። የአመራር ልምዶቹ ለአዲስ አበባ ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ እድገት ስላበረከቱት አስተዋፅዖ ማስረጃዎች ሊያሳዩ አልቻሉም። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሥራ አጥ ተመራቂዎች በመኖራቸው፣ ዘላቂ ለውጥና ትራንስፎርሜሽንም አልታየም። ተመራቂዎችን የሚያስታጥቁ አግባብነት ያላቸው ክህሎት ባለመኖሩ ስራ ፈት ተመራቂዎች ተፈጥረዋል። የፈጠራ አሸናፊዎችን ለመሸለም እና ለማነሳሳት የተደረገው አሰራር ቢሮክራሲያዊ፣ ዘላቂ ያልሆነ እና ከእውነታው የራቀ ነው። ይህም በኮሌጆች ላይ መዘዞችን አስከትሏል፤ የአሰልጣኞችን ለስራ መነሳሳት ዝቅ አድርጓል። በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የትራንስፎርሜሽን እና የግብይት አመራር ዘይቤዎች ተጨማሪ ውጤቶች ለማስመዝገብ እና የፈጠራ ስራዎችን ለማበረታታት ከፍተኛ ሚና እንዳላቸው ቢታመንም በተግባር ግን ተፈጻሚ አልሆኑም። የሽልማት እና የማበረታቻ ፓኬጆች፣ የቡድን ግንባታ፣ የግል ጥረቶች እና ጥበበኛ የሀብት አጠቃቀም አልታየም። በተጨማሪም የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ውስብስብ ችግሮች እና ፈተናዎች የናሙና ኮሌጆችን አመራር ፈትኗል። ስለዚህ በናሙና ኮሌጆቹ ፈጠራን ለማነሳሳት የዘመኑን የአመራር ዘይቤዎች በማጣመር ተራማጅ እና ተለዋዋጭ የአመራር ዘይቤዎችን መጠቀም አስፈላጊ እና ወሳኝ ሆኖ በመገኘቱ ተመራማሪው የተቀናጀ ተለዋዋጭ አመራር ንድፈ ሀሳብ አበልጽጓል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ፣ የአመራር ልምዶች፣ ውጤታማ አመራር፣ የዘመኑ አመራር ንድፈ ሐሳቦች እና የተቀናጀ ተለዋዋጭ አመራር ንድፈ ሐሳብ

The findings showed that complex problems and challenges faced the sample colleges' leadership practices. Therefore, blending the contemporary leadership styles to initiate creativity, invention and innovation was found crucial to the progressive changes in the sample colleges. The proposed leadership theory was blended with dynamic leadership theory to mitigate problems and challenges faced by the sample colleges.

**Keywords:** TVET policy; leadership practices; effective leadership; contemporary leadership theories; blended dynamic leadership theory.

## Exploring principals' leadership practices and students' pass rate in secondary schools at West Arsi Zone, Ethiopia

Desta Kaweti Bekere

### ABSTRACT

The study was aimed at exploring principals' leadership practices and its influence on students' pass rate in the secondary schools of West Arsi Zone, Ethiopia. Philosophically, a Pragmatic Research Paradigm with a mixed-method research approach was employed. The study employed an Explanatory Sequential Mixed Method design to extract the perception of teachers, heads of departments, principals, vice-principals, and supervisors using both quantitative data followed by qualitative data to supplement each other and interpreted separately and combined at the end of the discussion for better grasping the problems under the study. Data were gathered from 225 teachers and 115 heads of departments using Multistage Random Sampling techniques while 11 school principals, five vice-

## የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የርእሰመምህራን የአመራር ልምምድ እና የተማሪዎች የማለፍ መጠን፡ በምዕራብ አርሲ ዞን የተደረገ መጣኝና ገላጭ ትንተናዊ ጥናት፤

በደስታ ቃዌቲ በከሬ

### አጠቃሎ

ይህ ጥናት በምዕራብ አርሲ ዞን 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የርእሰመምህራንን የአመራር ልምምድ እና በተማሪዎች የማለፍ መጠን ላይ ያለውን ዝምድና ለመቃኘት ያለመ ነው።ለዚህም ይረዳ ዘንድ የተግባራዊ ምርምር ፓራዲም ፍልስፍናን ከቅይጥ የምርምር አቀራረብ ጋር ተጠቅሟል። በተጨማሪም የማብራሪያ ቅደም ተከተል ቅይጥ ዘዴ ንድፍ በመጠቀም፣የመምህራንን፣የትምህርት ክፍል ሓላፊዎችን፣ ርዕሳነ - መምህራንን፣ ምክትል ርእሳነ -መምህራንን እና ሱፐርቫይዘሮችን ሁለቱንም መጠናዊ ና ገለጭ መረጃዎች በመጠቀም፣እርስ በእርስ ለመደጋገፍ እና በተናጥል ለመተርጎም ውይይት ተደርጓል፤በውይይቱ መጨረሻ ላይ ተጣምረው ለችግሮቹ በተሻለ ሁኔታ ማጥናት በሚያስችል መንገድ ተመርጧል።መረጃ የተሰበሰበው ከ225 መምህራን እና ከ115 የትምህርት ክፍል ኃላፊዎችን በዘፈቀደ ባለብዙ ደረጃ ናሙና ቴክኒክ በመጠቀም ሲሆን፣ 11

principals and four supervisors took part on an interview using Purposive Sampling techniques. Questionnaires, semi-structured interview and document analysis were instruments for data collection. Data were analysed using frequency, mean, standard deviation, independent sample t-test, and Pearson product-moment correlation analysis and thematic analysis techniques. The study found that the current principals' leadership practices in terms of 'setting directions', 'developing people', 'developing schools' and 'managing teaching-learning programme' were weak. The study also revealed that there is a positive relationship between principal leadership practices in 'setting direction' and 'developing schools' and students' pass rate while there is no significant relationship with 'developing people' and 'managing teaching-learning programme' and students' pass rate. Student-related, home-environment related, and teacher-related problems were found to be strong challenges while school-leadership related hurdles, lack of physical resources and material facilities and other external factors were found moderately challenging to school leaders in the process of supporting students' pass rates. The study also suggested strategies such as the central government playing their role; developing school leaders' commitment and capacities; enhancing teaching-learning; mobilising and allocating school resources; and working on school autonomy.

**Keywords:** Principals; leadership practices; secondary schools; school leaders; students' pass rate; teachers; pragmatism; mixed approach; government.

የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን፣ 5 ምክትል ርእሰ መምህራን እና 4 ሱፐርቫይዘሮች የዓላማ ናሙና ቴክኒኮችን በመጠቀም ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ላይ ተሳትፈዋል። በተጨማሪም መጠይቆች፣ከፊል የተዋቀረ ቃለመጠይቅ እና የሰነድ ትንተና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተግባራዊ ተደርገዋል።መረጃው በድግግሞሽ ቆጠራ፣ አማካኝ ፣መደበኛ ልዩነት ፣ ገለልተኛ ናሙና ቲ-ሙከራ እና የፔርሰን ምርት-አፍታት ትንተና እና የቲማቲክ ትንተና ቴክኒኮች በመጠቃም ተተንትኗል።የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው፣አሁን ያሉት ርዕሳነ መምህራን አቅጣጫዎችን ከማስቀመጥ'፣ሰዎችን ከማሳደግ፣ትምህርት ቤቶችን ማሳደግ እና የመማር ማስተማር ፕሮግራምን ከመምራት አንፃር ደካማ ናቸው። በተጨማሪም 'አቅጣጫ በማውጣት'፣ 'ትምህርት ቤቶችን በማዳበር' እና በተማሪዎች የማለፍ ደረጃ መካከል አዎንታዊ ግንኙነት እንዳለ በጥናቱ የተረጋገጠ ሲሆን፣ 'ከማዳበር' እና 'የመማር ማስተማር መርሃ ግብር አስተዳደር' እና የተማሪዎችን ማለፊያዎች ጋር ጉልህ ግንኙነት የለውም። ከተማሪ ጋር የተያያዙ፣ከቤት-አካባቢ እና ከአስተማሪ ጋር የተያያዙ ችግሮች ጠንካራ ተግዳሮቶች ሲገኙ፣ከት/ቤት አመራር ጋር የተያያዙ መሰናክሎች ፣ የአካለዊ እና የቁሳቁስ እጥረት እና ሌሎች ውጫዊ ሁኔታዎች የተማሪዎችን የማለፍ ደረጃን በመደገፍ ሂደት ውስጥ የት/ቤት አመራሮች በመጠኑ ፈታኝ ሆነው ተገኝተዋል።ጥናቱ እንደ ማዕከላዊ መንግስት ሚናቸውን ለመጫወት የሚያነሳሷቸውን ስልቶችም ጠቁሟል።እነዚህም፣ የትምህርት ቤት መሪዎችን ቁርጠኝነት እና አቅም ማዳበር፣ የመማር-ማስተማር ህዳትን ማሳደግ፣ የትምህርት ቤት ግብዓቶችን ማሰባሰብ እና መመደብ ና ትምህርት ቤቶች ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ መስቻል ናቸው።

**ቁልፍ ቃላት**: ርዕሰ መምህራን፣የአመራር ልምዶች፣ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣የትምህርት ቤት መሪዎች ፣ የተማሪዎች መጠና ማለፊ፣ አስተማሪዎች ፣ ፕራግማቲዝም፣የተደባለቀ አቀራረብ፣መንግስት

# Exploring the implementation of cooperative training at technical and vocational education and training colleges in Oromia regional state, Ethiopia

Kebede Soressa Guta

## ABSTRACT

The study was conducted to explore the implementation of cooperative training in TVET colleges in Oromia regional state which involves TVET-enterprise partnerships. The study utilised a mixed-methods research design, employing a questionnaire, semi-structured interviews and observation to collect information from 247 participants. The participants include 80 instructors, 150 students selected to complete the questionnaire, five Vocational Counselling and Guidance Office heads and two enterprise focal persons sampled for interviews and 10 students to participate in group interviews in three groups. Cooperative training in the region failed to consider the local context in that some parts of the region relied on small enterprises established in rural and small towns while other colleges worked with medium and large-scale enterprises. The rapport between TVET and enterprises was complicated and mired with factors related to communication, commitment, budget and involvement of stakeholders. Enterprises did not participate in the planning process, had very little knowledge of learning outcomes of a given programme and were not involved in the assessment of trainees. Enterprises were not compensated for their participation in cooperative training and were not given warranty if any kind of damage occurred during cooperative

# የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማሰልጠኛ ኮሌጆች የትብብር ስልጠና፡ በኦሮሚያ ክልል የተደረገ ዳሰሳ፡

በከበደ ሶሬሳ ጉታ

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች የትብብር ሥልጠና አፈጻጸምን ለመዳሰስ የተደረገ ነው። ለዚህም ጥናቱ የቅይጥ ዘዴዎችን የምርምር ንድፍ ተጠቅሟል። ለዚህም ከ247 ተጠኝዎች የተዋቀሩ ቃለመጠይቆች እና ምልከታ በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል። በአጠቃላይ 80 መምህራን እና 150 ተማሪዎች መጠይቁን ለመሙላት የተመረጡ ሲሆን፣ አምስት የሙያ ምክርና መምሪያ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና ሁለት የኢንተርፕራይዝ ፎካል ሰዎች ለቃለ መጠይቆች ናሙና የተወሰዱ ሲሆን 10 ተማሪዎች በቡድን መጠይቅ ተሳታፊዎች ሆነዋል። በኦሮሚያ ክልል በትላልቅ ከትሞች ዉስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ከመካከለኛና ከትላልቅ ኢንተርፕራይዞች ጋር በመስራታቸው የተሻለ ሰልጠና ልመስጠት አድል ተፈጥሮላቸዋል። በገጠርና በትናንሽ ከተሞች የሚገኙ ኮሌጆች አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ጋር ለመስራት ስለሚግደዱ ያልዉን ክፍተት ለመሙላት ችግር ይግጥማቸዋል። ይህ ማልት በክልሉ ያለው የትብብር ስልጠና የአካባቢን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት አልቻለም ማለት ነዉ። በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና በኢንተርፕራይዞች መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ እና ቁርጠኝነት፣ በጀት እና ከባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ያካተተ ሆኖ አልተገኝም። የስልጠና አቅዱ ኢንተርፕራይዞችን አያሳትፍም፤ በአኢንተርፕራይዝ ያሉት አምቻኞች መማር ውጤት እውቀት በጣም ትንሽ ከመሆኑም ብትጨማሪ በሰልጣኞች ግምገማ ላይ ተሳትፎ የላችውም። በትብብር ማሠልጠና ላይ ለተሳተፉት ኢንተርፕራይዞች ካሳ አይከፈላቸውም። እንዲሁም የትብብር ማሠልጠና ወቅት ለሚደርስ ጉዳት ማካካሻ ዋስትና የላቸውም። ስለዚህ የትብብር ስልጠናው አስፈላጊ በሆነ በጀት ያልተደገፈ እና የአካባቢ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተማሪውን ፍላጎት ያሟላ ሆኖ አልተገኝም።

training. Thus, cooperative training was not supported by the necessary budget and it failed to consider local contexts and did not seem it to meet the needs of the learners.

**Keywords:** Cooperative training; Technical and Vocational Education and Training; enterprises; Partnership.

**ቁልፍ ቃላት:** - የትብብር ስልጠና፣ የቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት እና ስልጠና፣ ኢንተርፕራይዞ፣, አጋርነት፤

## Assessing the implementation of quality assurance policy in Ethiopian higher education institutions

Manaye Abera Shamalo

### ABSTRACT

In Ethiopia, quality assurance in higher education is one of the government's top priorities, just like in other developing nations. This thesis assesses the implementation of quality assurance (QA) policies in Ethiopian public higher education. More specifically, it concentrates on determining the effectiveness of quality assurance practices and identifying implementation gaps in line with HERQA/ETA focus areas. The key research questions were: "how and under what conditions do public universities in Ethiopia execute ETA quality assurance policies, and what contextual factors influence QA policy implementation?" The study is based on the concept that student learning is at the heart of universities' educational purpose, and that focusing on the key educational processes and situations that impact student learning quality makes QA procedures more successful. The study was based on a conceptual framework comprising important concepts in contingency and institutional theories, as well as quality assurance approaches. Two organisational

## የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ማረጋገጫ ፖሊሲ አተገባበር መገምገም፤

በማናዬ አበራ ሻማሎ

### አጠቃሎ

እንደሌሎች ታዳጊ ሀገራት ሁሉ፣ በኢትዮጵያ የከፍተኛ ትምህርት ጥራትን ማረጋገጥ መንግስት ቅድሚያ ከሚሰጣቸው ቁልፍ ጉዳዮች አንዱ ነው። ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጥራት ማረጋገጫ (QA) ፖሊሲዎችን አተገባበር ይገመግማል። ጥናቱ በተለይም የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ(HER-QA)/የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን(ETA) የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ የጥራት ማረጋገጫ ልማዶችን ውጤታማነት በመፈተሸ እና የአፈፃፀም ክፍተቶችን በመለየት ላይ ያተኩራል። የጥናት ዋናዎቹ ጥያቄዎች፣ "በኢትዮጵያ የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን(E-TA) የትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎችን እንዴት እና በምን ሁኔታዎች ውስጥ ይተገብራሉ? እና በትምህርት ጥራት ለማረጋገጥ የተዘጋጁ ፖሊሲዎች (QA)ትግበራ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩት ምን ምን ሁኔታዎች ናቸው?" የሚሉት ናቸው። ጥናቱ፣ ‹‹የተማሪዎች መማር የዩኒቨርሲቲዎች እምብርት ነው›› በሚለው ፅንሰ-ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው። የትምህርት ዓላማ እና የመማር ማስተማር ተግባራት፤ በተማሪው የመማር ጥራት ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድሩ ቁልፍ የትምህርት ሂደቶች እና ሁኔታዎች ላይ ማተኮር የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ (QA) ሂደቶችን የበለጠ ስኬታማ ያደርገዋል። ጥናቱ በድንገተኛ (contingency theory) እና ተቋማዊ ጽንሰ-

theories, Contingency Theory, and Neo-Institutional Theory were used to provide a theoretical lens for explaining how internal and external organisational settings impact the implementation of QA policies at HEIs. The study employed a qualitative research approach, which included semi-structured interviews, textual open-ended questions, and document analysis. Purposive sampling was used to choose four public institutions as data sources. The ETA and MoE were also added at the macro level to analyse the impact of institutional contexts on institutional quality audit practices. The findings show that the implementation of QA policies was not conceptualised in public higher education at large and that reality on the ground differs from the literature generated on the science of QA, instead being applied partially in public institutions. They lack proper QA structures, processes, and documented policies. The QA initiatives were carried out without a clear sense of direction and objectives, resulting in ineffective coordination. Self-evaluations were held symbolically at higher levels of institutions, and the outcomes of the evaluations were seldom used in an organised manner to enhance teaching-learning, faculty decision-making and planning processes. It might be inferred that the ETA's  quality assurance policies appear to be disconnected from internal quality improvement programmes in HEIs. It is suggested that HEIs design institutional quality QA policies, mobilise resources for institutional quality development, construct fully-fledged QA structures at all levels, and staff the structures with the appropriate human resources. HEIs should begin and carry out effective self-assessment of their operations, own it, and strive towards achieving their stated goals. It is critical that the ETA creates accreditation mechanisms for public HEIs,

ሀሳቦች (neo-institutional theory) ውስጥ የጥራት ማረጋገጫ አቀራረቦችን ባካተተ የፅንሰ-ሃሳባዊ ማዕቀፍ ላይ የተመሰረተ ነው። በጥናቱ የተቋማቱ የውስጥ እና የውጭ ድርጅታዊ ቅንጅቶች በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ ፖሊሲዎችን አፈፃፀም ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ለማብራራት ሁለት ድርጅታዊ ንድፈ ሃሳቦች ማለትም የድንገተኛ ፅንሰ-ሀሳብ (contingency theory), እና የኒዮ-ተቋም ቲዎሪ (neo-institutional theory) የንድፈ-ሐሳብ መነፅር ለማቅረብ ጥቅም ላይ ውለዋል። ጥናቱ የጥራት(የገላጭ) ምርምር ስልት (qualitative research approach) መሠረት ያደረገ ሲሆን አጥኚው ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆችን (semi-structured interviews)፣ ክፍት ጥያቄዎችን (open-ended questions) እና የሰነድ ትንተናን (document analysis) ከቁልፍ የመረጃ አቀባዮች መረጃ ለማሰባሰብ ተጠቅሟል። እንዲሁም ለጥናቱ አስፈላጊ መረጃዎች ከአራት የመንግሥት ከፍተኛ ተቋማት ለመሰብሰብ የዒላማ ናሙና አመራረጥ (Purposive sampling)ተጠቅሟል። ተቋማዊ ሁኔታዎች በተቋማዊ የጥራት ኦዲት ሂደት ላይ ያላቸውን ተፅእኖ ለመተንተን የትምህርት ሥልጠና ባለሥልጣን (ETA) እና የትምህርት ሚኒስቴር በዒላማ ናሙና አመራረጥ (Purposive sampling ) በማክሮ ደረጃ በጥናቱ ተካተዋል። በትንተናው መሰረት የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ (QA) ፖሊሲዎች ትግበራ በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በታለመላቸው ግብ መሰረት እንዳልተተገበሩና ይልቁንም በመሬት ላይ ያለው እውነታ በትምህርት ጥራት ማረጋገጫ (QA) አስተምሮት ላይ ከቀረቡ ንድፈ-ሀሳብ እንደሚለይና አተገባበሩም በከፊል እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በተጨማሪም ተቋማቱ ትክክለኛ የሆኑ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫ (QA) መዋቅሮች፣ ሂደቶች እና የሰነድ ፖሊሲዎች እንደሌላቸው የጥናቱ ውጤት ያመላክታል። በተተኳሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተከናወኑ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫ (QA) ተግባራት አተገባበር ግልጽ የሆነ አቅጣጫ እና ግብ ሳይኖር በመሆኑ ውጤታማ ያልሆነ ቅንጅት ያስከተለ መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል። በተተኳሪ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደረጃ የተከናወኑት የግለ-ግምገማ ሂደቶች (self-evaluation)

particularly at the institutional level. The ETA should be more independent, with greater autonomy and adequate resources to become a sustainable professional agency supporting the HE sectors.

**Keywords:** Higher education institutions; quality; quality assurance; quality assurance policies; policy; policy implementation.

ታቅደው ሳይሆን ለይስሙላ የተካሄዱ ሲሆኑ፣ እነዚህም የግለ-ግምገማ ውጤቶች የመማር ማስተማር፣ የመምህራን የውሳኔ አሰጣጥ እና የዕቅድ ሂደቶችን ለማጎልበት በተደራጀ መንገድ እምብዛም ለትምህርት ጥራት ማረጋገጥ ጥቅም ላይ እንዳልዋሉ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። እንዲሁም በጥናቱ ውጤት መሰረት በትምህርት ሥልጠና ባለሥልጣን የተዘጋጁ የከፍተኛ ትምህርት የጥራት ማረጋገጫ ፖሊሲዎች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ የውስጥ የጥራት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ጋር ግንኙነት አላቸው ተብሎ አይታሰብም። በመጨረሻም በጥናቱ ከተገኘው ውጤት በመነሳት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ ጥራት ያለው የውስጥ ጥራት ኦዲት (IQA) ፖሊሲዎችን በመንደፍ፣ ግብዓቶችን በማሰባሰብ ለተቋማዊ ጥራት ልማት በየደረጃው የተሟላ የውስጥ ጥራት ኦዲት (IQA) መዋቅሮችን ማቋቋም እና ለመዋቅሮቹ ተገቢውን የሰው ሃይል መመደብ እንደሚያስፈልግ በጥናቱ ተጠቁሟል። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሥራቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ በመገምገም፣ በባለቤትነት የተያዙ እና የታቀዱ አላማዎችን ለማሳካት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው በአጥኚው ተጠቋሟል። የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ለመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተለይም በተቋም ደረጃ የእውቅና አሰጣጥ ዘዴዎችን መፍጠር ወሳኝነት አለው። የትምህርት ሥልጠና ባለሥልጣን የከፍተኛ ትምህርት ዘርፍን በበቂ ሁኔታ የሚደግፍ ዘላቂ ፕሮፌሽናል ኤጀንሲ ለመሆን የበለጠ ራሱን የቻለ፣ በራስ የመመራት አቅም ያለው እና በቂ ሀብት የተመደበለት መሆን እንደሚገባው ጥናቱ ጠቁሟል።

**ቁልፍ ቃላት:**- የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ ጥራት፣ የጥራት ማረጋገጫ፣ የጥራት ማረጋገጫ ፖሊሲዎች፣ ፖሊሲ፣ ፖሊሲ ትግበራ፤

# Principals' leadership behaviour and academic achievement in secondary schools of Gedeo Zone, Ethiopia

Seyoum Gari Aleme

## ABSTRACT

Currently, schools require effective principals who actualise the academic success of all students. As accountability of principals' increases, many researchers are inspired to identify the effective types of leadership behaviours. Although these researchers reached an agreement on the decisiveness of leadership, they did not agree on the most effective type of leadership behaviour that promotes students' achievement. The researcher was initiated to conduct this study because of the prevalence of low students' achievement in the Gedeo Zone and the observed controversies regarding the effective types of leadership behaviours. The study's objective was to examine the effect of secondary school principals' leadership behaviours on students' achievement in Gedeo Zone, Ethiopia, and thereby to identify the effective type of leadership construct that enhances learners' success. The Explanatory Sequential Mixed Design was used. The Zone's three least and three best achievers were chosen as sample schools using the maximum variation strategy. The source of data was 141 teachers and 180 students selected by proportional stratified technique as well as 18 interviewees who were chosen purposively. Data were collected using questionnaires, interviews, and document analyses. The quantitative data were analysed using mean, standard deviation, T-test, correlation, regression, and graphs. The qualitative data were analysed through a content analysis approach. The findings of

# በጌዴኦ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የርዕሰ መምህራን የአመራር ባህሪ እና የአካዳሚክ ስኬት ፤ኢትዮጵያ

በስዩም ጋሪ አለሜ

## አጠቃሎ

በአሁኑ ወቅት፤ ትምህርት ቤቶች የሁሉንም ተማሪዎች አካዴሚያዊ ስኬትን ተግባራዊ የሚያደርጉ ውጤታማ ርእሰ መምህራን ይፈልጋሉ። የርእሰ መምህራን የተጠያቂነት አድማስ እየሰፋ በመምጣቱ ፣ ብዙ ተመራማሪዎች ውጤታማ የአመራር ባህሪያትን ለመለየት በከፍተኛ ተነሳሽነት ጥናት በማድረግ ላይ ይገኛሉ። ምንም እንኳን እነዚህ ተመራማሪዎች፤ የአመራር ሚና ቁልፍ እንደሆነ ሁሉም የሚስማሙበት ቢሆንም፣ ተማሪዎች ስኬታማ እንዲሆኑ በማስቻል ረገድ በጣም ውጤታማና ተመራጩ የአመራር ባህሪ አይነትን መለየት ላይ መግባባት ላይ አልተደረሰም። በዞኑ በተደጋጋሚ የተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ ሆኖ መታየትና በጣም ውጤታማ የአመራር ባህሪ አይነትን በተመለከተ የጥናቶች ውጤት አወዛጋቢ መሆናቸው፤ ተመራማሪው በጉዳዩ ላይ ጥናት እንዲያደርግ አነሳስቶታል። የጥናቱ አላማ ፤ በጌዴዮ ዞን የ2ኛ ደረጃ ት/ቤት ርእሰ መምህራን የአመራር ዘይቤ በተማሪዎች ውጤት ላይ ያለውን ተጽእኖ በመፈተሽ፣ የተማሪዎችን ስኬት የሚያጎለብት ውጤታማ የአመራር አይነትን ለመለየት ነው። ጥናቱን ለማካሄድ ገላጭ ተከታታይ ውህድ የጥናት ዲዛይን ተተግብረል፡፤ በሁለት ጫፍ የሚታዩ ባህሪ መምረጫ ስልትን በመጠቀም፣በተማሪዎች ውጤት ላይ በመሞርኮዝ ከዞኑ ሶስት ዝቀተኛ እና ሶስት ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸውን በድምሩ ስድስት ናሙና ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ላይ ተሳትፈዋል። በተመጣጣኝ ስትራቲፋይድ ቴክኒክ የተመረጡ 141 መምህራን እና 180 ተማሪዎች እንዲሁም፣ ሆን ተብሎ የተመረጡ 18 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው መላሾች ተሳታፊ ሆነዋል። መረጃ የተሰበሰበው መጠይቆችን፣ ቃለመጠይቆችን እና የሰነድ ትንታኔዎችን በመጠቀም ነው። የቁጥር መረጃው አማካኝ፣ መደበኛ መዛባት፣ ቲ-ሙከራ፣ ተዛማጅነት፣ ሪግሬሽን እና ግራፎችን በመጠቀም ተንትኗል። የጥራት መረጃው የተተነተነው በይዘት

this study showed that effectively practicing instructional and transformational behaviours in integrative ways enhanced students' achievement; exhibiting high-task behaviours that focused on teaching-learning increases students' success while high relationships intended to get mere affiliation deterred achievement; a strong correlation exists between preserving of a positive school climate and students' achievement; principals' leadership effect reaches learners through mediators indirectly and comprehensive leadership constructs are preferred as an effective style. Based on these findings, principals are recommended to employ integrative leadership which comprises ingredients of instructional, transformational, and positive school climate as their combined effect and which promote students' achievement by strengthening teaching-learning, transforming members and sustaining success respectively. Principals are advised to exhibit high-task behaviours in their engagements and alert members to play their role in improving students' learning. They also recommended making academic and affective environments favourable because such circumstances enhanced students' achievement.

**Keywords:** Explanatory Sequential Mixed Design; integrative leadership; leadership behaviours; leadership effect; learning centred leadership; maximal variation strategy; positive school climate; leadership effectiveness; leadership orientation; secondary schools; students' achievement.

ትንተና አቀራረብ ነው። መማር-ማስተማር ተኮር እና ትራንስፎርሜሽናል የአመራር ባህሪን በጥምረት የያዘውን የተቀናጀ የአመራር ዘይቤን በርእሰ መምህራን ውጤታማ በሆነ መንገድ መተግበር ተማሪዎች በትምህርታቸው ስኬታማ እንዲሆኑ እንደሚያስችል የዚህ ጥናት ግኝቶች ያሳያሉ። ለመማር ማስተማር ቅድሚያ የሚሰጥ ስራ ተኮር የአመራር ባህሪ በርአሰ መምራን ማሳየት የተማሪዎችን ስኬት እንዲጨምር ሲደረግ፣ መወደድን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ግንኙነት ተኮር የአመራር ዘይቤ የተማሪዎችን ውጤታማነት ያደናቅፋል። በአዎንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ እና በተማሪዎች ስኬታማነት መካከል ጠንካራ ግንኙነት መኖሩ በጥናቱ ተረጋግጣል። የርእሰ መምህራን የአመራር በጎ ተፅዕኖ ተማሪዎች ዘንድ የሚደርሰው በተዘዋዋሪ በሌሎች ድልድይነት መሆኑ በጥናቱ ታውቀል፡፤አንድ የአመራር ዘይቤ ከመከተል ይልቅ የተለያየ የአመራር ባህሪ በተቀናጀ መልኩ መጠቀም ውጤታማ እንደሚያደርግ የጥናቱ ግኝቶች አረጋግጠዋል፡፤በእነዚህ ግኝቶች መሰረት፣ ርእሰ መምህራን መማር-ማስተማር ተኮር፣ ትራንስፎርሜሽናል እና አዎንታዊ የት/ቤት ድባብ ማጠናከርን በአንድነት ያካተተ የተቀናጀ አመራር ዘይቤን እንዲከተሉ ይመከራሉ። ምክንያቱም ጥምር ውጤታቸው የመማር ማስተማርን በማጠናከር፣ አባላትን በማብቃት እና የተገኘ ውጤትን በማስቀጠል የተማሪዎችን ስኬታማነት ለማረጋገጥ ያሰችላል። ርእሰ መምህራን ተግባር ተኮር ባህሪን እንዲያሳዩ ይመከራሉ ምክንያቱም የነሱ ተሳትፎ አባሎቻቸው የተማሪዎችን ትምህርት ለማሻሻል ሚናቸውን እንዲጫወቱ ያነቃቃል። ርዕሰ መምህራን የትምህርት ቤቱን አካዳሚክ እና የእችላለሁ አስተሳሰብ ድባብ በማስፋት የተማሪዎችን ስኬታማነት እንዲያሳድጉ ይመከራሉ።

**ቁልፍ ቃላት**:- ገላጭ ተከታታይ ድብልቅ ንድፍ፣ የተቀናጀ አመራር፣ የአመራር ባህሪያት፣ የአመራር ውጤት፣ መማር-ማስተማር ተኮር አመራር፣ ከፍተኛ ልዩነት ስልት፣ አወንታዊ የትምህርት ቤት ድባብ ፣ የአመራር ውጤታማነት፣ የአመራር ትኩረት፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የተማሪዎች ስኬት፤

# Evaluating the management of school improvement programme implementation in the secondary schools in Wolaita Zone, Ethiopia

Tesema Abebe Abire

## ABSTRACT

The concept 'school improvement' indicates the plan to improve the quality of teaching and learning in a school. Quality education is a prominent agenda across the world, and countries such as Ethiopia are implementing various quality improvement initiatives. The Ethiopian Education and Training Policy (1994), which included the school improvement programme (SIP) as part of the educational reforms, was brought about to improve the quality of education. The purpose of this study was to evaluate the management of the school improvement programme implementation in the secondary schools in the Wolaita Zone, Ethiopia. The study aims to understand the participants' experiences with the school improvement programme and then be able to understand the challenges and suggest ways to improve the SIP. A mixed methods research approach was used to complete the study. Moreover, of the mixed methods sub-divisions, a convergent/concurrent triangulation design is used. A quantitative questionnaire and qualitative methods (focus group interviews and document analysis) were used for data collection. A total of 37 managers and 250 teachers participated in the study. A questionnaire with closed-ended and open-ended questions, which secured a 99 percent response rate, was administered to collect data from the selected teachers and managers (principals, vice-principals and HODs). During the qualitative phase,

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤቶች ማሻሻያ መርሃግብር ትግበራ አመራርን መገምገም በወላይታ ዞን በሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፡ወላይታ ዞን ኢትዮጵያ

በተሰማ አበበ አብሬ

## አጠቃሎ

‹‹የትምህርት ቤት መሻሻል›› ጽንሰ-ሐሳብ በትምህርት ቤት ውስጥ የመማር እና የማስተማር ጥራት ለማሻሻል የተነደፈ እቅድን ያመለክታል፡፡ ጥራት ያለው ትምህርት በአለም ዙሪያ ጎልቶ የሚታይ አጀንዳ ሲሆን፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራት የተለያዩ የጥራት ማሻሻያ ስራዎችን በመተግበር ላይ ናቸው። የኢትዮጵያ ትምህርት እና ስልጠና ፖሊሲ (1994) የትምህርት ማሻሻያ አካል የሆነውን የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር (SIP)ን ያካተተው የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እየሰራ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አላማ በወላይታ ዞን በሚገኙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃግብር አተገባበርን ለመገምገም ነው። በዚህም ጥናቱ በትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃግብር ላይ የተሣታፊዎችን ልምድ በመረዳት፣ ያሉትን ተግዳሮቶች በመለየት የመፍትሄ ሃሳብ በማቅረብ የመርሃግብሩን አተገባበር ለማሻሻል ከፍተኛ ጥቅም ያስገኛል። ይህ ጥናት የተከተለው ድብልቅ(ቅይጥ) የምርምር ዘዴን ነው፡፡ በዋናነትም፣ ከተደባለቁ የምርምር ዘዴዎች ንዑስ ክፍልፋዮች፣ ከሁለትና ከዚያ በላይ የመረጃ ምንጮች ተገኘ ዉጤት ማመሳከር ጥቅም ላይ ውሏል። ከዚህም በላይ የአሃዛዊ መጠይቅ እና የአሃዛዊ ያልሆነ መረጃ አሰባሰብ ዘዴዎች (የትኩረት የቡድን ቃለ-መጠይቆች እና የሰነድ ትንተና) ለመረጃ ስብስብ ጥቅም ላይ ውለዋል። በጥናቱ 37 የትምህር ቤት አመራሮች (ር/መምህራን፤ ም/ር/መምህራንና የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች) እና 250 መምህራን ተሳትፈዋል። ከተመረጡት መምህራን እና አመራሮች (ርዕሳነ መምህራን፣ ምክትል ርዕሳነ መምህራን እና የትምህርት ክፍል ተጠሪዎች) መረጃ ለመሰብሰብ 99 በመቶ ምላሽ የሚሰጥ፣ ዝግ እና ክፍት

10 supervisors, 10 school improvement committee members, 10 Woreda Education Office SIP experts and four zone SIP experts participated in the focus group interviews. Qualitative findings are not as positive as the quantitative findings on most of the issues that were evaluated. The researcher is of the opinion that this is because of the nature of the qualitative participants, their position, knowledge and experience of SIP management, which differs from that of the quantitative participants. The study results make a contribution to the research on the management practice of SIP implementation, especially since no study on this issue has been conducted in the Wolaita Zone of Ethiopia before. It was possible to make several meaningful recommendations for the management of SIP implementation in the Wolaita Zone. They inter alia pertain to: the Zone Education Department (ZED) and the Woreda Education Office (WEO) staff, cluster supervisors, school principals and the school improvement committees who should give continuous support for managing the school improvement programme. This can be done by relevant stakeholders facilitating training, allocating an adequate budget, mobilising the school community towards supporting SIP, and making stakeholders aware of the school improvement programme and school improvement resources. Important findings relate to improvement in the planning, organising, leading and monitoring and evaluation of the programme.

**Keywords:** Management of the school improvement programme; conceptualising school improvement; mixed methods approach; management functions; planning; organising; leading; monitoring and evaluation; secondary schools.

ጥያቄዎች ያሉት መጠይቅ ተዘጋጅቷል። በአሃዛዊ ባልሆነ መረጃ አሰባሰብ 10 ሱፐርቫይዘሮች፣ 10 የት/ቤት ማሻሻያ ኮሚቴ አባላት፣ 10 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የትምህርት መሻሻል ባለሙያዎች እና የአራት ዞን ትምህርት መምሪያ የትምህርት መሻሻል ባለሙያዎች በትኩረት ቡድን ቃለ ምልልስ ተሳትፈዋል። በአብዛኛዎቹ የተገመገሙ ጉዳዮች ላይ እንደ አሃዛዊ ግኝቶች የአሃዛዊ ያልሆኑ ግኝቶች አወንታዊ አይደሉም። ይህ የሆነበት ምክንያት የአሃዛዊ ያልሆነ ቡድን ተሳታፊዎች ባህሪ፣ የት/ቤት መሻሻል መርሃግብር የሚመሩ አካላት አቋም፣ እውቀት እና ልምድ ከአሃዛዊ መረጃ ሰጪ ተሳታፊዎች ስለሚለይ መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል። የጥናቱ ውጤት በትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃግብር አተገባበር ላይ ለሚደረገው ጥናት አስተዋፅዖ አለው፤ በተለይም በዚህ ጉዳይ ላይ በዞኑ ከዚህ በፊት በዚህ የጥናት ርዕስ ምንም ጥናት አልተደረገም። በወላይታ ዞን ለትምህርት ቤት መሻሻል መርሃግብር ትግበራ አመራር በርካታ ጠቃሚ ምክሮችን መስጠት ተችሏል። እነሱም የዞኑ ትምህርት መምሪያ እና የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ የክላስተር ሱፐርቫይዘሮች፣ የት/ቤት ርእሰ መምህራን እና የት/ቤት ማሻሻያ ኮሚቴዎች የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃግብርን ለመምራት የማያቋርጥ ድጋፍ ማድረግ አለባቸው። ይህንንም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ስልጠናዎችን በማመቻቸት፣ በቂ በጀት በመመደብ፣ የትምህርት ቤቱን ማህበረሰብ በማስተባበርና ት/ቤት መሻሻል መርሃግብርን መደገፍ እና ባለድርሻ አካላት ስለትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር እና የትምህርት ቤት ማሻሻያ ግብዓቶች ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ነው። በመጨረሻም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የፕሮግራሙን እቅድ በማዘጋጀት፣ በመምራት፣ በመቆጣጠር እና በመገምገም የትግበራውን ሂደት ለማሻሻል እንደሚያግዙ አጥኚው ያምናል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር አመራር፣ የት/ቤት መሻሻል ጽንሰ ሃሳብ፣ የተደባለቁ/የተቀላቀሉ ዘዴዎች አቀራረብ፣ የአመራር ተግባራት፣ እቅድ ማውጣት፣ ማደራጀት፣ መምራት፣ ክትትል እና ግምገማ፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፤

# The implementation of the improvement programme in public primary schools of Oromia towns surrounding Finfine, Ethiopia

Wakweya Gudeta Moreda


## ABSTRACT

The purpose of this study was to examine and describe the implementation of the School Improvement Programme in public primary schools of Oromia Regional State towns surrounding Finfine, Ethiopia. The research was conducted using the constructivist paradigm with the qualitative research approach. Among different types of qualitative research designs, phenomenology was used to address the problem of the implementation of the improvement programme in public primary schools of Oromia National Regional State towns surrounding Finfine, Ethiopia. The participants of the study were selected purposefully. Accordingly, Regional State Education Bureau's three towns education offices, three CRC and six schools were selected. From these institutions, one team leader from Oromia Education Bureau, three team leaders of the school improvement team from each Town Education Office, three CRC supervisors from CRC, six principals, six PTA chairpersons and seven teachers from each sample school were selected. The data were collected from these participants using interviews, focus group discussion, observation and review documents. The data collected was categorised into themes and analysed accordingly. The findings of the study reveals that a limited number of strategies, planning, monitoring and evaluation and training were used to implement school improvement though


# የመንግስት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የማሻሻያ መርሃ-ግብር ትግበራ፡ በፊንፊኔ ዙሪያ በሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞች፤

በዋቅወያ ጉደታ ሞረዳ


## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ በኦሮሚያ ክልል ፊንፊኔ ዙሪያ በሚገኙ ከተሞች የመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሃ-ግብር አፈፃፀምን ለመመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው ኮንስትራክቲቪስት ፓራዲም ከአይነታዊ (qualitative) ምርምር አቀራረብ ጋር በመጠቀም ነው። ከተለያዩ አይነታዊ የምርምር ዓይነቶች መካከል ፌኖሜኖሎጂ ዲዛይን ጥቅም ላይ ውሏል። የጥናቱ ተሳታፊዎች purposive sampling ዘዴን በመጠቀም ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት የክልሉ ትምህርት ቢሮ፣ ሶስት የከተማ ትምህርት ጽ/ቤቶች፣ ሶስት CRC እና ስድስት ትምህርት ቤቶች ተመርጠዋል። በዚህም መሰረት ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አንድ ቡድን መሪ ፣ ከእያንዳንዱ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሦስት የትምህርት ቤት ማሻሻያ ቡድን መሪዎች፣ ከCRC ሦስት ፐርቫይዘሮች፣ ስድስት ርዕሰ-መምህራን፣ ስድስት የወላጅ-መምህር ህብርት(P-TA) ሰብሳቢዎችና ሰባት መምህራን ከእያንዳንዱ ናሙና ትምህርት ቤት ተመርጠዋል። ለጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በቃለመጠይቅ፣ የትኩረት ቡድን ውይይት (FGD)፣ በምልከታ እና የሰነዶችን ትንተና በመጠቀም ነው። የተሰበሰበው መረጃ በጭብጦች ተከፋፍሎ ተተንትኗል። የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየዉ ምንም እንኳን በሥነጽሑፍ እና በትምህርት ሚኒስቴር መመሪያዎች ውስጥ ብዙ የትምህርት ቤት ማሻሻያ ስልቶች(School Improvement Strategies) ቢኖሩም በእነዚህ ናሙና ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሀግብርን ለመተግበር ውስን \የእቅድ፣ የክትትል እና የግምገማ እና ስልጠና ስልቶች ጥቅም ላይ ውለዋል። በአጠቃላይ የህብረተሰቡን በተለይም የት/ቤቱን ማህበረሰብ የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ ላይ ያለውን ተሳትፎን በሚመለከት የተጠበቀውን ያህል አለመሆኑን የጥናቱ ግኝት አረጋግጧል። በትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅድ

there are many strategies in the literature and MoE guidelines. The findings of the study concerning the participation of the community in general and school community in particular in planning school improvement is not as expected. The school leadership and management team prepared it with no or limited participation of these bodies and the awareness made to the school community is not sufficient. The findings of the study also indicated that no principal of the school uses instructional leadership. Some school principals had no know-how about leadership approaches to lead schools as they are graduating in one particular subject of teaching. Even though the contribution of CPD is great for good implementation of school improvement, it is not implemented as it should. The awareness different parties have on CPD is different. The training and experience sharing on the implementation of CPD is very low as it is challenged by different problems among which is teachers' resistance, lack of resources, overburdening of teachers and lack of incentives. In addition, the implementation of action research is also challenged by lack of skill and knowledge, interest and work overload and lack of support from leadership at a different level of the hierarchy of the education system of the regional state. As it can be understood from the findings of the study, active learning methods were used in classroom instruction. However, most of the time teachers use the lecture method to save their time and believe that the learners can understand the lesson if the teacher lectures rather than the learners working by themselves. The findings of the study also indicated that teachers do not produce supplementary material for reference. The community participation in general and participation of parents, in particular, is not sufficient as it is expected. The school environment is not conducive to implementing school improvement and

አዘገጃጀት ላይ የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ ውስን መሆን እና እቅዱን ለሚያዘጋጁት አካላት በቂ ግንዛቤ ያልተሰጠ መሆኑ ጥናቱ አረጋግጧል፡ ፡ እንዲሁም የትኛውም የት/ቤት ርእሰ መምህር የመማር-የማስተማር አመራር ስልትን (Instructional Leadership) እንደማይጠቀም የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። አንዳንድ የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን በአንድ የተለየ ትምህርት አይነት የተመረቁ በመሆናቸው ስለመሪነት አቀራረቦች (Leadership Approaches) ያላቸው ግንዛቤ አናሳ ነው። ምንም እንኳን፣ ለትምህርት ቤት ማሻሻያ ጥሩ ትግበራ የCPD አስተዋፅዖ ከፍተኛ ቢሆንም መተግበር በሚገባው መጠን አልተተገበረም። በCPD ላይ የተለያዩ ወገኖች ያላቸው ግንዛቤ የተለያየ ነው። በCPD አተገባበር ላይ ያለው የሥልጠና እና የልምድ ልውውጥ በጣም ዝቅተኛና በተለያዩ ችግሮች እየተፈተነ ያለ ነው። ከነዚህም መካከል የመምህራን ፍላጎት ማነስ፣ የግብዓት እጥረት፣ የመምህራን የስራ ጫና እና የማበረታቻ አለመኖር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡ ፡ በተጨማሪም በክህሎትና በእውቀት ማነስ ፣ በፍላጎት ማነስ እና በስራ መብዛት እንዲሁም በክልሉ የትምህርት ስርዓት ተዋረድ በተለያየ ደረጃ ያለው አመራር ድጋፍ ማነስ ምክንያት የተግባር ጥናትና ምርምር አተገባበር የሚፈለገውን ያህል ስራ ላይ አልዋለም። ከጥናቱ ግኝቶች መረዳት እንደሚቻለው በክፍል ውስጥ ትምህርት አሳታፊ የመማር ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ይሁን እንጂ አብዛኛውን ጊዜ መምህራን ጊዜያችንን ይቆጥብልናል በሚል ምክንያት የገለጻ (lecture) የማስተማር ዘዴን የሚጠቀሙ ከመሆኑም በተጨማሪ በገለጻ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎቹ ትምህርቱን የበለጠ እንዲረዱት ያስችላል ብለዉ ያምናሉ። የጥናቱ ግኝት መምህራን ለማጣቀሻነት ተጨማሪ ጽሑፎችን እንደማያዘጋጁ አመልክቷል፡ ፡ በአጠቃላይ የማህበረሰብ፣ በተለይም የወላጆች ተሳትፎ በሚጠበቀው መልኩ በቂ አይደለም። የትምህርት ቤት ማሻሻያን ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት አካባቢው የሚፈለገውን ያህል ምቹ አይደለም፤ እንዲሁም የትምህርት ቤት ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅርቦት እጥረት መኖሩን ጥናቱ አመልክቷል፡ ፡ የትምህርት ቤት ገቢን በሚመለከት በጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየው፣ ከትምህርት ቤቱ የሚገኘው ገቢ ለትምህርት ቤት ማሻሻያ ትግበራ በመንግስት ለሚመደበዉ የበጀት

there is also a lack of facilities to implement school improvement. The finding of the study, in regard to school's income, revealed that the income generated by the school is not sufficient to supplement the government budget for the good implementation of school improvement. As the finding of the study revealed, the stakeholders viewed that the implementation of the school improvement is not effective because of different challenges. The shortage of human resources, lack of training, non-participation in planning, lack of commitment of leadership and teachers and limited monitoring and evaluation are among the challenges that hinder the effective implementation of school improvement. Based on the findings of the study, recommendations were forwarded. These recommendations are: using diversifying strategies, using a participatory approach in the planning process, revising the criteria for the selection of school principals, providing capacity building to the role-players of school improvement based on their role and responsibility in the implementation of school improvement, strengthening the structure of the CRC, strengthening school pedagogical centres, rethinking the implementation of CPD, creating the opportunity to teachers to conduct action research, strengthening the mechanism of monitoring and evaluation of the implementation of school improvement, strengthening community participation, creating a conducive learning environment and fulfilling educational facilities. Finally, the Whole School Approach Model together with TQM was proposed for the implementation of school improvement.

**Keywords:** School improvement programme; implementation; community involvement; learning environment; teaching and learning process; primary school; public primary school; Oromia Regional State towns surrounding Finfine; Total Quality Management; quality; education.

እጥረትን ለመቅረፍ በቂ አለመሆኑን ጥናቱ አመልክቷል። ባለድርሻ አካላት የትምህርት ቤትን ማሻሻያ አተገባበር ለማገዝ የሚያደርጉት እገዛ በተለያዩ ተግዳሮቶች ምክንያት ውጤታማ እንዳልሆነ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል። እነዚህም የሰው ሃይል እጥረት፣ የስልጠና ማነስ፣ በእቅድ አለመሳተፍ፣ የአመራርና የመምህራን ቁርጠኝነት ማነስ፣ የክትትልና ግምገማ ውስንነት የት/ቤት ማሻሻያ ውጤታማ እንዳይሆን እንቅፋት ከሆኑ ተግዳሮቶች መካከል ናቸው። በጥናቱ ውጤት ላይ በመመርኮዝ የሚከተሉትን ምክረ-ሀሳቦች ቀርበዋል። እነሱም፣ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን መጠቀም፣ በዕቅድ ሂደት ውስጥ አሳታፊ አቀራረብን መጠቀም፣ የት/ቤት ርእሰ መምህራን ምርጫ መስፈርትን ማሻሻል፣ ለትምህርት ቤት መሻሻል ሚና ያላቸው ተዋናዮች በት/ቤት ማሻሻያ ትግበራ ውስጥ ባላቸው ሚና እና ኃላፊነት ላይ በመመስረት የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን፣ የCRC መዋቅርን ማጠናከር፣ በየት/ቤቶች የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከላትን ማጠናከር፣ የ CPD አተገባበርን እንደገና ማጤን፣ መምህራን የተግባር ጥናት እንዲያካሂዱ እድል መፍጠር፣ የት/ቤት መሻሻል ትግበራ የክትትል እና ግምገማ ዘዴን ማጠናከር፣ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ማጠናከር፣ ተስማሚ የትምህርት አካባቢ መፍጠር፣ እና የትምህርት መገልገያዎችን ማሟላት ናቸዉ። በመጨረሻም ጥናቱ ለትምህርት ቤት ማሻሻያ መርሀ-ግብር ትግበራ ይሆን ዘንድ ሁል-አቅፍ የትምህርት ቤቱ ሞዴል (the whole school Approach Model) ከ አጠቃላይ የጥራት አስተዳደር(TQM) ጋር ቀርቧል።

**ቁልፍ** ቃላት፡-የትምህርት ቤት ማሻሻያ ተሳትፎ፣ የመማር ማስተማር አካባቢ፣የመማር እና ማስተማር ሂደት፣የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት፣የመንግስት አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ በፊንፊኔ ዙሪያ ያሉ የኦሮሚያ ክልል ከተሞች፣ አጠቃላይ የጥራት አስተዳደር (TQM)፣ጥራት፣ትምህርት።

Year of Graduation 2023

# Practices and challenges in financial resource management at selected government secondary schools of Wolaita Zone in Ethiopia

Abraham Ololo Ossa


## ABSTRACT

The government of Ethiopia places a very high priority for poverty alleviation as part of its overall goals for socio-economic development. As a result, education is one of the four priority sectors that were identified as a major tool for the poverty alleviation strategy. The main objective of any educational system is to cultivate the individual capacity for problem-solving and adaptability to the environment by developing the necessary knowledge, ability, skill and attitude. To offer effective and efficient education for generations, human resources along with material, financial and time resources should efficiently be utilised for schools to attain their goals. This shows that educational activity cannot be successfully run without adequate financial support in addition to human, material and time resources. Therefore, to enhance educational activities, sound financial management is necessary. Accordingly, this research examined the practices and challenges in financial resource management at selected government secondary schools and put forward possible recommendations to overcome those challenges that hinder effective utilisation of school funds.

This study was qualitative in nature and used a case study that allowed the researcher to achieve the study's goals of gaining an in-depth understanding of


# በወላይታ ዞን ኢትዮጵያ በተመረጡ የመንግስት 2ኛ ደረጃ ትም/ቤቶች የገንዘብ አጠቃቀም አሰራር ሥርዓትና ተግዳሮቶች ላይ የተደረገ ጥናት

በአብርሃም ኦሎሎ ኦሣ


## አጠቃሎ

ድህነትን መቀነስ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት አጠቃላይ ግቦች አንዱ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል። የድህነት ቅነሳ ዋነኛ ስትራቴጂ ተብሎ ከተለዩት አራቱ ዘርፎች መካከል አንዱና ዋነኛዉ ትምህርት ነዉ። የትምህርት ሥርዓት ዋና አላማዉ አስፈላጊውን እውቀት፣ ችሎታ፣ ክህሎት እና አመለካከት በማዳበር ችግሮችን የመፍታት እና ከአካባቢው ጋር የመላመድ አቅምን ለትዉልድ ማጎልበት ነው። ዉጤታማና የተቀላጠፈ ትምህርት ለትዉልድ በአግባቡ ለመስጠት ትም/ቤቶች የተመደበላቸዉን ግብአቶች ማለትም የሰዉ ኃይል፤ቁሳቁስ፤ገንዘብና ጊዜን አሰራርን ተከትሎ በአግባቡና ዉጤታማ በሆነ መልኩ በሥራ ላይ ማዋል አለባቸዉ። ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የትምህርት ሥራን ዉጤታማ ለማድረግ የሰዉ ኃይልን፤ቁሳቁስና ጊዜን በአግባቡ መጠቀም እንደተጠበቀ ሆኖ ያለ በቂ ገንዘብ እና ያለ ትክክለኛ የትም/ቤት ገንዘብ አሰራር ማሰብም እንደማይቻል ነዉ። በመሆኑም የትምህርት ሥራን ዉጤታማ ለማድረግ ትክክለኛ የትም/ቤት ገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት እጅግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት በወላይት ዞን በተመረጡ የመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የገንዘብ ሀብት አስተዳደር አሠራሮች በመፈተሽ እና ተግዳሮቶች በመለየት ላይ ያተኮረ ሲሆን ትምህርት ቤቶች የተመደበላቸዉን ገንዘብ ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲጠቀሙ የሚያስችል ምክረ ሐሳቦችን በመለየት ላይ ያጠነጠነ ነዉ።

ይህ ጥናት ኳልታቲቭ/ qualitative/ የጥናታዊ ጽሑፍ ሂደትን የተከተለ ሲሆን የጥናቱን ዓላማ ለማሳካትና በወላይት ዞን በተመረጡ የመንግስት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የገንዘብ ሀብት

practices and challenges in school finance management at selected government secondary schools. Based on the analysis made and the reflection on the data, it is posited that school principals and other school governing body (SGB) members were not in charge of performing their duties effectively to manage school funds efficiently due to many reasons. Underperforming of principals and other SGB members in financial management resulted from employing less qualified accounting staff that maintain poor records and fail to observe accounting procedures. Moreover, there was a lack of professionalism in some areas as far as management of schools' finance is concerned and this called for qualified personnel in the management of school finances. It is important for school administration to understand that business management goes beyond allocating cash items but has to look at the school as an investment which would in due time pay dividends to the government but not at the study area. As a result, schools experienced problems of poor financial management. Mismanagement of funds led to shortage of critical resources as money was not available for the purchasing of the necessary equipment and other school needs which often resulted in the unsatisfactory performance of the school community, parents, teachers, students and other stakeholders of schools.

To enhance educational activities, sound financial management is necessary. Therefore, school principals in collaboration with other SGB members must be in charge of managing school resources to enhance the transparency in the deployment of resources. As a result, this study recommends that school principals as chief financial officers and other SGB members must have an authority of clarifying the purpose of the budget process, choose the

አስተዳደር አሠራሮች ለመፈተሽ እና ተግዳሮቶች ለመለየት ኬዝ ስታዲ/case study/ የጥናታዊ ጽሑፍ ሥነ-ዜዴን የተከተለ ነዉ። ከመረጃ ትንታኔ ከተገኘዉ ነፀብራቅ ማየት እንደተቻለዉ፤ በብዙ ምክንያቶች የት/ቤቶች ርእሳነ- መምህራን እና ሌሎች የት/ቤት አስተዳደር አካል የት/ቤቶችን የገንዘብ ሐብት በብቃትና በኃላፊነት ለማስተዳደር መቸገራቸዉንና የተጣለባቸዉን ኃላፊነት በብቃት እንዳልወጡ ማረጋገጥ ተችሏል። በሙያዉ ያልሰለጠኑ ባለሙያዎች በዘርፉ መመደባቸዉ የትም/ቤቶችን የገንዘብ መረጃ በአግበቡ እንዳይሰረና እንዳይዙ እንዲሁም በሥራ ዉጤታማ እንዳይሆኑ ትልቁ ምክንያት ሆነዋል። በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች በዘርፉ የሰለጠነ የሰዉ ኃይል እጥረት መኖሩ ትልቁ ምክንያት ሆኖ ታይተል። የትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት ለትምህርት ቤቶች የገንዘብ ሐብት ከመመደብ ባሻገር አፈጻጸሙን በአግባቡ በመከታተል ትምህርት ቤቶችን እንደገቢ ምንጭ በመጠቀም ትርፋማ መሆን የሚገባቸዉ ቢሆንም ጥናቱ በተካሄደባቸዉ ተቋማት የዚህ ዓይነት አሰራር ማየት አልተቻለም። በዚህ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ደካማ የትምህርት ቤት ገንዘብ አስተዳደር ችግሮች አጋጥሟቸዋል። በመሆኑም ይህ ዓይነት ደካማ የትምህርት ቤቶች የገንዘብ ሐብት አጠቃቀም ሥርዓት በትምህርት ቤቶች የገንዘብ ሐብት እጥረት የሚያስከትል በመሆኑ ለትምህርት ቤቶች አስፈላጊዉን ግብአትና ቁሳቁሶችን በአግባቡ ማሟላት የማይቻል በመሆኑ የትምህርት ቤት ባለድርሻ አካላት ማለትም ተማሪ ወላጆች ፣ መምህራን እና ለሌሎች የትምህርት ቤት ባለድርሻ አካላት አፈጻጸማቸዉ ዝቅተኛ እንዲሆን አስችሏል።

የትምህርት ሥራን በአግባቡና በዉጤታማነት ለመምራት ተገቢና አሰራን የተከተለ የትምህርት ቤት የገንዘብ ሐብት አጠቃቀም እጅግ አስፈላጊ ነዉ። ስለሆነም የትምህርት ቤት ርእሰ መምህራን ሌሎች የትምህርት ቤት አመራር አካላት በቅንጅት በመሥራትና ኃላፊነታቸዉን በአግባቡ በመወጣት የትምህርት ቤት የገንዘብ ሐብት አጠቃቀም ግልፅኝነትን በማዳበር የትምህርት ቤት ግብዓቶችን የመምራት ሃላፊነት አለባቸው። በመሆኑም ይህ ጥናት የትምህርት ቤቶች ርዕሳነ መምህራን እንደዋና የትምህርት ቤት የገንዘብ አስተዳደር አካላት እንዲሁም ለሎች የትምህርት ቤት አመራር አካላት የትምህርት ቤት የገንዘብ

best strategy for implementing the budget, and monitor and control the budget not only to administer school funds effectively and efficiently but also to initiate and effectively invite participation among all intended stakeholders in school financial administration that leads to effective and efficient supplementing of school funds.

**Keywords:** Government; education; financial resource management; school governing bodies; school principals; leadership; monitoring; evaluation; transparency.

ሐብት አጠቃቀምን ግልጽ የማድረግ፤የትምህርት ቤት የገንዘብ ሐብትን ለመምራት የተሻለ ስልት የመቀየስ፤የትምህርት ቤት የገንዘብ ሐብት የመምራት፤የመቆጣጠር እና በየጊዜዉ አፈጻጸሙን የመገምገም ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን ለትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ባለድርሻ አካላትን የማነሳሳት፤ የማሳተፍና የመምራት ኃላፊነት እንዳለባቸዉ ምክረ ሐሳብ አቅርበዋል።

**ቁልፍ ቃላት:**- መንግስት; ትምህርት; የትምህርት ቤቶች የገንዘብ ሐብት አስተዳደር; የትምህርት ቤት አስተዳደር አካላት; የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን; አመራርነት; መከታተል; ግምገማ ; ግልጽነት .

# The challenges of principals in implementing quality education in secondary schools of Gedeo Zone, Ethiopia

Alemu Girma Eshete

## ABSTRACT

The central aim of this study was to investigate the challenges of principals in implementing quality education in secondary schools of Gedeo Zone, Ethiopia. The specific objectives of the study were to: identify the challenges faced by principals in implementing quality education in secondary schools, identify strategies and roles that principals used in implementing quality education in secondary schools, and find out how the principals deal with the challenges they face in implementing quality education in secondary schools. The main research question that this study sought to answer was: "What challenges do principals face in implementation of quality education in secondary schools?" To address this question comprehensively, a mixed-methods research approach was used to collect data, making use of questionnaires and interviews.

# በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርትን ለመስጠት ርእሳነ መምህራን የሚያጋጥሟቸው ተግዳሮቶች፣ በኢትዮጵያ ጌዴኦ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት፤

በአለሙ ግርማ እሸቴ

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በጌዴኦ ዞን 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርትን በመተግበር ረገድ ርዕሳነ መምህራን የሚያጋጥሟቸውን ፈተናዎች መመርመር ነበር። የጥናቱ ንዑስ ዓላማዎችም፣ ርእሰ መምህራን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በጥራት በመተግበር የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶች በመለየት፣ ትምህርትን ለማስፈጸም የተጠቀሙባቸውን ስልቶችና ሚናዎች መለየትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርት በመተግበር ላይ እና ርእሰ መምህራን የሚያጋጥሟቸውን ተግዳሮቶችና የሚጠቀሟቸውን መፍትሄዎች መለየት ናቸው፡ ፡ ይህ ጥናት ሊመልሰው የፈለገው ዋና የጥናት ጥያቄ፣ "በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራት በአፈጻጸም ረገድ ርእሰ መምህራን ምን ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል?"

The participants included five secondary school principals, 157 teachers and 123 school leaders selected through purposive and simple random sampling techniques from 12 secondary schools that participated in the study.

The findings suggest that most secondary school principals encounter multiple problems in their attempts to implement quality education. Though most principals have a sound theoretical knowledge of their roles, they experience practical impediments in their implementation endeavours. These barriers include a lack of basic instructional materials, student textbooks, teachers' guides, and school facilities, shortages of electric power, a lack of competent and qualified teachers and a lack of active participation of stakeholders. Principals are not motivated to mobilise the concerned bodies and stakeholders to minimise the existing barriers. The quality of the principals' leadership and their academic background were below standard. To address these challenges, it is recommended that principals create a school environment that will mobilise the stakeholders in a meaningful manner. Furthermore, the government should focus on providing the infrastructure for teaching-learning in secondary schools to alleviate the challenges that affect the implementation of quality education.

**Keywords:** Secondary schools; mixed-methods research; quality education; instructional leadership; principal's role; transformational leadership; followership; administration; management; zone.

የሚል ሲሆን፣ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፣ መጠይቆችን እና ቃለመጠይቆችን በመጠቀም መረጃን ለመሰብሰብ የተደባለቀ የጥናት ሥነ-ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በጥናቱ ከተሳተፉት አስራ ሁለት የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች በዓላማ እና በቀላል የዘፈቀደ ናሙና ቴክኒኮች የተመረጡ አምስት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራን፣ 157 መምህራን እና 123 የት/ቤት አመራሮች ተሳታፊዎች ሆነዋል። የጥናቱ ግኝቶች እንደሚያመለክቱት አብዛኞቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ርእሰ መምህራን ጥራት ያለው ትምህርትን ለመተግበር በሚያደርጉት ሙከራ በርካታ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ ርእሰ መምህራን ስለ ሚናዎቻቸው ጥሩ የንድፈ ሃሳብ እውቀት ቢኖራቸውም፣ በተግባራዊ ጥረታቸው ላይ ተግባራዊ እንቅፋቶች ያጋጥማቸዋል። እነዚህ መሰናክሎች የመሠረታዊ መማሪያ ቁሳቁሶች እጥረት፣ የተማሪ መማሪያ መጽሐፍት፣ የመምህራን መመሪያ እና የትምህርት ቤት መገልገያዎች፣ የኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት፣ ብቁ እና ንቁ መምህራን እጥረት እና የባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ማነስ ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ ርእሰ መምህራኑ የሚመለከታቸውን አካላትና ባለድርሻ አካላትን በማሰባሰብ ያሉትን ማነቆዎች ለመቀነስ አልተነሳሱም፤ የሚሰጡት አመራር ጥራት እና የአካዳሚክ ዳራዎቻቸው ከደረጃ በታች ናቸው። በመሆኑም ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ባለድርሻ አካላትን ትርጉም ባለው መልኩ የሚያንቀሳቅስ የትምህርት ቤት አካባቢ እንዲፈጥሩ ይመከራል። በተጨማሪም መንግስት በትምህርት ጥራት ትግበራ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር መሰረተ ልማቶችን በማሟላት ላይ በትኩረት ሊሰራ ይገባል።

**ቁልፍ ቃላት:-** ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ የተቀላቀሉ የጥናት ሥነ-ዘዴዎች ፣ ጥራት ያለው ትምህርት፣ የትምህርት አመራር፣ የርእሰ መምህር ሚና፣ የለውጥ አመራር፣ ተከታይነት፣ አስተዳደር፣ አያያዝ፣ ዘን፤

# Quality of pre-service teacher training at regional state colleges in Ethiopia

Berhanu Desalegn Mirado


## ABSTRACT

The study examined the quality of pre-service teacher training at regional state colleges in Ethiopia. The study aimed to investigate the views and experiences of educational managers, teacher educators, and student teachers regarding the quality of pre-service teacher training and how their views and experiences help explain reasons for poor performance in the colleges of teacher education. Philosophically, the study employed pragmatism that prioritises the practical consequences of the methods used in answering the research questions. A mixed method approach was used to collect qualitative and quantitative data to get the whole picture of the problem. In the study, four purposefully selected regional state teacher education colleges that use the same academic legislation were involved. A simple random technique was used to select 212 teacher educators, 294 student teachers, and 94 educational managers (deans, vice-deans, stream officers, and department heads). A purposive sampling technique was used to select 16 teacher educators and eight deans (deans and academic vice- deans from sampled colleges) for the interviews. Moreover, a purposive sampling technique was used to select student teachers for four focused group discussions. Questionnaires, semi-structured interviews, and focus group discussion guides were used as data collection instruments. Descriptive statistics such as percentages, frequency distribution, means, and standard deviations were utilised to analyse quantitative data. Among the inferential data analysis techniques, one-


# የክልል ኮሌጆች የቅድመ መደበኛ መምህራን ስልጠና ጥራት፤

በብርሃኑ ደሳለኝ ሚራዶ


## አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ የሚገኙ የክልል ኮሌጆች የቅድመ መደበኛ መምህራን ስልጠና ጥራትን ይፈትሻል። ለዚህም ረዳው ዘንድ የትምህርት ስራ አስኪያጆችን፣ መምህራንን፣ የተማሪ አስተማሪዎችንና ተማሪዎችን አስተያየት እና ልምድ በመረጃነት ተጠቅሟል። ጥናቱ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ተግባራዊ ውጤቶችን የሚያስቀድም ፕራግማቲዝምን ፍልስፍና ተጠቅሟል። የችግሩን አጠቃላይ ገጽታ ለማግኘት ጥራት ያለው እና መጠናዊ መረጃን ለመሰብሰብ እንዲቻልም የተደባለቀ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። ለዚህም ጥናቱ አራት ሆን ተብለው የተመረጡ የክልል መምህራን ትምህርት ኮሌጆች ላይ ትኩረት አድርጓል። በመሆኑም፣ 212 የመምህራን አስተማሪዎች፣ 294 የተማሪ መምህራን እና 94 የትምህርት አስተዳዳሪዎች (ዲኖች፣ ምክትል ዲኖች፣ የዥረት መኮንኖች እና የዲፓርትመንት ኃላፊዎች) በመረጃ ምንጭነት ተጠቅሟል። እነዚህን ተጠኝዎች ለመምረጥም ቀላል የዘፈቀደ ቴክኒክ ስራ ላይ ውሏል። ለቃለ መጠይቁ 16 መምህራንን እና ስምንት ዲኖች (ዲኖች እና የአካዳሚክ ምክትል ዲኖች ከናሙና ኮሌጆች) ለመምረጥ ዓላማ ያለው የናሙና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በተጨማሪም፣ ለአራት ተኮር የቡድን ውይይቶች የተማሪ መምህራንን ለመምረጥ ዓላማ ያለው የናሙና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። መጠይቆች፣ ከፊል የተዋቀሩ ቃለመጠይቆች እና የትኩረት ቡድን የውይይት መመሪያዎች እንደ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። የቁጥር መረጃን ለመተንተን እንደ መቶኛ፣ የድግግሞሽ ስርጭት፣ መንገዶች እና መደበኛ ልዩነቶች ያሉ ገላጭ ስታቲስቲክስ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ከኢንፌርሺያል መረጃ ትንተና ቴክኒኮች መካከል፣ የአንድ-መንገድ (ANOVA) የናሙና ቡድኖችን እይታ እና ተሞክሮ ለማነፃፀር ጥቅም ላይ ውሏል። የጥራት መረጃው ተዓማኒነቱን እና እውነተኛነቱን በማስጠበቅ በተለዩ ጭብጦች እና ንዑስ ጭብጦች ላይ ተመርኩዞ ተተንትኗል። የጥናቱ

way ANOVA was employed to compare the views and experiences of sample groups. The qualitative data were analysed based on identified themes and sub-themes through narration maintaining its trustworthiness, credibility, and genuineness. The findings revealed that teachers did not use active learning/teaching strategies that foster quality learning; students did not show commitment to their learning and teacher educators did not use diversified samples of students‘ work to assess their students. Instead, teacher educators use traditional assessment methods that encourage a surface approach to learning. The study also revealed that the practicum programme, which is a key for quality teacher training, was inadequately planned and budgeted for. Moreover, the partnership between the college and the schools was loose and school mentors were not adequately trained to assist and guide the mentees and the supervision from the college lacks consistency. Besides, there was a discrepancy between what students learn in college and what they face in independent teaching. The findings further revealed that in the CTEs, there was no well-established internal quality assurance system. The researcher recommended that the CTEs should develop a quality teaching model that defines quality teaching in the context of teacher education. Teacher educators should be given adequate capacity building training on contemporary teaching methods that enhance students' active construction of knowledge. There is a need to standardise the assessment system in the colleges. The colleges should promote new modes of assessment over traditional assessment methods. The CTEs should establish an independent internal quality assurance unit fully mandated to perform overall activities related to assuring the quality of the core process of the colleges. The CTE should adequately

ውጤት መምህራን ጥራት ያለው ትምህርትን ለመስጠት የሚያበረታቱ ንቁ የመማር/የማስተማር ስልቶችን አለመጠቀማቸውን አሳይቷል። ተማሪዎችም ለትምህርታቸው ቁርጠኝነት አላሳዩም። የተማሪ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸውን ለመገምገም የተለያዩ የተማሪዎችን ስራ ናሙናዎችን አልተጠቀሙም። በምትኩ የመምህራን አስተማሪዎች የተለመዱ የግምገማ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ለመምህራን ጥራት ያለው ስልጠና ቁልፍ የሆነው የተግባር መርሃ ግብር በበቂ ሁኔታ የታቀደና በጀት የተያዘለት አለመሆኑም ጥናቱ አረጋግጧል። ከዚህም በላይ በኮሌጁ እና በትምህርት ቤቶች መካከል የነበረው አጋርነት የላላ ሆኖ ተገኝቷል፡ ፡ የት/ቤት አማካሪዎች መምህራንን ለመርዳት እና ለመምራት በቂ ሥልጠና ባለማግኘታቸው ከኮሌጁ የሚመጣው ቁጥጥር ወጥነት የጎደለው ነው። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች በኮሌጅ በሚማሩት እና በገለልተኛ የማስተማር ሂደት ውስጥ በሚገጥማቸው መካከል ልዩነት ተይቷል። በተጨማሪም ጥናቱ፣ በሲቲኤዎች (CTE) ውስጥ፣ በሚገባ የተረጋገጠ የውስጥ የጥራት ማረጋገጫ ሥርዓት አለመኖሩን አሳይቷል። ተመራማሪው በሲቲኤዎች ጥራት ያለው የማስተማር ሞዴልን በማዘጋጀት ከመምህራን ትምህርት አንፃር ጥራት ያለው ትምህርትን የሚገልጽ እንዲሆን መክረዋል። የተማሪዎችን የነቃ የእውቀት ግንባታ በሚያሳድጉ ወቅታዊ የማስተማር ዘዴዎች ላይ የመምህራን መምህራን በቂ የአቅም ግንባታ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል። በኮሌጆች ውስጥ የምዘና ስርዓቱን ደረጃውን የጠበቀ ማድረግ ያስፈልጋል። ኮሌጆቹ በባህላዊ የግምገማ ዘዴዎች ላይ አዳዲስ የግምገማ ዘዴዎችን ማስተዋወቅ አለባቸው። ሲቲኤዎች የኮሌጆችን ዋና ሂደት ጥራት ከማረጋገጥ ጋር የተያያዙ አጠቃላይ ተግባራትን እንዲያከናውን ሙሉ ኃላፊነት ያለው ራሱን የቻለ የውስጥ ጥራት ማረጋገጫ ክፍል ማቋቋም አለበት። ሲቲኤዎች በት/ቤት ላይ የተመሰረተ የመማሪያ ፕሮግራም (ተግባር) በበቂ ሁኔታ ማቀድ እና መተግበር ያለበት ከተመሳሳይ ትምህርት ቤቶች ጋር ጠንካራ አጋርነት በመፍጠር ነው። በመጨረሻም፣ የተግባር መርሃ ግብሩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ለት/ቤት አማካሪዎች እና የኮሌጅ አስተማሪዎች በቂ ስልጠና ሊሰጥ እንደሚገባ የጥናቱ ውጤት ያመላክታል።

plan and implement a school-based learning programme (practicum) establishing strong partnerships with catchment schools. Adequate training should be given to school mentors and college tutors on making the practicum programme more effective.

**Keywords:** Quality of teaching and learning; assessment; practicum experience; quality assurance; teacher education, teacher education colleges; mixed methods research; pragmatism; quality education.

**ቁልፍ ቃላት**:- የመማር እና የመማር ጥራት፣ ምዘና፣ የተግባር ልምድ፣ የጥራት ማረጋገጫ፤ የመምህራን ትምህርት፣ የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች፣ ቅይጥ ዘዴዎች ምርምር፣ ተግባራዊነት፣ ጥራት ያለው ትምህርት፤

# Exploring the implementation of school improvement programme at selected secondary schools of Woliata Zone, Ethiopia

Fanose Zana Ganta

## ABSTRACT

School improvement is an essential programme for the realisation of quality education. The programme is expected to help the schools in improving the academic performances of their learners' achievements. The implementation of SIP in Woliata Zone secondary schools was ineffective due to a lack of smooth communication among learners, teachers and the community. The study's main objective was to investigate and explore the implementation of the SIP at selected secondary schools in Woliata Zone, Ethiopia. The quality of education in secondary schools, in terms of school improvement and factors of school improvement, is well documented in existing literature. The qualitative research methodology was utilised to meticulously examine and investigate the implementation of the SIP at selected secondary schools in

# የት/ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር አተገባበር፡ በወላይታ ዞን በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ላይ የተደረገ ጥናት፤

በፋኖስ ዛና ጋንታ

## አጠቃሎ

የትምህርት ጥራትን ለማምጣት የትምህርት ቤት መሻሻያ መርሃ ግብር አስፈላጊ ነው። የማሻሻያ መርሃ ግብሮች ትምህርት ቤቶች የተማሪዎቻቸውን ውጤት አካዳሚያዊ ክንዋኔዎችን ለማሻሻል እንዲረዳቸው ይጠበቃል። በወላይታ ዞን 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የSIP ትግበራ በተማሪዎች፣ መምህራን እና በህብረተሰቡ መካከል የተግባቦት ችግር በመኖሩ ውጤታማ አልነበረም። የዚህ ጥናት ዋና አላማ በወላይታ ዞን በተመረጡ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የSIP አፈፃፀምን መመርመር እና ማሰስ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ጥራት በትምህርት ቤት መሻሻል እና የትምህርት ቤት መሻሻል ምክንያቶች በተለያዩ ስነ-ጽሑፎች በደንብ ተመዝግቧል። ይህ ጥናት በወላይታ ዞን የተመረጡ 2ተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የጥራት አፈጻጸምን በጥልቀት ለመመርመር እና ችግሩ የሚፈታበትን አቅጣጫ ለማሳየት ነው፤ ለዚህም ጥናቱ የSIP አተገባበር ዘዴ በጥቅም ላይ እንዲወል አድርገዋል።ጥናቱ የተካሄደው በወላይታ ዞን በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። መረጃ የተገኘው ከአራት ርዕሰ መምህራን፣ ከአራት ሱፐርቫይዘሮች፣ ከአራት

the Woliata Zone. The study was conducted at four selected secondary schools in the Woliata Zone. Data were generated from a purposive sampling of four principals, four supervisors, four SIP coordinators and 24 senior teachers through in-depth interviews and focus group discussions respectively. Emerging themes from the generated data were established through basic points which were complemented by the Constant Comparative Analysis. The strategies for successful SIP implementation in the school and the implementation of the SIP domains and stages were the main influences on how the school improvement programme plan was implemented. For exploring SIP implementation in schools effectively, expectations of stakeholder performance are not realistic for several reasons, particularly because of the aspects of SIP and the limited contributions of stakeholders in schools. The study's greatest value or significance was in providing insight into SIP as well as suggestions for problem-solving. It is possible to conclude from the findings that the SIP has a direct impact on how well the school performs. Since such schools continue to perform poorly due to a low degree of SIP implementation, the schools ought to have handled the change process appropriately. As a final step, strategies to raise academic achievement at the school were suggested, including monitoring SIP cycles, building trust among all stakeholders, establishing a connection between the schools and other institutions through experience sharing, implementing recognition systems, and providing aid to the underperforming schools.

**Keywords:** School improvement; secondary school; learner achievement; leadership and management; implementation of the project; school effectiveness; teaching and learning strategies; stakeholder involvement; learning environment; qualitative approach.

SIP አስተባባሪዎች እና ሀያ አራት ከፍተኛ መምህራን፣ በጥልቅ ቃለ ምልልስ እና የትኩረት ቡድን ውይይት ነው። የተሰበሰበው መረጃም በቋሚ ንጽጽር ትንተና ተደርጎበታል። በትምህርት ቤቱ ስኬታማ የSIP ትግበራ ስልቶች እና የSIP ጎራዎችን እና ደረጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ የት/ቤት ማሻሻያ መርሃ ግብር እቅድ በሚገባ ተተንትኗል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ የSIP ትግበራን በብቃት ለመፈተሽ፣ ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁት አፈጻጸም በብዙ ምክንያቶች የተነሳ ተጨባጭ አይደሉም። በተለይ በSIP ገጽታዎች እና በትምህርት ቤቶች ውስጥ ባለድርሻ አካላት ያላቸው አስተዋፅዖ ውስን ነው። የጥናቱ ትልቁ እሴት ወይም ጠቀሜታ ስለ SIP ግንዛቤ ማስጨበጥ እና ለችግሮች አፈታት ምክሮች መስጠት ነው። ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት፣ SIP በትምህርት ቤቶች እንዴት በጥሩ ሁኔታ እንደሚሰራ እና ምን አይነት ተጽዕኖ እንዳለው መደምደም ይቻላል። በSIP ትግበራ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያሉ ትምህርት ቤቶች ደካማ አፈጻጸም ስለሚያሳዩ፣ ትምህርት ቤቶቹ የለውጡን ሂደት በተገቢው መንገድ ማካሄድ ነበረባቸው። በትምህርት ቤቶች የትምህርት ውጤትን ከፍ ለማድረግ ከሚረዱ ስልቶች መካከል የSIP ዑደቶችን መከታተል፣ በሁሉም ባለድርሻ አካላት መካከል መተማመን መፍጠር፣ በትምህርት ቤቶችና በሌሎች ተቋማት ማለትም የተሻለ አፈፃፀም ያላቸው የትምህርት ተቋማት መካከል የልምድ ልውውጥ ማድረግ፣ የዕውቅና አሰጣጥ ስርዓቶችን መተግበር እና ዝቅተኛ አፈጻጸም ለሚያሳዩ ተቋማትና ለትምህርት ባለሙያዎች እገዛ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ሆነው ተገኝተዋል።

**ቁልፍ ቃላት:**- የትምህርት ቤት መሻሻል፣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የተማሪ ስኬት፣ አመራር እና አስተዳደር፣ የፕሮጀክቱ ትግበራ፣ የትምህርት ቤት ውጤታማነት፣ የማስተማር እና የመማር ዘዴዎች፣ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ፣ የመማሪያ አካባቢ፣ ጥራት ያለው አቀራረብ፤

# Department of Educational Studies

Year of Graduation 2021

## Assessing the practices of technical and vocational education and training curriculum design and development in Ethiopia

Yadessa Tolossa Woyessa

### ABSTRACT

The general objective of the study was to assess the existing practices and major factors affecting the design and development of the Ethiopian TVET curriculum and explore considerations to be taken to design and develop TVET curricula that befit Ethiopia. The purpose of the study was to explore and understand the meanings TVET practitioners and stakeholders of Ethiopian TVET programme credited to the practices of TVET curriculum design and development in Ethiopia. Hence, the study employed a qualitative research approach in phenomenological design and was undertaken within the interpretive paradigm to understand the lived experience of the curriculum designers, developers and implementers in Ethiopia. Accordingly, three regional states of Ethiopia were selected and one government-run TVET college from each regional state, ie, a total of three TVET colleges were taken as sample representatives for the study using purposive and convenience sampling methods. The study was delimited to the practices of curriculum design and development of the building construction fields of study. This is because firstly, it is impossible to encompass all available TVET fields of training in the study; secondly, building

## የኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት ግምገማ ጥናት

በያዴሳ ቶሎሳ ወዬሳ

### አጠቃሎ

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት አካሄድን እንዲሁም በሥርዓተ-ትምህርቱ ቀረጻና ዝግጅት ሂደት ተፅእኖ የሚፈጥሩ ዋና ዋና ጉዳዮችን መገምገምና ለኢትዮጵያ የሚመጥን የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ ለማዘጋጀት ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸውን ጉዳዮች ለመመርመር ነው። አያይዞም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላትን በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት አሠራሮችን በተመለከተ ያላቸውን አረዳድና የሚሰጡትን ሥፍራ ለመዳሰስና ለመረዳት ጭምር ነው። ጥናቱ የተከተለው በፌኖሜኖሎጂያዊ የጥናት ንድፍ፣ ዓይነታዊ/ገለጻዊ የምርምር አቀራረብ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ የስርዓተ ትምህርት አዘጋጆች እና ፈጻሚዎችን የህይወት ልምድ ለመረዳት በሚያግዘው በትርጉም ፓራዳይም (interpretive paradigm) መሠረት ነበር። በዚህም ሦስት የኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥታት እንዲሁም ከየክልሉ አንድ በመንግስት የሚተዳደር የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ በአጠቃላይ ሦስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች በአመቺ/ግኝት እና የሆን ተብሎ ንሞናን /የናሙና አወሳድ/ ስልትን በመጠቀም ለጥናቱ ተመርጠው ነበር። ጥናቱ በሕንፃ ግንባታ የትምህርትና መስኮች የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር። ይህም የሆነበት ምክንያት በመጀመሪያ፣ ሁሉንም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ዘርፎች በጥናቱ ውስጥ ማካተት የማይቻል በመሆኑ፣

construction technology sector is one of the those sectors which much focus is given to by the government of Ethiopia and thus is the training field found in abundance in the country. Two data gathering tools were mainly used to gather information in this study. These were interviews and document reviews. Therefore, the researcher first reviewed different related literature and strategic documents to understand the background of the problem and to see what has been done in reference to the problem. Accordingly, working and policy documents such as TVET strategies, guidelines, manuals, legislation, curriculum frameworks and guides, as well as education sector development programmes and other written documents and literature related to TVET curriculum design and development that were available at federal, regional and TVET college levels were reviewed and analysed. Other countries' experiences visa-a-vis TVET curriculum design and development were also reviewed and used as sources of information. The interviews were held with curriculum development officials at the Federal TVET Agency and sampled regional TVET agencies as well as principals, heads of department and trainers from sampled TVET colleges that were providing training in the fields of building construction works. The interview participants consisted of two TVET curriculum development officials from the Federal TVET Agency, three TVET curriculum development officials from three sampled regional TVET agencies, three TVET college principals from three sampled TVET colleges, three heads of department of building construction work fields from three sampled TVET colleges, and three trainers of building construction work fields from three sampled TVET colleges. Accordingly, it could be investigated from the study that the way the outcome-based TVET system

ሁለተኛ የሕንፃ ግንባታ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ መንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ በመሆኑ ከዚህም የተነሳ በሀገሪቱ በብዛት የሚገኙት የስልጠና መስኮች በዚህ ዘርፍ ዙሪያ በመሆኑ ነበር። በዚህ ጥናት ውስጥ መረጃን ለመሰብሰብ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በዋናነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን እነዚህም ቃለ መጠይቅ እና የሰነድ ግምገማ ነበሩ። በተጨማሪም፣ የችግሩን አመጣጥ ለመረዳት እና ከችግሩ ጋር በተያያዘ ምን ተግባራት እንደተከናወኑ ለመገንዘብ የተለያዩ ተዛማጅ ጽሑፎች፣ መጣጥፎችና ሰነዶች ተዳሰዋል። በዚህም መሠረት በፌዴራል፣ በክልል እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች የሚገኙ ከሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት ጋር ተዛማጅነት ያላቸው የሥራና የፖሊሲ ሰነዶች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ስትራቴጂዎች፣ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች፣ ሕግና ደንቦች፣ የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፎችና መመሪያዎች፣ እንዲሁም የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራሞችና ሌሎች ተዛማጅ ጽሑፎች በዝርዝር ተዳሰዋል። በተጨማሪም፣ የሌሎች ሃገሮች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥርዓተ ትምህርት ቀረፃና ዝግጅት ልምድ ተወስደው ለጥናቱ መረጃ ምንጭነት አገልግለዋል። ከፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና ከክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ኃላፊዎች፣ በናሙና ከተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ርእሰ መምህራን፣ የትምህርትና ሥልጠና ክፍል ኃላፊዎችና እንዲሁም በህንፃ ግንባታ ሥራዎች ዙሪያ ሥልጠና እየሰጡ ካሉ አሰልጣኞች ጋር ቃለ ምልልስ ተደርጓል። በቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎችን ናሙና አወሳሰድ በተመለከተ ከፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ሦስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ኃላፊዎች፣ ከተመረጡ የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች ሦስት ባለሙያዎች፣ ከተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ሦስት ርዕሳነ መምህራን፣ ከተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ሦስት የሕንፃ ግንባታ ዘርፍ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ ከተመረጡ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጆች ሦስት የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ኃላፊዎች እንዲሁም ሦስት

is perceived and eventually executed and the processes and steps that were followed in order to design and develop TVET curriculum in Ethiopia had impact on the present TVET curriculum developed. Besides, the way other countries' experiences were espoused and adapted led to an inappropriate curriculum design and development approach. Moreover, the Ethiopian TVET system following only one curriculum development approach for designing and developing TVET curriculum for all trades, blue and white collar work-related vocational education and training resulted in a non-beneficial TVET curriculum. It was also noted from the study that the wrong perception of stakeholders' roles and responsibilities in curriculum development activities led to TVET curriculum development with improper training content selection and unfair training time allotment, which greatly impact on the TVET curriculum implementation and training delivery. Therefore, the study suggested that the curriculum that addresses individual, societal and employers' needs should be designed and the labour market demand analysis needs to be undertaken before OS mapping is designed. In doing so, it is recommended that Ethiopia should benchmark itself against best practices of various developed and developing countries which have succeeded in an outcome-based TVET system and when the TVET system is adopted from other countries, it should be with tangible reasons and justifications. Furthermore, it is recommended that attention should be paid to practical training programmes and a combination of practice and theory time should be provided for all course types. In addition, the environmental situation of the country and the degree of importance of each unit of competence for

የህንጻ ግንባታ መስክ አሰልጣኞች ተሳትፈዋል። በዚህም መሠረት ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት እየተከናወነ የነበረበትን መንገድ በተለይም በኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርትን ለመቅረጽና ለማዘጋጀት እየተከናወኑ ያሉ የትግበራ ሂደቶች በአሁኑ ጊዜ ባለው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት ስልቶች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደሩ ከጥናቱ ውጤት መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም፣ የሌሎች አገሮች ተሞክሮዎች የተወሰዱበትና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር ለማዛመድ የተኬደበት መንገድ ተገቢ ያልሆነ የሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት አካሄድ እንዲኖር አድርጓል። በተጨማሪም የኢትዮጵያ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት ለሁሉም ሰማያዊና ነጭ ኮሌታ ሙያዎች አንድ ዓይነት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀርጻና ዝግጅት ስልት መከተሉ አዋጭ ያልሆነ ውጤት ማስገኘቱ ጥናቱ አመላክቷል። የባለድርሻ አካላት በሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት ሂደቱ ላይ ያላቸው ሚናና ኃላፊነት የተሳሳተ ግንዛቤ መያዛቸው ለተገቢ ያልሆነ የሥልጠና ይዘት መረጣና የሥልጠና ጊዜ ምደባ እነዲሁም በሥርዓተ ትምህርት አተገባበርና ሥልጠና አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ጥናቱ አረጋግጧል። ስለሆነም የግለሰቦችን፣ የማህበረሰብ እና የሥራ ቀጣሪዎችን ፍላጎት ያካተተ ሥርዓተ ትምህርት እንዲቀረጽና እንዲዘጋጅ ዘንድ በቅድሚያ የስርዓተ ክወና ካርታ ከመዘጋጀቱ በፊት የሥራ ገበያ ፍላጎት ትንተና መካሄድ እንዳለበት ጥናቱ ጠቁሟል። በዚህም ኢትዮጵያ ከተለያዩ ከበለጸጉ እና በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት ውጤትን መሠረት ያደረገ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት መልካም ተሞክሮዎች አንፃር ራሷን መመዘን እንደሚገባት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት በሌሎች አገሮች ሲተገበር በተጨባጭ የጋጠሙ ስኬቶችንና ተግዳሮቶችን መመልከት እንደሚገባ ተመክሯል። ለተግባራዊ የሥልጠና መርሃ ግብሮች ትኩረት መስጠት እና ለሁሉም ኮርስ ዓይነቶች በቀቀቂ የተግባር እና የንድፈ ሐሳብ ክፍለ-ጊዜ መሰጠት እንዳለበት ተመክሯል። በተጨማሪም የሀገሪቱንና አካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታ እንዲሁም ለቅጥር ሥራ እና ለግል ሥራ ፈጠራ የሚጠቅሙትን የብቃት አሃዶች ከግምት

employment and self-employment needs to be considered.

**Keywords:** Technical and Vocational Education and Training (TVET); TVET curriculum; TVET curriculum design and development.

ውስጥ አስገብቶ ሥርዓተ ትምህርት መቀረጽ እንደሚኖርበት በመፍትሄ ሃሳብነት ቀርቧል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ቀረጻና ዝግጅት

# Department of Inclusive Education

Year of Graduation 2023

## Professional preparation of special needs educators for inclusion in regular primary schools in Ethiopia

Aemiro Tadesse Mergia

### ABSTRACT

Entrenched in the constructivism research paradigm, this qualitative phenomenological study examined the professional preparation of special needs educators for inclusion in regular primary schools in Ethiopia to propose strategies to enhance their professional preparation. Inclusive education is important because it ensures the provision of better quality education for all. Further, it is anchored on social justice. A purposive sample of 12 special needs educators, seven (n=7) males and five (n=5) females participated in the study. Face-to-face semi-structured individual interviews, non-participant observations, and document analysis were used to generate data. A phenomenological data analysis method was used in the study. Embedded in the medical, social and human rights models of disability, a discrete model was used for the professional preparation of special needs educators for inclusion in Ethiopian regular primary schools using a combination of lecturer-centred and

## በኢትዮጵያ ለአካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት መምህራን ሙያዊ ዝግጅት

በአእምሮ ታደሰ መርጊያ

### አጠቃሎ

ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ለአካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት መምህራን ሙያዊ ዝግጅትን በመፈተሽ፣ ሙያዊ ዝግጅታቸው የሚጎለብትበትን ስልቶች አቅርቧል። የተሻለ ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም በመስጠት ረገድ አካቶ ትምህርት እጅጉን ጠቃሚ ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ አስራ ሁለት የልዩ ፍላጎት መምህራን፣ ሰባት (n=7) ወንድ እና አምስት (n=5) ሴት በመረጃ ምንጭነት ተሳትፈዋል። መረጃውን ለመሰብሰብም ፊት ለፊት የተካሄዱ እና በከፊል የተዋቀሩ የግለሰብ ቃለ-መጠይቆች፣ ተሳትፎ ያልተደረገባቸው ምልከታዎች፣ እንዲሁም የሰነድ ትንተናዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በጥናቱ ውስጥ ፍኖሜኖሎጂካል መረጃ ትንተና ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በኢትዮጵያ ለአካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት መምህራንን ለማሰልጠን በህክምና፣ በማህበራዊ እና በሰብአዊ መብት የአካል ጉዳተኝነት ሞዴሎች የተቃኘ ዲስክሪት ሞዴል (discrete model) የሚተገበር ሲሆን ሰልጣኝ ተኮር እና አሰልጣኝ ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን ባጣመረ መልኩ ይሰጣል። የልዩ ፍላጎት መምህራን ሙያዊ ሚናቸውን እና ኃላፊነታቸውን የሚወጡት በአካል ጉዳተኝነት የህክምና ሞዴል አስተሳሰብ ላይ

trainee-centred pedagogy. Special needs educators' execution of their professional roles and responsibilities was grounded in the medical discourse of disability. Such included supporting Learners with Special Educational Needs (LSENs) including identification, assessment, guidance and counselling, and individualised support of these children. Special needs educators had both positive and negative experiences in inclusion in regular primary schools in Ethiopia inclusive of the improvement of stakeholders' attitudes and understanding of inclusion and LSENs, cultivation of collaborative working cultures and structures among stakeholders, promotion of accessibility of regular school environment to children with disabilities and enhancing the academic and social development of these children. Although the agency and social justice of special needs educators propelled the delivery of goods and services of special needs educators in Ethiopian regular primary school classes, they lacked professional preparation to serve learners with diverse and unique needs including competence in Braille and Sign Language. Several individual and institutional capacity building orientated strategies including institutionalisation of modules on inclusive education, praxis embedded training, teacher trainee-centred pedagogy, cooperative learning, enforcement of national teacher education policies and legislation, and fieldwork in special and regular schools could enhance the professional preparation of special needs educators for inclusion in regular primary schools. This study is a springboard for future studies on the professional preparation of special needs educators for inclusion in regular primary schools.

ተመስርቶ ነው። ይኸውም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መደገፍ ላይ ያተኮረ ሲሆን መለየት፣ መገምገም፣ መመሪያ እና ምክር መስጠት፣ እንዲሁም ለተማሪዎች የሚደረግን ግላዊ ድጋፍ ያካትታል። የልዩ ፍላጎት መምህራን በኢትዮጵያ አካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የባለድርሻ አካላት አመለካከትን በማሻሻል፣ ስለ አካቶ ትምህርት እና ልዩ ፍላጎት ስላላቸው ተማሪዎች ግንዛቤን በማሳደግ፣ የባለድርሻ አካላትን የትብብር ባህሎች እና አወቃቀሮችን በማጎልበት፣ የመደበኛ ትምህርት ቤቶች አካባቢያዊ ተደራሽነትን በማሳደግ፣ እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ልጆች አካዴሚያዊ እና ማህበራዊ እድገትን እንዲሻሻል በማድረግ ረገድ አዎንታዊ እና አሉታዊ ተሞክሮዎች አሏቸው። የልዩ ፍላጎት መምህራን ጉዳይ የሚመለከታቸው ኤጀንሲዎች እና የማህበራዊ ፍትህ አገልግሎቶች በኢትዮጵያ አካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት መምህራን አገልግሎት እንዲዳዲረስ ቢያበረታቱም፣ የልዩ ፍላጎት መምህራን በብሬይል እና በምልክት ቋንቋ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለማገልገል የሚያስችል ሙያዊ ዝግጅት የላቸውም። በርካታ የግል እና ተቋማዊ አቅም ግንባታ ተኮር ስልቶች ማለትም በአካቶ ትምህርት ላይ ሞጁሎችን ተቋማዊ ማድረግ፣ ፕራክሲስ (praxis) የተካተተ ስልጠና መስጠት፣ የሰልጣኝ መተኮር የትምህርት አሰጣጥ ዘዴን መተግበር፣ የትብብር ትምህርት ዘዴን መጠቀም፣ የሀገር አቀፍ የመምህራን ትምህርት ፖሊሲዎች እና ህግጋት ትግበራ ማድረግ፣ እንዲሁም በልዩ እና መደበኛ ትምህርት ቤቶች የመስክ ስራዎችን ማካሄድ የልዩ ፍላጎት መምህራንን ሙያዊ ዝግጅት ሊያሳድጉ ይችላሉ። ከላይ ከተገለጹት የጥናቱ ውጤቶች በተጨማሪ፣ ይህ ጥናት በአካቶ መደበኛ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት መምህራን ሙያዊ ዝግጅት ላይ ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶች መነሻ ሆኖ ያገለግላል።

**ቁልፍ ቃላት:**- ልጆች፣ ኢትዮጵያ፣ አካቶ፣ አካቶ ትምህርት፣ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ሙያዊ ዝግጅት፣ መደበኛ ክፍል፣ የልዩ ፍላጎት መምህራን፣ ድጋፍ

**Keywords:** Children; Ethiopia; inclusion; inclusive education; learners with special educational needs, primary school; professional preparation, regular classroom; special needs educators; support.

# Department of Mathematics Education

Year of Graduation 2019

## Investigating the influence of pre-calculus mathematics refreshment module to first year engineering students in an Ethiopian university

Asnake Muluye Bekele

### ABSTRACT

The quality of mathematics knowledge attained by students entering university in Science, Technology, Engineering and Mathematics (STEM) fields has been decreasing. There is a need to enhance students' mathematical knowledge in order to maintain the standards of a STEM curriculum at university. The rationale of this study was to investigate the influence of the Pre-Calculus Mathematics Refreshment module taught using Meta-cognitive skills and Co-operative Learning (MCL), or Co-operative Learning (CL) only, or Traditional lecture (T) intervention method to first-year pre-engineering students on their Applied Calculus 1 in an Ethiopian university. The study further investigated the influence of the Pre-Calculus Mathematics Refreshment module for MCL, or CL, or T intervention method on male and female students' achievement. The refreshment module and Applied Calculus 1 scores were measured through post-test and normal classroom scores of Applied Calculus 1

## የቅድመ-ካልኩለስ የሂሳብ መከለሻ ሞጁል፣ በኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ የአንደኛ ዓመት የምህንድስና ተማሪዎች ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመር፤

በአስናቀ ሙሉዬ በቀለ

### አጠቃሎ

በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሒሳብ (STEM) ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ያላቸው የሂሳብ ዕውቀት እየቀነሰ መጥቷል። በመሆኑም በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና እና ሒሳብ ሥርዓተ-ትምህርት ደረጃዎችን ለመጠበቅ የተማሪዎችን የሂሳብ እውቀት ማሳደግ ያስፈልጋል። የዚህ ጥናት ዋና አላማ እራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት እና በሕብረት መማር ወይም በሕብረት መማር ብቻ ወይም በተለምዶ ትምህርት የማስተማር ስልት ጣልቃ የመግባት ዘዴን በመጠቀም፣ የመጀመርያ ዓመት የቅድመ ምህንድስና ተማሪዎችን በመውሰድ በኢትዮጵያ ዩንቨርስቲ በቅድመ አፕላይድ ካልኩለስ የሂሳብ ክለሳ ሞጁሉን ተፅእኖ መመርመር ነው። ጥናቱ ይበልጥ ደግሞ የቅድመ-ካልኩለስ የሂሳብ ክለሳ ሞጁል እራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት እና በሕብረት መማር ወይም በሕብረት መማር ወይም የባህላዊ የትምህርት አሰጣጥ ስልት የጣልቃ ገብነት ዘዴ በወንድ እና ሴት ተማሪዎች ስኬት ላይ ያለውን ተጽእኖ የበለጠ መርምሯል። የክለሳ ሞጁሉ እና የተተገበረው የካልኩለስ 1 ውጤቶች የተለኩት በድህረ ፈተና እና በተለመደው የክፍል ነጥብ በተተገበረው

results. The dependent variables were student achievement in the pre-Calculus Refreshment Module and Applied Calculus 1.

Out of 29 universities in Ethiopia, only four were selected to participate in this study. The population of this study was all pre-engineering first-year students in those universities in 2016/2017. The sample consisted of 200 pre-engineering university students who studied in four of Ethiopian universities and one class was randomly selected by lottery method from existing pre-engineering classes in each university. Two experimental groups which were taught MCL and the other CL intervention method and two of them were control groups upon whom the control novice with the traditional lecture method and control without intervention was applied. In each group, 50 students of 25 males and 25 females were purposely selected from the sampled class. A pre-calculus mathematics pre-test was administered first, where the average scores of all students with a pre-test result was below 33%. Then, first MCL and CL intervention methods were discussed and exercised for one week before implementing the study. For the study, selected pre-calculus mathematics topics were taught in all classrooms for 32 periods i.e. 50min x32= 26.7hrs at the beginning of the first semester parallel with Applied Calculus 1 for the academic year 2016/2017. The statistical tools used under this procedure include descriptive statistics percentages, mean and standard deviation and inferential statistics, T-test, and one-way analysis of variance (one-way ANOVA). The results show statistically significant differences (Sig 0.00) at the significance level (0.05) between students that learnt the pre-Calculus Refreshment Module and the control group which did not. Among the students who  learned the pre-Calculus Refreshment Module through

የካልኩለስ 1 ውጤት መሰረት ነው። ጥገኛ ተለዋዋጮቹ በቅድመ-ካልኩለስ ክለሳ ሞጁል እና አፕላይድ ካልኩለስ የተማሪዎች ውጤት 1 ሲሆኑ፣ በኢትዮጵያ ከሚገኙ 29 ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በዚህ ጥናት ለመሳተፍ የተመረጡት አራቱ ብቻ ናቸው። የጥናቱ አካላይ (Population) በ2016/2017 ከላይ በተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ሁሉም የቅድመ ምህንድስና የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች ነበሩ። ናሙናው በኢትዮጵያ በአራቱ ዩኒቨርሲቲዎች የተማሩ 200 የቅድመ ምህንድስና ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ያካተተ ሲሆን፣ አንድ ክፍል በየዩኒቨርስቲው ካሉት የቅድመ ምህንድስና ትምህርቶች በተገኘው አጋጣሚ በእጣ የማውጣት ዘዴ በመጠቀም ተመርጠዋል። ሁለት የሙከራ ቡድኖች፣ አንዱ ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት እና በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብነት፤ ሌላኛው በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብነት ዘዴ እና ሁለቱ የቁጥጥር ቡድኖች ናቸው። የቁጥጥር ቡድኖቹ አንደኛው በተለምዶ ንግግር ዘዴ ጣልቃ ገብነት እና ሁለተኛው የቁጥጥር ቡድን ያለ ጣልቃ ገብነት ናቸው። በእያንዳንዱ ቡድን 50 ተማሪዎች፣ 25 ወንድ እና 25 ሴት ሆን ተብሎ ከናሙናው ክፍል ተመርጠዋል። የቅድመ-ካልኩለስ ሒሳብ የቅድመ-ፈተና መጀመሪያ የተካሄደ ሲሆን፣ የሁሉም ተማሪዎች አማካይ የቅድመ-ፈተና ውጤት ከ33 በመቶ በታች ነበር። ከዚያም ጥናቱን ከመተግበሩ በፊት በመጀመሪያ ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት የመማር እና  በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴዎችን በተመለከተ ለአንድ ሳምንት ያህል በውይይት እንዲለማመዱት ተደረገ። ለጥናቱ የተመረጡ የቅድመ-ካልኩለስ የሂሳብ ርእሶች በሁሉም ክፍሎች ለ 32 ጊዜያት ማለትም 50 ደቂቃ x32= 26.7ሠዓታት  በመጀመሪያው ሴሚስተር መጀመሪያ ላይ ከአፕላይደ ካልኩለስ 1 ጋር  በትይዩ በ2016/2017 የትምህርት ዘመን ትምህርቱም ተካሄደ። በዚህ ጥናት አሰራር ስር ጥቅም ላይ የሚውሉት ገላጭ አሀዛዊ መረጀዎች መቶኛ የአማካይ ውጤት እና መደበኛ የልየታ ሥራ እና ድምዳሚያዊ አኃዛዊ መረጃ፣ቲ-ቴስት እና የአንድ-መንገድ የልየታ ትንተናን (ANOVA) ያካትታሉ። ውጤቶቹ የቅድመ-ስሌት ክለሳ ሞጁል በተማሩ ተማሪዎች እና ባልተማሩት የቁጥጥር ቡድን መካከል በአስፈላጊ ደረጃ (0.05) ሲሆን፣ በስታቲስቲካዊ ጉልህ ልዩነቶች ሲግ (Sig)0.00

MCL, CL and the T method, students in the MCL and CL groups' post-test scores were significantly different from the T group in pre-calculus results both with Sig of 0.00. But there was no significant difference between MCL & CL groups where the Sig is 0.97. Additionally, the female students in the MCL group was not significantly different from the CL and T group, on an impact of the refreshment module in Applied Calculus 1 mathematics where Sig is 0.994 and 0.237 respectively, and CL female group scores were significantly different from T group in Applied Calculus 1 results with Sig 0.042. The male students in the MCL and CL groups were significantly different from T group in Applied Calculus 1 with Sig of 0.07 and 0.012 respectively. Also, there was a positive correlation between the Pre-Calculus Refreshment Module and Applied Calculus 1 with a correlation coefficient of 0.835. Lastly, the result of pre-calculus mathematics post-test scores with the female students in MCL relatively increased than male students, than in CL and T groups, which indicated that MCL benefits more female students than male students. The differences were more in favour of pre-calculus mathematics refreshment with the MCL intervention method. To improve success in engineering participation of all students, it is recommended that a pre-calculus module should be offered by all universities for first-year engineering students. It was shown that structured co-operative learning with purpose has significant gains for effective instruction, and to increase the success rate of female students, this study has proven that they are trainable and therefore, meta-cognition skills have to be nurtured for female students.

ያሳያሉ። ከተማሪዎች መካከል የቅድመ-ካልኩለስ ክለሳ ሞጁልን በራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕውቀት እና በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴ እና በሕብረት የተማሩ፤ በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴ ብቻ የተማሩ እና በተለምዶ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የተማሩ ተማሪዎች፤ ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት በሚማሩ ቡድኖች ውስጥ ከተካተቱ ተማሪዎች የድህረ ፈተና ውጤቶች በተለምዶ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ቡድን በቅድመ ስሌት ውጤቶች ሁለቱም ,,,ሲግ (Sig) 0.00 አግኝተዋል። ነገር ግን ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት በተማሩ ቡድኖች እና በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴ ብቻ የተማሩ ቡድኖች መካከል ምንም ልዩ የሚባል የደረጃ ልዩነት አልታየም። በጥናቱ መሰረት ዉጤቱ ሲግ (Sig) 0.97 ነበር። በተጨማሪም ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት በተማሩ ቡድን ውስጥ ያሉ ሴት ተማሪዎች በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴ ብቻ ከተማሩት እና በተለምዶ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ከተማሩት ቡድን በክለሳ ሞጁሉ ተጽእኖ በአፕላይድ ካልኩለስ 1 ሂሳብ ሲግ(Sig) 0.994 እና 0.237 በቅደም ተከተል ያገኙ ሲሆ ፣ በሕብረት የመማር ጣልቃ ገብ ዘዴ ብቻ የተማሩ የሴቶች ቡድን ውጤት በተለምዶ የትምህርት አሰጣጥ ከተማሩት ቡድን በእጅጉ የተለየ አልነበረም፤ ምክንያቱም የአፕላይድ ካልኩለስ 1 ውጤቶች ሲግ 0.042 ነበር። ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት በተማሩ ቡድኖች ውስጥ ያሉ ወንድ ተማሪዎች በአፕላይድ ካልኩለስ 1 ከሲግ 0.07 እና 0.012 በቅደም ተከተል ከተለምዶ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ቡድን በእጅጉ የተለዩ ነበሩ። እንዲሁም በቅድመ-ካልኩለስ ክለሳ ሞጁል እና በአፕላይድ ካልኩለስ 1 መካከል በ0.835 አዎንታዊ የተዛምዶ ቁርኝት እንዳለ ተምልክቷል። በመጨረሻም የቅድመ-ካልኩለስ የሂሳብ ድህረ ፈተና ውጤት ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት የተማሩ ሴት ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በአንጻራዊ ሁኔታ በሕብረት ከሚማሩ እና በተለምዶ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ከተማረዉ ቡድን ይልቅ ጭማሪ ማሳየቱን ያሳያል። ይህም ጭማሪ ራስን በራስ ስለምናውቀው

እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት ከተማሩት ወንድ ተማሪዎች የበለጠ ሴት ተማሪዎችን እንደሚጠቅም የጥናቱ ግኝት አመልክቷል። ልዩነቶቹ ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት ዕዉቀት እና በሕብረት ከመማር የጣልቃ ገብነት ዘዴ ጋር በተያያዘ ለቅድመ-ካልኩለስ ሂሳብ ክለሳ የበለጠ የሚደግፉ ነበሩ። በዚህ ጥናት መሰረት የሁሉንም የምህንድስና ተማሪዎች ተሳትፎ ስኬት ለማሻሻል የቅድመ-ካልኩለስ ሞጁል በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለመጀመሪያ ዓመት የምህንድስና ተማሪዎች መሰጠት እንዳለበት ይመከራል። ዓላማ ያለው የተቀናጀ የትብብር ትምህርት ለውጤታማ ትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ትርፋማ እንደሚያደርግ፣ እንዲሁም የስኬት ደረጃን ከማሳደግ አንጻር ሴት ተማሪዎች ብቁ መሆናቸውን ጥናቱ በሚገባ አረጋግጧል። ስለዚህም ሴት ተማሪዎች ራስን በራስ ስለምናውቀው እውቀት በመጠየቅ ክህሎት እና በሕብረት የመማር ስነዘዴ የሒሳብ ትምህርት ችሎታቸውን ማሳደግ ይቻላል።

## Year of Graduation 2022

# The use and effect of Geogebra software in Calculus at Wachemo University, Ethiopia: an investigation

Tola Bekene Bedada

## ABSTRACT

With the rapid growth of technology in the 21st century, traditional teaching and learning methods are considered outdated and not suitable for the active learning processes of the constructivist learning approach. The adjustment of existing methods and the development of new ones to teach and learn calculus with the help of technology is needed. This study aimed to investigate the effect of the use of GeoGebra mathematical software on university students' learning

# በካልኩለስ ትምህርት የጂኦጂብራ ሶፍትዌር አጠቃቀም እና ያስገኘው ውጤት፡ በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ ኢትዮጵያ የተደረገ ጥናት፤

በቶላ በቀና በዳዳ

## አጠቃሎ

ተለምዷዊው የመማር ማስተማር ዘዴ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመጠቀም አመቺ አይደለም። በዚህም የተነሳ ካልኩለስን በቴክኖሎጂ እገዛ ለማስተማር እና ለመማር ተለመዱ የነባር ዘዴዎችን ማስተካከል እና አዳዲሶችን ማሳደግ ያስፈልጋል። ይህ ጥናት የጂኦጂብራ የሂሳብ ሶፍትዌር አጠቃቀም በዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የካልኩለስ ትምህርት ላይ ያለውን ተጽእኖ ለመመርመር ያለመ ነው። በዚህም የጂኦጂብራ የሂሳብ ሶፍትዌርን መጠቀም በተማሪዎች የካልኩለስ ብቃት እና የተማሪዎች

of calculus. It explored the effect of using GeoGebra Mathematical software on students' proficiency in calculus and students' attitudes to using GeoGebra software to learn calculus. To improve the learning process, the study developed a cycle model that posits nine steps. This cycle was implemented in the study. To achieve the goal of the study, a mixed research methodology was employed. In the quantitative part of the study, a quasi-experiment with a pretest post-test design and questionnaires was used. A case study was used to collect data for the qualitative part of the study. The study was conducted at a university in the Southern Nations and Nationalities region of Ethiopia. The data were collected over four weeks in semester two of the 2020/2021 academic year. The quantitative data were analysed using SPSS version 27 while the qualitative data were coded into themes and analysed using computer software ATLAS.ti 9. The results indicated that the GeoGebra classroom-oriented approach to learning differential calculus with the use of the developed cycle model had a more positive effect on students' conceptual and procedural understanding when compared to students who were taught using a traditional teaching approach. Students in the experimental group showed greater improvement in procedural understanding, with an effect size of d = 1.2 and a percentile gain of 49%; in conceptual understanding of differential calculus, however, the students showed only slight improvement with an effect size of d = 0.02 and a percentile gain of 2%. Students expressed positive perceptions towards the use of GeoGebra for learning differential calculus. While the GeoGebra oriented learning approach to calculus has the potential to improve proficiency, it remains critically important that it should be designed (cycle model) and aimed to fill a specific gap. Based on the results,

የጂኦጂብራ ሶፍትዌርን ካልኩለስ ለመማር ባላቸው አመለካከት ላይ ያለውን ተጽእኖ ዳስሷል። የመማር ሂደቱን ለማሻሻል ጥናቱ ዘጠኝ ደረጃዎችን የያዘ ዑደት ሞዴል አዘጋጅቷል. ይህ ዑደት በጥናቱ ውስጥ ተተግብሯል። የጥናቱ ግብ ላይ ለመድረስ ቅይጥ የምርምር ዘዴ ስራ ላይ ውሏል። በጥናቱ የቁጥር ውሂብ፣ ከፈተና በፊት በኋላ ያለው ንድፍ እና መጠይቆች ያለው የኳሲ ሙከራ ጥቅም ላይ ውሏል። የጥናቱ የጥራት ክፍል መረጃን ለመሰብሰብ የጉዳይ ጥናት ጥቅም ላይ ውሏል። ጥናቱ የተካሄደው በኢትዮጵያ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል በሚገኘው ዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን፣ መረጃው የተሰበሰበው በ2020/2021 የትምህርት ዘመን በሁለተኛው ሴሚስተር በአራት ሳምንታት ውስጥ ነው። የቁጥር መረጃው የተተነተነው በኤስፒኤስኤስ ስሪት 27 ሲሆን፣ የጥራት መረጃው በገጽታ ተቀርጾ በኮምፒዩተር ሶፍትዌር ATLAS.ti 9 ተተንትኗል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው የጂኦጂብራ ክፍል ተኮር የካልኩለስ ትምህርት የዳበረ ዑደት ሞዴል አጠቃቀም አሳይቷል። የጂኦጂብራ ሶፍትዌርን መጠቀም ተለምዷዊውን የማስተማር ዘዴ ከመጠቀም ጋር ሲወዳደር፣ በተማሪዎች የፅንሰ-ሀሳብ እና የአሰራር ግንዛቤ ላይ የበለጠ አዎንታዊ ተጽእኖ አሳይቷል። በመሆኑም፣ በሙከራ ቡድን ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሥርዓት ግንዛቤ ላይ የበለጠ መሻሻል አሳይተዋል፤ የውጤት መጠን d = 1.2 እና መቶኛ 49%፣ ስለልዩነት ካልኩለስ በፅንሰ-ሃሳባዊ ግንዛቤ፣ ነገር ግን ተማሪዎቹ መጠነኛ መሻሻል አሳይተዋል፤ የውጤት መጠን d=0.02 እና በመቶኛ 2 በመቶ ብልጫ አሳይቷል። ተማሪዎች ጂኦጂብራን በመጠቀም ልዩነትን ካልኩለስ ለመማር ያላቸውን አዎንታዊ ግንዛቤ ከፍ ያለ ነው። የጂኦጂብራ ተኮር የመማር አካሄድ የካልኩለስ ቅልጥፍናን የማሻሻል አቅም ቢኖረውም፣ መቀረጹ (ሳይክል ሞዴል) እና የተለየ ክፍተት ለመሙላት ያለመ መሆኑ በጣም አስፈላጊ ነው። በዉጤቶቹ ላይ በመመስረት ለትግበራ እና ለወፊት ምርምራ ተጨማሪ ጥናቶችን ማካሄድ አስፈላጊ መሆኑን ይመከራል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- ሳይክል ሞዴል፣ ካልኩለስ፣ ኢትዮጵያ፣ ጂኦጂብራ፣ ግንዛቤዎች፣ የተማሪ ብቃት፤

additional imperatives for practice and future research are recommended.

**Keywords:** Cycle Model, Calculus, Ethiopia, GeoGebra, Perceptions, Student proficiency.

# Department of Psychology of Education

Year of Graduation 2021

## The implementation of pre-school policy at school-based grade R classes of schools in the southern region of Ethiopia

Biniam Birru Aberra

### ABSTRACT

While visiting pre-schools in rural areas of the southern region of Ethiopia, I became aware of the early childhood education (ECE) problems that emanated from ECE policy and its implementation. The problems I observed included that the school building was not well constructed for it had broken doors and windows, unclean and narrow rooms and the school campus did not have enough space to allow kids to play freely. In addition, there were no learning materials and playground facilities and teachers did not have qualifications at all. From my subsequent observations that I had made with other pre-schools in a rural area, I observed the same problems. This situation prompted me to carry out this research. The overall purpose of this study was to establish the nature of ECE policy implementation at school-based Grade R classes of schools in southern Ethiopia. To achieve this aim, I employed the qualitative descriptive design for it helped me to capture and describe in-depth views, perceptions, meanings and

## ቅድም-መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ አተገባበር በ R ክፍል ትምህርት ቤቶች፡ በደቡብ ክልል የተደረገ ጥናት፤

በቢኒያም ብሩ አበራ

### አጠቃሎ

በደቡብ ክልል ገጠራማ አካባቢዎች የሚኙትን ቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶችን በጎበኜሁበት ወቅት በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ አተገባበር ላይ ችግሮችን ተገነዘብኩ። ከታዘብኳቸው ችግሮች መካከል የትምህርት ቤቶቹ$ ህንፃዎች፥ በሮችና መስኮቶች የተሰበሩ፣ ክፍሎቹም ንፁህ ያልሆኑ እና ጠባቦች መሆናቸውን ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ የትምህርት ቤቶቹ ግቢ ህፃናት በነፃነት እንዲጫወቱ የሚያስስችል በቂ ቦታ የላቸውም። በቂ የመማሪያና የመጫወቻ ቁሳቁሶችም አልነበሩም። መምህራኑም ለማተማር የሚያስችል ምንም አይነት ብቃት አልነበራቸውም። በቀጣይነት በገጠር ካሉ ሌሎች ቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች ላይ ካደረኳቸው ምልከታዎች በመነሳት ተመሳሳይ ችግሮችን ተመልክቻለሁ። ይህ ሁኔታ ይህንን ጥናት እንዳደርግ አነሳስቶኛል። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ኢትዮጵያ በሚገኙ በቅድመ-መደበኛ ትምህርት ቤቶች በት/ቤት ተኮር የቅድመ-መደበኛ ክፍሎች የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ አተገባበርን ምንነት ማረጋገጥ ነው። የዚህን ጥናት ዓላማ ለማሳካት ቁጥራዊ ያልሆነ የጥናት ዘዴ ተጠቅሜአለሁ። ለዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ የአስራ ሁለት የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ ባለሙያዎች ጥልቅ እይታዎችን፣ አመለካከቶችን፣ ትርጉሞችን እና ተግባራትን እንድረዳና እንድገልጽ ረድቶኛል።

practices of ECE policy practitioners. The major theories that informed this study are maturation, learning and interaction theories that promote holistic development of children via ECE programmes. There were 38 purposively selected subjects who participated in the study. The findings of the study revealed that practitioners had a lack of knowledge about policy implementation and did not teach correctly in the classrooms. Teachers taught Grade R with inadequate material resources and support; there was a lack of policy guidelines, standards, common curriculum, teamwork and supervision. Based on the findings, I recommended an interaction model of policy implementation that integrates bottom-up and top-down approaches to promote positive and an active interplay between the policy managers at the top and implementers at the local level.

**Keywords:** Early childhood education; pre-school education; Ethiopian early childhood education; Education policy implementation; policy framework.

የዚህ ጥናት ዋና ዋና ንድፈ ሀሳቦች የብስለት፣ የመማር፣ የመስተጋብር ጽንሰ-ሀሳቦች በቅድመ-መደበኛ ፕሮግራሞች የልጆችን ሁለንተናዊ ዕድገት የሚያበረታቱ ናቸው። በጥናቱ ላይ ሆን ተብሎ የተመረጡ የጥናቱን ዓላማ የሚያሳኩ ሰላሳ ስምንት ተሳሳታፊዎች ነበሩ። የጥናቱ ግኝቶች ፖሊሲውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ባለሙያዎችና ፈጻሚዎች በቂ ዕውቀት እንደሌላቸውና በክፍል ውስጥ በትክክል እንደማያስተምሩ አረጋግጧል። መምህራን በቂ ባልሆኑ ቁሳዊ ማቴሪያሎች እና ድጋፍ አስተምረዋል። የፖሊሲ መመሪያዎች፣ ደረጃዎች፣ የጋራ ሥርዓተ ትምህርት፣ የቡድን ሥራ እና የቁጥጥር እጥረትም ታይቷል። በመጨረሻም አጥኚው ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት በፖሊሲ አተገባበር መስተጋብር ሞዴል ከታች ወደ ላይ እና ከላይ ወደ ታች ያሉትን አቀራረቦች በማዋሃድ በከፍተኛ ደረጃ በሚገኙ የፖሊሲ አስተዳዳሪዎች እና በአካባቢ ደረጃ ባሉ ፈጻሚዎች መካከል አዎንታዊ እና ንቁ የሆነ መስተጋብር አስፈላጊ መሆኑን ይመክራል።

**ቁልፍቃላት፡-**የልጅነት ትምህርት፣ የመፅዋለ ሕጻናት ትምህርት፣ የኢትዮጵያ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት፣ የቅድመ-መደበኛ ትምህርት ፖሊሲ ትግበራ፣ የፖሊሲማዕቀፍ

# Indigenous play as a psychotherapeutic technique with young adolescents experiencing socio-emotional and behavioural difficulties in Hawassa City, Ethiopia

Tarekegn Tadesse Gemeda

## ABSTRACT

The study aimed to examine the extent of indigenous play or teret-teret, as a psychotherapeutic technique to assist young adolescents in their adjustment from socio-emotional and behavioural difficulties. Following a mixed methods research approach, the study was conducted in three

# ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የስነምግባር ችግሮችን ለማከም ሀገር በቀል ጨዋታዎች እንደ ስነልቦና ህክምና ቴክኒክ የሚጫወቱት ሚና፡ የሀዋሳ ከተማ ታዳጊ ወጣቶች ላይ የተደረገ ጥናት፤

## በታረቀኝ ታደሰ ገመዳ

## አጠቃሎ

ጥናቱ ዋና ዓላማ የሀገር በቀል ጨዋታዎች ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና የስነምግባር ችግሮችን ለማከም የሚጫወቱትን ሚና ለመፈተሽ ነው። በተጨማሪም፣ እንደ ሳይኮቴራፒዩቲካል ቴክኒክ ታዳጊ ወጣቶችን ከማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና

phases. The qual then QUANT in the main study followed by QUANT - QUANT and finally qual was employed. Two hundred ninety-nine participants, with 13 in Phase 1; 221 in Phase 2, and 65 in Phase 3, were involved in the study. Thirteen participants were purposively selected based on their experiences and merits for Phase 1, while 221 were selected through multi-level probability sampling techniques for Phase 2. Among the 65 participants for Phase 3, five were selected randomly whereas 60 were selected purposely. Three data-gathering instruments, comprising in-depth interviews, archive analysis, and questionnaires were employed. This design explored the quality of 62 manifestations of indigenous teret-teret for use in psychotherapy. The qualitative phenomenological study confirmed teret-teret as a relevant psychotherapeutic technique, practised in Ethiopia for the adjustment of young adolescents who experience socio-emotional and behavioural difficulties. The intervention study revealed statistically significant differences between the participants who received teret-teret psychotherapy and those who did not receive teret-teret psychotherapy. It was found that teret-teret psychotherapy advanced the socio-emotional and behavioural competencies of the participants. The cross-sectional survey study verified a 43% prevalence rate of composite SEBD, with 50% being anxiety/depression, 45% somatic complaints, 44% attention problems, 43% delinquency, and 42% aggression respectively. Implications were discussed about applying indigenous child-friendly stories, teret-teret, as psychotherapeutic techniques to help young adolescents who display socio-emotional and behavioural difficulties at schools and in community settings.

ባህሪ ችግሮች ለማስተካከል እንዲችሉ ለመርዳት ያለመ ነው። ጥናቱ ድብልቅ ዘዴዎችን በመከተል፣ በሦስት ደረጃዎች ተካሂዷል። በዋናው ጥናት QUAL ከዚያም፣ QUANT በመቀጠል QUANT - QUANT እና በመጨረሻም QUAL ጥቅም ላይ ውሏል። ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ተሳታፊዎች፣ ከ13 ጋር በደረጃ 1፣ 221 በደረጃ 2 እና 65 በደረጃ 3 ላይ በጥናቱ ተሳትፈዋል። ለክፍል 113 ተሳታፊዎች ባካበቱት ልምድ እና መልካም ብቃታቸው መሰረት በዓላማ የተመረጡ ሲሆን፣ 221ቱ ደግሞ በባለብዙ ደረጃ የአቅም ናሙና ቴክኒኮች ተመርጠዋል። ከደረጃ 2 ከ65ቱ ተሳታፊዎች መካከል 65ቱ ተሳታፊዎች መካከል አምስቱ በዘፈቀደ ሲመረጡ፣ 60ዎቹ ሆን ተብሎ ተመርጠዋል። ጥልቅ ቃለ-መጠይቆችን፣ የማህደር ትንተና እና መጠይቆችን ያካተቱ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ስራ ላይ ውለዋል። ይህ ንድፍ በሳይኮቴራፒ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የ62 አገር በቀል ተረት-ተረቶች መገለጫዎችን ጥራት ዳስሷል። የጥራት ፍኖሜኖሎጂ ጥናት ተረት-ተረትን እንደ አግባብነት ያለው ሳይኮቴራፒዩቲካል ቴክኒክ መሆኑን አረጋግጧል፡ ፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና ባህሪ ችግሮች ያጋጠሟቸውን ወጣት ታዳጊዎች ማስተካከል። የጣልቃ ገብነት ጥናቱ በተረት-ተረት ሳይኮቴራፒ በተቀበሉት ተሳታፊዎች እና በተረት-ተረትን ሳይኮቴራፒ ባልተቀበሉት መካከል በስታቲስቲካዊ ጉልህ ልዩነት አሳይቷል። የተረት-ተረትን ሳይኮቴራፒ የተሣታፊዎችን ማህበራዊ-ስሜታዊ እና ባህሪ ብቃቶች እንዳሳደገው ታውቋል። በክፍል-አቋራጭ የዳሰሳ ጥናት፣ ጥናቱ 43% የተቀናበረ SEBD ስርጭት መጠን አረጋግጧል፤ በዚህም፣ በቅደም ተከተል 50% ጭንቀት/ድብርት፣ 45% somatic ቅሬታዎች፣ 44% የትኩረት ችግሮች፣ 43% ጥፋተኝነት እና 42% ጠበኝነት ሆነው ተገኝተዋል፡ ፡ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰብ አካባቢዎች ማህበረሰባዊ-ስሜታዊ እና ባህሪ ችግሮችን የሚያሳዩ ወጣት ታዳጊዎችን ለመርዳት አገር በቀል ለልጆች ተስማሚ የሆኑ ታሪኮችን፣ ተረት-ተረትን እንደ ሳይኮቴራፒዩቲካል ቴክኒኮች ስለመተግበር አንድምታ ተብራርቷል።

**ቁልፍ ቃላት፡** ማህበራዊ-ስሜታዊ እና ባህሪ ችግሮች፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና ባህሪ ብቃቶች፣ ሀገር በቀል ጨዋታ፣ ተረት-ተረት፤

**Keywords:** Socio-emotional and behavioural difficulties; socio-emotional and behavioural competencies; indigenous play; teret-teret.

# Department of Science and Technology Education

Year of Graduation 2022

## The use of the multiple representation approach in enhancing the learning of fluid mechanics in undergraduate physics classes in Ethiopia

Ashenafi Legesse Segni

### ABSTRACT

The inadequate understanding of fluid mechanics is a phenomenon widely experienced by undergraduate physics students. The study aimed to establish students' preconceptions on this topic, then develop multiple representation teaching sequences and establish the effect thereof in two iterations. Multiple intelligence theory, variation theory, and cognitive theory were used to guide the study. This study was conducted at two Ethiopian universities. Students' pre-conceptions were first categorized and then analysed using categories and frequency counts. This informed the development of a multiple representation approach aimed at enhancing the learning of fluid mechanics. The research methods used to evaluate multiple representations' effectiveness comprised a quasi-experimental design. Open-ended questionnaires, the Fluid Mechanics Concept Inventory, and the Test of Multiple Representation Approach Related Attitudes were used to collect data from N = 128 undergraduate students,

## በኢትዮጵያ በመጀመሪያ ዲግሪ በፊዚክስ ትምህርት፣ የበርካታ ውክልና አጠቃቀም አቀራረብን በመጠቀም የፈሳሽ መካኒኮችን ትምህርት ማሳደግ፤

በአሸናፊ ለገሰ ሰኚ

### አጠቃሎ

የመጀመሪያ ዲግሪ የፊዚክስ ተማሪዎች የፈሳሽ ሜካኒክስ ክስተትን በስፋትና በበቂ ሁኔታ ከመገንዘብ አንጻር ክፍተት አለ። የዚህ ጥናት ዓላማ በዚህ ርዕስ ላይ የተማሪዎች ቅድመ-ግንዛቤ ላይ በመመስረት ያለውን ክፍተት ለማጥናት ነው። ከዚያም በርካታ የውክልና ትምህርት ቅደም ተከተሎችን ማዘጋጀት፣ ውጤቱን በሁለት ድግግሞሾች ላይ ለማረጋገጥ. ሞክሯል። ጥናቱን ለመምራት የበርካታ ኢንተለጀንስ ቲዎሪዎች፣ የልዩነት ንድፈ ሃሳብ እና የግንዛቤ ንድፈ ሃሳብ ስራ ላይ ውለዋል። ይህ ጥናት የተካሄደው በሁለት የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ነው። የተማሪዎች ቅድመ ግምቶች በመጀመሪያ ተከፋፍለዋል፤ ከዚያም ምድቦችን እና የድግግሞሽ ቆጠራዎችን በመጠቀም ተንትነዋል። ይህ የፈሳሽ ሜካኒክስ ትምህርትን ለማሻሻል የታለመ ብዙ የውክልና አቀራረብን አሳውቋል። የበርካታ ውክልና ውጤታማነትን ለመገምገም ጥቅም ላይ የዋሉት የምርምር ዘዴዎች ኳሲ-ሙከራ ንድፍ ላይ ያተኮሩ ናቸው። ክፍት የሆኑ መጠይቆች፣ የፈሳሽ ሜካኒክስ ፅንሰ-ሀሳብ ኢንቬንቶሪ እና የበርካታ ውክልና አቀራረብ ተዛማጅ አመለካከቶች ፈተና ከ N = 128 የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች፣ 64 በድግግሞሽ I እና 64 በ በድግግሞሽ II መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ ውለዋል። እያንዳንዱ ድግግሞሽ ከሁለት ዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ

64 in Iteration I and 64 in Iteration II. Every iteration consisted of two groups of students selected from two universities. Before any intervention, the students' prior knowledge was established by using the open-ended questionnaire and fluid mechanics conceptual inventory. Both groups received instruction based on both the multiple representation approach and the traditional lecture method. The first version of the multiple representations only used four representations, which resulted in no significant difference between the experimental and control groups. Before the second intervention, the new group of students included 64 students, of whom 32 were from each group. The second development of the multiple representations followed, using eight representations. This resulted in a significant difference between the intervention and control groups on both the open-ended questionnaire and the fluid mechanics conceptual inventory. The results showed that using eight multiple representations was significantly more effective compared to using two, three, or four in the students' understanding of fluid mechanics concepts. In addition, students had positive attitudes towards the use of the multiple representation approach. The study included two phases; perhaps it would have been better to include more than two phases. It is recommended that scholars in this field conduct further research on other physics topics.

**Keywords:** Alternative conception; conception model; categorising; model analysis; multiple representations; physics education; variation theory.

ሁለት ተማሪዎችን ያቀፈ ነበር። ለዚህም የተማሪዎቹ ቀዳሚ ዕውቀት በፈሳሽ ሜካኒክስ ሃሳባዊ ክምችትን በተቋቋመው ክፍት መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጉል፤ ይህም ከማንኛውም ጣልቃ ገብነት በፊት ተከናውኗል። ሁለቱም ቡድኖች በበርካታ የውክልና አቀራረብ እና በባህላዊ የማስተማር ዘዴ ላይ ተመስርተው መመሪያ አግኝተዋል። የበርካታ ውክልናዎች የመጀመሪያው እትም አራት ውክልናዎችን ብቻ ተጠቅሟል። ይህም በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድኖች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አልፈጠረም። ከሁለተኛው ጣልቃ ገብነት በፊት፣ አዲሱ የተማሪዎች ቡድን 64 ተማሪዎችን ያካተተ ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ 32ቱ ከእያንዳንዱ ቡድን የተውጣጡ ናቸው። የበርካታ ውክልናዎች ሁለተኛ እድገት፣ ስምንት ውክልናዎችን በመጠቀም የተከናወነ ሲሆን፣ ይህም በሁለቱም ክፍት በሆነው መጠይቅ እና በፈሳሽ ሜካኒክስ ጽንሰ-ሀሳባዊ ክምችት ላይ ባሉ ጣልቃ-ገብ እና የቁጥጥር ቡድኖች መካከል ከፍተኛ ልዩነት አስገኝቷል። ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት ስምንት ውክልናዎችን መጠቀም በተማሪዎች ፈሳሽ ሜካኒክስ ፅንሰ-ሀሳቦች ውስጥ ሁለት፣ ሶስት ወይም አራት ከመጠቀም ጋር ሲነፃፀር የበለጠ ውጤታማ ነው። በተጨማሪም፣ ተማሪዎች ባለብዙ ውክልና አቀራረብ አጠቃቀም ላይ አዎንታዊ አመለካከት ነበራቸው። በአጠቃላይ ጥናቱ ሁለት ደረጃዎችን ያካተተ ሲሆን፣ ምናልባት ከሁለት በላይ ደረጃዎችን ማካተት የተሻለ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በመነሳት አጥኚው፣ በዚህ ዘርፍ ያሉ ምሁራን በሌሎች የፊዚክስ ርእሶች ላይ ተጨማሪ ጥናት እንዲያደርጉ ይመከራል።

**ቁልፍ ቃላት:**- አማራጭ ጽንሰ-ሐሳብ፣ የፅንሰ-ሀሳብ ሞዴል፣ መከፋፈል፣ ሞዴል ትንተና፣ በርካታ ውክልናዎች፣ የፊዚክስ ትምህርት፣ ልዩነት ንድፈ ሐሳብ፤

# Analysis of foreign aid effectiveness on economic development in Ethiopia

Tagese Helore Lamore

## ABSTRACT

In this study, the effectiveness of foreign aid on economic development and poverty alleviation in Ethiopia during the period of 2011 to 2020 was analysed. On the one hand, government reports have indicated that the country is economically one of the fastest growing in Africa, a position that has been seconded by international financial institutions and other bilateral donors. On the other hand, the country remains on the list of poorest countries in the world. A qualitative approach was applied in investigating the problems related to foreign aid effectiveness in Ethiopia. The study used both primary and secondary data open-ended interviews and focus group discussions were used to generate data from key informants and focus group participants. Content analysis of documents was done using aid flow records, reports of government and United Nations agencies, policy manuals, research findings, books and journals from secondary data sources. The data analysis focused on trends in economic development and foreign aid flow to Ethiopia during the past decade (2011 – 2020), and the role aid plays in economic development and poverty alleviation and its effectiveness in Ethiopia. The primary data sources show that economic performance in Ethiopia during the past decade was sluggish and poverty alleviation targets remained unmet. The number of people below the poverty line remained high and the expected economic transition from an agriculture-led to an industry-led economy did not happen. The results of the effectiveness of foreign aid on

# በኢኮኖሚ ልማት ላይ የውጪ ዕርዳታ ውጤታማነት፤

ታገሰ ሄሎሬ ላሞሬ

## አጠቃሎ

በዚህ ጥናት በኢትዮጵያ እ.አ.አ ከ2011 እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ የውጭ እርዳታ በምጣኔ ሀብት እድገት እና ድህነት ቅነሳ ላይ ያስከተለው ውጤታማነት ተተንትኗል፡፡ በአንድ በኩል የሃገሪቷ የምጣኔ ሀብት በአፍሪካ አህጉር ደረጃ በፍጥነት እያደጉ ከሚገኙት አንዱ እንደሆነ መንግስት በየጊዜው ሲነግረን የነበረ ሲሆን በዚህ ረገድ የአለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማትና ሌሎች የሁለትዮሽ ላጋሾችም በተመሳሳይ መልኩ ሲያስተጋቡ ቆይተዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን ሃገሪቷ በዓለም ላይ ካሉት እጅግ በጣም ድሃ ሃገሮች ተርታ ተመድባ ትገኛለች፡፡ ጥናቱ በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ የውጭ እርዳታ እና እገዛ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረጉ ችግሮችን ለመለየት ዓይነታዊ የጥናት አካሄድ ስርዓት ተከትሏል፡፡ በጥናቱ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ መረጃዎች  የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎች እና ከሁለተኛ ወገን የተገኙ መረጃዎች ናቸው፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር ተያይዞ ተገቢ ቃለ መጠይቆች የተፈለገ መልስ በሚሰጥበት አካሄድ የተከናወነ ሲሆን ከአጠቃላይ የጥናቱ ሂደት አንጻር አስፈላጊ መረጃዎችን ከቡድን ውይይት ተሳታፊዎችና ቁልፍ መረጃ ሰጪ ከተባሉ አካላት ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ በሰነዶች ይዘት ትንተና እና ግምገማ ሂደትም አጠቃላይ የእርዳታ ፍሰት መረጃዎችና፣ ሪፖርቶች ከመንግስት አካላት እና ከተባበሩት መንግስታት ኤጀንሲዎች የተወሰዱ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎንም የፖሊሲ ማንዋሎች፣ የጥናት ግኝቶች፣ መጽሐፍትና ጋዜጦች እንደሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ተወስደዋል፡፡ የመረጃ ቋት ትንተና ሂደትም በዚህ ጥናት ውስጥ ስለ አጠቃላይ ምጣኔ ሀብት ወይም የሃገሪቷ ልማት እና  ላለፉት  አስር አመታት ማለትም እ.አ.አ ከ2011 እስከ 2020 ዓ.ም ድረስ ወደ ኢትዮጵያ ከውጪ የገቡ እርዳታዎች ላይ ትኩረት ሲያደርግ በአጠቃላይ በሃገሪቷ የምጣኔ ሃብት ዕድገት እና በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ላይ የነበረቸው ሚናና ውጤታማነት ከግምት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ከመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች እንዳመለከቱት ባለፉት አስር አመታት የኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት አፈጻጸም

poverty alleviation in aid-recipient countries are still inconclusive. Political affiliation, lack of accountability mechanisms, poor collaboration among actors, poor infrastructure and political instability are additional hindering factors in Ethiopia. In line with the perceptions of the primary data sources, institutional capacity is one of the major bottlenecks in Ethiopia hindering foreign aid effectiveness. Regardless of the increasing trend in aid flow into economic sectors in Ethiopia, the effect on poverty alleviation was found to be minimal and its effectiveness hampered by many factors from both the aid recipients' and the donors' sides. This study therefore recommends that the factors hindering aid effectiveness in Ethiopia be meaningfully investigated to develop effective country-specific strategies for better use of foreign aid in economic development.

**Keywords:** Economic development; foreign aid; poverty alleviation; aid effectiveness.

በጣም አዝጋሚ እና የተወጠነው የድህንት ቅነሳ ስትራቴጂ እና ግብም የተፈለገውን አላማ እና ግብ እንዳልመታ ተለይቷል። በሃገራችን ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩ ዜጎች አሁንም ቢሆን ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናረ የሚገኝ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞም አጠቃላይ የምጣኔ ሀብት እድገት ከግብርና መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ለማሸጋገር የተሞከረው ጥረት ተግባራዊ ሆኖ አልተገኘም። የውጪ ዕርዳታ በተቀበይ አገሮች የድህነት ቅነሳም ሆነ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ያለው ውጤታማነት ያልተቋጨ መከራከሪያ ሆኖ ተገኝቷል። አጠቃላይ የሃገራችን የፖለቲካ ሁኔታ፣ የተጠያቂት ስርዓት ያለመኖር፣ የተዋናይ ወገኖች ያለመተባበር እና ትብብራቸውም ደካማ መሆን፣ የመሰረተ ልማት አለመሟላት እና የፖለቲካ ሁኔታ አለመረጋጋት በኢትዮጵያ የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ የበኩላቸውን አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድረዋል። በዚህ ጥናት ውስጥ ከመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ከተገኙት ጥቆማዎች አንጻር በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ እርዳታ ፍሰት ውጤታማነት ላይ ማነቆ ከሆኑት ጉዳዮች የተቋማት የአቅም ውስንነት አንዱ ነው። በኢትዮጵያ ለምጣኔ ሀብት እድገት ካሉት የእርዳታ ፍሰት ጋር ተያይዞ ፍሰቱ የጨመረ ቢሆንም እንኳን በሃገሪቷ በድህነት ቅነሳ ላይ ግን እየተወጣ ያለው ሚና ዝቅተኛ ከመሆኑም በላይ ውጤታማነቱ ከሁለቱም ከእርዳታ ተቀባይ እና ሰጪ ወገኖች ከሚመነጩ በርካታ መንስኤዎች ተደናቅፏል። ይህ ጥናት ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ እርዳታ ውጤታማ እንዳይሆን ያደረጉ ጉዳዮች በጥልቀት ተመርምሮ እና ተጠንቶ ከውጭ የሚገኝ እርዳታ በተሻለ ሁኔታ ለሃገሪቷ የምጣኔ ሀብት እድገትና ድህነት ቅነሳ የተሻለ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚያስችሉ ስትራቴዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን የበኩሉን አስተያየት ያቀርባል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- የእርዳታ ውጤታማነት፣ የምጣኔ ሀብት እድገት፣ የውጭ እርዳታ፣ ድህነት ቅነሳ

# College of Economic and Management Sciences

# Department of Business Management

Year of Graduation 2021

## A proposed trust management model for organisations: The case of the Ethiopian Banking Sector

Getachew Wagaw Temesgen

### ABSTRACT

Ethiopia, a developing country on the African continent, has experienced double-digit growth during the last decade. To sustain this growth, the country needs a sound and healthy banking sector. Consensus exists that trust is a valuable resource that can make a difference. It influences the quality of relationships between an organisation and its employees and management. It enables organisations such as banks to retain their most valuable employees and customers and improve organisational functioning. Most leaders agree that high levels of trust are critical to the success of their organisations. In this study, the existing theoretical principles and models relating to trust were analysed in-depth and followed up by an empirical study to determine to what extent trust management practices were being applied. A quantitative survey was conducted on a probability sample of 405 participants from the eight largest banks in Ethiopia. From the measured items, 54 usable factors were identified by using exploratory factor analysis. The calculated Cronbach alpha values indicated satisfactory internal consistency. While the Pearson product-moment correlation applied to the factors indicated a dominance of statistically significant positive correlations. Various informative results emerged from the

## ለተቋማት የተዘጋጀ የእምነት አስተዳደር ሞዴል - የኢትዮጵያ ባንክ ዘርፍ ንጥል ጥናት

በጌታቸው ዋጋው ተመስገን

### አጠቃሎ

በአፍሪካ አህጉር ታዳጊ ከሆኑ ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ ችላለች። ይህንን እድገት ለማስቀጠል ሀገሪቱ አስተማማኝና ጤናማ የባንክ ዘርፍ ያስፈልጋታል።

እምነት (መተማመን) በተቋማት መካከል ልዩነት መፍጠር የሚችል ዋጋ ያለው ሃብት እንደሆነ የጋራ መግባባቶች አሉ። በተቋማትና በሠራተኞች እንዲሁም አመራሩ መካከል በሚኖረው የሥራ ግንኙነት ላይ እምነት (መተማመን) አወንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩም በላይ ሠራተኞችንና ደንበኞችን ይዞ በማቆየት እንደ ባንክ ላሉ ተቋማት የዕለት ተዕለት ሥራቸውን ለማሻሻል ይረዳቸዋል። አብዛኛዎቹ መሪዎች እንደሚስማሙት እምነት (መተማመን) የሰፈነበት የሥራ አካባቢ መፈጠር ለተቋማት ስኬት ወሳኝ ነው።

በዚህ ጥናት ከእምነት (መተማመን) ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ንድፈ-ሃሳቦች፣ መርሆዎችና ሞዴሎች ከተተነተኑ በኋላ የእምነት አስተዳደር ምን ያህል እየተተገበረ እንደሆነ ለመረዳት በኢትዮጵያ ካሉ ስምንት ትላልቅ ባንኮች በዕድል ሰጪ ንሞና ዘዴ (Probability Sampling) የተመረጡ 405 ሠራተኞችን በማሳተፍ መጠናዊ የዳሰሳ ጥናት (Quantitive Survey) ተካሂዷል።

ከቀረቡ የመለኪያ ጥያቄዎች ውስጥ ገላጭ የፋክተር ትንተና ዘዴ (Exploratory Factor Analysis) በመጠቀም 54 ፋክተሮች ተለይተዋል። የተሰሉ የክሮንባች አልፋ ዋጋዎች (Cronbach Alpha Values) በመለኪያ ጥያቄዎች መካከል አጥጋቢ የሆነ ውስጣዊ ወጥነት (Internal Consistency) እንዳለ ሲያመላክቱ የፒርሰን ፕሮዳክት

empirical survey, among which were the relatively weak application of trust management practices such as trust drivers and trust builders. Some barriers were also identified such as the trustworthiness of co-workers/team members, the immediate supervisor, and top management. Thus, it was evident that proper trust management practices had not been fully established within the banking sector in Ethiopia. There was thus a need for some guidelines in this regard. An integrated trust management model was therefore developed, and tested, through Structural Equation Modelling, and validated to satisfy this need.

**Keywords:** Organisational trust; trust management; building trust; trust drivers; trust busters; trust repair; maintaining trust; trust outcomes; banking sector; Ethiopia.

ሞመንት ተዛምዶ (Pearson Product-Moment Correlation) ደግሞ በፋክተሮች መካከል ጉልህ የሆነ ስታትስቲካዊ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን አመላክቷል።

ከጥናቱ የተለያዩ መረጃ ሰጭ ውጤቶች የተገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ውስጥ እምነት አምጭ እና እምነት ገንቢ ተግባራት በተመለከተ በአንጻራዊነት ድክመት ያለባቸው መሆኑን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል። እንዲሁም የሥራ ባልደረቦች (የቡድን አባላት)፣ የቅርብ ሃላፊዎች እና የበላይ አመራሩ ተዓማኒነት በባንክ ዘርፉ ውስጥ ላለው የእምነት አስተዳደር ስርዓት መሰናክል እንደሆኑ ጥናቱ አመላክቷል። በዚህ መሰረት በኢትዮጵያ የባንክ ዘርፍ ውስጥ አግባብነት ያለውና ትክክለኛ የእምነት አስተዳደር ስርዓት አተገባበር በተሟላ ሁኔታ እንደሌለ በጥናቱ ግልጽ ሆኗል። በመሆኑም ይህንን ጉዳይ በተመለከተ አንዳንድ መመሪያዎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ይህንን ፍላጎት ለማሟላት በመዋቅር እኩልታ ሞዴል (Structural Equation Modelling) የተመዘነ የተቋማት የእምነት አስተዳደር ሞዴል በዚህ ጥናት ተዘጋጅቷል።

**ቁልፍ ቃላት**:- ተቋማዊ እምነት፣ እምነት አስተዳደር፣ እምነት ግንባታ፣ እምነት አምጭ፣ እምነት ሸርሻሪ፣ እምነት ጥገና፣ እምነት ጥበቃ፣ የመተማመን ውጤት፣ የባንክ ዘርፍ፣ ኢትዮጵያ

# Department of Finance, Risk Management, and Banking

Year of Graduation 2023

## The nexus between financial inclusion, financial stability and economic growth in sub-Saharan Africa

Meshesha Demie Jima

### ABSTRACT

Scholars and several global and international development agencies have been advocating the importance of financial inclusion for financial stability, social welfare improvement and sustainable economic growth. Within this general framework, the sub-Saharan African (SSA) countries have been striving to develop and implement financial inclusion strategies to realise stability and sustainable economic growth. However, theories and empirical findings lack consensus on the major drivers of financial inclusion and financial stability. In addition, there are disagreements on the relationships between financial inclusion, financial stability and economic growth, resulting in disparity in the design and application of strategies and policies. The aim of this study is, thus, to examine the key drivers of financial inclusion and financial stability, assess the co-integrating long-run relationships, as well as determine the causalities that exist between financial inclusion, financial stability and economic growth for the selected SSA countries for the period of 2000 to 2019. The study used the General Methods of Moments (GMMs) for the dynamic panel data, Autoregressive Distributed Lags (ARDL) for the panel co-integration tests and panel Granger non-causality tests to verify the causation

## ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በኢኮኖሚ እድገት መካከል ያለው ትስስር፤

በመሸሻ ደሚ ጅማ

### አጠቃሎ

ምሁራን እና በርካታ አለምአቀፍ የልማት ተቋማት የፋይናንሺያል አካታችነት ለፋይናንስ መረጋጋት፣ ለማህበራዊ ደህንነት መሻሻል እና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ እድገት አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባሉ። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት የተረጋጋ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትን እውን ለማድረግ የፋይናንሺያል አካታችነት ስትራቴጂዎችን በመቅረጽ ተግባራዊ ለማድረግ ሲጥሩ ቆይተዋል። ከዚህ አንጻር ያለው አንድ ችግር የፋይናንሺያል አካታችነትን እና የፋይናንስ መረጋጋትን የሚወስኑ ዋና ዋና አመላካቾች በንድፈ ሃሳብ እና በተጨባጭ ግኝቶች ደረጃ ወጥነት የጎደላቸው መሆኑ ነው። ከዚህ በፊት የተደረጉ ጥናቶች በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በኢኮኖሚ ዕድገት መካከል ባሉ ግንኙነቶች ላይ አለመግባባቶች መኖራቸውን ይጠቁማሉ። ይህም ሁኔታ በስትራቴጂ እና በፖሊሲዎች ቀረጻ እና አተገባበር ላይ ልዩነት አስከትሏል ። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም ለፋይናንሺያል አካታችነት እና ለፋይናንስ መረጋጋት መንስኤ የሆኑ ቁልፍ አመላካቾችን በመመርመር መለይት፣ በፋይናንሺያል አካታችነት እና በፋይናንስ መረጋጋት መካከል ያለውን ግንኙነት መለየት እና በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋትና በኢኮኖሚ እድገት መካከል ያለውን አጠቃላይ ግንኙነት መገምገም ነው። ለዚህ ጥናት ከሰሃራ በታች ያሉ 26 የአፍሪካ ሀገራት የተወሰዱ ሲሆን፤ በነዚህ ሀገራት ከ2000 እስከ 2019 ባሉት አመታት ውስጥ የታዩ የተለያዩ የፋይናንስና

between the variables. Composite indices were developed for financial inclusion and institutional quality using a Principal Component Analysis (PCA) technique. The results of this study revealed that the lags effect, economic growth, financial stability, financial deepening, inflation, efficiency, profitability and liquidity position were found to be important drivers of financial inclusion in the region. On the other hand, financial stability is determined by its lags effect, financial inclusion, institutional quality, digital technology adoption and global financial crises. The study also found that there is a long-run relationship between financial inclusion, financial stability and economic growth. Moreover, there is a pairwise bi-directional Granger non-causality between financial inclusion, financial stability and economic growth in the region, implying possible complementarity. Specifically, economic growth drives both financial inclusion and financial stability in most of the low income SSA countries, whereas financial inclusion promotes financial stability and economic growth for most of the middle-income economies. In this study, considering the broad and multi-dimensional aspects of financial inclusion, the use of a composite index to assess the interaction between financial inclusion, financial stability and economic growth helped to have a comprehensive picture and address the problems that may arise from the use of individual indicators. The findings of the study further confirmed that both macro and micro economic factors are important drivers of financial inclusion and financial stability. In addition, there are joint and separate causalities between financial inclusion, financial stability, and economic growth, and hence the SSA countries should follow a holistic approach, and develop and implement policies and strategies that ensure inclusive

ኢኮኖሚ አመላካቾች መረጃ ጥቅም ላይ ውሏል። ጥናቱ ተለዋዋጭ የፓነል መረጃ አጠቃላይ የአፍታ ዘዴዎችን (GMMs)፣ አውቶሬግሬሲብ የተከፋፈለ (Lags፣ ARDL) የፓነል ውህደት ሙከራዎችን እና የፓነል ግራንገር ምክንያታዊ ያልሆኑ ሙከራዎችን በመጠቀም በተለዋዋጭ ሂደቶች መካከል ያለውን ምክንያታዊ ግንኙነት ለማረጋገጥ አስችሏል። በዚህ ጥናት የዋና አካል ትንተና (PCA) ቴክኒክን በመጠቀም የተዋሃዱ መረጃ ጠቋሚዎችን (Indexes) ለፋይናንሺያል አካታችነት እና ለተቋማዊ ጥራት ማዘጋጀት ተችሏል። የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው የምጣኔ ሀብት ዕድገት፣ የፋይናንስ መረጋጋት፣ የፋይናንስ ጥልቀት፣ የዋጋ ንረት፣ ቅልጥፍና፣ ትርፋማነት እና የፈሳሽ ሀብት ለቀጣናው የፋይናንሺያል አካታችነት ዋና መንስዔዎች ናቸው። በሌላ በኩል የፋይናንሺያል አካታችነት፣ የተቋማት ጥራት፣ የዲጂታል ቴክኖሎጂ ተቀባይነት እና የአለም አቀፍ የፋይናንስ ቀውስ ደረጃ የፋይናንሺያል መረጋጋትን በዋናነት እንደሚወስኑት ጥናቱ አሳይቷል። በተጨማሪ በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በኢኮኖሚ እድገት መካከል የረጅም ጊዜ ግንኙነት መኖሩን ጥናቱ ያረጋገጠ ሲሆን፤ በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በክልሉ የኢኮኖሚ እድገት መካከል ምክንያታዊ ያልሆነ (ዘፈቀዳዊ) የእርስ በርስ ግንኙነት መኖሩንም ለማወቅ አስችሏል። ይህም በተጠቀሱት አመላካቾቹ መካከል ያለውን ተዛማጅነት ያሳያል። በተለይም ከሰሃራ በታች ባሉ ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት የምጣኔ ሀብት ዕድገት የፋይናንስ ተሳትፎን እና የፋይናንስ መረጋጋትን ሊያመጣ የሚችል ሲሆን፣ መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገራት ደግሞ የፋይናንስ አካታችነት ለፋይናንስ መረጋጋት እና ለኢኮኖሚያዊ እድገት አስፈላጊ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል። በዚህ ጥናት ውስጥ የፋይናንሺያል አካታችነትን ሰፊ እና ሁለገብ ገፅታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት የተቀናጀ መረጃ ጠቋሚ (Index) ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉ በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በኢኮኖሚ እድገት መካከል ያለውን መስተጋብር ለመገምገም ከማስቻሉም በላይ ጥናቱ ሰፊ እይታ እንዲኖረው በማድረግ በጥናቱ ላይ ሊነሱ የሚችሉ ክፍተቶችን ለመዝጋት ረድቷል። በዚህ ጥናት የማክሮ እና ማይክሮ ኢኮኖሚክ አመላካቾች ለፋይናንሺያል አካታችነት እና

and sustainable growth. In addition, the adoption of financial regulations should consider the synergy between financial inclusion, financial stability and economic growth. Thus, policy-makers, government advisors and financial sector regulators should not trade-off between financial inclusion, stability and economic growth while adopting strategies and policies in the region.

**Keywords:** Financial inclusion; financial stability; economic growth; sub-Saharan Africa; principal component analysis; panel unit root test; panel ARDL co-integration test; panel granger non-causality test.

ለፋይናንሺያል መረጋጋት መንስኤዎች መሆናቸው ተረጋግጧል። በተጨማሪም በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንሺያል መረጋጋት እና በኢኮኖሚ እድገት መካከል የጋራ እና የተናጠል ምክንያቶች በመኖራቸው፣ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት ሁሉን አቀፍ አካሄድ በመከተል፣ አካታች እና ዘላቂ እድገትን የሚያረጋግጡ ፖሊሲዎችን እና ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት እና መተግበር እንዳለባቸው ጥናቱ ይመክራል። የፋይናንስ ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ ከተፈለገ በፋይናንሺያል አካታችነት፣ በፋይናንስ መረጋጋት እና በኢኮኖሚ እድገት መካከል ያለውን ጥምረት ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የመንግስት አማካሪዎች እና የፋይናንስ ሴክተር ተቆጣጣሪዎች ፖሊሲዎችን በሚያወጡበትና ስትራቴጂዎችን በሚነድፉበት ጊዜ የፋይናንሺያል አካታችነትን እና የፋይናንስ መረጋጋትን መነሻ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

**ቁልፍ ቃላት፡** የፋይናንሺያል አካታችነት፣ የፋይናንሺያል መረጋጋት፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ሀገራት፣ ዋና አካል ትንተና፣ የፓነል ዩኒት ስር ሙከራ፣ የፓነል ARDL ውህደት ፈተና፣ የፓነል ግራንገር መንስኤ ያልሆነ ሙከራ፤

# College of
# Human Sciences

# Department of Communication Science

Year of Graduation 2017

## Participatory development communication in Ethiopia: A local development organisation in focus

Adem Chanie Ali

### ABSTRACT

This research explores the perception and practice of participatory communication for development. To this end, the study focuses on a leading local non-governmental organisation (NGO) named Organisation for Rehabilitation and Development in Amhara (ORDA), Ethiopia. This qualitative case study was based on the participatory development communication model which has been assumed to bring about sustainable socio-economic change in a country (Melkote & Steeves, 2001; Mefalopulos, 2008; Servaes, 2008). The data were collected using in-depth interviews, focus group discussions (FGD), document analysis and field observation. The collected data were organised and analysed in the form of content and thematic analysis. The results revealed an economic oriented and topdown approach to development communication as the dominant conceptions, and the majority of the research participants perceived the concept 'participation' as mere contributions of labour and materials which are not real participation, but co-option. Only a few of the management members of ORDA conceptualised the idea of 'participation' as an empowerment process in which the organisation's official document is also stated. Besides, the results showed no genuine participation

## አሳታፊ የልማት ኮሙኒኬሽን በኢትዮጵያ፡ በሀገር ውስጥ የልማት ድርጅት ላይ ያተኮረ ጥናት፤

በአደም ጫኔ አሊ

### አጠቃሎ

ይህ ጥናት ሰለ አሳታፊ የልማት ተግባቦት (ኮሚኒኬሽን) ያለን አረዳድና እና አተገባበሩን ይመረምራል ። ጥናቱ የሚያተኩረው በኢትዮጵያ በሚገኘው የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ) በተባለ በአማራ ክልል ግንባር ቀደም የሆነ ሀገር በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ላይ ነው። ይህ ዓይነታዊ ንጥል ጥናት የተመሰረተው የአንድን ሀገር ዘላቂ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ በታሰበው የአሳታፊ ልማት ኮሙዩኒኬሽን ሞዴል ላይ ነው (ሜልኮቴ እና ስቲቨስ፣ 2001፣ መፋሎፑሎስ፣ 2008፣ሰ ርቫስ፣ 2008)። የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው ጥልቅ ቃለ መጠይቆችን፣ ቡድን ተኮር ውይይት፣ የሰነድ ትንተና እና የመስክ ምልከታን በመጠቀም ሲሆን፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች በይዘት እና ጭብጥ ትንተና መልክ ተደራጅተው ተተንትነዋል። የጥናቱ ውጤት ኢኮኖሚ ተኮር ልማትና እና ከላይ ወደ ታች የልማት ተግባቦት አቀራረብ ዋና የልማት አረዳድ መሆናቸውን ያሳያል። አብዛኛዎቹ የምርምሩ ተሳታፊዎች 'ተሳትፎ' የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ እንደ የጉልበት እና የቁሳቁስ አስተዋፅኦ ብቻ በማድረግ የተገነዘቡት ሲሆን፣ ይህ ግን እውነተኛ የልማት ተሳትፎ ሳይሆን ለይስሙላ የሚድርግ ተሳትፎ ነው። የአማራ መልሶ መቋቋም ድርጅት የማኔጅመንት አባላት ጥቂቶቹ ብቻ 'ተሳትፎ' የሚለውን ሀሳብ እንደ የማብቃት ሂደት አድርገው በመረዳት የድርጅቱ ይፋዊ ሰነድ ከገለጸዉ ጋር ተመሳሳይ አረዳድ እንዳላቸዉ ያሳያል። በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውጤት የአካባቢው ማህበረሰብ በአመልድ የልማት ስራ ሂደት ውስጥ ሀቀኛ ተሳትፎ እንዳላደረጉ ያሳያል። በአጠቃላይ

of the local community in ORDA's development process. Generally, these results could lead us to conclude that participatory communication was the missing link in the development process. That is, communication was perceived as a transmission of development information and an image building activity, not a process of empowerment. The major communications practices of ORDA were also best described as one-way top-down which could reveal the legacy of modernisation and dependency theories of the development literature. The study further indicated pressing factors such as those that are individual, organisational and environmental-related, affecting the implementation of ORDA's participatory development communication. The results of the study further indicated that participatory development communication was not used as a means of liberation from the chain of poverty, the dependency syndrome and other underdevelopment problems which deeply persist in the region. Based on the findings, the study recommends the mainstreaming of participatory development communication, both at the perceptual and practical level, for achieving sustainable development in rural Amhara region, Ethiopia.

**Keywords:** Development communication; participation; participatory communication; development; top-down; bottom-up; holistic development; human development; empowerment; poverty; development paradigms.

እነዚህ ውጤቶች አሳታፊ ተግባቦት በልማት ሂደት ውስጥ የሌለ ዋና ጉዳይ ነው ወደሚል መደምደሚያ ሊያደርሱን ይችላሉ። ይህ ማለት ተግባቦት እንደ የልማት መረጃ ማስተላለፊያ እና ገጽታ ግንባታ ስራ እንጂ የማብቃት ሂደት ተደርጎ አይታሰብም ማለት ነው ። የአመልድ ዋና ዋና የተግባቦት ስራዎች አንድ ጎናዊ የተግባቦት መንገድ ከመከተላቸውም በላይ ከላይ ወደ ታች ፍሰት ያላቸው ስለሆነ፣ ይህ ደግሞ በልማት ጽሁፎች ውስጥ የዘመናዊነት እና የጥገኝነትን ንድፈ ሐሳቦች ተብለው የሚታወቁት ውርስ መሆኑን ያሳያል። ጥናቱ በተጨማሪ ግለሰባዊ፣ ድርጅታዊ እና አካባቢያዊ ጉዳዮች የአመልድ አሳታፊ የልማት ግንኙነት ትግበራ ላይ ተጽእኖ የፈጠሩ አንገብጋቢ ጉዳዮች መሆናቸውን ለማመላከት ሞክሯል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያመለክተው አሳታፊ የልማት ተግባቦት ከድህነት ሰንሰለት፣ ከጥገኝነት አስተሳሰብና እና ሌሎችም በክልሉ ውስጥ ጎልተው ከሚታዩ የልማት እጦት ችግሮች መላቀቅያ መንገድ ሆኖ ጥቅም ላይ እየዋለ እንዳልሆነ ያሳያል። እንደ መውጫ መንገድ ጥናቱ በአማራ ገጠራማ አካባቢዎች ዘላቂ ልማትን ለማስመዝገብ ሀቀኛ አሳታፊ የልማት ተግባቦት በአረዳድና በአተገባበር ደረጃ መሪ ሆኖ መውጣት እንዳለበት ምክረ ሀሳብ ያቀረባል።

**ቁልፍ ቃላት፡** የልማት ተግባቦት ፣ ተሳትፎ፣ አሳታፊ ተግባቦት፣ ልማት፣ ከላይ ወደ ታች የተግባቦት ዘዴ ፣ ከታች ወደ ላይ የተግባቦት ዘዴ ፣ ሁለንተናዊ ልማት፣ የሰው ልጅ ልማት፣ ማብቃት፣ ድህነት፣ የልማት እሳቤዎች

Year of Graduation 2020

# A critical osocio-historical analysis of the evolution of freedom of expression in the three most recent government of Ethiopia (1930-2014)

Adugnaw Dessie Seyoum

## ABSTRACT

This historical study analyses the holistic dynamics of Ethiopia, taking into account political, social, economic, cultural, religious, and media development aspects, with a focus on the three most recent governments (1930–2014), in relation to freedom of expression. The analysis indicates that the Feudalist-Imperial system was clearly the extension of centuries-old imperial hegemony which had used religious, cultural and patriotic hegemony to stifle freedom of expression. During the Socialist-Military regime every sphere of society, including acts of expression, were oriented towards the revolution and socialist political ideology. During the current ethnically based so-called Revolutionary-Democratic regime, freedom of expression has been stifled by means of legislation, government and party structures, complex surveillance, and social networks. While the instruments of repression have differed, relatively speaking, from government to government, the extent of repression has remained similar over a number of centuries. Threats to freedom of expression derive from rulers or governments, in which instance they are entrenched through policies, laws and bureaucracies, from religious and cultural hegemonies, from poverty and a related lack of education and access to information, and from conflicts, rivalry and wars. These threats have their

# ሀሳብን የመግለጽ ነፃነት በሶስት የኢትዮጵያ መንግሥታት (1930-2014)፡ ሂሳዊ ማኅበረ-ታሪካዊ ትንታኔ፤

አዱኛው ደሴ ስዩም

## አጠቃሎ

ይሄ ጥናት የሀገሪቱን ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ እና ሀይማኖታዊ ሁኔታን ያካተቱ አጠቃላይ ታሪካዊ ሂደቶች ከሃሳብ ነፃነት ጋር ያላቸውን ተዛምዶ በዋናነት በሦስቱ የቅርብ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስታት (1930-2014) ላይ አተኩሮ የሚተነትን ነው። ጥናቱ እንደሚያሳየው ለሺ ዘመናት ተጽእኖ የነበረው ባላባታዊና ንጉሳዊ ስርአት ቀጣይ በሆነው በንጉዊው መንግስት ሀይማኖትን፣ ባህልን እና አርበኝነትን በማስጠበቁ ሂደት የሃሳብ ነፃነት ሲታፈን ቆይቷል፡ ፡ በሶሽሊስታዊውና ወታደራዊው መንግስት ከሶሻሊዝም ፅንሰ-ሀሳብ ውጭ የሆነ ማነኛውም ነገር ሁሉ ቦታ እንዳይኖረው ተደርጓል። "ብሄር-ብሄረሰባዊ" ተብሎ በሚታወቀው ጎሳዊ(ethnic based) በሆነው ስርአት ደግሞ "አብዮታዊ-ዲሞክራሲ" ተብሎ የሚታወቀውን ፅንሰ-ሀሳብ ለማስጠበቅ ህግ፣ መንግሰታዊና እና የፓርቲ እንዲሁም የስለላ እና የማህበረሰብ መዋቅሮች የሃሳብ ነፃነትን ማፈኛ መንገዶች ሆነዋል። ባጠቃላይ የአገዛዞቹ ሃሳብን የማፈኛ መንገዶች በአገላለጽ የአንዱ ከሌላው ቢለያዩም መሰረታዊ ባህሪያቸውና መገለጫቸው ለዘመናት ተመሳሳይ ነበር። ሀሳቦች በዋናነት በመንግስታት/ገዥዎችና ፖለሲዎቻቸው፣ ህጎቻቸውና መዋቅሮቻቸው እንዲሁም በሃይማኖቶች እና ባህሎች፣ በድህነት እና በመረጃ እጥረት አልፎም በግጭቶች እና ጦርነቶች ምክንያት ይታፈናሉ። እነዚህ አፈናዎች የሚመነጩት ከማህበረሰቡ መሰረት ተነስተው በሂደት ሰንሰለት ከሚየያዙ ሶስት ወሳኝ ነገሮች ነው። እነዚህም የራስ አምልኮት(ናርሲሲዝም/Narcissism)፣ ቡድናዊ አብርሆት/Ethno-Luminary-Thought እና ሳያውቁ ማወቅ/Certainity-Uncertainity Dilemma ናቸው። እነዚህ ነገሮች ተጣምረው በራሳቸው ፒራሚዳዊ የአፈና ወጥመድ ከመስራታቸውም በተጨማሪ ከእነሱ

origins in three main interrelated causal or determining factors, namely the Certainty–Uncertainty Dilemma, Ethno-Luminary Thought and Narcissism, which together form a pyramid beneath which freedom of expression in Ethiopia has been trapped. This pyramid is identified in the study as the Social Pyramid, or the Pyramid of Repression Instruments, and it in turn gives rise to an overall web of suppression, that is, the Pyramid Trap of Repression. The study concludes that the repression of freedom of expression in Ethiopia is likely to remain intact, insofar as the threats to freedom of expression and the factors giving rise to those threats persist. While limited gains concerning the right to freedom of expression are achieved periodically, these are routinely undone and rolled back, since the Pyramid Trap of Repression is not dismantled.

**Key** words: Freedom of expression; Bottom-to-top perspective; Threats to freedom of expression; religious and cultural hegemonies; poverty; law; rivalries and wars; Feudalist-Imperial System; Socialist-Military Regime; Revolutionary-Democratic Rule; Certainty-Uncertainty-Dilemma; Ethno-Luminary-Thought; Narcissism; Di-spiral of silence; Web of Repression; and Pyramid Trap Theory.

ጋር በአቻ ከሚፈጥሩት ማህበረሰባዊ ፒራሚድ እና ማፈኛ መሳሪያዎች ፒራሚድ ጋር በመቀናጀት ቡድናዊነትን ማእከል ያደረገ አጠቃላይ የአፈና መረብ ይመሰርታሉ። በመሆኑም ምንም እንኳ አልፎ-አልፎ የሀሳብ ነፃነት የሚያመጡ የሚመስሉ ጅማሮዎች የታዩ ቢመስልም ጅማሮዎቹ ወዲያው ተቀልብሰዋል። ስለዚህ የአፈና መገለጫዎች እና በዋናነትም የአፈናው ምንጮች በመሰረታዊነት የማይቀየሩ በመሆናቸው ወደፊትም የሀሳብ አፈናው በነበረው ሂደት የሚቀጥል ይሆናል።

**ቁልፍ** ቃላት:-የሀሳብ ነፃነት አፈና፣ የሀሳብ ማፈኛ መንገዶች፣ የሀሳብ ነፃነት አፈና ምንጮ፣ የራስ አምልኮ(ናርሲሲዝም/፣ቡድናዊ አብርሆት/ Ethno-Luminary-Thought፣ ሳያውቁ ማወቅ/ Certainity-Uncertainity Dilemma፣ፒራሚዳዊ የአፈና ወጥመድ፣ የአፈና መረብ፣ የሀሳብ ነፃነት አፈና ቀጣይነት

# Department of English Studies

Year of Graduation 2021

## English as a foreign language instructors' conceptions and applications of communicative language teaching in grammar lessons: the case of four private universities in Ethiopia

Alamirew Kassahun Tadesse

### ABSTRACT

Communicative Language Teaching (CLT) has been adopted in various countries in the world. This is especially true in an EFL context in Ethiopia where it has received considerable attention both at policy and classroom levels. This study aimed to investigate English as a Foreign Language (EFL) instructors' conceptions and applications of CLT in teaching grammar lessons in private universities in Ethiopia. Due to the nature of the issues addressed in the study, the mixed-methods approach was employed. The data for the study were collected from 25 EFL instructors teaching in four private universities through semi-structured interviews, a quantitative questionnaire, and classroom observation. The qualitative data collected from the semi-structured interviews and classroom observation were analysed thematically, using deductive thematic analysis. The quantitative data garnered through the questionnaire were analysed using the latest version of SPPS (version 20) available at the time of data analysis. While the study highlighted four major EFL instructors' misconceptions stemming from the discrepancies in understanding

## እንግሊዘኛን እንደ ውጭ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴን (CLT) ከሰዋሰው ትምህርት ረገድ ያላቸው አረዳድና ትግበራ:- በአራት የግል ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የተደረገ ጥናት

በአላምረው ካሳሁን ታደሰ

### አጠቃሎ

ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ (CLT) በተለያዩ የአለም ሀገራት ተቀባይነት አግኝቷል። ይህ በተለይ በኢትዮጵያ እንግሊዝኛን እንደ የውጭ ቋንቋ (EFL) በማስተማር አውድ በፖሊሲም ሆነ፣ በክፍል ደረጃ ከፍተኛ ትኩረት ያገኘበት እውነታ ነው ያለው። ይህ ጥናት በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የግል ዩኒቨርሲቲዎች እንግሊዘኛን እንደ የውጭ ቋንቋ (EFL) የሚያስተምሩ መምህራን ፣ ከሰዋሰው ትምህርት ጋር በተያያዘ ስለ CLT ያላቸውን አረዳድ እና አተገባበርን ለመመርመር ያለመ ነው። በጥናቱ ውስጥ ቅይጥ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው በአራት የግል ዩኒቨርሲቲዎች ከሚያስተምሩ 25 የEFL መምህራን በከፊል የተዋቀሩ ቃለ መጠይቆችን፣ መጠይቆችን እና የክፍል ውስጥ ምልከታን በመጠቀም ነው። በከፊል መዋቅራዊ ቃለ-መጠይቆች እና በክፍል ምልከታዎች የተሰበሰቡት የጥናቱ መረጃዎች ይዘታዊ ትንታኔን (deductive thematic analysis) በመጠቀም ተንትነዋል። በመጠይቁ ውስጥ የተገኘው የቁጥር መረጃ የተተነተነው በመረጃ ትንተና ጊዜ ያለውን የቅርብ ጊዜውን የSPPS (ስሪት 20) በመጠቀም ነው። ጥናቱ "ተግባቦታዊ"ን (communicative) በመረዳት ረገድ ካለው የተሳሳተ ግንዛቤ የመነጨ አራት ዋና ዋና የEFL መምህራንን አመለካከቶችን አጉልቶ ቢጠቁምም፣ የአብዛኛዎቹ

the term communicative, it revealed that the majority of the EFL instructors' conceptions of CLT were consistent with the CLT literature. To that effect, the study illuminated the EFL instructors' conceptions of grammar and CLT concerning the teacher's role, the learners' role, the types of teaching materials, the place for grammar in CLT as well as the methods of teaching grammar lessons and assessing the learners' performance in grammar lessons. Nevertheless, the classroom practices of the majority of the EFL instructors were inconsistent with their conceptions of CLT because they predominantly employed the lecture method to teach grammar lessons. The study also found various socio-cultural and economic variables practically affecting the application of CLT in teaching grammar lessons in private universities in Ethiopia. Consequently, the study identified teacher-related factors, student-related factors, institutional factors, curriculum-related factors, and system-related factors as the main difficulties of implementing CLT in teaching grammar lessons. The study recommends that measures that align policy with practice should be taken to ensure that the instructors' conceptions are realised in classroom situations, thereby minimising the discrepancies between their conceptions and their classroom practices.

**Keywords:** Communicative language teaching; conceptions; application; mixed-methods approach; deductive thematic analysis; phenomenographic approach; communicative competence; grammar; authentic materials; explicit grammar teaching; classroom practices; continuous.

የEFL መምህራን የCLT ፅንሰ-ሀሳቦች/አረዳዶች ከCLT ሥነ-ጽሑፍ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን አሳይቷል። በዚህም መሰረት፣ ጥናቱ የEFL መምህራን ከCLT ጋር በተያያዘ በሰዋስው ትምህርት ውስጥ የመምህሩን ሚና፣ የተማሪውን ሚና፣ የማስተማሪያ ቁሳቁስ ዓይነቶችን፣ በCLT ውስጥ የሰዋሰው ቦታን እንዲሁም የሰዋስው ምህርቶችን የማስተማር እና የመገምገም ዘዴዎችን እና በሰዋሰው ትምህርቶች ውስጥ የተማሪዎች አፈፃፀምን አሳይቷል። ቢሆንም፣ የአብዛኞቹ የEFL መምህራን የክፍል ልምምዶች ከCLT ፅንሰ-ሀሳቦቻቸው/አረዳዶቻቸው ጋር የሚቃረኑ ሆነዋል፤ ምክንያቱም በዋናነት የሰዋሰው ትምህርቶችን ለማስተማር የገለፃ ዘዴን (lecture method) ይጠቀሙ ነበር። ጥናቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ የግል ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሰዋሰውን ትምህርት በማስተማር ላይ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በተግባር ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ አረጋግጧል። ስለሆነም፣ ጥናቱ ከመምህራን ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣ ከተማሪዎች ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣ ተቋማዊ ሁኔታዎች፣ ከስርአተ ትምህርት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች እና ከትምህርት ስርዓት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች CLTን ተጠቅሞ የሰዋሰው ትምህርቶችን በማስተማር ጥረት ላይ ዋና ዋና ችግሮች እንደሆኑ ለይቷል። በመጨረሻም፣ ጥናቱ የመምህራኑ የCLT አረዳድ እና ትግበራ ክፍተቶችን ለመሙላት ፖሊሲዎች ከተግባር ጋር የሚያቀናጁ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይመክራል።

**ቁልፍ ቃላት:**- ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፣ ጽንሰ-ሐሳቦች/አረዳዶች፣ ትግበራ፣ ድብልቅ ዘዴዎች፣ ይዘታዊ ትንተና፣ phenomenographic ዘዴ፣ ተግባቦታዊ ብቃት፣ የሰዋሰው ህጎች ላይ የተመሰረተ/ያተኮረ የሰዋስው ትምህርት፣ የክፍል ውስጥ ልምምዶች፣ ቀጣይነት ያለው

# Practices and challenges in implementing alternative assessment in communicative English skills course: the case of three Ethiopian universities

Motuma Hirpassa Minda

## ABSTRACT

Prompted by increased concern about the quality of assessment, the present study investigated the practices and challenges in implementing an alternative assessment in a communicative English skills course at three Ethiopian universities. The study mainly focused on the components of an alternative assessment the instructors used, the reaction of the students towards the alternative assessment, alignment between the teaching objectives and assessment strategies, the challenges of alternative assessment implementation, and strategies to overcome the challenges in the course. To this end, 128 instructors and 230 students participated in the study based on the comprehensive and stratified sampling techniques respectively. Based on a pragmatism research philosophy, a mixed-method research approach was employed. In the view of convergent parallel mixed-method research design, both quantitative and qualitative data were obtained from both primary and secondary sources through a questionnaire, classroom observation and focused group discussions. Descriptive and inferential data analysis methods were employed to address the objectives of the study. Similarly, instructional and assessment document analysis was also made to determine the alignment between the instructional and assessment materials. The overall results of the study revealed that the instructors assessed 70% of the teaching module of the

# በመግባቢያ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ክህሎት ኮርስ አማራጭ ምዘና የመተግበር ልምምዶች እና ተግዳሮቶቻቸው፡ በሦስት የተመረጡ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የተደረገ ጥናት

በሞቱማ ሂርጳሳ ምንዳ

## አጠቃሎ

የምዘና ጥራት አሳሳቢነት በመጨመሩ የተነሳ፣ ይህ ጥናት የእንግሊዝኛ መግባቢያ ቋንቋ ክህሎት ኮርስ አማራጭ ምዘናን፣ በሦስት የተመረጡ የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲዎች ተግባራዊ ለማድረግ ያሉትን አሠራሮችና ተግዳሮቶች መርምሯል። ጥናቱ በዋናነት ያተኮረው መምህራን በተጠቀሙባቸው የአማራጭ ምዘና ክፍሎች፣ ተማሪዎች ለአማራጭ ምዘና የሚሰጡት ምላሽ፣ የማስተማር አላማዎች እና የምዘና ስልቶች አሰላለፍ፣ የአማራጭ ምዘና አተገባበር ተግዳሮቶች እና በትምህርቱ ውስጥ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ስልቶች ላይ ነው። ለዚህም፣ 128 መምህራን እና 230 ተማሪዎች እንደየቅደም ተከተላቸው ሁሉን አቀፍ እና የተዘረጉ የናሙና አወጣጥ ቴክኒኮችን መሰረት በማድረግ በጥናቱ ተሳትፈዋል። በገቢራዊ ምርምር ፍልስፍና ላይ በመመስረት፣ የተደባለቀ የምርምር ዘዴ ሥራ ላይ ውሏል። በተጣመረ ትይዩ የምርምር ንድፍ እይታ፣ መጠናዊ እና ጥራት ያለው መረጃ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ምንጮች በመጠይቅ፣ በክፍል ምልከታ እና በትኩረት የቡድን ውይይት የተገኙ ናቸው። የጥናቱን ዓላማዎች ለመፍታት ገላጭ እና ገላጭ

course using an instructor-based traditional assessment approach. Congruently, 90% of the students were also more enthusiastic to participate in traditional assessments than in alternative assessment methods. The alignment between the instructors' assessment items and the intended learning outcomes of the course was (c = 0.1291) very low where the mismatch between the objectives of the course and the assessment method is a function of the constraints of instructional materials and poor classroom conditions, wrong perceptions of instructors and students, the instructor- and student-related factors, the multifaceted objectives of the course, and the demanding nature of alternative assessment in descending order. The prescriptions for the cure also lie in the employment of constructive alignment strategies, bringing about improvements in education policy and curriculum development, instructors' education and training, instructional supply and in instructors' salaries and workloads.

**Keywords:** Alternative assessment; alignment strategies; challenge; communicative English skills course; implementation.

የመረጃ ትንተና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በተመሳሳይም የማስተማሪያ እና የግምገማ ሰነድ ትንተና በማስተማሪያ እና በግምገማ ቁሳቁሶች መካከል ያለውን አሰላለፍ ለመወሰን ተዘጋጅቷል። የጥናቱ አጠቃላይ ውጤት እንደሚያሳየው መምህራኑ 70% የትምህርቱን የማስተማሪያ ሞጁል አስተማሪን መሰረት ያደረጉ ባህላዊ ምዘና ዘዴዎችን በመጠቀም ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ 90% የሚሆኑት ተማሪዎች ከአማራጭ የምዘና ዘዴዎች ይልቅ፣ በባህላዊ ምዘና ለመሳተፍ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል። በአስተማሪዎቹ ግምገማ ዕቃዎች እና በትምህርቱ የታቀዱ የትምህርት ውጤቶች መካከል ያለው አሰላለፍ (c = 0.1291) በጣም ዝቅተኛ ሲሆን፣ የትምህርቱ ዓላማዎች እና የግምገማ ዘዴው አለመመጣጠን የመማሪያ ቁሳቁሶች ገደቦች እና ደካማ የክፍል ሁኔታዎች ናቸው። ስለ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች የተሳሳተ ግንዛቤ፣ አስተማሪ እና ከተማሪ ተያያዥ ምክንያቶች፣ የትምህርቱ ዘርፈ ብዙ ዓላማዎች እና የአማራጭ ምዘና አስፈላጊነት አረጋግጠዋል። በተጨማሪም፣ ገንቢ የአሰላለፍ ስልቶችን በመጠቀም፣ በትምህርት ፖሊሲ እና ስርዓተ-ትምህርት ልማት፣ የመምህራን ትምህርት እና ስልጠና፣ የትምህርት አቅርቦት እና የመምህራን ደመወዝ እና የስራ ጫና ላይ ማሻሻያዎችን እንደሚያመጣ ይታመናል።

**ቁልፍ** ቃላት፡- አማራጭ ግምገማ፣ የአሰላለፍ ስልቶች፣ ፈተና፣ የመግባቢያ የእንግሊዝኛ ችሎታ ኮርስ፣ ትግበራ።

# Department of History

Year of Graduation 2017

## The nexus between water supply infrastructure and socio-economic developments in Amhara region, Ethiopia, 1941-2005

Derb Tefera Tassew

### ABSTRACT

This thesis examines the historical introduction and spatial expansion of modern water supply infrastructure in the Amhara region across the three successive regimes: imperial, military, and EPRDF. It attempts to explore the institutional set-up of the three governments together with their policies and strategies. The study also aims to give an idea about the socio-economic changes registered because of improved access to safe water. Furthermore, it assesses the water consumption and conservation pattern of the society and the environmental impact of the water infrastructure development. Modern infrastructure development in Ethiopia traced its beginning back to the late 19th century. Safe drinking water supply had been one of those modern infrastructures introduced in Addis Ababa. Not long afterwards, it proliferated into the provinces. In the Amhara region, drinking water supply infrastructure construction began in the early 20th century. However, this thesis inquired whether there was a programmed water supply infrastructure development before the mid-1950s or not. The water supply work started gaining momentum and became a state programme in the late imperial period. However, it was affected by financial, technological

## በአማራ ክልል በውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት እና በማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እድገቶች መካከል ያለው ትሥሥር (1941-2005)

በደርብ ተፈራ ጣሰው

### አጠቃሎ

ይህ ጥናት በአማራ ክልል በሦስቱ ተከታታይ ሥርዓቶች ማለትም፣ በንጉሱ፣ በወታደራዊው እና በኢህአዴግ ዘመነ መንግስታት፣ የዘመናዊ የውኃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ታሪካዊ አጀማመርና እድገትን ይመረምራል። የሶስቱን መንግስታት ተቋማዊ አደረጃጀት፤ፖሊሲ እና ስትራቴጂም ለመመርመርም ይሞክራል። ጥናቱ በተሻሻለ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ምክንያት ስለተመዘገቡት ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ጭምር ሀሳብ ለመስጠት ያለመ ነው። ከዚህ ባለፈም የህብረተሰቡን የውሃ ፍጆታና ጥበቃ አሰራርን እና የውሃ መሠረተ ልማት ዝርጋታ አካባቢያዊ ተፅእኖን ይገመግማል። ዘመናዊ የመሰረተ ልማት ግንባታ በኢትዮጵያ ስረ-መሰረቱን ወደ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ይስባል። የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተዋወቁት ዘመናዊ መሠረተ ልማቶች መካከል አንዱ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ወደ ክፍለ ሃገሮች ተስፋፍቷል። በአማራ ክልል የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ግንባታ የተጀመረው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው። ነገር ግን ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከ1950ዎቹ አጋማሽ በፊት በፕሮግራም የተያዘ የውኃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ዝርጋታ መኖሩን ወይም አለመኖሩን ጠይቋል። የውኃ አቅርቦት ሥራው መፋጠን የጀመረውና የመንግሥት ትልቁ ፕሮግራም የሆነው በንጉሠ ነገሥቱ መገባደጃ ዘመን ላይ ነበር ። ነገር ግን ዘርፉ በገንዘብ፣ በቴክኖሎጂ እና በሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት ፣ ተገቢ ተቋም በአለመኖሩ፣ ጉድለት ያለበት የአመራር ስርዓት እና ተገቢ ባልሆኑ የአተገባበር

and trained human resource constraints, lack of appropriate institutions, defective management systems, and improper implementation methods. The military government had strengthened water supply institutions and improved workers' expertise. These developments helped the water supply infrastructure work to be executed in a programmed manner. Yet, financial restraints, the incessant political chaos of the time and the accompanied disruptive working environment had greatly impacted the temporal and spatial coverage of the water supply infrastructure development. The promising start of the Derg period did not continue with a similar pace during the early years of the EPRDF rule. Despite the efforts made to set up water institutions at regional, zonal and Woreda (district) levels, no significant achievement was recorded in the field. The aftermath of the civil war together with internal and external challenges epitomised the transition period had impinged on the water supply work. This thesis testifies to the emergence of some socio-economic changes in the region. Yet, the slow progress of the water supply infrastructure work had stalled the socio-economic change that should have been registered through improved access to safe water supply. Despite the observable environmental degradation, the thesis argues that the retarded water supply work had nothing to do with the dearth of fresh water. While the trend shows steady growth of water consumption level across the three regimes, the conservation habit of the population remained low.

**Keywords:** Ethiopia; Amhara Region; imperial regime; infrastructure; rural water supply; socio-economic development; urban water supply; the military regime; water conservation and consumption pattern; the EPRDF regime; accessibility; inaccessibility; environmental impact.

ስልት ምክንያቶች ተጎጂ ሆኗል። የወታደራዊው መንግስት የውሃ አቅርቦት ተቋማትን አጠናክሯል፤ የሠራተኞችን ሙያዊ ችሎታ አሻሽሏል። እነዚህ እድገቶች የውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ሥራዉ በፕሮግራም እንዲከናወን አግዘዋል። ሆኖም የፋይናንስ ውስንነቶች፣ በጊዜው የነበረው የማያባራ የፖለቲካ ትርምስ እና ምቹ ያልሆነ የስራ አካባቢ በውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ዝርጋታ የጊዜ አፈፃፀም እና የቦታ ሽፋን ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድረዋል። ተስፋ ሰጭው የደርግ ዘመን ጅምር ስራዎች በኢህአዴግ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በተመሳሳይ ፍጥነት አልቀጠሉም። የውሃ ተቋማትን በክልል፣ በዞንና በወረዳ ለማቋቋም ጥረት ቢደረግም፤ በዘርፉ እዚህ ግባ የሚባል ስኬት አልተመዘገበም። የሽግግር ጊዜው መገለጫ የሆኑት ከእርስ በርስ ጦርነቱ በኋላ ያሉ ትርምሶችና የውስጥ እና የውጪ ችግሮች ፤ የውሃ አቅርቦት ስራዉ ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል። ይህ ጥናት በክልሉ ጥቂት የማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጦች መከሰታቸውን ይመሰክራል። ሆኖም የውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ሥራው አዝጋሚ በመሆኑ በተሻሻለ የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ዕውን መሆን ሊመጣ የሚችል የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ለውጥ እንዲገታ አድርጓል። የሚታየው የአካባቢ መራቆት እንዳለሆኖ፣ የተጓተተው የውኃ አቅርቦት ሥራ ከንጹሕ ውኃ እጥረት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለው ጥናቱ የመከራከሪያ ነጥቡን ያነሳል። የውሃ ፍጆታ ደረጃ በሦስቱም የአገዛዞች ዘመናት የማያቋርጥ እድገት ሲያሳይ፤ የህዝቡ ቁጠባ ልማድ ግን ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል።

**ቁልፍ** ቃላት: ኢትዮጵያ; የአማራ ክልል፤ ኢምፔሪያል አገዛዝ; መሠረተ ልማት; የገጠር ውሃ አቅርቦት; ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እድገት; የከተማ የውሃ አቅርቦት; ወታደራዊ አገዛዝ; ውሃ የጥበቃ እና የፍጆታ ንድ፤; የኢህአዴግ አገዛዝ፤ ተደራሽነት፤ ተደራሽ አለመሆን፤ የአካባቢ ተጽዕኖ፡

# Department of Development Studies

Year of Graduation 2019

## The impact of microfinance in the development of micro and small enterprise owned by women in Addis Ababa, Ethiopia

Amarech Bekalo Sapa

### ABSTRACT

Poor people benefit from microfinance and positively improve their poverty and socio-economic conditions. Microfinance support serves as a development tool to redress the exclusion of the poor from the development process and outcomes in the mainstream intervention frameworks. As developing countries and poverty contexts are diverse and contextual, comprehensive knowledge about and empirical evidence on the impact of microfinance is scant. Specifically, the impact of microfinance services on the development of micro and small enterprises (MSEs) owned by women is scant. The findings of available studies and policy practice reports on microfinance in Ethiopia are not holistic in terms of a theoretical lens and methodological pluralism. Available studies do not consider the impact of microfinance and non-financial services on women-owned MSEs at household, individual and enterprise levels thereby reducing the poverty context and holistic empowerment at these levels. This study used multiple theoretical and conceptual frameworks: Hulme's (2000, p. 79 - 81) microfinance impact assessment tool, debates on survivalist and growth-orientation perspectives of MSEs (Harvie, 2003, p. 27; Snodgrass & Biggs, 1996, p. 43; Hallberg, 2001, p. 19; Nichter & Goldmark,

## አነስተኛ የብድር ተቋማት በሴቶች በተያዙ በጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ልማት ላይ ያለው ተጽእኖ፡ በአዲስ አበባ የተደረገ ጥናት፤

በአማረች በቃሎ ሳፓ

### አጠቃሎ

አነስተኛ የብድር ተቋማት የሰዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን በአዎንታዊ መልኩ ያሻሽላሉ። የአነስተኛ የብድር ተቋም ድጋፍ ድሆች ከልማት ሂደት እንዳይገለሉ እና በዋና ዋና ጣልቃ ገብነት ማዕቀፎች ውስጥ ያሉትን ውጤቶች ለማስተካከል እንደልማት መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል። በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት እና የድህነት ሁኔታዎች የተለያዩ አውድ በመሆናቸው፣ ስለ አነስተኛ የብድር ተቋም ተፅእኖ ያለው አጠቃላይ እውቀት እና ተጨባጭ ማስረጃዎች ጥቂት ናቸው። በተለይም የአነስተኛ ብድር ተቋም አገልግሎቶች በሴቶች በባለቤትነት በሚመሩ ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ልማት ላይ ያለው ተፅዕኖ አነስተኛ ነው። የማይክሮ ፋይናንስን በተመለከተ በኢትዮጵያ የሚገኙ ጥናቶች፣ ግኝቶች እና የፖሊሲ ሪፖርቶች ከንድፈ ሃሳባዊ ዕይታ እና ከስልታዊ ብዝሃነት አንፃር ሁለንተናዊ አይደሉም። የተገኙትም ጥናቶች የማይክሮፋይናንስ እና ገንዘብ ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች በሴቶች ባለቤትነት በተያዙ በመከከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች በቤተሰብ፣ በግለሰብ እና በድርጅት ደረጃ ያላቸውን ተጽእኖ ከግምት ውስጥ አያስገባም። በዚህም ምክንያት የድህነትን አውድ እና አጠቃላይ አቅምን በእነዚህ ደረጃዎች ይቀንሳል። ይህ ጥናት በርካታ የንድፈሃሳባዊ እና የፅንሰ-ሃሳባዊ ማዕቀፎችን ተጠቅሟል። ለምሳሌ፣ ያህል የሁልሜ (2000፣ ገጽ 79 - 81) የማይክሮ ፋይናንስ ተፅእኖ ግምገማ መሳሪያ፣ የመካከለኛ ደረጃ ኢንተርፕራይዞች የመኖር እና የእድገት ተኮር አመለካከቶች (ሀርቬይ፣ 2003: ገፅ 27፣ ሲኖገራስ እና ቢግስ፣ 1996 ገፅ 43፣ ሃልበርግ፣

2005, p. 67), the women empowerment continuum model of interpretation (Filmon, 2009, p. 87) and policy practice at the epicentre of governance and policy decision-making (Addis Ababa, Ethiopia's capital). The assessment considered three elements of microfinance impact assessment, generating primary evidence from 120 micro and small business owners (women entrepreneurs) whose firms stayed two years and above in the market and as clients of selected microfinance institutions. The clients considered were those who accessed at least two loan cycles and above. The respondents were randomly selected from three randomly selected microfinance institutions and a survey questionnaire was administered. The datasets were analysed using multiple tests (non-parametric statistical tests such as Pearson Correlation, Paired-Sample, Chi-Square, Wilcoxon Rank and McNemar tests) as well as parametric tests which were conducted using the logit econometric model. These tests were conducted to determine statistical difference of microfinance services after programme intervention and the contribution of total loans taken on expenditure and businesses' investment. The results indicated both developmental or survivalist firms. The result also indicated the empowerment of the women (MSEs owners). A significant number of women entrepreneurs owning MSEs improved their living house, cash savings, household income, child education, household health, household food and diet, business investment, and decision-making status in their households. In terms of policy support, the study identified that there were specific affirmative interventions (as stipulated in the policy documents) to support women entrepreneurs owning MSEs in terms of targeted financial services, provision of working and selling premises,

2001፣ ገጽ 19፣ ኒቾተር እና ጎልድማርክ፣ 2005፣ ገጽ 67) ትርጉምሴቶችን ማብቃት ቀጣይነት ያለው የአተረጓጎም ሞዴል (ፊልሞን፣ 2009፣ገጽ 87)፣ የፖሊሲ አሠራር በአስተዳደራዊ እና የፖሊሲ ውሳኔ አሰጣጥ ማዕከል (አዲስአበባ፣ኢትዮጵያ) የተጠቀመባቸው ምንጮች ናቸው፡፡ ምዘናው ሶስት የጥቃቅንና ፋይናንስን ተፅእኖ ምዘና ገምግሟል። ይህም ከ120 የጥቃቅንና አነስተኛ ነጋዴዎች ባለቤቶች (ሴት ስራ ፈጣሪዎች)፣ ድርጅታቸው ለሁለት አመትና ከዚያም በላይ በገበያ ላይ የቆዩ እና በተመረጡ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ደንበኞች የመጀመሪያ ደረጃ ማስረጃዎችን በማሰባሰብ ነው። ከግምት ውስጥ የገቡት ደንበኞች ቢያንስ ሁለት ዙር ብድር እና ከዚያ በላይ ማግኘት የቻሉ ናቸው። ምላሽ ሰጪዎቹ እንዳመቺነቱ ከተመረጡት ሶስት የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ተመርጠው የዳሰሳ ጥናት ተካሄዷል። የመረጃ ስብስቦቹ በርካታ ሙከራዎችን በመጠቀም ተተንትነዋል፡፡ (እንደ ፒርሰን የተዛምዶ መለኪያ፣ ጥንድ ናሙና ፣ ቺ ሻየር፣ የዊልኮክሰን የደረጃ ልኬት እና እንደ ኤም ሲ ኒማር ቴስት ያሉ የልኬት ሙከራ የመሳሰሉት የአሀዛዊ መረጃ ሙከራዎች)፣ እንዲሁም የፓራ ሜትሪክ ሙከራዎች ኢኮኖሚ ሞዴል ተካሂደዋል፡ ፡ እነዚህ ሙከራዎች የተካሄዱት ከፕሮግራም ጣልቃ ገብነት በኋላ የማይክሮ ፋይናንስ አገልግሎቶችን የአሀዛዊ መረጃ ልዩነት እና ለወጪ እና ለንግድ ሥራ ኢንቨስትመንት የተወሰዱ አጠቃላይ ብድሮች አስተዋፅ ለማየት ነው፡፡ የጥናቱ ውጤቶች ሁለቱንም የእድገት ወይም ከኪሳራ የተረፉ ኩባንያዎችን ያመለክታሉ። የጥናት ውጤቱም የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ድርጅት ባለበት ሴቶችን ማብቃት አስፈላጊ መሆኑን አመልክቷል። በዚህ ጥናት ጥቃቅንና አነስተኛ ደረጃ የንግድ ድርጅት ባለቤት የሆኑ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች የመኖሪያ ቤታቸውን፣ የገንዘብ ቁጠባን፣ የቤተሰብ ገቢን፣ የልጆች ትምህርትን፣ የቤተሰብ ጤናን፣ የቤተሰብ ምግብ እና አመጋገብን፣ የንግድ ኢንቨስትመንትን እና በቤተሰባቸው ውስጥ የመወሰን ደረጃን አሻሽለዋል። የፖሊሲ ድጋፍን በተመለከተ በጥናቱ ጥቃቅንና አነስተኛ ደረጃ የንግድ ድርጅት ባለቤት ለሆኑ ሴት ሥራ ፈጣሪዎች ኢላማ ያደረገ የፋይናንስ አቅርቦት፣ የመስሪያና የመሸጫ ቦታ አቅርቦት፣ የሥልጠናና የክህሎት ልማትን በመንደፍና በመተግበር ረገድ

designing and implementing training and skill development programmes, market networking and tax support on their products and sales. The study recommends that different institutions that work on women empowerment and women associations have to design women- focused affirmative policy and strategy interventions to scale-up the positive results (growth-orientation of the MSEs) and address the bottlenecks that limit women entrepreneurs who own MSEs from accessing services that can transform the survivalist MSEs to profitable and empowering businesses for women. The recommendations are proposed to link women empowerment with working policy support.

**Keywords:** Microfinance; business development services; MSEs, women owners; survivalist and growth-oriented firms; Addis Ababa.

ልዩ ዕርምጃዎች መውሰድ እንዳለባቸው ጥናቱ ጠቁሟል። ሴቶችን በማብቃት ስራ ላይ የተሰማሩ የተለያዩ ተቋማት እና የሴቶች ማህበራት በሴቶች ላይ ትኩረት ያደረገ አዎንታዊ ፖሊሲና ስልት በመንደፍ አዎንታዊ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደምያስፈልግና (በጥቃቅንና አነስተኛ ደረጃ ያሉ የሴቶች የንግድ ድርጅቶች ልማትና ዕድገት ላይ ያተኮረ ማለት ነው) እና ጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች ባለቤት የሆኑ ሴት ሥራ ፈጣሪዎችን የሚገድቡትን ማነቆዎች መቅረፍ እንዳለባቸው ጥናቱ ይመክራል። በተጨማሪም በገበያው ላይ ያሉትን ጥቃቅንና አነስተኛ የሴት የንግድ ተቋማትን ትርፋማ ለማድረግና እና የሴቶችን አቅም መጎልበት የምያስችሉ የክህሎት ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው ጥናቱ ይጠቁማል። ስለዚህ በጥናቱ የቀረቡት ምክሮች በተለያዩ ተቋማት ሴቶችን ለማብቃት የምሰሩ ስራዎች የፖሊሲ ድጋፍ እንደምያስፈልገው ተመላክቷል።

**ቁልፍ ቃላት:** ማይክሮ ፋይናንስ; ንግድ የልማት አገልግሎቶች፤ መካከለኛ እና አነስተኛ ድርጅት፣ የሴቶች ባለቤቶች; እድገት-ተኮር ድርጅቶች; አዲስ አበባ።

## Year of Graduation 2020

# Coping mechanisms of food insecure households in urban Ethiopia

Tilahun Girma Argaw

## Abstract

With an increasing rate of urbanisation in East Africa, and with the highest prevalence rate of undernourished population than any region in the developing world, the issue of food access insecurity in urban areas has received considerable attention. While there are noticeable differences between big, medium- and small-sized towns, the variation in the household's response to food access insecurity across urban

# በኢትዮጵያ ከተሞች የምግብ ዋስትና የሌላቸው ቤተሰቦች የምግብ አቅርቦት እጦት መቋቋሚያ ዘዴዎች

በጥላሁን ግርማ አርጋው

## አጠቃሎ

በምስራቅ አፍሪካ የከተሞች መስፋፋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ እና በማደግ ላይ ካሉ አገሮች ውስጥ ከየትኛውም አካባቢ በበለጠ የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ያለባቸው ሰዎች ቁጥር እየጨመረ በመምጣቱ በከተሞች የምግብ አቅርቦት እጦት ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት አግኝቷል። በትልልቅ፣ መካከለኛ እና አነስተኛ ከተሞች መካከል የሚስተዋሉ ልዩነቶች ቢኖሩም፣

hierarchies remains largely unexplored. This study aimed to investigate the social, economic and demographic factors in coping with food access insecurity among households in urban slum areas of Ethiopia.

The study used both secondary and primary data sources. The national surveys of household consumption and expenditure survey and welfare monitoring surveys of 2004/5, 2010/11, and 2015/16 was used to analyse the food security situation in Ethiopia across time and urban hierarchies. Primary data of 500 households and three focus group discussions were conducted from slum areas of Addis Ababa, Hawassa, and Sheki representing a big city, medium- and small-sized town, respectively. The household survey data were subjected to descriptive statistical analysis and a standard regression model to investigate the relationship between factors such as household structure and composition, economic resources, social protection programmes and projects, and urban-rural linkages with coping with food access insecurity across urban hierarchies. A global model and three site-specific regression models were constructed.

Descriptive results from both the primary and the secondary data sources have revealed that the proportion of the households affected by food shortage varies across the urban hierarchy that food insecurity was highest in the small-sized town as compared with the medium-sized town and the big city. The quality of food consumed was consistently low among female-headed households regardless of their socio-economic characteristics when compared with male-headed households. The result of the regression analysis for the global model has shown that economic resources (asset and source of income) predict nearly half of the variability in coping with food access insecurity. Household structure and composition such

በከተሞች ውስጥ ባሉ ተዋረዶች ውስጥ ለምግብ አቅርቦት እጦት ቤተሰቡ የሚሰጠው ምላሽ ልዩነት አሁንም ገና በበቂ ሁኔታ አልተጠናም። ይህ ጥናት በኢትዮጵያ በከተሞች ባሉ ጎስቋላ መንደሮች ውስጥ በሚገኙ አባወራዎች የምግብ አቅርቦት እጦትን ለመቋቋም የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ሕዝብ ጉዳዮችን ለመመርመር ያለመ ነው።

ጥናቱ የሁለተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል. በ2004/5፣2010/2011 እና በ2015/16 የተካሄዱት የቤተሰብ ፍጆታና ወጪ የዳሰሳ ጥናት እና የማህበራዊ ደህንነት ዳሰሳ ጥናቶች በኢትዮጵያ ያለውን የምግብ ዋስትና ሁኔታ በጊዜ እና በከተማ ደረጃ ለመተንተን ውለዋል። የ500 አባወራዎች የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ እና የሶስት የቡድን ውይይት የተካሄደው ትልቅ ከተማን፣ መካከለኛ እና አነስተኛ ከተማን በወከሉት ከአዲስ አበባ፣ ሀዋሳ እና ሸኪ ከተማ እንደቅደም ተከተላቸው ነው። የቤተሰብ ዳሰሳ መረጃው እንደ ቤተሰብ አወቃቀር እና ስብጥር፣ የኢኮኖሚ ሀብቶች፣ የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች እና የከተማ-ገጠር ትስስሮች በከተሞች የምግብ ተደራሽነት እጦትን ለመቋቋም በመሳሰሉት ሁኔታዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመመርመር ገላጭ ስታቲስቲካዊ ትንታኔ ተደርጓል። አንድ ጥቅል ሞዴል እና ሶስት ቦታ-ተኮር የሪግሬሽን ሞዴሎች ተዘጋጅተዋል።

ከዋና እና የሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች የተገኘው ገላጭ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በምግብ እጦት የተጎዱ አባወራዎች ቁጥር በከተማ ተዋረድ የተለያየ ሲሆን በአነስተኛ ከተማ ያለው የምግብ ዋስትና እጦት ከመካከለኛው ከተማ እና ከትልቁ ከተማ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ነበር ። በማናቸውም የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ ቢገኙም ቤተሰቦች የሚመገቡት ምግብ ጥራት በሴቶች በሚመሩ ቤተሰቦች ዘንድ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል። የጥቅል ሞዴል የሪግሬሽን ትንተና ውጤት እንደሚያሳየው የኢኮኖሚ ሀብቶች (ንብረት እና የገቢ ምንጭ) የምግብ አቅርቦትን እጦት ለመቋቋም ያለውን ሁኔታ ግማሽ ያህሉን ይወስናል። የቤተሰብ መዋቅር እና ስብጥር እንደ ጾታ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ ትምህርት ደረጃ፣ የቤተሰብ መዋቅር እና በቤተሰብ ውስጥ ያሉ የህጻናት ልጆች ጥምርታ የመቋቋሚያውን ሁኔታ ሩቡን ያህል ይሸፍናል። የማህበራዊ ጥበቃ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች አንድ አስረኛውን

as gender and education of the head of the household, family structure (nuclear/ extended), and the ratio of young children in the household predict a quarter of the variability in coping. Social protection programs and services predict one-tenth; the remaining variability in coping is explained by the combined effect of all the factors involved.

The significance of these factors in predicting coping with food access insecurity, however, varies across the urban hierarchies. The contribution of economic factors in predicting coping is the highest at the big city (Addis Ababa); household structure and composition took the leading role in predicting coping at the small-sized town (Sheki); the significant factors in predicting coping at the medium sized town (Hawassa) was the combined effect of all the factors involved. Household characteristics such as female headship, a higher ratio of young children, low education of the household head, lack of access to the financial loan, asset and income poverty, and weak linkages with kin structure at rural areas increase vulnerability to food insecurity and put households under stress to cope with food access insecurity.

The study results show that the traditional urban-rural dichotomy may not suffice to portray the degree of food insecurity, as well as the mechanisms how food insecure households strive to cope with food access insecurity, which varies across the continuum of urban hierarchies. Those who wish to support food insecurity challenges need to be sensitive to the variability of factors in coping with food access insecurity across urban hierarchies. During policy, design and program implementation policymakers and international partners need to consider that the needs and coping mechanisms of urban households vary across urban hierarchies besides the

ያህል ድርሻ አላቸው። በመቋቋሚያ ላይ ያለው የቀረው ሁኔታ የሚገለፀው በተካተቱት ሁሉም ምክንያቶች ጥምር ውጤት ነው።

የምግብ አቅርቦት እጦትን ለመቋቋም የእነዚህ ምክንያቶች ጠቀሜታ በሁሉም የከተማ ተዋረድ ይለያያል። መቋቋምን በመተንበይ ረገድ የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች አስተዋፅዖ በትልቁ ከተማ (አዲስ አበባ) ከፍተኛ ነው፤ በትንሽ ከተማ (ሸኪ) ውስጥ መቋቋምን በመወሰን ረገድ የቤተሰብ መዋቅር እና ስብጥር የመሪነት ሚና አለው። በመካከለኛው ከተማ (ሐዋሳ) ያለውን ሁኔታ ለመቋቋም የሚረዱት ዋና ዋና ምክንያቶች የተካተቱት የሁሉም ምክንያቶች ጥምር ውጤት ነው። የቤተሰብ ባህሪያት እንደ ሴት የቤተሰብ ሀላፊነት፣ የትናንሽ ሕፃናት ከፍተኛ ጥምርታ፣ የቤተሰብ ሀላፊ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ፣ የፋይናንስ ብድር እጥረት፣ የንብረት እና የገቢ ድህነት፣ እና ገጠር ከሚኖሩ ዘመድ አዝማድ ጋር ያለው ግንኙነት ደካማ መሆን ለምግብ እጦት ተጋላጭነትን ይጨምራል፤ ቤተሰቦችንም በከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።

የጥናቱ ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት ተለምዷዊው የከተማ እና የገጠር ክፍፍል የምግብ ዋስትና እጦት ደረጃን ለማሳየት በቂ አለመሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። እንዲሁም በቂ የምግብ ዋስትና የሌላቸው ቤተሰቦች የምግብ አቅርቦት ሁኔታ እና ይህን ችግር ለመቋቋም የሚረዷቸው ምክንያቶች በከተማ ተዋረድ የተለያዩ መሆናቸውን ጥናቱ አመላክቷል። በመሆኑም የምግብ ዋስትና ችግርን ለመደገፍ የሚፈልጉ አካላት በከተማ ተዋረድ ያሉ የምግብ ተደራሽነት እጥረቶችን ለመቋቋም የሚያግዙ ሁኔታዎች የተለያዩ መሆናቸውን ልብ ሊሉ ይገባል። የፖሊሲ ንድፍ አውጪዎች እና የፕሮግራም ትግበራ አለምአቀፍ አጋሮች የከተማ ቤተሰቦች ፍላጎቶች እና የመቋቋሚያ ዘዴዎች ከሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ-ሕዝብ ተለዋዋጮች በተጨማሪ በከተማ ተዋረድ እንደሚለያዩ ሊገነዘቡ እንደሚገባ የጥናቱ ውጤት ይመክራል።

**ቁልፍ ቃላት:** የምግብ ዋስትና ማጣት፥ መቋቋም፥ ምርታማ ሴፍቲኔት፥ ከተሜነት፥ የከተማ ተዋረድ፥ የከተማ-ገጠር ትስስር፥ የቤተሰብ ስብጥር፥ ማህበራዊ ደህንነት፥ የኢኮኖሚ ምንጭ፥ የካሎሪ ቅበላ፥ የምግብ ፍጆታ

other social, economic and demographic variables.

**Keywords:** food insecurity, coping, productive safety net, urbanisation, urban hierarchy, urban-rural linkage, household composition, social protection, economic resource, calorie intake, food consumption.

## Challenges of development in modern Ethiopia: history, trajectories and implications

Yerasework Kebede Hailu

### ABSTRACT

Ethiopia has a long history of pushing for modernisation and development. The modernisation drive was aimed at transforming Ethiopia from a feudal 'traditional' society to a 'modern' society. What is unique about Ethiopia is that it survived direct colonisation because the Ethiopian forces defeated the invading colonial Italian army at the Battle of Adowa in 1896. This means that Ethiopia has been in charge of its development trajectory, compared to other African societies that languished under direct colonial administration, albeit within a world dominated by Euro-North American-centric modernity. Ironically, Ethiopia just like other African states, is still struggling with challenges of development. This thesis is a deeply historical analysis of the challenges of development in modern Ethiopia. Its focus is on the history and the trajectory of development initiatives and implications. Theoretically, the thesis is predicated on a decolonial epistemic perspective, that is accompanied by the colonial matrix of power, knowledge and being, as its units of analysis. The findings indicate that even though Ethiopia survived direct

## በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የዕድገት ተግዳሮቶች፡ ታሪክ፣ ሂድቶች እና አንድምታዎች

በየራሴወርቅ ከበደ ሃይሉ

### አጠቃሎ

ኢትዮጵያ ለዘመናዊነት እና ለልማት ጥርት በማደረግ የረጅም ጊዜ ታሪክ አላት። የዘመናዊነተ ፍላጎት ኢትዮጵያን ከፊውዳል 'ባህላዊ' ማኅበረሰብ ወደ 'ዘመናዊ' ማኅበረሰብ ለመቀየር ያለመ ጉዞ ነው። ኢትዮጵያን ልዩ የሚያደርጋት በ1896 (እ.ኤ.አ.) በአድዋ ጦርነት ላይ የኢትዮጵያ ጦር የወራሪውን የጣሊያን ጦር በማሸነፍ ከቅኝ ግዛት ያመለጠች መሆኗ ነው። ይህ የሆነው ዩሮ-ሰሜን አሜሪካን ማዕከል ባደረገው ዘመናዊነት ተጽእኖ ሰር ባለ ዓለም ውስጥ ቢሆንም፣ በቀጥታ ቅኝ አገዛዝ ሥር ከነበሩት ሌሎች የአፍሪካ ማኅበረሰቦች ጋር ሲነፃፀር ኢትዮጵያ የራሷን የዕድገት ጉዞ ስትመራ ቆይታለች። የሚገርመው ግን ኢትዮጵያ እንደሌሎቹ የአፍሪካ ሀገራት አሁንም በልማት ፈተናዎች እየታገለች ነው። ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የዕድገት ተግዳሮቶችን የሚያሳይ ጥልቅ ታሪካዊ ትንታኔ ነው። ጥናቱ ትኩርት ያደረገው በታሪክ፣ በልማት ሂደቶች እና አንድምታዎች ላይ ነው። በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ጥናቱ ከ "ዲኮሎኒያል ኢፒስቴሚክ" እይታ የተተነበየ ሲሆን፣ የትንታኔ ክፍሎቹም በቅኝ አገዛዘ የኃይል፣ የእውቀት እና በመሆን ላይ የተመሰረተ ነው። ግኝቶቹ እንደሚያሳዩት ምንም እንኳን ኢትዮጵያ በ1896 (እ.ኤ.አ.) ከቀጥተኛ ወረራ ብትተርፍም የእውቀት ኢምፓየር በዘመናዊነት ስም ያሰክተተውን፣ የእድገት፣ የስልጣኔ፣ የልማት ጦር እና የነጻነት ወረራዎችን በማስወገድ ረገድ አልተሳካላትም። ስለዚህም ልክ እንደሌሎች

physical conquest in 1896 (the physical empire), it did not succeed in avoiding the invasion by the cognitive empire with its modernist tropes of progress, civilisation, development and emancipation. Thus, just like other African states, Ethiopia became enchanted by modernity's rhetoric of salvation, civilisation, progress, development and emancipation, to the extent of embarking on a trajectory of self-colonisation. Methodologically, the thesis combined the use of a detailed literature review and interviews with experts, complemented by context analyses and the use of relevant official documents. The key recommendation of the thesis is that of a 'decolonial turn' which entails epistemic freedom as the key to an autonomous development trajectory, not only for Ethiopia, but also for the rest of the dependent countries of the Global South.

**Keywords:** Modernization; modernity; development; colonialism; coloniality; decoloniality; decolonisation.

የአፍሪካ ሀገራት፣ ኢትዮጵያ የዘመናዊነትን የመዳን ፣ የስልጣኔ፣ የእድገት፣ የልማት እና የነጻነት ንግግሮችን እያዜመች፣ራስን በራሰ በቅኝ የመግዛት (self-colonization) ሂድት ውስጥ ገባች። ጥናታዊ ጽሑፉ የተከተለው ዘዴ በዐውደ-ጽሑፉ ትንታኔዎች የተሟሉ እና አግባብነት ያላቸውን ኦፊሴላዊ ሰነዶችን በመጠቀም ዝርዝር የስነ-ጽሑፍ ግምገማን እና ከባለሙያዎች ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ በማካተት ነው። የጥናቱ ቁልፍ ምክረ ሃሳብ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለተቀሩት የግሎባል ደቡብ ጥገኛ አገሮችም ከቅኝ ግዛት የተላቀቀ '*decolonial turn*' ፣የእውቀት ነፃነትን ዋና ያደርገ ራስ ገዝ የዕድገት ሂደቶችን መከትል ነው።

**ቁልፍ ቃላት፡** ዘመናዊነት ፣ ልማት ፣ ቅኝ አገዛዝ ፣ ከቅኝ ግዛት ነጻ ማድረግ

## Year of Graduation 2023

# Public housing policy and the housing needs of residents in informal settlements in Ethiopia: the case of Addis Ababa

Demeke Haile Abshir

## ABSTRACT

The research, entitled "Public housing policy and the housing needs of residents in informal settlements in Ethiopia: The case of Addis Ababa", aims to examine how the socio-economic status of informal

# የመንግስት የቤት ፖሊሲና የኢመደበኛ ሰፋሪዎች የቤት ፍላጎት በኢትዮጵያ፡ በአዲስ አበባ የተደረገ የናሙና ጥናት፤

በደመቀ ሀይሌ አብሽር

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት የመኖሪያ ቤት ፖሊሲው የኢመደበኛ ሰፋሪዎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ያገናዘቡ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚገነቡ የመንግስት መኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ላይ ያለውን ተግዳሮት ለመመርመር ያለመ ሲሆን፤ በአዲስ አበባ ውስጥ በተለይ በቦሌ እና የካ ክ/ከተሞች በሚገኙት ኢ-መደበኛ ሰፈራ ነዋሪዎች

settlers and housing policies affect the availability of affordable public housing for low-income households living in the Bole and Yeka informal settlements, located in Addis Ababa, Ethiopia. This research is based on significant theoretical concepts, such as "Housing by People"; "A Shack as a House in Process"; "Progressive Housing Development" by Turner, "Creating an Enabling Environment" by Mangin, and "Self-improvement" by Abrams, among others. The focal areas of the study—Bole and Yeka informal settlements— do not adhere to the city's spatial planning regulations, thus making them vulnerable to eviction by city officials. The study used a mixed-methods research design, incorporating both quantitative and qualitative methods. The research shows that despite its flaws and past failures, the traditional public housing development and provisioning approach remains prevalent in developing nations like Ethiopia. This study has shown that self-help housing through settlement upgrading may be a more effective solution for housing needs in informal settlements such as Bole and Yeka, than relying solely on conventional public housing models and policies. Yet, this study shows how the self-help housing effort without secured tenure in informal settlement areas, such as Bole and Yeka of Addis Ababa, Ethiopia, does not promote high satisfaction levels among the informal dwellers. The study findings also make it possible and appropriate for the researcher to critique Turner's concept of informal settlements as a "temporary solution" to the urban housing shortage. Key study recommendations include adopting settlement upgrading through self-help housing as an alternative to conventional public mass housing provision approaches and policy discourse. This unlocks the potential of urban informal settlers' self-help housing and adopts a proactive

ላይ የተደረገ ጥናት ነው። ጥናቱ በዘርፉ ጎልተው በሚታወቁት አለምአቀፍ ምሁራን ንድፈ ሃሳቦች ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ በተለይም የ ጆን ተርነርን "Housing by People", "A shack as a House in Process"; "Progressive housing development" እና የዊሊያም ማንጂንን "Creating Enabling Environment…" እንደዚሁም የ ቻርለስ አብራምስን "Self-Improvement" የተባሉ ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት አድርጓል። ጥናቱ ያተኮረባቸው በቦሌ እና በየካ የሚገኙት መደበኛ ያልሆኑ የሰፈራዎችን ሲሆን እነዚህ የሰፈራ አካባቢዎች ከከተማው የመሬት አጠቃቀም እቅድና ደንቦች ጋር የተጣጣሙ አለመሆናቸው ለመፈናቀል ተጋላጭ ያደርጋቸዋል። ጥናቱ ሁለቱንም መጠናዊ እና አይነታዊ ዘዴዎችን ያካተተ የድብልቅ- የምርምር ንድፍ ተጠቅሟል። የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው ልማዳዊው የመንግስት የቤቶች ልማት እና አቅርቦት ሂደት በግልጽ የሚታዩ ውድቀቶች እና ጉድለቶች ቢኖሩበትም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ታዳጊ ሀገራት አሁንም በስፋት በመተግበር ላይ ይገኛል። ይህ ጥናት እንደሚያመለክተው እንደ ቦሌ እና የካ በመሳሰሉት ኢመደበኛ ሰፈራዎች የሚገኙትን ነዋሪዎች የቤት ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት በተለመደው የመንግስት ሰፋፊ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ሞዴሎች እና ፖሊሲዎች ላይ ብቻ ከመተማመን ይልቅ እነዚህን ነባር ሰፈራዎች (ቤቶች) በራስ አገዝ የአሰራር ዘዴ ማሻሻሉ የበለጠ ውጤታማ መፍትሄ ይሆናል። ሆኖም፣ ጥናቱ በተጨማሪ እንደሚያሳየው በራስ አገዝ የሚከናወን የመኖሪያ ቤት ማሻሻል ስራ በይዞታ ዋስትና ማረጋገጫ ካልተደገፈ በስተቀር የነዋሪዎችን እርካታ ለማስገኘት አስተማማኝነት ይጎድለዋል ። ተርነር ኢመደበኛ ሰፈራዎችን ለከተማ የመኖሪያ ቤት እጥረት እንደ "ጊዜያዊ መፍትሄነት" ባቀረበው ጽንሰ-ሃሳብ ላይ ተመራማሪው በጥናቱ ግኝት ላይ ተመርኩዞ ትንታኔያዊ ትችት ለማቅረብ አስችሎታል። የጥናቱ ቁልፍ ምክረ-ሀሳቦች፡ በልማዳዊነት እንደአቅጣጫ ከተያዘው የመንግስት የሰፋፊ ቤቶች አቅርቦት እና የፖሊሲ ዲስኩሮች ይልቅ ራስ-አገዝ ተኮር የሆኑ የመኖሪያ ሰፈሮች ማሻሻልን እንደ የተሻለ አማራጭ ቆጥሮ መቀበልን እና መከተልን አካተዋል። ይህም የራስ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ማሻሻል አማራጭ እንደ አዲስ አበባ ባሉት ከተሞች የሚገኙ ኢ-መደበኛ ሰፋሪዎችን እምቅ

approach to deter the future development of new informal settlements in urban peripheral areas, such as Addis Ababa. The study recommends a broader model called 'supported self-help housing', to address the housing needs of low-income residents through a holistic, affordable and responsive provision manner, particularly in cities, like Addis Ababa. This model aims to contribute to the existing body of knowledge and further the development of theories on assisted self-help housing.

**Keywords:** Public housing policy; housing need; informal settlement residents; Ethiopia.

አቅም በመጠቀም የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመቅረፍ በር ይከፍታል፤ ጥናቱ የኢመደበኛ ሰፈራዎች በማሻሻል የቤት ፍላጎትን ስለማሟላት ካቀረበው ምክረ-ሀሳብ በተጨማሪ፣ ለወደፊቱ አዲስ አበባን በመሰሉ ከተሞች ውስጥ  አዳዲስ ተመሳሳይ ሰፈሮች  መፈጠርና መስፋፋትን ለመከላከልም ንቁ ስልታዊና ተከታታይነት ያለው የክትትልና የቁጥጥር ስርአት መከተል አስፈላጊ መሆኑን ይመክራል። እንደዚሁም፣ ጥናቱ በተለይ እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ውስጥ የሚታየውን ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን ነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት ፍላጎት በዘላቂነት በተመጣጣኝ የዋጋ አቅርቦት ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል ታስቦበት 'በመንግስት የሚደገፍ የራስ-አገዝ መኖሪያ ቤት ልማት' በሚል ስያሜ በጥናቱ የቀረበው ሁሉን-አቀፍ ሞዴል ተግባራዊ እንዲደረግ ይመክራል። ይህ ሞዴል  በ ራስ-አገዝ የመኖሪያ ቤት ዘርፍ ያለው ነባራዊ እውቀት አካል እና ወደፊትም በመስኩ አዳዲስ ንድፈ-ሃሳቦችን ለማርቀቅ እና የማዳበር ለሚደረጉ የምርምር ስራዎች  አስተዋፅኦ እንዲኖረው ይጠበቃል::

**ቁልፍ ቃላት፡**- የመንግስት የመኖሪያ ቤት ፖሊሲ፣ የመኖሪያ ቤት ፍላጎት፣ የኢ-መደበኛ ሰፈራ ነዋሪዎች፣ ኢትዮጵያ፤

## Climate change, adaptation and livelihood changes in the Lake Tana Basin: implications for food security and poverty

Naod Mekonnen Anega

### ABSTRACT

The main objective of the thesis is to examine the effect of climate change and adaptation on livelihood patterns and the concomitant implications for poverty and food security. The thesis uses a mixed-method research approach to address the study objectives. In this regard, the thesis applied various types of data collection techniques including a household survey,

## የአየር ንብረት ለውጥ፣ መላመድ እና የኑሮ ለውጥ ለምግብ ዋስትና እና ለድህነት ያላቸው አንድምታ፡ በጣና ሀይቅ ተፋሰስ ላይ የተደረገ ጥናት፤

በናኦድ መኮንን አነጋ

### አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ መላመድ እና የኑሮ ደረጃ፣ በድህነት እና በምግብ ዋስትና ላይ ያለውን ተፅእኖ መመርመር ነው። ለዚህም ጥናቱ ድብልቅ ዘዴን ይጠቀማል። ለዚህም  ጥናቱ በቅድሚያ የተለያዩ ቴክኒኮችን በመጠቀም መረጃ አሰባስቧል፡፡ እነዚህም ቴክኒኮች፣  የቤተሰብ ዳሰሳ፣ የትኩረት ቡድን ውይይት፣ ቁልፍ መረጃ ሰጪ ቃለ መጠይቅ፣

focus group discussions, key informant interviews, in-depth interviews and participatory scenario development workshops. The thesis reveals that there is a decline in rainfall and a rise in temperature in the Lake Tana Basin. In line with this, a time series analysis of the relationship between climate change variables and crop production showed that changes have occurred in the variables that have led to a reduction in crop production. In order to respond to these negative effects, community members have used various modern and traditional adaptation techniques. Climate change and adaptation strategies have both brought about changes in livelihood patterns in the Lake Tana Basin. Accordingly, the study has assessed the effect of changes in livelihood patterns on food security and poverty. The results show that the observed changes in livelihood patterns (caused by climate change and adaptation) have affected different components of poverty and food security. And with regard to the components of livelihood assets, the thesis shows that almost all of them are under climate threat but with different levels of vulnerability. Another finding is that the current adaptation strategies are not pro-poor. The result of a ranking exercise using local criteria shows that while afforestation, tree planning, shifting cultivation and modern irrigation ranked relatively at the top as pro-poor strategies, improved seeds and improved animal hybrids ranked lowest.

**Keywords:** Climatic changes; Tana Lake; sustainable living; food security; climatic changes; risk assessment.

ጥልቅ ቃለ-መጠይቅ እና አሳታፊ ሁኔታ ልማት አውደ ጥናቶች ናቸው። በጣና ሐይቅ ተፋሰስ ላይ የዝናብ መጠን መቀነስ እና የሙቀት መጠን መጨመር መኖሩን ጥናቱ ያሳያል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአየር ንብረት ለውጥ ተለዋዋጮች እና በሰብል ምርት መካከል ያለውን ግንኙነት አስመልክቶ በተደረገው ተከታታይ ትንተና፣ በሰብል ምርት መቀነስ ምክንያት፣ በተለዋዋጮች ላይ ለውጦች መከሰታቸውን ያሳያል። ለዚህ አሉታዊ ተጽእኖ ምላሽ ለመስጠት የህብረተሰቡ አባላት የተለያዩ ዘመናዊ እና ባህላዊ መላመድ ቴክኒኮችን ተጠቅመዋል። የአየር ንብረት ለውጥ እና መላመድ ስልቶች በጣና ሀይቅ ተፋሰስ የአኗኗር ዘይቤ ላይ ለውጥ አምጥተዋል። በዚህም መሰረት በጥናቱ የኑሮ ዘይቤ ለውጥ በምግብ ዋስትና እና በድህነት ላይ ያለውን ተጽእኖ ገምግሟል። ውጤቱ እንደሚያሳየው የኑሮ ለውጦች (በአየር ንብረት ለውጥ እና መላመድ) በተለያዩ የድህነት እና የምግብ ዋስትና አካላት ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል። የመተዳደሪያ ንብረቶችን አካላት በተመለከተ፣ (ሁሉም ማለት ይቻላል) በአየር ንብረት ስጋት ውስጥ እንዳሉ፣ ነገር ግን የተለያየ የተጋላጭነት ደረጃ ላይ መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል። ሌላው የጥናቱ ግኝት አሁን ያሉት የማስተካከያ ስልቶች ለድሆች ደጋፊ

አይደሉም። የአካባቢ መመዘኛዎችን በመጠቀም የደረጃ አሰጣጡ ውጤት እንደሚያሳየው የደን ልማት፣ የዛፍ እቅድ፣ የእርሻ ለውጥ እና ዘመናዊ መስኖ በአንፃራዊነት ከድህነት ተኮር ስትራቴጂዎች አንደኛ ደረጃ ላይ ሲቀመጥ፣ የተሻሻሉ ዘሮች እና የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን መጠቀም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

**ቁልፍ ቃላት:**- የአየር ንብረት ለውጦች፣ ጣና ሀይቅ፣ ዘላቂ ኑሮ፣ የምግብ ዋስትና፣ የአየር ንብረት ለውጦች፣ የአደጋ ግምገማ፤

# The contributions and challenges of civil society in development and governance in context of the post-1991 developmental state of Ethiopia

Zigiju Samuel Beyene


## ABSTRACT

The primary objective of this study was to analyse the contributions and challenges of civil society in governance and development and state-civil society relations in context of the post-1991 contemporary Ethiopia. To achieve this objective, a mixed-method approach was used where data from qualitative sources were embedded into the quantitative sources and analysed. To understand the role of civil society and state-civil society relations in the post-1991 period of Ethiopia, three periods were considered (i.e., 1991 to 2004; 2005 to 2017 and 2018 to date) due to the shift in the enabling environment of civil society over these periods. Factors such as external context and internal context were considered and analysed. The role of civil society in development and governance was analysed considering the three major operational areas of civil society (i.e., advocacy, services delivery, and watchdogging). State-civil society relations were also examined focusing on different parameters. The analysis was conducted by way of comparison based on the three periods using Friedman's Analysis of Variance. Both the external and internal contexts were found to be conducive and better during the first and third periods while they were not enabling during the second period. The role of civil society in service delivery was found to be similar and better in all the three periods,


# በኢትዮጵያ ድህረ 1991 ልማታዊ መንግስት ውስጥ ሲቪክ ማህበራት በልማት እና አስተዳደር ያበረከቱት አስተዋፅኦ እና የገጠማቸው ተግዳሮት

በዝግጁ ሳሙኤል በየነ


## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በድህረ-1991 ኢትዮጵያ በመንግስትና በሲቪክ ማህበራት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲሁም ሲቪክ ማህበራት በአገሪቱ አስተዳደርና ልማት ያበረከቱትን አስተዋፅኦ እና ተግዳሮት መተንተን ነው። ይህንን ዓላማ ለማሳካት ከጥራት ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ወደ መጠናዊ ምንጮች የተካተቱበት እና የሚተነተኑበት ድብልቅ የጥናት ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በድህረ 1991 የኢትዮጵያ ዘመን የሲቪክ ማህበረሰብ በአስተዳደርና ልማት ያላቸውን ሚና እንዲሁም በመንግስትና ሲቪክ ማህበራት መካከል ያለውን ግንኙነት ለመረዳት ሶስት ጊዜዎች (ማለትም ከ1991 እስከ 2004፣ 2005 እስከ 2017 እና ከ 2018 ወዲህ) የተወሰዱ ሲሆን ይህም በእነዚህ ሶስት ወቅቶች በአገሪቱ አስቻይ ሁኔታዎች ላይ በተፈጠሩ ለውጦች ምክኒያት ነው። በዚህ ጥናት ውስጥ የሲቪክ ማህበራት ውጫዊ አውድ እና ውስጣዊ ሁኔታዎችም ግምት ውስጥ ገብተው ተተንትነዋል። የሲቪክ ማህበራት በልማትና በአስተዳደር ያላቸውን ሚና ለመተንተን ሶስቱ ዋና ዋና የስራ መስኮቻቸው (ማለትም ተሟጋችነት፣ አገልግሎት አሰጣጥ እና ጠባቂነት) ግምት ውስጥ ገብተዋል። እንደዚሁም የመንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ግንኙነት በተለያዩ መለኪያዎች ላይ በማተኮር ተፈትሸዋል። ትንታኔው የተካሄደው በንፅፅር በሶስት ወቅቶች ላይ በመመስረት፣ የፍሪድማንና የቫሪየንስን የትንታኔ ዘዴ በመጠቀም ነው። በአንደኛው እና በሦስተኛው ክፍለ-ጊዜዎች ውስጥ ውጫዊ እና ውስጣዊ ሁኔታዎች ምቹ እና የተሻሉ ሆነው የተገኙ ሲሆን፣ በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ምቹ አልነበሩም። በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሲቪል ማህበራት ሚና በሦስቱም ጊዜያት ተመሳሳይ እና የተሻለ ሆኖ የተገኘ ቢሆንም የተሟጋችነት እና

but in terms of advocacy and watchdogging, it was better during the first and third periods while it was completely paralysed during the second period. Regarding state-civil society relations, the first period was characterised by cooperation between the state and civil society, but the relationship lacked the principles of engagement and formality. During the second period, the relationship was characterised by confrontation and even denial of a rights-based civil society. The third period was characterised by cooperation and a smooth relationship. Finally, regarding the non-formal institution, i.e., Iddir, it has been an essential institution that not only plays a complementary role to formal civil society but also contributes to development and governance in its own right. However, Iddir's potential contribution has been constrained by lack of attention and support from the government. Based on the findings of the study, recommendations are made to concerned actors including the government, the formal civil society organisations and the non-formal civil society - Iddir.

**Keywords:** Civil society; external context; internal context; advocacy; service delivery; watchdogging; Iddir; governance; development; Ethiopia; government; Addis Ababa.

የጠባቂነት ሚናቸው ግን በመጀመሪያና በሶስተኛ ጊዜ የተሻለ ነበር። በሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ግን ሚናቸው ሙሉ በሙሉ ከስሟል። የመንግስት እና የሲቪል ማህበረሰብ ግንኙነትን በተመለከተ በመጀመሪያው ወቅት ግንኙነታቸው በመተባበር ላይ የተመሰረተ ቢሆንም በመርህ ላይ የተመሰረተ ግንኙነት አልነበረም። በሁለተኛው ወቅት በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት በግጭት የተሞላ ከመሆኑም ሌላ ሰብዓዊ መብት ላይ አተኩረው የሚሰሩ ሲቪክ ማህበራት መብቶችን በመርገጥ ይገለጻል። ሦስተኛው ጊዜ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት በትብብር እና በመልካም ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው። በመጨረሻም መደበኛ ካልሆኑ ሲቪክ ማህበራት መካከል ዕድር ላይ ትኩረት በማድረግ ትንተና የተካሄደ ሲሆን ዕድር ለመደበኛ ሲቪክ ማህበራት ደጋፊ ሚና ከመጫወት ባለፈ በራሱ ለልማትና ለአስተዳደር የበኩሉን አስተዋፅኦ የሚያደርግ ወሳኝ ተቋም ነው። ይሁን እንጂ የዕድር አስተዋጽኦ በመንግስት ትኩረትና ድጋፍ ማነስ የተነሳ ተገድቧል። በጥናቱ ውጤት ላይ በመመስረት ለሚመለከታቸው አካላት፣ ማለትም ለመንግስት፣ ለመደበኛ የሲቪል ማህበራት እና መደበኛ ላልሆኑ የሲቪል ማህበራት ምክረ ሳቦች ቀርበዋል።

**ቁልፍ ቃላት**፡- ሲቪል ማህበራት፣ ውጫዊ አውድ፣ ውስጣዊ አውድ፣ ሞጋችነት፣ አገልግሎት አሰጣጥ፣ ጠባቂነት፣ ዕድር፣ አስተዳደር፣ ልማት፣ ኢትዮጵያ፣ መንግስት፣ አዲስ አበባ፤

# Department of Health Studies

Year of Graduation 2018

## Substance abuse among undergraduate students at a university in Ethiopia.

Teka Tesfay Asgedom

### ABSTRACT

This convergent parallel mixed methods study based on Social Ecological Model investigated substance abuse among undergraduate university students at one of the universities in Ethiopia. For quantitative strand of study, data was collected from 422 randomly selected undergraduate students. Data were analysed using Statistical Package for Social Sciences version 17. For qualitative strand, face-to-face interviews were conducted with 17 purposefully selected participants directly involved with students abusing substances. The findings revealed that factors at individual, interpersonal, institutional, community and societal levels affect substance abuse among university students. The study also uncovered loopholes in the policies, guidelines, and programme implementations in the prevention, control, and management of substance abuse at the university. Based on the findings, the researcher developed guidelines based on the findings of the study, the critical literature review, and the inputs from the experts who reviewed the guidelines. The researcher assumes that implementation of the guidelines will reduce substance use and substance abuse among university students.

**Keywords:** Addictive substance; Perception; Substance Abuse; Substance use; Undergraduate Students.

## የቅድመ-ምረቃ ተማሪዎች የአደንዛች እፅ መጠቀም-- በአንድ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ላይ

በተካ ተስፋይ ኣስገዶም

### አጠቃሎ

ይህ convergent parallel mixed methods የሚባል የጥናት ዘዴ፣ Social Ecological የሚባል ሞዴልን በመጠቀም የተደረገ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የአንድ ዩኒቨርሲቲ ቅድመ-ምረቃ ተማሪዎች አደንዛዥ እፅ የመጠቀም ሁኔታን መርምሯል። ለ quantitative ዘዴ 422 በእጣ የተመረጡ ተማሪዎች ቃለ-መጠይቅ የተደረገላቸው ሲሆን፣ ዳታው 17ኛውን የSPSS ቨርዥን በጠቀም ተተንትኗል። ለ qualitative ዘዴ፤ ይሁነኝ ተብለው ከተመረጡ 17 የአደንዛዥ እፅ ተጠቃሚ ተማሪዎች ጋር የፊትለፊት ቃለ-መጠይቅ ተደር ጓል።

የጥናቱ ውጤቶች፣ የግል፣ከሰዎች ጋር የለ ግንኙነት፣ የተቋማት፣ የማህበረ-ሰብ እና የህብረተ-ሰብ ሁኔታዎች የተማሪዎችን የአደንዛዥ እፅ የመጠቀም ሁኔታ ላይ ሚና እንዳላቸው አመላክተዋል። ጥናቱ በተጨማሪም፣ የአደንዛዥ እፅ በመከላከል ዙሪያ የሉት ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች እና ፕሮገራሞች ላይ ያሉ ክፍተቶችን ገልጧል። አጥኙው፣ በጥናቱ ውጤቶች እና ለጥናቱ በተሰበሰቡ ፅሁፎች ላይ ተመስርቶ የአደንዛዥ መከላከል መመሪያዎች (guide-lines) ያዘጋጀ ሲሆን፣ የተዘጋጁት መመሪያዎችም የዘርፉ ባለሙያዎች ሂሳዊ ግብኣቶችን በማካተት እንዲዳብሩ ተደርጓል። የእነዚህ መመሪያዎች መተግበር የአደንዛዥ እፅ መጠቀምን ሊቀንስ እንደሚችል የአጥኚው እምነት ነው።

**ቁልፍ ቃላት፡-** ሱስ የሚያስይዝ ንጥረ ነገር፣ ግንዛቤ፣ የአደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀም፣ የዕቃ አጠቃቀም፣ የመጀመሪያ ዲግሪ ተማሪዎች።

Year of Graduation 2021

# Assessment of the availability of public health services in humanitarian responses in Gambella, Ethiopia

Deng Chuol Yiech

## ABSTRACT

The purpose of the research was to assess the availability of public health services in response to humanitarian crises in Gambella, Ethiopia. This informed the development of a public health service protocol for humanitarian emergency responses in Ethiopia. The objectives of the study were explored and identify current humanitarian health emergency needs and responses, describe the availability of public health services required for humanitarian emergency responses, study and critically analyse different humanitarian responses in respect of health care services and related protocols in other countries, develop a context-specific and needs-based protocol for humanitarian emergency responses in Gambella, Ethiopia, and clarify the policy and programme implications of such a protocol. A mixed-method research design was used to conduct the study. Data were collected from 32 health facilities to assess the availability of required resources and public health services. A checklist and in-depth interview guide were used to collect the data. The quantitative data were analysed using simple descriptive statistics using frequency distribution tables and graphs. Thematic analysis was employed to analyse the qualitative data. The study revealed a lack of resources which threatened the availability of public health services in humanitarian emergencies. The ever-increasing number of refugees

# በጋምቤላ ክልል የሚያስፈልጉ የህዝብ ጤና አገልግሎቶች አቅርቦትን ለሰብአዊ ድንገተኛ ምላሾች ላይ የተደረገ ጥናት፤

ዶንግ ቾል የች

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በጋምቤላ ክልል የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት ለሰብአዊ ድንገተኛ ምላሾች ያለውን አቅርቦት ለመገምገም ነው። በኢትዮጵያ የሰብአዊ ድንገተኛ ምላሾችን በተመለከተ የህዝብ ጤና አገልግሎት ፕሮቶኮል ላይ በመመስረት የጥናቱ ዓላማዎች ተዳሰዋል፤ ወቅታዊ የሰብአዊ ጤና አስቸኳይ ፍላጎቶችን እና ምላሾችን በመለየት ለሰብአዊ ድንገተኛ ምላሾች የሚያስፈልጉ የህዝብ ጤና አገልግሎቶችን ተገምግመዋል። በሌሎች ሀገራት የጤና አጠባበቅ አገልግሎቶችን እና ተዛማጅ ፕሮቶኮሎችን በተመለከተ የተለያዩ ሰብአዊ ምላሾችን በማጥናት እና በጥልቀት ተንትነዋል። በጋምቤላ ውስጥ ለሰብአዊ ድንገተኛ ምላሾች አውድ-ተኮር እና ፍላጎቶችን መሰረት ያደረገ ፕሮቶኮል በማዘጋጀት የዚህ ፕሮቶኮል ፖሊሲ እና ፕሮግራም አንድምታዎችን ያብራራል። ጥናቱን ለማካሄድ የተደባለቀ ዘዴ የምርምር ንድፍ ጥቅም ላይ ውሏል። ከ32 የጤና ተቋማት የተሰበሰበ መረጃ የሚፈለገውን ግብአት እና የህዝብ ጤና አገልግሎት ለማረጋገጥ ነው። መረጃውን ለመሰብሰብ የማረጋገጫ ዝርዝር እና ጥልቅ የቃለ መጠይቅ መመሪያ ጥቅም ላይ ውሏል። የቁጥር መረጃው የድግግሞሽ ማከፋፈያ ሠንጠረዦችን እና ግራፎችን በመጠቀም ቀላል ገላጭ ስታቲስቲክስን በመጠቀም ተንትኗል። የጥራት መረጃን ለመተንተን ይዘታዊ ትንታኔ ስራ ላይ ውሏል። ጥናቱ በሰብአዊ ድንገተኛ አደጋዎች የህዝብ ጤና አገልግሎት አቅርቦትን አደጋ ላይ የሚጥል የግብዓት እጥረት አጋልጧል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጣው የስደተኞች ውሱን ሀብቶች ከመጠን በላይ በመጨመራቸው መድሃኒቶችን፣ ሌሎች የጤና እቃዎችን እና ቁሳቁሶችን እንዲከማቹ አድርጓል።

overstretched the limited resources, leading to stockouts of medicines, other health commodities and equipment. The absence of emergency preparedness, poor coordination of services, coupled with a lack of integration of services, exacerbated public health service delivery. The study findings informed the development of a public health service protocol for humanitarian responses in Ethiopia. The study further recommended further research on other factors that might affect humanitarian responses and coordination.

**Keywords:** Assessment; availability; emergency; Gambella; health services; health systems strengthening; humanitarian responses; public health; refugees; required resources.

የአደጋ ጊዜ ዝግጁነት አለመኖር የአገልግሎቶች ቅንጅት ካለመኖር ጋር ተዳምሮ የህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት አሰጣጥ አስቸጋሪ አድርጎታል። የጥናቱ ግኝቶች በኢትዮጵያ ለሰብአዊ ምላሾች የህብረተሰብ ጤና አገልግሎት ፕሮቶኮል መዘጋጀቱን ያሳውቃል። ጥናቱ ተጨማሪ የሰብአዊ ምላሾችን እና ቅንጅቶችን ሊነኩ በሚችሉ ሌሎች ነገሮች ላይ ተጨማሪ ምርምርን መክሯል።

**ቁልፍ ቃላት:**- ግምገማ፣ ተገኝነ፣ ድንገተኛ አደጋ፣ ጋምቤላ፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የጤና ስርዓቶች ማጠናከር፣ የሰብአዊ ምላሾች፣ የህዝብ ጤና፣ ስደተኞች፣ አስፈላጊ ሀብቶች፤

## Strategies to enhance the quality and safety drinking water in Burayu Town, Oromia Regional State, Ethiopia

Kebede Eticha Gela

### ABSTRACT

The purpose of this research was to develop strategies to enhance the quality and safety of household drinking water (HDW) in Burayu Town, Oromia Regional State, Ethiopia and other similar settings. Quantitative, non-interventional and cross-sectional research design and a risk-based approach to HDW safety were employed. The data was collected from 265 households using an interview schedule and testing of water samples for faecal contamination indicators based on the membrane filtration technique. Descriptive and explanatory methods which include bivariate and multiple logistic regression analysis were used to analyse the data.

## የንፁህ መጠጥ ውሃ ጥራትና ደህንነትን ለማሳደግ የተነደፉ ስልቶች ቡራዩ ከተማ ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት

ከበደ ኢቲቻ ገላ

### አጠቃሎ

የዚህ ጥናት አላማ የመጠጥ ውሃ ጥራት እና ደህንነትን በቤታሰብ ደራጀ ለማሳደግ የሚየስችሉ ስትራቴጂዎችን ለቡራዩ ከተማ (ኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት)፣ እና በሌሎች መሰል አካባቢዎች፣ ማዘጋጀት ነው። ለዚህም፣ መጠናዊ ጣልቃ-ገብ ያልሆነ እና አቋራጭ የምርምር ንድፍ እና የቤታሰብ መጠጥ ውሃ የደህንነት ስጋት ላይ የተመሰረተ አቀራረብ ስራ ላይ ውለዋል። የጥናቱ መረጃ የተሰበሰበው ከ265 አባወራዎች የቃለ መጠይቅ መርሃ ግብር እና የውሃ ናሙናዎችን ማጣሪያ ቴክኒኮችን( membrane filtration technique) በመመርመር ነው። ውሂቡን(ዳታ) ለመተንተን የሁለትዮሽ እና በርካታ የሎጂስቲክ ሪግሬሽን ትንተናን የሚያካትቱ ገላጭ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። ውጤቶቹ እንደሚያሳዩት፣

The results revealed that 10.9% of all the sample households had low-risk drinking water safety on combined water sample test and HDWI analysis. However, 57.0% of all the water samples, 82.1% of bottled water and 78.6% of the households treated drinking water samples using chlorine products which were free of contamination indicators. Only 19.2% of the low-risk HDW quality test results were aligned with the same risk level on the combined analysis. Diarrhoea occurrence among children under five years of age was associated with lack of HDW safety risk perception (OR 2.8, 95% CI 1.3 -6.3), lack of latrine (OR 4.9, 95% CI 1.2 - 20.0) and regular cleaning of food utensils by the households (OR 4.0, 95% CI 1.2 -13.6). Lowrisk HDW safety was associated with household water treatment (HWT) practices (AOR 12.6.0, 95%CI 1.2 – 125.0) and with low- risk HDWI results having 58.0% (n=29) overlap on this risk level. Low-risk microbial water quality findings were associated with bottled water (AOR 4.3, 95%CI 1.5 – 12.9) and HWT using chlorine products (AOR 3.2 95%CI 1.1 – 9.8), household's higher income (AOR 5.3 95% CI 1.4 – 20.2) and frequency of water container cleaning (AOR 2.6, 95% CI 2.5 – 5.1). This research further identified that HWT practices were associated with HDW safety risk perceptions that increased the practice by 72.0 % (AOR 0.28, 95% CI: 0.09–0.90) and with households' ability to conduct HWT (AOR 7.7 95%CI 3.7 -15.9). In conclusion, the safety of drinking water at household level is a big concern and comprehensive strategies are required to address the problem.

**Keywords:** Diarrhoea; drinking water quality and safety; drinking water treatment; hygiene; behaviour change; bottled water; risk-based approach; sanitation; safely managed drinking water; Ethiopia.

10.9% የሚሆኑት የናሙና ቤተሰቦች በተቀናጀ የውሃ ናሙና ምርመራ እና የቤታሰብ መጠጥ ውሃ ህይተ (sanitary inspection) ትንታኔ ዝቅተኛ የመጠጥ ውሃ ደህንነት ስጋት ነበራቸው። ነገር ግን 57.0% የውሃ ናሙናዎች፣ 82.1% የታሸገ ውሃ እና 78.6% በቤት ዳራጃ ክሎሪን በመጠቀም የተከሙ የመጠጥ ውሃ ናሙናዎች ከብክለት የፀዱ ናቸው። ይህ ዝቅተኛ ስጋት 19.2% ብቻ ከተቀናጀዉ ትንታኔውጤቶች ጋር ተመሳሳይ የሰጋት ደረጃ ጋር ተስተካክለዋል። ከአምስት አመት በታች ባሉ ህጻናት ላይ የሚከሰተው ተቅማጥ የቤታሰብ መጠጥ ውሃ የደህንነት ስጋት ግንዘቤ መጠት (OR 2.8, 95% CI 1.3 -6.3), የሽንት ቤት መጠት (OR 4.9, 95% CI 1.2 - 20.0) እና የምግብ እቃዎችን አዘውትሮ አለማጽዳት ጋር የተያያዘ ነው። ዝቅተኛ የቤታሰብ የመጠጥ ውሃ ደህንነት ስጋት ከቤተሰብ ውሃ ህክምና (HWT) ልምዶች (AOR 12.6.0, 95%CI 1.2 - 125.0) ዝቅተኛ የቤታሰብ መጠጥ ውሃ ህይተ (sanitary inspection) ስጋት ጋር የተያያዘ ስሆን በዝህም 58.0% (n=29) መደራረብ አለቻዉ ።

**ቁልፍ ቃላት:** ተቅማጥ፤ የመጠጥ ውሃ ጥራት እና ደህንነት; የመጠጥ ውሃ አያያዝ; ንጽህና፤ የባህሪ ለውጥ; የታሸገ ውሃ፤ በአደጋ ላይ የተመሰረተ አቀራረብ፤ የንጽህና አጠባበቅ፤ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚተዳደር የመጠጥ ውሃ; ኢትዮጵያ።

# Immunisation safety surveillance in Asosa Zone, Ethiopia

Muluken Asres Alemu

## ABSTRACT

Background surveillance for immunisation safety is a scheme for guaranteeing immunisation safety through identifying, reporting, investigating and countering to adverse events following immunisations (AEFIs). Most of the AEFI surveillance reports are delivered through health care providers, it is imperative to be clear not only about the factors such as awareness and incidence of reporting, but rather the health care providers' knowledge, perceptions and practice regarding AEFIs. **Purpose of the study:** The purpose of this research was to assess immunisation safety surveillance in Asosa zone, Ethiopia, detect barriers in the health care providers' existing guidelines, and develop an immunisation safety surveillance pocket manual for health care providers. **Methods:** A convergent parallel mixed research method was used. Three hundred respondents participated for the quantitative design and nine participants were included for the qualitative design. Data were analysed through the Statistical Package for Social Sciences (SPSS) 25.0 version and Atlas Ti 8 for quantitative and qualitative approaches, respectively. **Results**: Of the total sample, 94.7% had heard about AEFI, but only 22.3% were able to define AEFI as per the World Health Organization (WHO) standard definition. Some (45.7%) of the respondents were not informed that AEFI surveillance had to be practised in each health facility. Most respondents, (90.7%) were not trained in immunisation safety surveillance. Nearly, 42% of the respondents had below the average value and 56% had more than mean

# አሶሳ ዞን የክትባት ደህንነትና ክትትል ላይ የተደረገ ጥናት፤

በሙሉቀን አስረስ አለሙ

## አጠቃሎ

ሰባት ዋና ዋና መለኪያ የሚባሉትን እንዲሁም አራት መለስተኛ መለኪያዎችን አቀናጅቶ ተጠቅሞባቸዋል። ሶስቱ የአሰራር መለኪያዎች ለየብቻ ከተጠቀምንባቸው የየራሳቸው ጠንካራ እና ደካማ ጎን አላቸው። ሶስቱንም አቀናጅተንና በአንድነት ከተጠቀምንባቸው ግን የተሻለ ንጽጽራዊና ጥራት ያለው የብቃት መለኪያ ይሆናሉ። ስለሆነም፣ ከመነሻው ከንድፈሀሳባዊ አሰራሮች በመነሳት፣ ለአየር መንገዶቹ የብቃት ጥናት እንዲመች ንጽጽራዊ የተቀናጀ አሰራርን ሞዴል ሊነደፍ ችሏል። የዚህ ጥናት አወቃቀርና ስልት የተመሰረተው ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ ማለትም ዓመታዊና የአፈጻጸም ሪፖርቶቻቸውን ከየራሳቸው መረብ በማሰባሰብ ላይ ነው። አየር መንገዶቹ ያላቸውን እጅግ ብዙ የፋይናንስና የአፈጻጸም ሪፖርቶችን የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን ተጠቅሞ ማሰባሰብ የማይሞከርና ከፍተኛ ወጭም የሚያስከትል ነው። በዚህም የተነሳ ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን ማሰባሰቡ ጊዜንና ገንዘብን ከመቆጠቡም በላይ በቀላሉ ለመተንተንና ውጤቱን ለማወቅ ያመቻል። በዚህም ምክንያት በገቢ ደረጃቸው ከተመረጡት አንድ መቶ ትላልቅ አየር መንገዶች ውስጥ፣ ቀላል የናሙና አመራረጥ ስልትን በመጠቀም ሰማንያው ተመርጠዋ። በመጀመሪያ ደረጃ BSCው የግብአትና የምርት ውጤት መለኪያዎች ተለይተዋል። ቀጥሎ የDEA ሞዴሉ የብቃት መለኪያዎችን በደረጃ ተቀምጠው፣ ደካማ መለኪያዎችን ለየአየር መንገዶችን ደረጃ መለያ ተደርገዋል። በሶስተኛ ደረጃ፣ SFA ሞዴሉ የቴክኒክ ብቃትንና በዘፈቀደና በቴክኒክ ብቃት ማነስ ሊከሰቱ የሚችሉ ስህተቶችን ተለይተዋል፡ ፡ በመጨረሻ በሁለቱ ዘዴዎች የተገኘው የቴክኒክ ብቃት ግምት በንጽጽራዊነት ተተንትነዋል። ጥናቱ የኢትዮጵያን አየር መንገድን እጅግ ብቃት ካላቸውና ብቃት ከሌላቸው አየር መንገዶችና ከአካባቢም አየር መንገዶች ጋር በማነጻጸር በተለየ ትኩረት ገምግሟል። እጅግ ጥልቅ ጥናት ከተካሄደ በኋላ፣ ሚዛናዊ የድንበር ሽፋን ሞዴል ተሰርቶለታል። በዚህ ሞዴል መሰረት የሶስቱን ሞዴሎች ጥንካሬ በአንድነት በመጠቀም ብቃትን መለካትና ቀደም ሲል ስራ ላይ የዋሉትን አንድና ሁለት ሞዴሎችን አቀናጅቶ ከመጠቀም እጅግ የተሻለ ውጤት ይኖረዋል። የተጠቀምኩበትና የተቀናጀው ስትራተጂክ ሞዴል የአየር መንገዶችን አሰራር ቴክኒካዊ ብቃት የመለካቱን አሰራር ቀለል

with the regional analysis. After extensive tests have been conducted, the 'Balanced Frontier Envelopment' model is developed. According to this model, it is a paramount to measure efficiency with combining the strength of three models together and gives better results than the previous one or two combined models. The developed and integrated strategic model enhances measuring of the operating technical efficiency of airlines. This model benefits the airlines industry in many ways such as minimising the cost and maximising profit through managing technical efficiency which leads to the success of the airlines. From the model perspective, therefore, results of the DEA model is much higher than the result of the SFA model. The DEA model is easier to manipulate than the SFA model because the former does not need the functional form while the later requires a functional form. Furthermore, according to the efficiency finding of the study, first, the European regional airlines are relatively more efficient than the rest of regions in the world. Second, the North America regional airlines are the second more efficient regional airlines in the world. Third, the Ethiopian airlines are the most efficient in Africa when compared with Egypt Air, Kenyan Airways and South African Airways. Fourth, high revenue does not necessarily lead to the technical efficiency of the firm.

**Kewords:** Operational performance; technical efficiency; Balanced Scorecard; Data Envelopment Analysis; Stochastic Frontier Analysis; efficiency estimate; financial performance; world airlines and ethiopian airlines; comparative model; strategic management; input and output variables; random error; technical inefficiency; panel data; regional analysis; revenue; cost minimization; profit maximization; efficiency assessment.

ያደርገዋል። ይህ ሞዴል ወጭን መቀነስን፣ የአየር መንገዶችን ውጤታማነት ከፍ የሚያደርገውን ትርፋማነትን ማሳደግን በመሳሰሉ ሁኔታዎች፣ ለአየር መንገዶች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። ስለዚህም፣ ከሞዴሎቹ አንፃር ስንመለከት በDEA ሞዴል የተገኘው ውጤት በSFA ከተገኘው ከፍ ያለ ነው። የDEA ሞዴል ምናባዊ ቅጽን (Functional form) ስለማይጠቀምና የSFA ሞዴል ያንን ስለሚጠቀም የመጀመሪያው ከሁለተኛው ይልቅ ለአሰራር ያመቻል። ከዚህም በላይ በጥናቱ በተገኘው የብቃት መለኪያ መሰረት፣ የአውሮፓ አየር መንገዶች ከሌሎች አየር መንገዶች የተሻለ ብቃት አላቸው። ሁለተኛ የሰሜን አሜሪካ አየር መንገዶች በዓለም ከሚገኙ አየር መንገዶች በብቃት በሁለተኛ ደረጃ የሚመደቡ ናቸው። ሶስተኛ ከግብፅ፣ ከኬንያና ከደቡብ አፍሪካ አየር መንገዶች ጋር ሲነጻጸር፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካ እጅግ ብቃት ያለው አየር መንገድ ነው፡ ፡ አራተኛ፣ ከፍተኛ ገቢ ማግኘት የድርጅቶቹን የብቃት ደረጃ በግድ የሚወስን አይደለም።

**ቁልፍ ቃላት:**- የተግባር አፈጻጸም ፥ ቴክኒካል ቅልጥፍና፥ ሚዛኑን የጠበቀ የውጤት ካርድ (ቢኤስሲ)፥ የመረጃ ኢንቬሎፕመንት ትንተና (ዲኢኤ)፥የውጤታማነት ግምት፥ የፋይናንስ አፈጻጸም፥ የአለም አየር መንገድ፥ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፥ የንፅፅር ሞዴል፥ ስትራቴጂካዊ አስተዳደር; ግብአት እና የውጤት ተለዋዋጮች፥ የዘፈቀደ ስህተት፥የቴክኒክ ብቃት ማነስ፥ ፓነል ውሂብ፥ የክልል ትንተና ፥ የገቢ፥ ወጪን ማሳነስ፥ ትርፍ ከፍተኛ ፥ የውጤታማነት ግምገማ

## An interest rate commission agent banking system (AIRCABS)

Ameha Tefera Tessema

### ABSTRACT

An interest rate commission agent banking business model was developed in the year 2015 by Ethiopian, Ameha Tefera Tessema. It is defined as a system adopted by the bank to be an agent for investors' loan funding to entrepreneurs getting the fund seller and buyer agreement to administer the loan after disbursement by retaining a reasonable interest rate commission from the agreed investors' loan funding credit price. The research sought to investigate the effect of investor loan funding, credit risk and liquidity crunch, on AIRCABS sustainability and profitability. To test the viability of an interest rate commission agent banking system, the researcher collected primary data using structured survey questionnaires from a sample population of 300 bank professionals and secondary data using twenty-three years' financial statements, which were published in the period from 1 July 1993 to June 2016, of one government bank and 15 private commercial banks in Ethiopia. To test the research hypotheses, coefficient of variation, canonical correlation and multinomial logistic regression statistical tools were employed and to analyse the survey questionnaires the Cronbach alpha, kuder-Richardson, coefficient of variation and factor analysis were used. The statistical results showed that AIRCABS was not affected by credit risk and the liquidity crunch and the increase of investor loan funding increased AIRCABS' sustainability and profitability. Calculating the discrete market deposit interest incentive, taking into account the depositor

## የወለድ ተመን ኮሚሽን ወኪል የባንክ አሰራር ሥርዓት (AIR-CABS)፤

አመሃ ተፈራ ተሰማ

### አጠቃሎ

በወለድ ምጣኔ ላይ ተመስርቶ በሚከፈል ኮሚሽን ላይ የተመሰረቱ የባንኮች አሰራር ሞዴል በኢትዮጵያዊዉ አመሃ ተፈራ ተሰማ ጥቅምት 2008 ዓ.ም ተፈጥሮአል። አሰራሩ ባንኮች የኢንቨስተሮች ወኪል በመሆን፣ ለስራ ፈጣሪዎች የሚያበድሩትና ብድር ፈንድ ገዥና ሻጮን የሚያገናኙበትና ሲሆን፣ ባንኮች በሚደረሱበት ስምምነት መሰረት ከወለዱ የሚታሰብ ገቢ የሚያገኙበት ነው። ይህ ጥናት ያተኮረው የኢንቨስተሮች ብድር ፈንድ፣ ከብድር ጋር ተያይዞ የሚመጣ ስጋትና የፋይናንስ ፍሰት በወለድ ምጣኔ ላይ ተመስርቶ፣ በሚከፈል ኮሚሽን ላይ የተመሰረቱ ባንኮች ዘላቂነትና ትርፋማነት ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ መመርመር ላይ ነው። በወለድ ምጣኔ ላይ ተመስርቶ የሚከፈል ኮሚሽን ላይ የተመሰረቱ ባንኮችን ዘላቂነት ለመፈተሽ አጥኚው(አመሃ ተፈራ ተሰማ) በስርዓት በተደራጀ መጠይቅ ከ300 ናሙናዎች ከኢትዮጵያ፣ ማለትም  የባንክ ሰራተኞች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግና የሃያ ሶስት ዓመታት የተደራጀ የፋይናንስ ሪፖርቶችን በመጠቀም ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎችን አሰባስቧል። እነዚህ ሪፖርቶች በአንድ የመንግስትና 15 የግል ባንኮች፣ ከጁላይ 1፣ 1993 እስከ ጁን 2016 ታትመው የወጡ ናቸው። የጥናቱን መላምት ለማረጋገጥ ተለዋዋጭነቱን (Coefficient of variation)፣ canonical correlation እና multinomial logistic regression የተሰኙ የስታቲስቲክስ መለኪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። በመጠይቅ የተገኘውን መረጃ ለመተንተንም Cronbach alpha, kudre Richardson, coefficient of variation እና factor analysis የተሰኙ ፕሮግራሞች ተግባራዊ ተደርጓል። በጥናቱ ውጤት መሰረት፣ የስታቲስቲክሱ ውጤት እንደሚያመለክተው ከብድር ጋር ተያይዞ የሚመጣ ስጋትና የፋይናንስ ፍሰት በወለድ ምጣኔ ላይ ተመስርቶ በሚከፈል ኮሚሽን ላይ የተመሰረቱ ባንኮች አሰራር ተፅዕኖ እንደማያሳድርና የኢንቨስተሮች የብድር ፈንድ

who later shifted to an investor position to get a proportionate credit price instead of a deposit interest rate on the fund already invested by the bank which later shifted to an agent position, elicited increasing stability of money deposited by depositors.

**Keywords:** Investor loan funding; discrete market deposit interest rate; agent bank model; profitability and sustainability; stable deposit.

ከፍ ማለት የባንኮቹን ዘላቂነትና ትርፋማነት ከፍ እንደሚያደርግ ታይቷል። ባንክ ውስጥ ካስቀመጠው ድርሻና የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ፣ ከባንክ ከሚያገኘው ወለድ ይልቅ የተሻለ የብድር ወለድ ድርሻ ለማግኘት ሲል ወደ ኢንቨስተርነት የተለወጠ የባንክ ገንዘብ አስቀማጭ ደንበኛ የገንዘቡ መጠንና ዋስትና የተሻለና አስተማማኝ ደረጃ ላይ እንደሚሆን ጥናቱ አመልክቷል።

**ቁልፍ ቃላት፡**- ያበዳሪዉ ገንዘብ፣ የገንዘብ ተቀማጭ ማበረታቻ ወለድ፣ ያበዳሪዉ ወኪል ባንክ አሠራር፣ ትርፋማነት፣ ዘለቄታዊነት፣ የተረጋጋ የባንክ ቍጠባ ገንዘብ

# Corporate governance, antecedents and performance implications in the Ethiopian non-financial share companies: a contingency perspective

Anteneh Eshetu Tizazu

## ABSTRACT

Corporate governance has been a hot bed for scholars from diverse disciplines. Managers whose interests are not congruent with that of shareholders' do not have the incentive to maximise shareholder value. Agency Theory implicitly assumes corporations as arenas of the principal-agent conflict. On the other hand, organisational perspectives maintain that firms differ in their adopted corporate governance level depending on the environmental contingencies in which they operate. This study develops a contingency framework by synthesizing Agency Theory and Organization Theory. The aims of this study are to examine the effect of firm level contingencies on corporate governance and examine the moderating impact of firm level contingencies on the relationship between corporate governance and firm

# የኮርፖሬት አስተዳደር፣ ቀዳሚ ምክኒያቶችና በተቋም አፈጻጸም ላይ ያለው ተፅዕኖ በኢትዮጵያ በሚገኙ የፋይናንስ ባልሆኑ የሽርክና ኩባንያዎች ላይ:የ ኮንቲንጀንሲ ምልከታ

በአንተነህ እሸቱ ትዕዛዙ

## አጠቃሎ

የኮርፖሬት አመራር በተለያዩ ሙያ ዘርፎች ለተሰማሩ ምሁራን አስቸጋሪ ጥያቄ ሆኖ ቆይቷል፡ ፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት ደግሞ፣ ከሽርክናው አባላት ጥቅም ጋር የማይጣጣም ፍላጎት ያላቸው ማኔጀሮች የሽርክና አባላትን ትርፍ ከፍ የማድረግ ፍላጎቱ አይኖራቸውም። በውክልና መስራት ላይ ያተኮሩ ንድፈ ሀሳቦች (Agency theory) ኮርፖሬሽኖች በአመራሩና በባለቤቶቹ መካከል ዓይነተኛ ግጭት የሚካሄድባቸው መስኮች ናቸው ይላሉ። በሌላ በኩል፣ ድርጅታዊ አስተሳሰብ (Organizational perspective) ተቋማት እንደ የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ፣ የሚከተሉት የአስተዳደር ዘይቤም ይለያያል የሚል አመለካከት አላቸው። የዚህ ጥናት አላማ የውክልና አመራርን ንድፈ ሀሳብና የድርጅትን ንድፈ ሀሳብ በማዋሀድ ሊያሰራ የሚችል መፍትሄ ለመሰንዘር ነው። በዚህም በተቋም ደረጃ ያለው እርግጠኛ ያልሆነ ሁኔታ በኮርፖሬት አመራሩ ላይ ያለውን ተፅዕኖ መመርመርና በኢትዮጵያ በሚገኙ የፋይናንስ

financial performance in the Ethiopian non-financial share companies. Data were collected from public and private sources for 42 companies covering the period 2009-2013. For the first time, the overall corporate governance index is constructed from board structure, ownership structure, disclosure and transparency. By specifying fixed effect regression models, the study accounts for the presence of unobserved firm heterogeneity. Moreover, a moderation fixed effect model is specified for the corporate governance-performance relationship. Results show that firms choose their corporate governance in response to contexts in which they operate. High-risk firms have good corporate governance. Corporate governance is enhanced if the largest owner is government or bank. Findings show not only the positive influence of corporate governance on financial performance but also the positive effect of corporate governance on financial performance is enhanced where there are high agency problems. Firm growth, firm-level risk and identity of the largest shareholder, moderate the relationship between corporate governance and firm financial performance. The study contributes to the literature by providing evidence that firms endogenously choose their corporate governance and the effect of corporate governance on performance depends on firm-level contingencies. For practice, the positive link between corporate governance and financial performance informs us that instituting and enforcing corporate governance should be taken seriously. Areas that require priority include the legal frameworks and their enforcement, additional corporate governance standards, strong financial markets, particularly a stock market. Future research can build on the limitations of the study. For instance, researchers

ያልሆኑ ተቋማት ውስጥ በተቋም ደረጃ አጠራጣሪ ሁኔታ ከተቋም ደረጃ ባለው አመራርና በፋይናንስ አተገባበር ላይ ባላቸው ግንኙነት የሚጫወተውን የማስተባበር ሚና ያጠናል። ለዚህም ከ2001-2005 ዓመተ ምህረት ያሉ መረጃዎች ከ42 የመንግስትና የግል ኩባንያዎች ተሰብስቧል፡ ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ከቦርድ አወቃቀር፣ ከባለ ድርሻዎች ማንነት፣ እንዲሁም ከመረጃ አሰጣጥና ከግልጸኝነታቸው በመነሳት ለሁሉም የኮርፖሬት አመራር የሚሰራ ጠቋሚ ማውጣት ተችሏል። በመሆኑም fixed effect regression model በመጠቀም፣ በድርጅቱ ውስጥ በግልጽ የማይታዩ ልዩነቶች መኖራቸውን ለማውጣት ተችሏል፡ ፡ ከዚህም በላይ፣ በኮርፖሬት አመራርና የስራ አፈጻጸም መካከል ያለውን ግንኙነት ለመወሰንም a moderation fixed effect model የተሰኘው ተለይቷል። የዚህ ውጤት የመለከተውም ተቋማት የኮርፖሬት አመራራቸውን የሚመርጡት በተሰማሩበት መስክ ላይ ተመስርተው መሆኑን ነው። ከፍተኛ ስጋት ያለባቸው ድርጅቶች የተሻለ የኮርፖሬት አመራር አላቸው። ከፍተኛውን ባለቤትነት የያዙት መንግስት ወይም ባንኮች በሚሆኑበት ጊዜ የኮርፖሬቱ አመራር የተሻለ ይሆናል። ግኝቶቹ የሚያሳዩት ኮርፖሬት አመራር በፋይናንስ አፈጻጸም ላይ ያለውን አዎንታዊ ተፅዕኖ ብቻ ሳይሆን በተቋማት ላይ ከፍተኛ ችግር ባለበትም ወቅት የኮርፖሬቱ አመራር በፋይናንስ አፈጻጸም ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ጭምር ያመለክታል። የድርጅቶቹ ዕድገት፣ በተቋም ደረጃ ያሉ መሰናክሎች እና የከፍተኛው የሽርክና ባለቤት ማንነት በኮርፖሬቱ አመራርና በድርጅቱ የፋይናንስ አፈጻጸም ላይ የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ። ጥናቱ ተቋማት ኮርፖሬት አመራራቸውን ከውስጣቸው እንደሚያወጡና ኮርፖሬት አመራር በአፈጻጸም ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ የሚወሰነው በተቋም ደረጃ ባለ አፈጻጸም መሆኑን በማሳየት ጥናቱ እስካሁን ባሉ ዕውቀቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ ይሆናል። ለተግባራዊ አፈጻጸም፣ በኮርፖሬት አመራርና በፋይናንስ አፈጻጸም መካከል ያለው አዎንታዊ ግንኙነት የሚያሳየን የኮርፖሬት አመራርን ማቋቋሙና መተግበሩ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ነው። በዚህ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣ የደንቦች መኖርና ትግበራ፣ ተጨማሪ የኮርፖሬት አስተዳደር ደረጃዎችን መወሰን፣ ጠንካራ የፋይናንስ ገበያ በተለይም ስቶክ

can increase the sample size, compare industries or perform cross-country studies.

**Keywords:** Corporate Governance; Agency Theory; Organization Theory; Contingency Perspective; Firm-Level Contingency; financial performance; non-financial share company; Ethiopia.

ማርኬት ናቸው። የጥናቱን ውሱንነት ለመተካት ወደፊት ሌሎች ጥናቶች (የናሙናውን መጠን በመጨመር፣ ኢንዱስትሪዎችን በማነፃጸር፣ በአገር አቀፍ ደረጃ ናሙና በመሰብሰብ፣ . . ወዘተ.) ሊካሄዱ ይችላሉ።

**ቁልፍ ቃላት:-** ኮርፖሬት አስተዳደር፣ በውክልና የማስተዳደር ንድፈ ሀሳብ፣ ተቋማዊ ንድፈ ሀሳብ፣ ኮንቲንጀንሲ ምልከታ፣ ተቋማዊ ምክኒያቶች፣የፋይናንስ አፈፃፀም፣ ፋይናንስ ያልሆኑ የሽርክና ኩባንያዎች

# Transformation leadership and marketing performance: the mediating role of organizational learning and customer orientation

Hailemariam Kebede Gelgile

## ABSTRACT

The making and breaking power of leadership has never been disputable. It is believed to be the single most important factor by which organisations used to exploit opportunities and survive hardships. Despite the fact that all functional areas are not immune to the consequences of good and bad leadership, marketing is uniquely sensitive. Unarguably, all leadership styles are not expected to equally impact marketing performance. A leader of character who inspires followers, helps employees to use their potential, allows employees to make and fix errors, and paves ways for employee advancement, is one typically needed by organisations. This kind of leader is even more critical for those organisations operating in a brutally competitive market like the brewing one in Ethiopia. This study is designed to investigate the direct and indirect impact of Transformational Leadership on marketing performance. Moreover, the moderating effect of leaders' experience and the

# ድርጅታዊ ልምድና ደንበኛ ላይ ማተኮር የለውጥ አመራር እና የግብይት አፈጻጸም ለማመቻቸት ያላቸው ሚና፤

ኃይለማርያም ከበደ ገልገሌ

## አጠቃሎ

የአመራር ስራ ነገሮችን ለማሳካት ወይንም ለማበላሸት ያላቸው ሚና አከራካሪ ሆኖ አያውቅም። ድርጅቶች አጋጣሚዎችን ለመጠቀምና ችግሮችን ለማለፍ ብቸኛው መንገድ የአመራር ክህሎት ብቃት መሆኑ ይታመንበታል፡ ፡ ሁሉም የስራ መስኮች ከጥሩ ወይም መጥፎ አመራር ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ነፃ ባይሆኑም የግብይት ጉዳይ ግን እጅግ ተጋላጭ ነው። ሁሉም የአመራር ስልቶች በግብይት ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ተመሳሳይ አለመሆኑ አያከራክርም። ድርጅቶች የሚፈልጉት ተከታዮቹን ማነቃቃት የሚችል፣ ሰራተኞች ያላቸውን አቅም አሟጠው እንዲጠቀሙበት የሚያበረታታ፣ ሰራተኞች ስህተት እንዲፈጽሙና ራሳቸው እንዲያርሙ የሚደግፍ የሚረዳ መሪ ነው። እንዲህ ዓይነቱ መሪ እጅግ ውድድር በሚበዛበት ሁኔታ በሚንቀሳቀሱ፣ ለምሳሌ በኢትዮጵያ እንዳሉት ዓይነት የቢራ ፋብሪካዎች ውስጥ፣ ወሳኝ ነው። ይህ ጥናት ያተኮረው በግብይት አፈጻጸም ውስጥ የለውጥ አመራርን ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅዕኖ መመርመር ላይ ነው፡ ፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ጥናቱ የአመራር ልምድ፣ የመሪው ፆታ፣ የአመራር ደረጃ እና የፋብሪካው ስፋትንም ከግምት በማስገባት ይተነትናል። ጥናቱ የተጠቀመው በአራቱ ለናሙናነት በተመረጡ

impact of group difference in leaders' gender, leaders' position and brewery sizes are studied. The unit of analysis are managers and decision-makers (committee members) from the four sample breweries (St. George Brewery, Meta Abo Brewery, Raya Brewery, and Habesha Brewery). The data are collected from 211 respondents. In the study, in addition to the data cleaning procedures, all the multivariate data analysis assumptions are ensured. A model is developed and tested using a survey methodology. Four properly validated instruments, one self-designed (for marketing performance construct) and three adopted (for transformational leadership, organisational learning, and customer orientation constructs) are used. The validation work is ensured through factor analysis (exploratory and confirmatory). Exploratory Factor Analysis (EFA) and Confirmatory Factor Analysis (CFA) are worked out using SPSS 21 and AMOS 21 packages respectively. Data is analysed through the structural equation modelling technique. Results show that, the Transformational Leadership style is positively and significantly associated with marketing performance, organisational learning, and customer orientation. Moreover, it is found that Transformational Leadership indirectly and positively impacts marketing performance. Nevertheless, the hypothesised moderation effect of experience for the impacts of Transformational Leadership on customer orientation failed to be significant. The study contributes a lot by narrowing the wide literature gap existed in the topic area in the context of the developing world. Secondary evidences are strongly discussed on the antecedents and outcomes of Transformational Leadership and marketing performance. Thus, it is the researcher's belief that now because of this study, value is added to the body of knowledge

(የቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ሜታ አቦ፣ ራያ እና ሐበሻ) ቢራ ፋብሪካዎች ያሉ ማኔጀሮችንና ውሳኔ ሰጭዎችን ነው። መረጃ የተሰባሰበው ከ211 ግለሰቦች ነው፡፡ በጥናቱ፣ የተሰባሰቡ መረጃዎችን ከማጽዳት አሰራሮችን ከመከተል በተጨማሪ፣ በርካታ ተለዋዋጭ መረጃዎችን (multivariate data analysis) ለመተንተን የተቀመጡ ግምቶች ሁሉ ተወስደዋል። የአጠናን ስርዓቱን በመከተል አንድ ሞዴል ተነድፎ የሚሰራ መሆኑ ተፈትሿል፡፡ ለዚህም አንድ በአጥኚው የተነደፈ (የግብይት አፈጻጸምን ለመለካት)፣ ሶስት ከሌሎች የተወሰዱ (ለአሻጋሪ አመራር፣ ድርጅታዊ አመራር፣ ደንበኛን የማስተናገድ ሁኔታን) በጠቅላላ አራት የተረጋገጡ መለኪያዎችን ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ግኝቱን የማረጋገጡ ስራ የተከናወነውም ገላጭና አረጋጋጭ የሆነውም factor analysis በመጠቀም ተከናውኗል። Exploratory factor analysis (EFA) እና Confirmatory factor analysis (CFA) የተሰራው እንደ ቅደም ተከተላቸው SPSS 21 እና AMOS 21 የተሰኙትን የስታቲስክስ ትንታኔ ስልቶችን በመጠቀም ነው። በተጨማሪም structural equation modeling መረጃውን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል። ይናቱ ውጤት እንደሚያሳየው አሸጋጋሪ የአመራር ስልት በአዎንታዊና በከፍተኛ ደረጃ ከግብይት አፈጻጸም፣ ከድርጅት መማር እና ከደንበኛ አያያዝ ጋር የተቆራኘ ነው። ከዚህም በላይ አሻጋሪ አመራር በተዘዋዋሪና አዎንታዊ በሆነ መልኩ የግብይት አፈጻጸም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር ሆኖ ተገኝቷል። ይሁንና፣ የስራ ልምድ፣ አሻጋሪ አመራር በደንበኛ አያያዝ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድር የራሱን ሚና ይጫወታል የሚለው ግምት ከፍተኛ ሆኖ አልተገኘም። ጥናቱ በታዳጊ አገሮች ውስጥ ይህንን ርዕስ በተመለከተ በስነ ጽሑፍ ደረጃ የነበረውን ሰፊ የአመለካከት ልዩነት ማጥበብ ችሏል። ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች አሻጋሪ አመራርና የግብይት አፈጻጸምን በተመለከተ ቀደም ሲል የነበሩትንና የጥናቱንም ውጤት በከፍተኛ ደረጃ ዘርዝሯል፡፡ በመሆኑም፣ ይህ ጥናት እስካሁን በነበረው እውቀት ላይ እሴት በመጨመሩ፣ በስራው ላይ የተሰማሩ ሙያተኞችም ሆኑ ተመራማሪዎች ትምህርት እንደሚያገኙበት አጥኝው ያምናል።

**ቁልፍ ቃላት:**- ተሻጋሪ አመራር፣ የግብይት አፈጻጸም፣ ድርጅታዊ ትምህርት፣ የደንበኛ አተያይ፣ የመሪዎች ልምድ፣ የአስተዳደር አቀማመጥ እና ድርጅታዊ መጠኖች።

and the study can benefit practitioners and academicians alike.

**Keywords:** Transformational Leadership; Marketing Performance; Organizational Learning; customer orientation; leaders experience; management position and organisational sizes.

# The impact of industry concentration on performance, exploring a comprehensive bank performance model: the case of the Ethiopian banking sector

Tesfaye Boru Lelissa

## ABSTRACT

There are wide empirical studies and literature that advocate for a strong link between financial sector development and economy growth. Nevertheless, similar to the situation in Sub-Saharan Africa, the share of the financial sector in the overall economy of Ethiopia is at a lower level and can be referred as a shallow financial market. In Ethiopia, reform measures to enhance the performance of this sector through liberalisation measures as well as economic plans, Growth and Transformation Plan I & II (GTP I& II) that set bank growth strategies were enacted in an attempt to augment their contribution to the economy. Despite such reforms and policy attentions, the banking system in Ethiopia is characterised by high concentration, with an observed dominance, of the state-owned banks. Nonetheless, the lack of indisputably conclusive and substantial disagreement in empirical results, the Structure- Conduct-Performance (SCP) theorists claim that

# የኢንዱስትሪ በአንድ አካባቢ መከማቸት በስራ አፈጻጸም ላይ የሚደርሰውን ተፅዕኖ ማሰስ፣ ሁሉን አቀፍ የባንክ አሰራር ሞዴል ላይ ያተኮረ፡ በኢትዮጵያ ባንክ ዘርፍ ላይ የተደረገ ጥናት፡፡

በተስፋዬ በሩ ሌሊሳ

## አጠቃሎ

በፋይናንስ ዘርፉ ዕድገትና በኢኮኖሚ ልማት መካከል ጠንካራ ትስስር መኖሩን የሚያመላክቱ በርካታ ጥናቶችና የጽሑፍ መረጃዎች አሉ፡፡ ይሁንና፣ ከሰሀራ በታች ባሉ አገራት እንዳለው ሁሉ፣ በየኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፉ በአጠቃላዩ ኢኮኖሚ ላይ ያለው ድርሻ አነስተኛ ነው፤ የፋይናንስ ገበያውም ገና ጅማሮ ላይ ያለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የፋይናንሱ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ድርሻ ከፍ ለማድረግ የኢኮኖሚውን አሰራር በማሻሻልና የባንኮችን ዕድገት ስልት ለመቀየስ በወጡት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 1 እና 2 የለውጥ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነት የማሻሻል እና የፖሊሲ እርምጃዎች ቢወሰዱም በኢትዮጵያ ያለው የባንኮች ስርዓት በአንድ አካባቢ የተከማቸና የመንግስት ባንክ የበላይነት በጉልህ የሚንጸባረቅበት ነው፡፡ የስትራክቸር-ኮንዳክት-ፐርፎረማንስ (SCP) ንድፈ ሀሳባውያን እንደሚሉት፣ ትክክለኛና ተጨባጭ የጥናት መኖር አለመኖር እንዲህ ዓይነቱ የኢንዱስትሪ አወቃቀር የተቋሙን ባህሪይና አሰራር ይወስናል፡፡ የዚህ ጥናት ዋንኛ ዓላማም የዚህን ንድፈሀሳብ ተቀባይነት ማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ጥናት የባንኮች አንድ አካባቢ መሰባሰብ በኢትዮጵያ ባንኮች አሰራር ላይ ተፅዕኖ አሳድረው

such kind of industry structure influences the conduct and performance of firms. The basic objective of this research is to test the validity of this view. A SCP analysis has been undertaken so as to examine whether the level of concentration influences performance of Ethiopian banks. In addition, it is aimed at investigating the impact of other non-structure factors on performances with an overarching purpose of exploring a comprehensive model of bank performances. The study employed an explanatory sequential mixed method approach that combined both quantitative and qualitative studies to explore the central and subsidiary questions. A quantitative approach is adopted to form a causal link among different variables with bank performance measures. A panel dataset from 1999 to 2015 for all (eighteen) commercial banks is used for the quantitative study. The quantitative study employs a two-stage estimation procedure to evaluate the impact of bank concentration on performance. In the first stage of the estimation process, a Data Envelopment Analysis (DEA) is employed to produce an efficiency estimates. The output of the DEA is later used as an input in the second stage of the estimation procedure, where a panel data regression model was employed to investigate the relationship between efficiency, concentration and other factors on profit and price performances. A qualitative approach that gathers data through semi-structured interviews with bank managers and regulatory staff is also used to justify the established relationship in the quantitative study as well as investigate the conduct of banks under a given industry structure and banking environment. The result of the integrated approaches rejects the structure performance hypothesis and supports the scale efficiency version of the efficiency hypothesis. Therefore, better

እንደሆነ ለመፈተሸ SCP ትንታኔ ተደርጓል። በተጨማሪም፣ ጥናቱ ለባንኮች አሰራር የሚሆን አንድ ወጥ ሞዴል መንደፍ እንዲቻልም ሌሎች መዋቅራዊ ያልሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ተደርጓል፡ ፡ ጥናቱ ዋንኛዎችንም ሆነ ደጋፊ ጥያቄዎችን ለመተንተን በመጀመሪያ አሀዛዊ መረጃዎችን፣ አከታትሎም ጥረት ላይ የተመሰረቱ ጥያቄዎችን ለመተንተን የሚያስችለውን ገላጭ ተከታታይ ቅይጥ ዘዴ(explanatory sequential mixed method) የተሰኘውን ስልት ተጠቅሟል። በባንኮች አሰራር መካከል ያለውን በአጋጣሚ የሚከሰትን ግንኙነት ለመተንተን አሀዛዊ (quantitative) የትንታኔ አሰራርን ጥቅም ላይ ውሏል። ለአሀዛዊው ትንታኔ የሁሉንም የንግድ ባንኮች (18 ናቸው) እ.አ.አ ከ1999 እስከ 2015 ያለውን አጠቃላይ መረጃዎች ለጥናቱ ውለዋል፡ ፡ በአንድ አካባቢ የመሰባሰቡ ነገር በባንኮች አሰራር ላይ ያስከተለውን ተፅዕኖ ለመገምገም አሀዛዊው ጥናት በሁለት ደረጃ አገማመት (two stage estimation) ዘዴ ስራ ላይ ውሏል። ይህ ጥናት በመጀመሪያው ደረጃ አገማመት ሂደት ብቃትን ለመለካት Data envelopment anal-ysis (DEA) የተሰኘውን ስልት ነው ተጠቅሟል። በብቃት፣ በመሰባሰብና በሌሎችም የትርፍና ዋጋ አሰራሮች መካከል ያለውን ግንኙነት ለመተንተን የdata regression model የተሰኘውን ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን፣ በData envelopment analysis (DEA) የተገኘውን ውጤት ለዚህኛው ትንታኔ እንደ ግብአት ተጠቅሟል። ከባንክ ማኔጀሮችና ከተቆጣጣሪ አካላት ሰራተኞች ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ የተሰባሰበው ጥራታዊ መረጃ በአሀዛዊው መረጃ የተገኘውን ግንኙነት ለማረጋገጥና ባንኮች በተወሰነ የኢንዱስትሪ አወቃቀርና አካባቢ የሚያሳዩትን ባህሪ ለመረዳት ረድቷል። ሁለቱን በመጠቀም መዋቅራዊ አፈጻጸም የሚለውን ንድፈ ሀሳብ ውድቅ ሲያደርጉት፣ የብቃት አሰራር scale effi-ciency version የተሰኘው ንድፈ ሀሳብ ትክክል መሆኑን አረጋግጠዋል። ስለዚህም፣ የተሻለ የባንክ አፈጻጸም የሚኖረው ባንኮች በኢንዱስትሪው ውስጥ ተባብረው ከመስራት ይልቅ በብቃት ከመስራት ነው። በንድፈ ሀሳብ ደረጃም ቢሆን በባንኮች መካከል የአቅም ልዩነትና በባለቤትነት ደረጃ ልዩነት እስካለ ድረስ በባንኮች መካከል ተባብሮ የመስራት ጉዳይ በቀላሉ ሊመጣ የሚችል ስልት አይደለም። ከዚህም በላይ ስራቸውን

bank performance is derived from efficient operation rather than from collusive power of the banks in the industry. Theoretically as well, it finds that bank collusion is not an easily pursued strategy among banks as long as there is a sizeable difference in bank size and ownership structure. Besides, there is a notable variation in their mission guiding their business motive. The test for efficiency variation through both parametric and non-parametric tests confirms that there is widely noted efficiency variation among banks operating in the country of which the state-owned banks are consistently on the top of the frontier. The quantitative study, whose results witnessed a different behaviour of banks than the one suggested by the SCP hypotheses, also finds that bank conduct is not necessarily a derivate of the industry structure and is shaped by several factors from the internal and external environment. Most importantly, regulation is found to have a significant role in shaping the behaviour of banks in the market. The study also finds that bank specific external and regulatory factors also explain the variation in performance of banks. Variables like ensuring income diversification, building resilient capital and a liquidity base, maintaining asset quality, narrowing trade deficits, ensuring market and economy growth among others remained pertinent policy variables that impact bank performances. A separate view on the policy direction under the GTP II shows a mixed result where requirements for branch agents' growth and bill purchases have negative effect on performance while others like loan growth, deposit growth, capital increase and asset quality control have positive implications. With the backdrop of such findings, the study recommends that bank regulators and policy-makers should have considerations to the multi-variables in the model in their attempt to design regulatory directives

ለማከናወን ባላቸው ተልዕኮም መካከል ቀላል የማይባል ልዩነት አለ። የብቃትን ልዩነት ለመለካት በባራሜትሪክም ሆነ ፓራሜትሪካዊ ባልሆነ መልኩ (parametric and non-parametric) የተካሄደው ውጤት የሚያመለክተው በአገሪቱ ውስጥ ባሉ ባንኮች መካከል ከፍተኛ የብቃት ልዩነት መኖር ሲሆን የመንግስት ባንኮን የመሪነት ሚናቸውን እንደጠበቁ ናቸው፡ ፡ በስትራክቸር-ኮንዳክት-ፐረፎረማንስ (SCP) ንድፈ ሀሳብ ከሚታየው የተለየ፣ የባንኮችን ባህሪይ የሚያመላክተው አሀዛዊው ውጤት የባንኮች አሰራር እንደማንኛውም ኢንዱስትሪ ሳይሆን ከተለያዩ ውስጣዊና ውጫው ሁኔታዎች ጋር ተጣጥሞ መሄድ እንዳለበት ነው። ከሁሉም በላይ ባንኮች በገበያ ውስጥ ያላቸውንና የሚኖራቸው ሚና በከፍተኛ ደረጃ የሚወሰነው በክትትል ያላቸው ብቃት ነው። የባንኮች ውስጣዊና ውጫዊ ክትትልም በባንኮች አፈጻጸም ላይ ልዩነት እንደሚያመጣ ጥናቱ ያሳያል። የገቢ ምንጭና ማስፋት፣ ችግሮችን መቋቋም የሚችል ካፒታልና የገንዘብ ፍሰት መኖር፣ የቋሚ ካፒታልን በአስተማማኝ ሁኔታ መያዝን፣ የትርፍ ጉድለትን መቀነስን፣ የገበያና የኢኮኖሚውን ዕድገት ማጠናከርን የመሳሰሉ በባንኮች አፈጻጸም ላይ ቀላል የማይባሉ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎችም ናቸው። ከዚህ በተለየ መልኩ በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 2 የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ የቅርንጫፎች ብዛትና የክፍያ መጠየቂያ ግዢ (bill purchase) በአሰራር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሲኖራቸው የብድር መጠን ከፍ ማለት፣ የክምችት ማደግ፣ የካፒታል መጨመር እና እሴትን በጥራት መቆጣጠር አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራሉ የሚል አመለካከት ይዟል። ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ግኝቶች ዳራ በመነሳት የባንክ ተቆጣጣሪዎችና ፖሊሲ አውጭዎች የባንኮችን አሰራር ለመከታተልና በማክሮ ኢኮኖሚ ፖሊሲያቸውን በሚያወጡበት ጊዜ በሞዴላቸው ውስጥ የተለያዩ ወሳኝ ሁኔታዎችን ማካተት እንደሚኖርባቸው ጥናቱ አስተያየቱን ይሰጣል። በተጨማሪም፣ ተቆጣጣሪው አካል ዘርፉ በአንድ አካባቢ እንዲከማች የሚያደርጉ ሁኔታዎችን መሻሻል ይኖርበታል። በቅርቡ የመንግስት ባንኮችን የማዋሀዱ እርምጃም በገበያው ውስጥ ባሉ በሌሎች ባንኮች አሰራር ላይ ተፅዕኖ የማሳደር አቅም ሊኖረው ስለሚችል በጥንቃቄ መታየት ይገባዋል። ባንኮችና ባንኮችን የሚቆጣጠሩ

and macro-economic policies intended to improve bank performance. In addition, the regulatory organ should limit measures that aggravate the concentration of the sector. The recently introduced actions such as mergers between state-owned banks need to be carefully considered as they potentially affect the performances of other banks in the system. Banks and regulatory moves should be directed towards improving bank efficiencies and regulatory rigidities in some fronts like bill purchases and branch growth requirements need to be flexed. The study extends the research on industry concentration and performance employing the structural models: (SCP) or Efficiency Hypothesis (ESH) and applying a direct measure of efficiency with extensive panel datasets to examine the Ethiopian banking system. Contributing to theory, the study showed how the non-structure factors result in banks behaving in a different way and sometimes in a different way than the one presumed by the structural theorists. Hence, it rejects the approach to determine the conduct of banks solely from the industry structure as it could lead to wrong generalisations. The study has introduced valuable but neglected factors from the previous structure-performance research. For instance, it has examined the effect of regulation on bank performances and finds that regulatory factors are more powerful influencers of market structure, banks' conduct and internal management decisions. Besides, the above stated theoretical contributions, the study makes an addition to the development of mixed methods research in the study of industry concentration through integrating quantitative and qualitative approaches to investigate a research question. The modified performance model developed in the study contributes to forthcoming research works related to industry structure, efficiency and bank performance.

አካላት የክፍያ መጠየቂያ ግዢና (bill purchase) በመሳሰሉ ጉዳዮች የባንኮችን አሰራር ብቃት በማሻሻልና ግትር አሰራሮችን በመለወጥ ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ጥናቱ structure-Conduct-Performance SCP ወይም የብቃት መላምት (ESH) የተሰኙትን መዋቅራዊ ሞዴሎች እንዲሁም የኢትዮጵያን ባንኮች ስርዓት ለመፈተሸ ብቃትን በቀጥታ መለካትንና የተቀመጡ ሰፊ መረጃዎችን በመጠቀም፣ የኢንዱስትሪዎችን በአንድ አካባቢ መሰባሰብም አካቷል። ለንድፈ ሀሳቡ ተጨማሪ ግኝት በማምጣትም፣ ጥናቱ non structured factors ባንኮች በተለያየ መልኩ እንዲያከናውኑ ምን ያህል እንደሚያስገድዱና እንዲሁም structured theorists ከሚቀበሉት አሰራር ውጭ እንዲያከናውኑ እንደሚያስገድዱ አሳይቷል፡ ፡ በዚህም መልክ፣ ከተሳሳተ ማጠቃለያ ላይ ስለሚጥል የባንኮች አሰራር የኢንዱስትሪውን የተለመደ አፈጻጸም ብቻ ይከተሉ የሚለውን አስተሳሰብ ውድቅ ያደርጋል። ከቀደምት ስትራክቸርድ ከሆኑ ቀደምት ጥናቶች ግኝቶች ውስጥ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ፣ ነገር ግን የተተው ሁኔታዎች በጉልህ እንዲወጡ አድርጓል። ለምሳሌም፣ በባንኮች አሰራር የቁጥጥር አሰራር የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በመመርመር ይህ በባንኮች ግብይት፣ በባንኮች አሰራርና በውስጥ ማኔጅመንት ውሳኔዎች ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እንደሚኖረው አመላክቷል። ከላይ ከተገለጹት ንድፈ ሀሳባዊ አስተዋፅዖዎች በተጨማሪ፣ የምርምር ጥያቄዎችን በመተንተኑ ሂደት አሀዛዊና ዓነታዊ መረጃዎችን አጣምሮ በመጠቀም በኢንዱስትሪው ውስጥ የተቀናጀ አቀራረብን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጥናቱ አሳይቷል። ይህ ጥናት አገልግሎት ላይ የዋለው የተሻሻለው ሞዴል ከኢንዱስትሪው አወቃቀር፣ ብቃትና አሰራር ጋር ተያይዞ ወደፊት ለሚደረጉ ጥናቶችም አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

# Industry and firm effects on the performance of financial services mediated by competitive advantage in Ethiopia

Yifru Tafesse Bekele

## ABSTRACT

The main objective of this study was to explain top management perceptions of industry and firm effects on firm performance through the mediation of competitive advantage in financial service firms operating in a regulated industry in a developing Ethiopian economy. The resource-based and industry-based views, constituting the two main schools of thought explaining performance variations among firms, were used as the theoretical foundation of this study. Porter's Five-Forces Framework was used during this process. The researcher employed a post-positivist paradigm using a cross-sectional survey design. A total of 27 financial service firms (15 banks and 12 insurance firms) that had functioned for three and more years were selected for the study. The unit of analysis was 'firms', while respondents were top-level managers with a total target population of less than 300. A census survey rather than a sample survey was undertaken. A total of 287 survey questionnaires were distributed (banks 180 and insurance industry 107), of which 215 were collected from 26 firms (15 banks and 11 insurance firms). Of the questionnaires, 206 were properly completed leading to a valid response rate of 71%. These were used for the data analysis. A variance-based PLS-SEM approach, which is relevant to evaluate the predictive effects of the industry and firm factors on firm performance, was

# በኢትዮጵያ የፋይናንስ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ሁኔታ እና የተቋም ብቃት በተወዳዳሪነት ብልጫ አማካኝነት አፈጻጸም ላይ የሚያሳድሩት ተፅዕኖ

በይፍሩ ታፈሰ በቀለ

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢትዮጵያ ለውጭ ባለሃብቶች ዝግ በሆነውና ቁጥጥር በሚደረግበት ታዳጊ ኢኮኖሚ ውስጥ የፋይናንስ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ሁኔታ እና የተቋም ብ

ቃት (ሀብትና አቅም) በተወዳዳሪነት ብልጫ አማካኝነት በአፈጻጸም ላይ ስለሚያሳድሩት ተፅዕኖ በከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የሥራ ሃላፊዎች ያላቸውን አመለካከት መመርመር ነበር። የጥናቱ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ያደረገው፣ በተቋማት መካከል ያለን ልዩነት ለመግለጽ ከሚታወቁት ሁለት ንድፈ ሃሳቦች ማለትም፤ የተቋም ሀብትና አቅም ብቃት (resource-based view) እና የኢንዱስትሪ ገላጭ ኩነቶች (industry-based view) ላይ ነብር፡ ፡ በጥናቱ ሂደት የፖርተርን አምስት ኃይሎች ማዕቀፍ (Porte's five forces framework) ጥቅም ላይ ውለዋል። አጥኚው ሁሉን አቀፍ የመረጃ ማሰባሰቢያ መጠይቆችን በሚያዘጋጅበት ወቅት፣ ድህረ-አዎንታዊ (post-positivist) የተሰኘውን አቀራረብም ለጥናቱ ጥቅም ላይ አውሏል። ለጥናቱ ሶስትና ከዚያ በላይ ዓመታትን ስራ ላይ የነበሩ፣ በጠቅላላው 27 የፋይናንስ አገልግሎት ተቋማት (15 ባንኮችና 12 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች) ተመረጠዋል፡ ፡ መጠይቅ የተደረገላቸው በጠቅላላው 300 ከፍተኛ ማኔጀሮች ሲሆኑ፣ ትንታኔ የተደረገው ግን በተቋም ደረጃ ነው። ጥናቱ የተካሄደው ናሙና በመምረጥ ሳይሆን፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሁሉ በማካተት ነበር። በጠቅላላ 287 መጠይቆች (180 ለባንኮች፣ 107 ለኢንሹራንስ ኩባንያዎች) ተበትነው፣ ከእነዚህ ውስጥ ከ26 ተቋማት (ከ15 ባንኮችና 11 ኢንሹራንስ ኩባንያዎች) 215 መጠይቆች ተሞልተው ተመልሰዋል። ከተመለሱት መጠይቆች መካከል 206 በአግባቡ የተመለሱ

used to explain the hypothesized model using Smart PLS 2.00 software as well as the Statistical Package for the Social Sciences programme. The assessment of the hypothesized model indicated that the R2 result on firm performance variance due to the combined industry effects and firm effects was 39%, indicating a moderately significant predictive accuracy of the model. The relative direct effect size (f2) of the industry on firm performance was 3%, while firms had a direct effect size of 2%, which was small. The combined indirect relative predictive accuracy of industry and firm effect sizes on firm performance through competitive advantage was high at 27%. This was driven by the relative substantial predictive power of firm effect on competitive advantage (f2 = 65%). Furthermore, the predictive capability (Q2) assessment result of the model indicated that both industry and firm effects had a 23% relevant predictive power on firm performance. The direct relative measure of the predictive relevance (q2) value of industry effect (q2 = 0.02) on firm performance was relatively higher than that of the firm effect (q2 = 0.01). Competitive advantage had a relative predictive power of 0.12, which was driven by the direct relative predictive capability of firm effect (q2 = 0.25) on competitive advantage. The overall assessment results of the structural model revealed that the model had satisfactory statistical power to predict the hypothetical research model. The hypothesis that industry effects had an influence on the performance of financial service firms was not supported. The results indicated that industry effects had a positive and non-significant relationship with firm performance, which points to competitiveness in the financial services industry. These results were achieved against the tenets of Porter's Five-Forces Framework. The hypothesis that

ሲሆን፣ የዚህ የአስተማማኝነት ምጣኔው 71% ሆኗል፤ እነዚህንም ላይ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡ ፡ በኢንዲስትሪና በተቋማት ደረጃ የተገመቱ ሁኔታዎች በተቋማት አፈጻጸም ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለመተንተን፣ ከልዩነት ተነስቶ ለትንታኔ አመች የሆነውን "Partial least square structural equation model" የተሰኘውን ስማርት PLS 2.00 ሶፍት ዌርና ለሶሻል ሳይንስ ፕሮግራሞች የሚያገለግለውን ስታቲስቲካል ፓኬጅ ጥቅም ላይ ውለዋል። የመላምታዊው ሞዴል ጥናት እንደሚያሳየው የR2 ውጤት በኢንዱስትሪውና በተቋሙ ጥምር ተፅዕኖ ምክንያት የአፈጻጸሙ ልዩነት 39% ነው። ይህ የሚያሳየው ሞዴሉ መካከለኛ ደረጃ ተቀባይ ያለው መሆኑን ነው፡ ፡ ኢንዱስትሪው በተቋሙ አፈጻጸም ላይ ያለው አንፃራዊ ተፅዕኖ መጠን (f2) 3% ሲሆን፣ ተቋሙ ያለው ቀጥተኛ ተፅዕኖ አነስተኛ ማለትም 2% ነው፡ ፡ ውድድር በሚኖርበት ሁኔታ ኢንዱስትሪዎችና ተቋማት በተቋሙ አፈጻጸም ላይ ያላቸው ጣምራ ተፅዕኖ ከፍተኛ ማለትም 27% ነው። ይህ ሊመጣ የቻለው ተወዳዳሪነት በተቋማት ላይ ያለውን ተፅዕኖ በአንፃራዊነት በበቂ ደረጃ (f2=65%) መተንበይ በመቻሉ ነው። በተጨማሪም፣ የሞዴሉ የመተንበይ ችሎታ (Q2) ላይ የተደረገው ጥናት የሚያሳየው ኢንዱስትሪውም ሆነ ተቋሙ በተቋሙ አፈጻጸም ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ 23% መሆኑን ነው። የኢንዱስትሪው ቀጥተኛው ተፅዕኖ (q2=0.02) የመተንበይ ተገቢነት (q2) በተቋማት አፈጻጸም ላይ ያለው ተፅዕኖ ድርጅቶች ካላቸው የበለጠ ማለትም (0.01) ነው። የተወዳዳሪነት ብልጫ(competitive advantage) አንፃራዊ ተገማች ኃይሉ 0.12 ነው። ይህ የተገኘው የተቋማት ተገማች ተፅዕኖ አቅም (q2-0.25)፣ በተወዳዳሪነት ብልጫ ጠቀሜታ ላይ ያለውን ተፅዕኖ በመውሰድ ነው። በመዋቅራዊው ሞዴል ላይ የተካሄደው አጠቃላይ ግምገማም ሞዴሉ ተገማቹን ስታቲስቲካዊ መላምት ለመተንበይ በቂ አቅም እንዳለው ያሳያል። የኢንዱስትሪው ተፅዕኖ በተቋሙ የፋይናንስ አገልግሎት ላይ ተፅዕኖ ያሳድራል የሚለው ግምት በጥናቱ አልተደገፈም፡ ፡ ውጤቱ የሚያሳየው የኢንዱስትሪው ተፅዕኖ ከተቋማት አፈጻጸም ጋር አዎንታዊና ጉልህ ያልሆነ ተዛማጅነት ያለው መሆኑን ነው። ይህ በፋይናንስ አገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ ተወዳዳሪነት መኖሩን ያሳያል። እነዚህ ውጤቶች ከፖርተር አምስት ኃይላት እምነት ተቃራኒ

firm effects had a positive predictive effect on firm performance was also not supported, indicating that resources and capabilities do not directly lead to improved firm performance. The direct effect of competitive advantage on firm performance was supported. The mediating effect of competitive advantage between industry effects and firm performance was not significant, while the mediation of competitive advantage between firm effects and firm performance was highly significant. The findings of this study revealed that firm effects were relevant through the mediation of competitive advantage in explaining performance variances among financial service firms, operating in a strictly regulated industry. The relative predictive power of firm effect on competitive advantage was high. Firm resources, particularly intangible resources and dynamic capabilities, are the key predictors of firm performance indirectly through the mediation of competitive advantage. Such an advantage may not last long given the excessive supervision and regulations that exist and the fact that firms are being dictated to by the government to comply with its strategic direction as opposed to pursuing their own firm specific strategies. Such practice could encourage competing financial firms to converge and pursue similar types of strategies and encourage imitations to gain short-term competitive advantage and superior performance. This finding contradicts the fundamental premise of the resource-based view and firm heterogeneity even though it tentatively supports the argument made by Foss and Knudsen (2003) who argue that heterogeneity is not a necessary condition to gain competitive advantage and superior firm performance. Financial service firms should not only develop and manage their resources and capabilities, but they should also monitor the changes in the industry.

ናቸው። በተቋማት አፈጻጸም ላይ የተቋማት ተፅዕኖ አዎንታዊ የትንበያ ውጤት ያስከትላል የሚለው መላምትም አልተደገፈም። ይህ የሚያመለክተው የሀብት ገፅታና አቅም በቀጥታ የተቋማትን አፈጻጸም የሚያሻሽሉ አለመሆኑን ነው። ተወዳዳሪነት ብልጫ በተቋማት አፈጻጸም ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ተረጋግጧል፡ ፡ በተቋማት አሰራርና በተቋማት አፈጻጸም መካከል የተወዳዳሪነት ጠቀሜታ ከፍተኛ ሲሆን፣ በኢንዱስትሪ አሰራርና በተቋማት አፈጻጸም ላይ የተወዳዳሪነት መኖር የሚያሳድረው ተፅዕኖ ጉልህ አይደለም። የጥናቱ ውጤት እንዳመለከተው፣ በቅርብ ክትትል በሚደረግባቸው በአንፃራዊ ደረጃ የመወዳደር ብቃት ባላቸው የፋይናንስ ተቋም አንዱስትሪዎች መካከል የአፈጻጸም ልዩነት ታይቷል። የመወዳደር ብልጫ ባላቸው ተቋማት አፈጻጸም ላይ የመተንበይ አቅምም በአንፃራዊነት የተሻለ ነው። የተቋም የሀብት ብቃት፣ በተለይም የማይዳሰሱ ሀብቶች እና የታታሪ ሰራተኞች መኖር በተዘዋዋሪ መንገድ የመወዳደር ብልጫ ያላቸውን ተቋማት አፈጻጸም ለመተንበይ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ከመጠን በላይ ክትትልና ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ፣ እንዲሁም ተቋማት የራሳቸውን ስልት በመከተል ፈንታ መንግስት ያወጣቸውን ስትራተጂዎች እንዲከተሉ በሚያስገድድበት ሁኔታ፣ እንዲህ ያለው የተወዳዳሪነት ብቃት ለረጂም ጊዜ ሊቀጥል አይችልም። እንዲህ ዓይነቱ አሰራር ተወዳዳሪ የፋይናንስ ተቋማት እንዲሰባሰቡና የአጭር ጊዜ ተወዳዳሪነትንና ከፍተኛ የአፈጻጸም ብቃት ላይ እንዲያተኩሩ ይገፋፋቸዋል። ጥናቱ በተወዳዳሪነት በላይነት ለመጠቀምና የቋማትን አፈጻጸም ብልጫነት ለማረጋገጥ የበርካታ ተቋማት መኖር የግድ አስፈላጊ አይደለም የሚለውን የፎስ (Foss) እና የኑድሰንን (Knudsen) (2003) ሀሳብ በጊዜያዊነት የሚቀበል ቢሆንም የዚህ ጥናት ውጤት በሀብትና አቅም ብቃት በተቋማት ብዝሀነት ላይ ከተመሰረተው አስተሳሰብ ተቃራኒ ነው። የፋይናንስ አገልግሎት ተቋማት የውስጥ የሀብት አቅማቸውንና ብቃታቸውን ማሳደግና መምራት ብቻ ሳይሆን፣ በኢንዱስትሪው ውስጥ የሚከሰቱ ለውጦችንም መከታተል ይኖርባቸዋል፡ ፡ ተቋማት ተወዳደሪ በሌለበትና የቅርብ ቁጥጥር ባለበት ሁኔታም ቢሆን፣ የተወዳዳሪነት ደረጃቸውን ከፍ በማድረግ ከፍተኛ አፈጻጸም ሊኖራቸው የሚችሉ መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል። የዚህ ጥናት

This finding highlights the fact that firms can create competitive advantage and enjoy superior performance in a closed and regulated industry. The findings of this research make a significant contribution to the existing debate on the resource-based and industry-based views in explaining the causes of firms' performance variations specifically in a regulated environment.

**Keywords:** Industry effects; firm effects; competitive advantage; firm performance; Five Forces; tangible resources; intangible resources; dynamic capabilities.

ውጤቶች በተለይ ለውጭ በለሀብት ዝግ በሆነበት እና ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ በሚንቀሳቀሱ ተቋማት መካከል ያለውን የአፈጻጸም ልዩነት በማሳየት በአሁኑ ወቅት በሀብትና አቅም ብቃት እና በኢንዱስትሪ ሁኔታ ተፅዕኖ ላይ ለተመሰረቱ አመለካከቶች ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ።

**ቁልፍ ቃላት:**- ኢንዱስትሪ ሁኔታ ተፅዕኖ, የተቋም ሃብትና አቅም, የተወዳዳሪነት ብልጫ, የተቋም አፈጻጸም, የፖርተርን አምስት ኃይሎች , የሚዳሰሱ ሀብቶች, የማይዳሰሱ ሀብቶች, ተለዋዋጭ የአቅም ብቃት.

Year of Graduation 2019

# A framework for competitive intelligence in strategic decision-making (SDM) in an Ethiopian conglomerate

Bezabih Bekele Tolla

## Abstract

The primary intent of this study was to develop a competitive intelligence (CI) programme implementation strategy framework for the effective use of CI in strategic decision-making (SDM) in a conglomerate, using embedded multiple units and a single-case exploratory study that is qualitatively dominant. The study therefore explored the strategic value of CI for SDM in a company that has a conglomerate structure and whose subsidiaries are vertically integrated. Despite the perceived usefulness of CI for distinctive SDM, the case conglomerate and its subsidiaries had collected and employed the available CI products to support their strategic, tactical, and other business decisions. Overall results indicated differences between the subsidiaries

# በኢትዮጵያ ኩባንያዎች ስልታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ይበልጥ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚረዳ የአሠራር ማዕቀፍ፤

በበዛብህ በቀለ ቶላ

## አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በድርጅታዊ ሥራ አፈጻጸም ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል መርሐ ግብርን ስልታዊ በሆነ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጥቅም ላይ በማዋል፣ በኢንዱስትሪዎች/ ኩባንያዎች ውስጥ የተካተቱ በርካታ ክፍሎችንና ሌሎችንም ወደ መረሀግብሩ አጠቃቀም ማስገባት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ጥናቱ የጎን አደረጃጀት እና የብዙ ድርጅቶች ጥምረትና የአወቃቀር ባህርይ ይፈትናል። ይህ ጥናት የተጠቀመው የገላጭ ጥናትና ምርምር ሰልት ሲሆን፣ ለመረጃ ትንተናው ዓይነታዊ የትንተና ዘዴምን ተጠቅሟል። ስለዚህም ጥናቱ ከተለያዩ ምንጮች መረጃን ስልታዊ በሆነ መንገድ የማሰባሰብ፣ የማቀናጀት እና የመተንተን፣ የአንድን ድርጀት ተወዳዳሪ የሆነ የሥራ አፈጻጸም ፕሮግራምን፣ መዋቅርና ስርዓት በተናጠል ወይም በጋራ ፕሮግራሙ ለተዘረጋላቸው ድርጅቶች ለሚተገብሩት ስልታዊ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ ምን እንደሆነ ለማጥናት ይሞክራል፡

and the headquarters and among the subsidiaries on CI practice (CI collection, CI coordination, CI sharing and CI effort) and CI usage for SDM and other decisions. Although a similar strategy development process (guided by the grand corporate strategy), management structure, decision-making process and orientation in the subsidiaries existed, these uniformities did not significantly result in a uniform level of application and usage of CI for SDM across the conglomerate. The conclusion is that CI application is very subjective and contextual even in a vertically integrated conglomerate. Through theory, literature review and empirical findings, synthesis and iteration, a middle-range theory that integrates the CI and SDM disciplines in terms of the contextual issues they both share is also constructed. The study also developed a novel way of crafting CI for SDM, which may fit into the existing structure and realities of the conglomerate so as to formalise CI. The CI programme implementation strategy framework was developed considering the proof of tested theories, best practices, existing context, strategy, decision-making process, structure, enabling factors and capabilities of the conglomerate. The CI programme implementation strategy framework, accompanied by a proposed CI structure, has immediate pragmatic utility. It could enable the conglomerate to initiate a formal CI programme without delay and to develop it following an organisational maturation cycle. The study makes an original contribution by conceptualising a CI programme implementation strategy for a unique case and theorising the case within a novel extension within middle-range theory (“SDM and CI application can be viewed in the contextual domains both share”). The exploratory study itself, which led to merging theory and best practices with empirical results and fitting

፡ ምንም እንኳን ከተለያዩ ምንጮች መረጃን ስልታዊ በሆነ መንገድ የማሰባሰብ፣ የማቀናጀት እና የመተንተን፣ የአንድን ድርጅት ተወዳዳሪነት የሚገልጽ ፕሮግራም ለየት ላለ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ጠቃሚ ነው ተብሎ ቢታሰብም፣ የጉዳዩ ባለቤቶች እና ተባባሪዎች ስልታዊ፣ ታክቲካዊ እና ሌሎች የንግድ ውሳኔዎችን ለመደገፍ የተወዳዳሪ ድርጅቶችን ምርቶች በመጠቀም ላይ ናቸው። በአጠቃላይ የምርምሩ ውጤቶች እንደሚያመለክቱት በቅርንጫፍ ቢሮዎች እና በዋና መሥሪያ ቤት መካከል እየታየ ያለው ልምምድ፣ ቅንጅት፣ መጋራት፣ ጥረት፣ እንዲሁም የተለያዩ መረጃዎችን ለስልታዊ ውሳኔ አሰጣጥና አጠቃቀም፣ በሌሎች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ዙርያ ያለውን አተገባበር በጉልህ ለማመላከት ተሞክሯል። ምንም እንኳን ተመሳሳይ ስልታዊ የልማት ሂደት የሚከተሉ (በዋናው ኮርፖሬት ስትራቴጂ የሚመሩ)፣ ተመሳሳይ የአስተዳደር መዋቅር፣ ተመሳሳይ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት እና በቅርንጫፍ ቢሮዎች ውስጥ ያሉ አቅጣጫዎች ቢኖሩም እንኳን፣ ጉልህ ውጤት እንዳላመጣና የተወዳዳሪ ድርጅትን የሥራ አፈጻጸም አጠቃላይ ስልታዊ የውሳኔ አሰጣጥ አተገባበር እና አጠቃቀም ወጥ በሆነ መንገድ እየሰሩበት አይደለም፡ ፡ በአጠቃላይ ከላይ ጥናቱ እንደሚያሳየው የተወዳዳሪ ድርጅት ዕውቀት መተግበሪያ ከላይ እንደተጠቀሰው በተቀናጀ አውድ እንኳን በጣም ለአድልዎ የታገለጠ መሆኑን ነው። ከንድፈ-ሀሳብ ከስነ-ጽሁፍ ግምገማ እና ከተጨባጭ ግኝቶች፣ ጥንቅር እና ድግግሞሽ፣ መካከለኛ ንድፈ ሃሳብ፣ በተወዳዳረሪ ድርጅቶች ዕውቀት ላይ የተመሠረተ እና ስልታዊ የውሳኔ አሰጣጥ ስርዓቶችን ከዐውዳዊ ጉዳዮች አንፃር በማዋሃድ ሁለቱም እንዲጋሩት ተደርጎ የተሰራ ነው። ጥናቱ በአዲስ መንገድ ከተለያዩ ምንጮች መረጃዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ የማሰባሰብ፣ የማቀናጀት እና የመተንተን አሰራርን ለስልታዊ ውሳኔ አሰጣጥ የሚሆንበትን ዘዴ አዘጋጅቷል፤ይህም የተወዳዳሪ ድርጅቶችን የአሠራር ሂደት መደበኛ ለማድረግ አሁን ካለው መዋቅር እና ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ሊያጣጥም ይችላል። የተወዳዳሪ ድርጅቶች አሠራር የድርጅቱን ጥቅም የሚያስጠብቅ ፕሮግራም ትግበራ ስልት ማዕቀፍ የተፈተኑ ንድፈ ሐሳቦችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱንና አወቃቀሩን፣ የማስቻል ሁኔታዎችን፣ እንዲሁም ስብስብ አቅሞችን ማረጋገጥን ከግምት ውስጥ

the theories and best practices into case conglomerate's realities, also makes the study unique in terms of its approach and outputs.

**Keywords:** Competitive intelligence (CI); Strategic Intelligence (SI); strategic decision-making (SDM); context; conglomerate (vertically integrated); embedded (multiple) units single-case design.

በማስገባት የተዘጋጀ ነው። የተወዳዳሪ ድርጅት አሠራር ፕሮግራም የትግበራ ስትራቴጂ ማዕቀፍ በታቀደው መሠረት ከብዙ ምንጮች መረጃን ስልታዊ በሆነ መንገድ በማሰባሰብ፣ በማቀናጀት እና በመተንተን ጥምረት ከፈጠሩት ድርጅቶች መዋቅር ጋር በመቆራኘት፣ ፈጣን ተግባራዊ አገልግሎት ይሰጣል። ይኸውም ስብስቡ የተወዳዳሪዎችን አሠራር በመረዳት በመደበኛ ፕሮግራሙ ሳይዘገይ እንዲጀምር እና ድርጅታዊ ብስለትን ተከትሎ እንዲያዳብር ያስችለዋል፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ ከተለያዩ ምንጮች መረጃን ስልታዊ በሆነ መንገድ የማሰባሰብ፣ የማቀናጀት እና የመተንተን መርሐ ግብር ስልትን በፅንሰ-ሀሳብ እና በንድፈ ሃሳብ በማዘጋጀት፣ በአዲስ መልክ በመስራት (የስልታዊ ውሳኔ አሰጣጥንና የድርጅቱን ተወዳዳሪነት የሚያሳይ መተግበሪያ አንድ አውድ እንዲጋሩ)ንድፈ ሀሳብ በማቅረብ የመጀመሪያ አስተዋፅዖ አድርጓል። ገላጭ የአጠናን ዘዴው በራሱ ንድፈ ሃሳቦችን እና ምርጥ ተሞክሮዎችን ከተጨባጭ ውጤቶች ጋር በማዋሃድ እንዲሁም ንድፈ ሃሳቦችንና ምርጥ ተሞክሮዎችን ከእውነታው ጋር አጣጥሞ በመሥራቱ የጥናቱን አቀራረብና በውጤት ልዩ ያደርገዋል።

**ቁልፍ ቃላት:** ተወዳዳሪ የማሰብ ችሎታ (CI)፤ ስልታዊ የማሰብ ችሎታ  (SI)፤ ስልታዊ ውሳኔ አሰጣጥ (ኤስዲኤም); አውድ; የተቀናጀ; የተከተተ (በርካታ) አሃዶች ነጠላ ንድፍ.።

Year of Graduation 2021

# Development of a theoretical model based on the evaluation of the impact of business process management as a dynamic capability on organisational performance' in the banking sector in a developing country context

Abebe Walle Menberu

## ABSTRACT

The most difficult question for companies in today's dynamic business world is to gain and sustain a competitive advantage. One of the reliable answers for such a call is going beyond product innovation, that is, the innovation of business processes. The most sought-after practice for attaining the goal of process innovation is business process management (BPM). Abundant empirical research on BPM is carried out especially in the developed world. But these research works are short of theoretical explanation, suffer from a limited stock of variables, and many recent studies look at single organisations and single BPM projects. Besides, most of the studies were undertaken within the context of developed economies which underlies little applicability in less developed economies. And yet these developing countries have been making huge investments in BPM undertakings which necessitate the conduct of empirical investigations to see whether such investments bring about good performance outputs. Hence, in an answer to the call for BPM theorisation especially in terms of research on developing economies, the research investigated how Dynamic Capabilities Theory

# በባንክ ዘርፍ በድርጅታዊ አፈፃፀም ላይ 'እንደ ተለዋዋጭ አቅም' የሥራ ሂደት አስተዳደር ያለውን ተፅእኖ በመገምገም ላይ የተመሠረተ የንድፈ ሃሳባዊ ሞዴል መፍጠር፡ በታዳጊ ሀገር አውድ የተደረገ ጥናት፤

በአበበ ዋለ መንበሩ

## አጠቃሎ

በአሁኑ ወቅት ተለዋዋጭ የንግድ ዓለም ውስጥ ላሉ ኩባንያዎች በጣም አስቸጋሪው ጥያቄ የውድድር ጥቅም ማግኘት እና ማስቀጠል ነው። ለዚህ ጥሪ አስተማማኝ የሆነው አንዱ መልስም ከምርት ፈጠራ ወደ ላቀው የሥራ ሂደት ፈጠራ መግባት ነው። የሂደት ፈጠራ ግቡን ለማሳካት በጣም የሚፈለገው ልምምድ ~~የቢዝነስ~~ የሥራ ሂደት አስተዳደር (BPM) ነው። በBPM ላይ የተካሄዱ በርካታ ተጨባጭ ጥናቶች አሉ፤ በተለይም ባደጉት አገሮች አገሮች ላይ ይከናወናሉ። ነገር ግን፤ የእነዚህ የምርምር ስራዎች የንድፈ ሃሳባዊ ማብራሪያ አጭር ናቸው፤ በተወሰኑ የተለዋዋጮች ክምችት(መጠኖች) አናሳ መሆን፤ ብዙ የቅርብ ጊዜ ጥናቶች ነጠላ ድርጅቶችን እና ነጠላ BPM ፕሮጀክቶችን ይመለከታሉ። በተጨማሪም፣ አብዛኛው ጥናቶች የተካሄዱት ባደጉ ኢኮኖሚዎች አውድ ውስጥ ሲሆን ይህም ባላደጉ ኢኮኖሚዎች ላይ ተግባራዊነት አነስተኛ ነው። ነገር ግን እነዚህ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በBPM ስራዎች ላይ ትልቅ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ላይ ናቸው። ስለዚህ እነዚህ ኢንቨስትመንቶች ጥሩ የአፈፃፀም ውጤቶችን ያመጣሉ የሚለውን ለማረጋገጥ ተጨባጭ ምርመራዎችን ማካሄድ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም፣ ለBPM ቲዮራይዜሽን ጥሪ በተሰጠው ምላሽ፣ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ኢኮኖሚዎች ላይ ከሚደረጉ ጥናቶች፣ ጥናቱ ተለዋዋጭ የአቅም ንድፈ ሐሳብ በማደግ ላይ ባለው አገር ሁኔታ BPM እንዴት እንደሚያብራራ መርምሯል። ስለዚህ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ የተመለከቱት ቁልፍ የምርምር ጥያቄዎች፡- የንግድ ሥራ አመራር ጽንሰ-ሀሳብን በንድፈ ሀሳብ እንዴት ልንይዘው

